# የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች

# ስልጠና ማዕከል

**ለረጅም ጊዜ የስራ ላይ ሰልጣኞች የተዘጋጀ**

**የስልጠና ሞጁል**

**መሰረታዊ የሥነ-ስርአት ህጎችን በተመለከተ**

**የኢፌድሪ ህገ-መንግስት መሰረታዊ**

**አቅጣጫወች**

**በፌደራል የፍትህ አካላት በለሙያወች ማሰልጠኛ ማእከል የተዘጋጀ**

# መሰረታዊ እና የስነስርአት ህጎችን በተመለከተ የኢፌዲሪ ሕገመንግስት መሰረታዊ መርሆዎችና አቅጣጫዎች

## ማውጫ


መግቢያ ........ 3
የሥልጠናው ዓላማዎች ........ 6
ምዕራፍ አንድ ........ 8
በወንጀል ፍትህ አስተዳደር የኢፌዲሪ ህገመንግስት መሰረታዊ መርሆዎች ........ 8
ምዕራፍ ሁለት ........ 68
ከውል ውጭ በሚደርስ ኃላፊነት ህግ የህገመንግስቱ መሰረታዊ መርሆዎች ........ 68
ምዕራፍ ሦስት ........ 80
በንብረት ህግ የህገመንግስቱ መሰረታዊ መርሆዎች ........ 80
ምዕራፍ አራት ........ 105
በውርስ ህግ የህገመንግስቱ መሰረታዊ መርሆዎች ........ 105
ክፍል አምስት ........ 115
በቤተሰብ ሕግ የህገ መንግስቱ መሰረታዊ ........ 115
መርሆዎች እና አቅጣጫዎች ........ 115
ክፍል ስድስት ........ 121
በውል ህግ የህገ መንግስቱ መሠረታዊ ........ 121
መርሆዎች እና አቅጣጫዎች ........ 121
ክፍል ሰባት ........ 133
ከንግድ እና ኢንቨስትመንት አንፃር የህገ መንገስቱ ........ 133
መሰረታዊ መርሆዎች እና አቅጣጫዎች ........ 133
ክፍል ስምንት ........ 145
ከአሰሪና ሰራተኛ ህግ አንፃር የህገ መንግስቱ ........ 145
መሠረታዊ መርሆዎች እና አቅጣጫዎች ........ 145
ክፍል ዘጠኝ ........ 158
ከአስተዳደር ህግ አንፃር የህገ መንግስቱ መሠረታዊ ........ 158
መርሆዎች እና አቅጣጫዎች ........ 158
ክፍል አስር ........ 175
ከታክስ ህግ አንፃር የህገ መንግስቱ መሠረታዊ ........ 175
መርሆዎች እና አቀጣጫዎች ........ 175

# መግቢያ

ሕገ መንግስቱ አሁን ያለውን ቅርጽና ይዘት ይዞ እንዲፀድቅ ለማድረግ ከፍተኛ የሆነ ሰብአዊና ቁሣዊ ዋጋ የተከፈለበት ሲሆን ከዚህ በኂላ የሁሉንም ርብርብ እና የነቃ ተሣትፎ የማይጠይቀው የሕገመንግስቱ እሴቶችና መርሆች ህብረተሰቡ እንዲረዳ ማድረግ የሕገመንግስቱን መርሆችና ድንጋጌዎች ማክበርና እንዲከበሩ በማድረግ ሕገ መንግስቱ የህብረተሰቡና የመንግስት የእለት ከእለት እንቅስቃሴ ተግባራዊ መመሪያ ማድረግ በሌላ አገላለጽ ህገ መንግስታዊነትን ማረጋገጥ ነው፡፡ የፍትህ አካላት መሰረታዊ ተልእኮ ተግባርና ኃላፊነት የሕገመንግስቱን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ የሚሰራና ሕገመንግስቱን ከማስከበርና የህገመንግስቱን እሴቶችና መርሆች ከማስረጽ ጋር ከፍተኛ የሆነ ቁርኝት ያለው ነው፡፡

የፍትህ አካላት የህገ መንግስቱን የበላይነትና ልእልና ለማረጋገጥ በህገ መንግስቱ እውቅና እና ጥበቃ የተሰጣቸውን ሰብዓዊ መብቶችና መሰረታዊ ነፃነቶች በአገሪቱ ግዛት ክልል በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግና የህገመንግስቱን መርሆችና እሴቶች ተግባራዊነት ለማረጋገጥ የተጣለባቸውን ግዴታና ኃላፊነት በሚፈጸመበት ጊዜ በተለያየ ጊዜ ወጥተው በሥራ ላይ የዋሉ የተለያዩ የህግ ማእቀፎች የህገመንግስቱን ግቦች በሚያሣካና ህገ መንግስታዊ መርሆችንና እሴቶችን በእለት ከእለት የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ገዥነት ያላቸው ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ የሕግ መተረጕምና የሕግ ማስፈፀም ሥራቸውን ማከናወን አለባቸው፡፡ ይህንንም ለማድረግ በአገሪቱ በግልጽ ታውጀው እየተሰራባቸው ያሉ የሕግ ማእቀፎች ይዘትና ትርጉም የሕገ መንግስቱን መርሆች እሴቶችና ድንጋጌዎች እንደዚሁም አገሪቱ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሕግጋት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች መርሆችና ሰነዶች ዋስትና እና ጥበቃ የተሰጣቸው የጠቅላላውን ሕዝብ፣የብሄር ብሄረሰብና ህዝቦች የቡድንና የግለሰብ መብትና ነፃነቶች ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማራመድና ለማስፈፀም የሚያስችል ግንዛቤ ክህሎትና አመለካከት እንዲያዳብሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ አንጻር የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የሕግ ማእቀፎቹ ከሕገ መንግስቱ ጋር ያላቸውን ትስስር እና የሕግ ማእቀፎቹን ሲተረጎሙም ሆነ ሲፈጸሙ የሕገ መንግስቱን መሰረታዊ ግቦች ማሣካት፣ህገ መንግስታዊ መርሆችንና እሴቶችን ማስፈፀም እና

ማስከበር መሰረታዊ ዓላማው ያደረገና ህገ መንግስታዊነትን ለማረጋገጥ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ ያለባቸውን ድርሻና ኃላፊነት ለማሣየት የሚችል ለውይይት መነሻ የሚሆን ሞጁል ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሞጁሉ ለመዳሰስ የተሞከሩት የህግ ማእቀፎች ህገ መንግስታዊ ግቦችን ለማሣካትና የህገመንግስቱን መርሆችና እሴቶች በማስፈፀም በኩል ያላቸውን ፋይዳ ሙሉ በሙሉ የሚዘረዝርና በተሟላ ሁኔታ የሚገልጽ ነው ተብሎ የቀረበ አይደለም፡፡ የማሰልጠኛ ሞጁሉ ዋነኛ ዓላማ የሥልጠናው ተሣታፊዎች ሥራቸውን በሚያከናውኑበትና የህግ ማእቀፎቹን ሲተረጉሙና ሲያስፈጽሙ ህገ መንግስቱን የማክበርና የማስከበር ኃላፊነታቸውን ከመወጣትና ህገ መንግስታዊነትን ለማረጋገጥ የሚችል ህገመንግስታዊ ግቦችን ታሳቢ ያደረገና አለምአቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነትና ይዘት አላማ አንፃር የህግ ማእቀፎቹን ለመገንዘብ የመነሻ ሐሳቦችን በማቅረብ ሰልጣኞች በሥራ ላይ በቆዩበት ጊዜ ያካበቱትን ልምድና ተሞክሮ የገጠሟቸውን ችግሮችና ችግሮቹን ለመፍታት ወደፊት ህግን በመተርጐምም ሆነ ህግን በማስከበር በኩል በአገር በክልልና በፍትህ አካላት በኩል ሊደረግ የሚገባውን ማስተካከያ ህገመንግስታዊነትን ከማረጋገጥና ከማስከበር ኃላፊነታቸው ጋር በማስተሣሠር ሰፊና ጥልቅ ውይይት ለማድረግ መነሻ የሚሆኑ ዋና ዋና ነጥቦችን ማቅረብ ነው፡፡

ሞጁሉ በአስር የተለያዩ እርሶች ዙሪያ እየተሰራባቸው ያሉ የህግ ማእቀፎች የህገ መንግስቱን መሰረታዊ ግቦች ለማሣካት ያላቸውን ፋይዳና ከህገ መንግስቱ መርሆችንና ድንጋጌዎች እንደዚሁም ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ህግጋት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችና ሰነዶችና መርሆች ተጣጥመው ሊተረጐሙ የሚችሉበትን አቅጣጫ ለመመርመርና ለመገንዘብና የተለያዩ ጥያቄዎችን አንስቶ ለመከራከር መነሻ ይሆናል በሚል እምነት ተዘጋጅቷል፡፡ በዚህ መሰረት በምእራፍ አንድ ህገ መንግስቱ የወንጀል ህግ ማእቀፎችን ቅርጽና ይዘትና የፍትህ አካላትን አደረጃጀትና አሰራር በመወሰን በኩል ያለውን ሚናና የወንጀል የህግ ማእቀፎችና የወንጀል የፍትህ ሥርአቱ ህገ መንግስቱን ግቦችና ከማሣካትና የህገ መንግስቱን የበላይነትና ልእልና ለማረጋገጥ እንደዚሁም ህገ መንግስታዊ እውቅና እና ጥበቃ የተሰጣቸውን ሰብአዊ መብቶችና መሰረታዊ ነፃነቶች ለማስከበርና ለማረጋገጥ የተጣለባቸውን ግዴታና ኃላፊነት በአጭሩ ለማሣየት ተሞክሯል፡፡

በምእራፍ ሁለት ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት ህግ በህገ መንግስቱ የተደነገገውን የመንግስት አሰራር ግልጽነትና ተጠያቂነት መርህ ተግባራዊ በማድረግ የተፈጥሮና የህግ ሰዎች በጉንዮሽ ለሚፈጽሙት የሰብአዊ መብት ጥሰት ተጠያቂ እንደሆኑና ተጐጅውን ካሣ እንዲከፍሉ በማድረግ በኩል ያለውን ሚና በአፈፃጸም የሚታዩ ችግሮችን፣ በምእራፍ ሶስት እንደዚሁም ከግል ንብረት ባለቤትነት መብት ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለውና ህገ መንግስታዊ እውቅና እና ጥበቃ የተሰጠውን ንብረትን የማውረስ መብትና የተለያዩ የአወራረስ ሥርአቶች በህገ መንግስቱ የተሰጣቸውን ጥበቃ ከውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ጋር ስላላቸው ትስስር በምእራፍ አራት በማካተት ተዘጋጅቷል፡፡

በህገ መንግስቱ የተረጋገጠው የቤተሰብ መብትና የፌደራልና የክልል የቤተሰብ ህግ ማእቀፎች መሰረታዊ መርሆችና እሴቶች በምእራፍ አምስት፣በምእራፍ ስድስት የመዋዋል ነፃነትና የውል ግንኙነቶች ህገ መንግስታዊ መርሆችንና እሴቶችን፣ በምእራፍ ሰባት በአገሪቱ የንግድ ኢንቨስትመንትን እንቅስቃሴ የሚመራባቸው ህገ መንግስታዊ የኦኮኖሚና የማህበራዊና የባህል አላማዎችና በንግድ ህግና ኢንቨስትመንት የህግ ማእቀፎችን ትስስር ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በምእራፍ ስምንት ከኢንቨስትምት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት የሚወስነው የህግ ማእቀፍ የሚመራባቸው ገዥ ደንቦችና አስተሳሰቦች፣ በምእራፍ ዘጠኝ በአገሪቱ ወጥተው እየተሰራባቸው ያሉትንና ወደፊትም የሚወጡት አስተዳደር የሕግ ማእቀፎችና አስተዳደራዊ ፍትህ አሰጣጥ ላይ ገዥ የሆኑ ህገመንግስታዊ መርሆችና እሴቶችና የአሰራር ሥርአቶች፣ በመጨረሻም በምእራፍ አስር በህገ መንግስቱ የፌዴራል የክልሎች ታክስ የማስከፈል ስልጣንና የታክስ አጣጣልና አሰባሰብ መሰረታዊ መርሆችና በአፈፃፀም ሒደት የሚታዩ ችግሮችን በሚመለከት በማስተዋወቅ ይጠናቀቃል፡፡

በእያንዳንዱ ርእስ ዙሪያ ውይይት ሊደረግባቸው የሚገቡ ተጨባጭ ጉዳዮች መሰረት ያደረገና የንድፈ ሐሳብ ጥያቄዎች ያሉ ሲሆን ስልጠናው በሚሰጥበት ጊዜ ሰልጣኞች እንዲረዳቸው እና እንዲወያዩባቸው ይደረጋል፡፡ ስለሆነም ሞጁሉ ለውይይት መነሻ እንደሆነ የተዘጋጀ መሆኑን በመገንዘብ ሞጁሉ አቀራረጽም ሆነ በይዘቱ ሊያዳብሩ የሚችሉ ሀሳቦችን በማንሣትና በሞጁሉ ያልተካተቱና ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች በማቅረብ ሰልጣኞች ያላቸውን ያካበተ ልምድና ተሞክሮ መለዋወጥና ህገ

መንግስታዊነትን ለማረጋገጥና ከማሰረጽ በእያንዳንዱ ርእስ ዙሪያ ግንዛቤቸው ክህሎታቸውን አመለካከታቸውን በማዳበር ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## የሥልጠናው ዓላማዎች

የሥልጠናው ጠቅላላ አላማ ሰልጣኞች የተለያዩ የህግ ማእቀፎቹን ሲተረጉሙና ሲያስፈጽሙ ህገ መንግስታዊ ግቦችን ለማሣካት በሚችልና ከህገ መንግስቱ መርሆች ድንጋጌዎችና እሴቶች ጋር በሚጣጣም ሁኔታ ለመተግበር የሚያስችላቸውን ገንዛቤ ሙያዊ ክህሎትና የአመለካከት ብቃት እንዲያዳብሩ ማድረግ ነው፡፡ በሞጁሉ ይህንን አጠቃላይና መሰረታዊ ዓላማ ለማሳካት የሚከተሉትን ዝርዝር ዓለማዎች ለማሣካት በሚችል መንገድ ተዘጋጅቷል፡፡ በስራ ላይ ስልጠና ተሳታፊ የሆኑ ባለሙያዎች ሰልጥነው ሲጨርሱ፣

- ህገ መንግስቱ የወንጀል ህግ ማእቀፎችን ቅርጽና ይዘት በመወሰን (ኮንስቲቲዩሽናል ክርሚናል ሎው) እንዲሟላ ለማድረግ ያለውን ገዥነትና አስገዳጅነት ይገልፃሉ፡፡
- የወንጀል የፍትህ ሥርአቱ ህገመንግስታዊ ግቦችን መርሆችንና እሴቶችን ተግባራዊ በማድረግ በኩል ያለበትን ኃላፊነትና ግዴታ በተግባራዊ ሂደት ያሉትን ችግሮችና የመፍትሄ ሀሳቦች ያብራራሉ፡፡
- መንግስት በህገ መንግስቱ የተጣለበት ሰብዓዊ መብቶች የማክበር የማስከበርና የማሟላት ግዴታ ለመወጣት በሚያደርገው እንቅስቃሴ የወንጀል ህግና የወንጀል የፍትህ ሥርአት ያለበትን ድርሻና ኃላፊነት ይዘረዝራሉ፡፡
- በህገ መንግስቱ የተደነገገ የተያዙ የተከሰሱና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች መብት በማክበርና በማስከበር ረገድ የፍትህ አካላት ያለባቸውን ስልጣን ኃላፊነትና ግዴታ በአፈፃፀም ሒደት የታዩ ችግሮችና የችግሮቹን የመፍትሔ ሐሳቦች ይገልፃሉ፡፡
- በአገሪቱ ግዛት ክልል በቀጥታና በጐንዮሽ የሚፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶት ፍትሀብሄራዊ ተጠያቂነት በማረጋገጥ ከውል ውጭ የሚያደርስ ኃላፊነት ህግ ያለውን ጠቀሜታና ፋይዳ ይገልጻሉ፡፡
- ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት ሕግ የመንግስት አሰራር ግልጽነትና ተጠያቂነት በማረጋገጥ በኩል ያለውን ፋይዳ ያብራራሉ፡፡

- መንግስት ሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በመከላከል በማስቆምና በመጨረሻም ጥሰቱ መፈፀሙ ሲረጋገጥ ውጤታማ እርምት(ኢፌክቲቭ ሪሜዶ) ተጎጂው እንዲያገኝ ከማድረግ አንፃር ከውል ውጭ የሚያደረስ ኃላፊነት ህግ ያለበትን ክፍተቶች እና ሊደረጉ ስለሚገባቸው ማሻሻያዎች ይገልጻሉ፡፡
- ህገ መንግስታዊ እውቅና እና ጥበቃ የተሰጣቸው መብቶች በመጣስ ጉዳት የደረሰበት ሰው ለጉዳቱ ኃላፊ ከሆነው ሰው ያለውን ካሣ የማግኘት መብት በውሣኔ አሰጣጥ ሂደት የሚታዩ ችግሮችንና የመፍትሔ ሐሳቦችን ያብራራሉ፡፡
- ህገ መንግስቱ ለግል ንብረት ባለቤትነት የሰጠውን እውቅና የንብረት ህግ ማእቀፎች ከዚህ መብት ጋር በተጣጣመ መንገድ ተፈፃሚ ለማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ ይገልፃሉ፡፡
- በህገመንግስቱ መሬትና የተፈጥሮ ሐብት የመንግስትና የሕዝብ ንብረት ሆነው የተደነገጉበትን ምክንያትና የመሬት ባለ ዞታነትና ተጠቃሚነት መብት ህገ መንግስቱ ስለሰጠው እውቅና እና ጥበቃ ይዘረዝራሉ፡፡
- የንብረት ባለቤት የሆነው ሰው በንብረቱ ላይ ስላለው መብትና መንግስት የሌላውን ሰው ንብረት ለህዝብ ጥቅም ሲወስድ ስላለበት ተነፃፃሪ ግዴታ እንደዚሁም በአፈፃፀም ሒደት ስለሚታዩ ችግሮችና የመፍትሔ ሐሳቦች ያብራራሉ፡፡
- ንብረትን ስለ ማውረስ መብት በህገ መንግስቱ እውቅና ስለተሰጣቸው የተለያዩ የአወራረስ ሥርአቶች ይገልፃሉ፡፡
- በውርስ ሊተላለፍ ስለሚችሉና ስለማይችሉ መብቶችና መሬትን ባለይዞታነትና መሬት የመጠቀም መብት በውርስ ሊተላለፍ ስለሚችልበት ህጋዊ ሁኔታ ያብራራሉ፡፡
- የወራሽነት መብት እና በመውረስ የሚያስፈልግ ችሎታ ህገ መንግስቱ ከተረጋገጠው የእኩልነት መብት ጋር ስላለው ተያያዥነትና ትስስር ያብራራሉ፡፡
- ቤተሰብ የመመሥረት መብትና የቤተሰብ የህግ ማእቀፎች ከህገ መንግስቱ መርሆችና እሴቶች ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ ለማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ በአፈጻጸም የሚታዩ ችግሮችንና የመፍትሄ ሀሳቦችን ይገልጻሉ፡፡
- የአስተዳደር ህግ በፌደራልና በክልል እንደዚሁም ከክልል በታች በተዋቀሩ አስተዳደር አካላት ወጥቶ ሥራ ላይ የሚውልበት አግባብና ከሕገ መንግስቱ መሰረታዊ መርሆች ጋር ለማጣጣም ስለሚቻልበት ሁኔታ ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡

- ስለ አስተዳደራዊ ፍትህ አሰጣጥና የአስተዳዳር መስሪያ ቤት ውሣኔዎች በፍርድ ቤቶች ሊታረሙ ስለሚችሉበት ሁኔታ ያብራራሉ፡፡
- የፌዴራልና የክልል የግብር ሥልጣንና ስለ ግብር አጣጣል መርሆች ያብራራሉ፡፡
- የፌዴራልና የክልል የግብር የህግ ማእቀፎች ተፈፃሚ በማድረግ ሒደት ስላጋጠው ችግሮችና የመፍትሔ ሐሳቦች ይገልፃሉ፡፡
- የሕገ መንግስቱ የተደነገጉ የኢኮኖሚ ማህበራዊ የባህል ዓላማዎች ከኢንቨስትመንትና የንግድ ማእቀፎች ያላቸውን ትስስር ይዘረዝራሉ፡፡
- የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ የሚመለከቱ የሕግ ማእቀፎች ከህገ መንግስቱና ከዓላም አቀፍ ስምምነቶች ጋር በማጣጣም ተግባራዊ ለማድረግ ስለሚቻልበት ሁኔታ ይገልፃሉ፡፡
- የውል ሕግ ድንጋጌዎች በሕገ መንግስቱ ከተደነገገው የነፃነት መብት በህገመንግስቱ ከተቀመጠው ኢኮኖሚያዊ ዓላማዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻልባቸውን መንገዶች ይዘረዝራሉ፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# በወንጀል ፍትህ አስተዳደር የኢፌዲሪ ህገመንግስት መሰረታዊ መርሆዎች

## *መግቢያ*

የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሉዓላዊነት መገለጫና በአገሪቱ የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ የሆነው የኢፌዲሪ ህገ መንግስት በአገሪቱ እየተሰራባቸው ካሉ መሠረታዊ እና የሥነ ሥርዓት የህግ ማዕቀፎችና ከፍትህ ሥርዓቱ ጋር የሚያስተሳስረው በርካታ ምክንያት አለው፡፡

ህገ መንግስቱ ከወንጀል ህግ ማዕቀፎች ማለትም የወንጀሎቹን ይዘትና የሚያስከትሉትን ቅጣት መጠንና ዓይነት በዝርዝር ከሚደነግገው የወንጀል ህግና ህጉ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ሥርዓት ከሚደነግገው የወንጀል የሥነ ሥርዓት ህግ እና እነዚህ የህግ ማዕቀፎች ተግባራዊ ከሚያደርጉ የፍትህ አካላት አደራጃጀትና አሰራር በሌላ

አነጋገር ከወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ ጋር በጥብቅ የሚተሳሰርባቸው መሠረታዊ ምክንያቶች አሉ፡፡

በመጀመሪያ የወንጀል የህግ ማዕቀፎቹና የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ አሠራርና እንቅስቃሴ ከህገ መንግስቱ መርሆዎችና መሠረታዊ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣሙና ህገ መንግስታዊ መርሆችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ቅርፅና ይዘት ያላቸውን ህጎች ህግ አውጪው እንዲያወጅ ያስገድዳል፡፡

በወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ ተዋናይ የሆኑ የመንግስት አካላት የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ በህገ መንግስቱ የተደነገጉ መርሆዎችን እና በህገ መንግስቱ ዕውቅና እና ጥበቃ የተሰጣቸው ሰብዓዊ መብቶችና መሠረታዊ ነፃነቶች በተሟላ ሁኔታ የሚያከብርና የሚያስከብር እንዲሆን ግዴታና ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን በግልፅ ይደነግጋል፡፡[1]

በሌላ አነጋገር ህገ መንግስቱ የወንጀል የህግ ማዕቀፎች በይዘታቸው ህገ መንግስታዊ እንዲሆኑ "ኮንስቲቲዩሽናል ክሪሚናል ሎው" እንዲታወጅ በማድረግና የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ህገ መንግስቱን መሠረት ያደረገ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል ህጋዊ መሠረት ይጥላል፡፡ የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ የሚሠራባቸው ህጎችም ሆነ የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ አመለካከትና የሥራ ባህል በፊት ከነበሩት ሥርዓቶች የተለየና በህገ መንግስቱ መርሆዎችና ድንጋጌዎች የታነፀ እንደሆኑ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በፌዴራል መንግስትም ሆነ በክልል መንግስታት የሚወጡ የወንጀል የህግ ማዕቀፎች የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ዕውን ለማድረግ የሚፈልጉትን ህገ መንግስታዊ ራዕይ ዕውን ለማድረግ የሚያስችሉና ህገ መንግስታዊ ግቦችን ለማሳካት አስፈላጊ የሆነ ይዘት ያላቸው ዝርዝር ድንጋጌዎች እንዲኖራቸው ገዢ ደንቦችን ይደነግጋል፡፡ ህግ አውጭው በየዕለቱ የወንጀል የህግ ማዕቀፎችን እያጠና የጎደሉትን እንዲያሟላ መሻሻል ያለበትን እንዲያሻሽል ህገ መንግስቲዊ ኃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡

የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ በዕለት ከዕለት የሥራ ዕቅድና እንቅስቃሴ በተናጠል በየአካባቢው የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ከመከላከልና አጥፊዎች ለፍርድ እንዲቀርቡ በማድረግ ሣይወስን ህገመንግስታዊ ራዕዩን ዕውን ለማድረግ ህገ መንግስታዊ ግቦችን ማሳካት መሠረታዊ ዓላማው ያደረገ የፌዴራልና የክልል የወንጀል ፍትህ ስርዓት ለማዋቀር ለመገንባት ህጋዊ መሰረት ይጥላል፡፡ የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ የህገ

መንግስቱን መሠረታዊ ዓላማ ለማሣካት የሚችል የወንጀል መከላከል የወንጀል ምርመራና የክስና ፍትሐዊ የፍርድ ሂደት ለማከናወን የሚችል ሁለገብ ጥናት እንዲያጠኑ በጥናቱ ላይ የተመሰረተ ዕቅድና ተግባራዊ እንቅስቃሴ የማከናወን መሠረታዊ ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለባቸው ግልፅ ያደርጋል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከተው ህገ መንግስቱ የወንጀል የህግ ማዕቀፎችና የወንጀል ፍትህ ሥርዓቱ እንቅስቃሴ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና ህገ መንግስታዊ እንዲሆን በማድረግና የወንጀል የህግ ማዕቀፎችና የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ የህገ መንግስቱን ራዕይና ግብ ለማሳካት የሚችል መሠረታዊ ዓላማ እንዲኖራቸውና፣የህግ መንግስቱን ግቦችና ዓላማዎችም ለማሣካት የሚችል ቅርፅና ይዘት እንዲሁም የማስፈፀም አቅም እንዲያዳብሩ በማድረግ ህገ መንግስታዊ መሠረት ይጥላል፡፡

## 1.1. <u>የወንጀል ህግና የህገ መንግስታዊ ራዕይና ግቦች</u>

### (ሀ)የወንጀል ህግና ህገ መንግስታዊ ራዕይና ግቦች በጠቅላላው

ከላይ በመግቢያው እንደተገለፀው የኢፌዲሪ ህገ መንግስት የወንጀል የህግ ማዕቀፎቹ ሊኖራቸው የሚገባውን ቅርፅና ይዘት በመወሰንና የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ አሠራር፣ የሥራ ባህልና አመለካከት ገዥ የሆኑ መርሆዎችንና ድንጋጌዎችን በመደንገግ የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ በሁለተናዊ መልኩ ህገ መንግስታዊ እንዲሆን ህጋዊ መሰረቶችን ይጥላል፡፡ ይኸ እንዳለ ሆኖ ህገ መንግስቱ ከዚህ ሰፋ ባለ ገፅታው የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱን ጠቅላላ እንቅስቃሴ የሚቆጣጠርበትን ገዢ አስተሳሰቦች በውስጡ አካትቶ የያዘ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ህገ መንግስቱ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ያላቸውን አገራዊ ራዕይ ዕውን ለማድረግና ያስቀመጧቸውን ህገ መንግስታዊ ግቦች ለማሳካት እንደሚያስችሉ በማመን በጠቅላላ አገላለፅ ያስቀመጧቸውን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀመሮች ለመግለፅና ለመሸከም የሚችሉ ሰፋፊ መርሆዎችንና ፅንሰ ሀሳቦችን ያቀፉ ድንጋጌዎችን የያዘ ሰነድ ነው፡፡

የኢፌድሪ ህገ መንግስት የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የግለሰቦች መብትና ነፃነት የተረጋገጠበት የብሔር ብሔረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት በተሟላ ሁኔታ የተከበረባት የበለፀገች ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ ኢትዮጵያን

ለመመሥረት ያላቸውን ራዕይ ዕውን ለማድረግ የሚያስችሉ ናቸው ተብለው የታመነባቸውና

- በአገሪቱ ውስጥ ዘላቂ ዋስትና ያለው ሰላም ለማረጋገጥ
- በአገሪቱ ውስጥ ህዝባዊ ዋስትና ያለው የፀና ዲሞክራሲ ለማስፈን
- በህግ የበላይነትና በኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፈቃድ ላይ የተመሠረተ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብና አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመገንባት ያስቀመጡትን ህገ መንግስታዊ ግብ ለማሣካት በማሰብ በተወካዮቻቸው አማካኝነት ያፀደቁትና በልዩ ሥርዓት የታወጀ የአገሪቱ የበላይ ህግ ነው፡፡

ስለሆነም የወንጀል የህግ ማዕቀፎች መሰረታዊ ዓላማ ቅርፅና ይዘት እንደዚሁም የወንጀል የፍትህ ስርዓቱ ሁለገብ እንቅስቃሴ ከላይ የተገለፀውን ህገ መንግስታዊ ራእይና ህገ መንግስታዊ ግቦች ለማሳካት የሚችል መሆን የሚገባው ነው፡፡ ምክንያቱም የህገ መንግስቱን ራዕይ ዕውን ለማድረግና ህገ መንግስቱ መሰረታዊ ግብ አድርጎ ያስቀመጣቸውን ዘላቂና ዋስትና ያለው ሰላም ለማረጋገጥ የህግ የበላይነትና ልዕልና የሰፈነበት ህዝባዊ መሰረት ያለው የፀና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ ከባድ ህገ መንግስታዊ ኃላፊነትና ተልዕኮ ቁልፍና ወሳኝ መሆኑ ነው፡፡ የወንጀል ህግና የወንጀል የፍትህ ስርዓቱ ወሳኝ ሚናም፡-

- በአገራችን ዘላቂና ዋስትና ያለው ሰላም ለማረጋገጥ የሚቻለው በአገራዊ ደህንነት በመንግስትና በህዝብ ጥቅም በግለሰቦች ደህንነትና መብት ላይ የሚፈፀሙ የወንጀል ድርጊት ዝግጅቶችና ሴራዎችን አስቀድሞ ለመከላከል ሲቻልና ወንጀሎቹ ከተፈፀሙ አጥፊዎችን በህግ ሥርዓት ተከታትሎ ለፍርድ ማቅረብና ለማስቀጣት ሲቻል መሆኑ ብዙ ማብራሪያ የሚያስፈልገው አይደለም፡፡
- በአገራችን የህግ የበላይነትና ልዕልና ለማስፈን የመንግስት አካላት እና ባለሥልጣናት እንደዚሁም ማናቸውም ሰው የዕለት ከዕለት ኑሮውን እና ተግባሩን ህግና ህግን መሰረት በማድረግ ለማከናወን የሚችል ሲሆንና ህግን በመጣስ የሌላውን ሰው የሲቪል ሌሎች መሰረታዊ መብትና ነፃነት የጣሱ ሰዎች በአገሪቱ አየተሰራባቸው ባሉ የህግ ማዕቀፎች መሰረት በዘር፣ቋንቋ፣የፖለቲካ አቋምና በሌሎች ማህበራዊ አቋማቸው ምክንያት ልዩነት ሣይደረግ ተጠያቂ ማድረግና ተጎጂዎች መብታቸውን በማስከበር ሲችሉና በደረሰባቸው ጉዳት ተገቢውን ካሣ ለማግኘት የሚችሉበት የህግ ማዕቀፍ ሲኖርና ህጉን የሚተገብር የፍትህ ስርዓትና መገንባት ሲቻል ነው፡፡

- በአገሪቱ ህዝባዊ ዋስትና ያለው የፀና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የመንግስት አካላት፡ የመንግስት ባለስልጣናት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የንግድ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማህበራትና ማንኛውም ሰው የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴውን በህገ መንግስቱና ሌሎች የህግ ማዕቀፎችና ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ የማከናወን የዳበረ ባህል ሲያዳብሩና የምርጫ ውድድሮች ጨምሮ ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ህግና ሥርዓትን መሰረት በማድረግ የሚከናወኑ ሲሆን ነው፡፡ ይህንን ለማረጋገጥ ህግ የሚጥሱ የመንግስት ባለስልጣናት፣ ፖለቲካ ድርጅት አመራሮች፣ አባሎች ደጋፊዎችና የፖለቲካ ድርጅቶችንና ሌሎች ህግ ወለድና የተፈጥሮ ሰዎች በህግ መሰረት ተጠያቂ ለማድረግ የሚችል የወንጀል የህግ ማዕቀፍና የወንጀል የፍትህ ስርዓት ሲኖር ነው፡፡
- በአገሪቱ የህግ የበላይነትና ልዕልና የተረጋገጠበት አንድ የኢኮኖሚና አንድ የፖለቲካ ሥርዓት ለመገንባት የአገሪቱን ሰላምና ደህንነት የሚያናጉ ከማናቸውም [3]አኳያ የሚፈፅሙ ጥቃቶች ለመከላከል ሲቻል የአገሪቱን ሰላምና ደህንነት የሚያናጉ የህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥሉ የወንጀል ስራዎች ሰላማዊ ኑሮ የሚያውኩ የተቀባበሩ የሽብርና ሌሎች የወንጀል ድርጊቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመከላከል ሲቻልና ወንጀል የተፈፀመ ጊዜ አጥፊዎች ለፍርድ በማቅረብ ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ ሲቻል ነው፡፡ እነዚህ መሰረታዊ ነጥቦች የጉዳዩን ተያያዥነት ለማሳየት በአመላካችነት ያቀረቡ ሲሆን ሌሎች በርካታ ነጥቦችን በመዘርዘር የወንጀል የፍትህ ሥርዓት የህገ መንግስቱን ራዕይ ዕውን በማድረግና ህገ መንግስታዊ ግቦችን ለማሣካት ያለበትን ከባድ ኃላፊነት ለማሳየት ይቻላል፡፡

ህገ መንግስታዊ ራዕዩንና ህገ መንግስታዊ ግቦችን ለማሣካት በአገሪቱ በተለያየ መንገድ የሚከሰቱ የተለያየ ባህሪ ባላቸው ተዋናዮች የሚፈፀሙ፣ የተፈጠረና ሊፈፀሙ የሚችሉ የተለያዩ ወንጀሎችን መሰረታዊ ይዘት ባህሪና የሚያስከትሉትን ቅጣት በተሟላ ሁኔታ የሚዘረዝር የወንጀል ህግ መሟላት አለበት፡፡ እንደዚሁም የወንጀል ህጉን የአፈፃፀም ሥርዓት የሚደነግጉ ከህገ መንግስቱ ድንጋጌ ጋር የሚጣጣሙ የወንጀል የህግ ማዕቀፎች መሟላት አለባቸው፡፡ በሌላ በኩል የህግ ማዕቀፎቹ መሟላት ብቻውን በቂ ባለመሆኑ የወንጀል ሥነ ስርዓት የህግ ማዕቀፎችን ህገ መንግስታዊ ግቦቹና በማሳካት በኩል ያላቸውን ፋይዳ በመረዳት የወንጀል የህግ ማዕቀፎችን ተግባራዊ ሊያደርጉ የሚችሉ ለአንድ ግብ የሚሰሩ ነገር ግን የተለያየ የስራ ድርሻ እና ኃላፊነት

ያላቸው የፍትህ አካላትን ማዋቀርና የፍትህ አካላቱን የማስፈፀም ብቃት መገንባት አለበት፡፡ ከዚህ አንፃር አሁን ሥራ ላይ ያሉ የወንጀል የህግ ማዕቀፎች ይዘት የፌዴራልና የክልል እና የፍትህ አካላት አደረጃጀት አሠራርና አመለካከት የህገ መንግስቱን መሠረታዊ ግቦች ለማሣካት የሚያስችሉና የህገ መንግስቱን ግብ የትኩረት ማዕከል በማድረግ የታወጁና የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ናቸው ወይ? የሚለውን ጥያቄ በማንሣት ለጥያቄው ምላሽ ለመስጠት ግልፅ ውይይት ማድረግ ያስፈልገናል፡

## (ለ) ህገ መንግስታዊ ግቦችና የወንጀል ህግ መሠረታዊ አላማ፡-

በህግ ማዕቀፎቹም ሆነ በፍትህ አካላቱ አደረጃጀት አሠራርና አመለካከት ላይ የሚታዩ ጉድለቶች በውይይት በዝርዝር የሚታዩ ሆኖ አገሪቱ በፌዴራልና በክልል የወንጀል የፍትህ አካላትን በማዋቀርና የወንጀል የህግ ማዕቀፎችን ከህገ መንግስቱ ጋር በሚጣጣም መንገድ ለማሻሻልና የፍትህ አካላቱን የማስፈፀም አቅም ለመገንባት እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡ በአገሪቱ እየተደረገ ያለው ህገ መንግስታዊ የለውጥ እንቅስቃሴ ውጤት የሆነው የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ ከላይ የገለፅናቸውን ህገ መንግስታዊ ግቦችን ማሣካት የወንጀል ህጉ መሠረታዊ ዓላማ መሆኑን “የወንጀል ህግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን የመንግስትን የሕዝቦቹን የነዋሪዎቹን ሰላም ደህንነት ሥርዓት መብትና ጥቅም መጠበቅና “ማረጋገጥ ነው” በማለት በአንቀፅ 1 በመጀመሪያው ፓራግራፍ ደንግጓል፡፡ የኢፌዲሪ የወንጀል ሕግ በጥቅል አገላለፅ የደነገገው የወንጀል ህጉና የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ መሠረታዊ ዓላማ ይዘት ጠቀሜታ በዝርዝር ሲታይ ከላይ የተገለፀውን ህገ መግንስታዊ ራዕይ ህገ መንገስታዊ ግቦች ማሣካት እንቅፋት የሚሆኑ ከባድና ቀላል ወንጀሎች የመከላከልና ወንጀል ሲፈፀም ጥፋተኞች እንዲቀጡ በርካታ ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ ነው፡፡

የወንጀል ህጉ አንቀፅ 1 የመጀመሪያው ፓራግራፍ የተደነገገው መሠረታዊ ዓላማ በዝርዝር ሲተነተን የወንጀል የፍትህ ስርዓቱ፣

- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአገሪቱን ፖለቲካዊ ሉአላዊነት የሚጥሱና የግዛት አንድነት በመጣስ አገሪቱ የመከላከያ ሀይሏን የውጭ ደህንነቷን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን መከላከልና ጥፋተኞች እንዲቀጡ በማድረግ

የሀገሪቱን ሠላም አገራዊ ደህንነቷን እና ህልውናዋን እንደዚሁም በሀገሪቱ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ህጋዊ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ግዴታና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን፣

- በኢፌዲሪ ህገ መንግስት መሠረት የመንግስት ሥልጣን ይዘው አገሪቱንና ክልሎችን የሚመሩና የሚያስተዳድሩ የፌዴራልና የክልል መንግስት ሰላምና ደህንነት የሚጥሱ ወንጀሎችና የመንግስት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙና በህገ መንግስቱና በህገ መንግስታዊ ሥርዓቱ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በብቃት በመከላከልና አጥፊዎች በፍርድ እንዲጠየቁ የማድረግ ህገ መንግስታዊ ተልዕኮና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን፣
- በማናቸውም የአገሪቱ ግዛት ክልል የሚገኝ የህብረተሰብ ክፍል ወይም ሕዝብ ሰላማዊ ኑሮ የሚያውኩ በህዝብ የኢኮኖሚ የትራንስፖርትና መገናኛ የውሃ እና ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ደህንነት መብትና ጥቅም ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን መከላከል እና አጥፊዎችን ለፍርድ የማቅረብ ግዴታና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን፣
- ሌሎች የተፈጥሮና የህግ ሰዎች በህይወት የመኖር መብትና ህልውና ንብረት፣ መብትና ጥቅም በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የመከላከልና አጥፊዎችን ለፍርድ የማቅረብ ኃላፊነት ያለበት መሆኑንና
- በአገሪቱ ዓለም አቀፍ ግዴታ የገባችላቸውን ዓላም አቀፍ ህግጋት በመተላለፍ በአገሪቱ ወይም በሌሎች አገሮች ሰላም ደህንነት መብትና ጥቅም ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች በመከላከልና በህጋዊ መንገድ በመቆጣጠር መሠረታዊ አላማው መሆኑን በአጭርና ጥቅል አገላለፅ የሚደነገግ ነው፡፡

በወንጀል ህጉ አንቀፅ 1 የመጀመሪያው ፓራግራፍ ሰላም፣ ደህንነት፣ ሥርዓት፣ መብትና ጥቅም የሚሉት አገላለፆች የየራሳቸው ትርጉም እና መልዕክት ያላቸው ናቸው፡፡ የህገ መንግስቱ ራይና ግብ ለማሣካት ይህንን የወንጀል ህጉንና የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ መሠረታዊ ዓላማ በተናጠል ሣይሆን የወንጀል ህጉ በጠቅላላውና እያንዳንዱ የወንጀል የህግ ድንጋጌ ህገ መንግስቱ ግብ ከማሣካትና የወንጀል ህጉ መሠረታዊ ዓላማ ለማረጋገጥ ያለውን ፋይዳ ባገናዘበ መንገድ መረዳት መተርጎምና ተፈፃሚ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የወንጀል ህጉና የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ ህገ መንግስታዊ ግቦቹን እና መሠረታዊ ዓላማውን ለማሣካት ሁለት አበይት ተግባራት ውጤታማ በሆነ መንገድ ማከናወን አለበት፡፡ ይኸውም ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት የቅድመ ወንጀል መከላከል ተግባራትን መፈፀምና ወንጀል በተፈፀመ ጊዜ በአፀፋ የማሠሩ የወንጀል መከላከል እርምጃዎችን መውሰድ ናቸው፡፡ እነዚህን ሁለት ተግባራት በርካታ የውጭ ፀሐፊዎች (ፕሮ አክቲቨ ክራይም ፕራቬንሽን እና ሪአክቲቨ ክራይም ፕራሴንሽን) በማለት ይገልጿቸዋል፡፡ የኢፌዲሪ የወንጀል ህግም የወንጀል ህግ ቀዳሚ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ወንጀል በተፈፀመ ጊዜ አጥፊዎች ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲታቀቡ ለሌሎች ማስተማሪያ እንደሆኑ ወይም እንዲሁም እንዲታረሙ ማድረግ መሆኑን በአንቀፅ 1 ሁለተኛው ፓራግራፍ በግልፅ ደንግጓል፡፡

የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ የመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል መከላከል ተግባራትን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፈፀም የዕለት ከዕለት የጥበቃና የፓትሮል ሥራ ህብርተሰቡን ባሳተፈ መንገድ መፈፀም አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የወንጀል መንስኤዎችን የወንጀል ፈፃሚዎቹንና የወንጀል ሰለባ የሆኑ ሰዎች እድሜ ፆታ ትምህርትና ማህበራዊ ሁኔታ ወይም በንብረት ላይ ወንጀሎች የሚፈፀሙባቸውን ጊዜዎች እና ሥፍራዎች በበቂ ሁኔታ መረጃ በማሰባሰብ በመተንተንና በማጥናት ወንጀሎቹን ለመከላከልና ለመቀነስ የሚያስችሉ የተለያዩ ሁለተኛ ደረጃ የወንጀል መከላከል ተግባራትን በማከናወን ወንጀልንና የወንጀል ስጋትን ለመቀነስ ውጤታማ እንቅስቃሴ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ አስተማማኝ የሆነ የወንጀል መረጃ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋት መረጃዎቹን በሚያሰባስብ በሚያጠናና የሚተነትን የወንጀል የመረጃና የጥናት ማዕከል በየአካባቢው በክልልና በአገር አቀፍ ደረጃ ማቋቋምና አገራዊ ክልላዊና አካባቢያዊ ይዘትና ተፈፃሚነት ያላቸው የተለያዩ የወንጀል መከላከል(ስትራቴጂ) ስልቶችን በመንደፍና የድርጊት መርሀ ግብር በመቅረፅ ውጤታማ የወንጀል መከላከል ተግባር ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከላይ ከተገለፁት የቅድመ ወንጀል መከላከል ተግባራት በተጨማሪ ወንጀል ከተፈፀመ በኂላ ፍትሐዊ በሆነ የፍርድ ሂደት አጥፊዎች ጥፋተኛ እንዲባሉና የአጥፊዎቹን የግል ሁኔታ፣ የወንጀሉን አፈፃፀምና የወንጀሉን ከባድነትና ያስከተለው ወይም ሊያስከትል የነበረውን ጉዳት ያገናዘበ የወንጀል ህጉን መሠረታዊ ዓላማ ለማሣካት የሚችል ቅጣትና

የጥንቃቄ እርምጃዎች ተፈፃሚ ማድረግ አለባቸው፡፡ የወንጀል የፍትህ ስርዓቱ የወንጀል ህጉ በተግባር ሲተረጎም ለአጥፊዎቹና ለህብረተሰቡ በማሣየት አጥፊዎቹ ወንጀል ከመፈፀም እንዲጠነቀቁ ወንጀል የመፈፀም ፍላጎትና ሀሳብ ያላቸው ሀሳባቸውን እንዲተው በማድረግና ተደጋጋሚ ወንጀለኝነትን በመቀነስ ወንጀልና የወንጀል ስጋትን ለመቀነስ የሚጥሩ መሆን አለባቸው፡፡

በአጠቃላይ የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ የተቀናጀና ውጤታማ የወንጀል መከላከል የወንጀል ምርመራ የክስና ሙግት በማከናወንና አጥፊዎች ለጥፋታቸው ተጠያቂ እንደሆኑ በማድረግ የአገሪቱ ዘላቂ ሰላም ደህንነት ለማረጋገጥ፣ የህግ የበላይነትና ልዕልና የተረጋገጠበት የፀና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የተያዘውን ህገ መንግስታዊ ግብ ለማሣካትና ህገ መንግስታዊ ራዕዩን ዕውን ለማድረግ የተጣለባቸውን ከባድ ህገ መንግስታዊ ኃላፊነት ለመወጣት ጥረት ማድረግ ያለባቸው መሆኑን በህገ መንግስቱ መግቢያ የተገለፁት ህገ መንግስታዊ ግቦችና እና የወንጀል ህጉንና የወንጀል የፍትህ ሥርዓት መሠረታዊ ዓላማና ግብ ከሚደነግገው ከወንጀል ህጉ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. አሁን ያሉት የወንጀል የህግ ማዕቀፎችና የፌዴራልና በክልል ደረጃ የተዋቀሩ የፍትህ አካላት አደረጃጀት አሠራርና አመለካከት የህገ መንግስቱን ራዕይና ህገ መንግስታዊ ግቦችን የወንጀል ህጉን መሠረታዊ ዓላማ ለማሣካት የሚያስችል ነው ብለው ያስባሉ? ለምን?
2. ህገ መንግስታዊ ራዕይን ዕውን ለማድረግና ህገ መንግስታዊ ግቦችን በተሟላ ሁኔታ ለማሣካት መሟላት እና መሻሻል ያለባቸው የህግ ማዕቀፎች የፍትህ አካላት አደረጃጀቶች አሠራሮችና በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ የሚንፀባረቁ አመለካከቶች አሉ ብለው ያስባሉ? አሉ ብለው የሚያስቡ ከሆነ በዝርዝር ይግለፁ?

## 1.2 የህገ መንግስት የበላይነትና ልዕልና እና የወንጀል ህግ

የኢፌዲሪ ህገ መንግስት የአገሪቱ የበላይ ሕግ መሆኑ የህገ መንግስቱ መሠረታዊ መርህ ሆኖ ተደንግጓል፡፡ በአገሪቱ የህገ መንግስቱ የበላይነትና ልዕልና በህገ መንግስቱ ሲታወጅ በመጀመሪያ በፌዴራል በክልል በማናቸውም ደረጃ የሚገኝ ማናቸውም የመንግስት

አካል እና ባለሥልጣን ውሣኔ የህገ መንግስቱን መሠረታዊ መርሆች እሴቶችና ድንጋጌዎች የሚያከብር መሆን አለበት፡፡ ማናቸውም ህግ የመንግስት አካል ወይም ስልጣን ውሣኔ ህገ መንግስቱን የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት የበላይነት የፌዴራልና በክልል ደረጃ የሚወጡ ህጎች የመንግስት አካላትን ባለሥልጣናት ውሣኔ ህገ መንግስታዊ መሆን ያለበት መሆኑን መሠረታዊ መርህ አድርጎ በመደንገግ የተወሰነ አይደለም፡፡ ህገ መንግስቱ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም ልማዳዊ አሠራር ከህገ መንግስቱ መርሆችና ድንጋጌዎች ጋር የማይቃረን መሆን እንዳለበትና የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም ልማዳዊ አሠራር ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን ይደነግጋል፡፡

ህገ መንግስቱ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሉዓላዊነት መገለጫና የሀገሪቱ የበላይ ህግ በመሆኑ ማንኛውም ዜጋ የመንግስት አካላት የፖለቲካ ድርጅቶች የንግድ ማህበሮችና ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው ሕገመንግስቱን የማስከበርና ለሕገ መንግስቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑና በህገ መንግስቱ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ በማናቸውም አኳኋን የመንግስት ሥልጣን መያዝ የተከለከለ እንደሆነ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የአገሪቱ ህግ አካል መሆናቸው የህገ መንግስት የበላይነት መገለጫና ማረጋገጫ መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 9 መሠረታዊ መርህ ሆኖ ተደንግጓል፡፡

የኢፌዴሪ ህገ መንግስት የበላይነት መሠረታዊ ይዘቱ መገለጫዎቹና በህገ መንግስቱ የተደነገጉ ክልከላዎቹ ከህገመንግስቱ አንቀፅ 8(2)ና አንቀፅ 9 በጠቅላላ አገላለፅ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም የህገ መንግስቱ አንቀፅ 9 ድንጋጌዎች የተደነገገውን መርህ በህገ መንግስቱ በመደንገጉ ብቻ ተግባራዊ አይሆኑም፡፡ የህገ መንግስት የበላይነትና ልዕልና የሚከበረው ሕገ መንግስቱንና ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ለማፍረሥና የመንግስት ሥልጣን በህገ መንግስቱ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ለመያዝ በዋና ወንጀል አድራጊነት እና በሌላ የወንጀል ተካፋይነት የሚንቀሣቀሡ የተፈጥሮና የህግ ሰዎች በወንጀል ተጠያቂ የሚሆኑበት የህግ ማዕቀፍ ሲኖርና የወንጀል ህጉ በተሟላ ሁኔታ በማስፈፀም ነው፡፡

የህገ መንግስቱ የበላይነትና ልዕልና ሊረጋገጥና ሊከበር የሚችለው በወንጀል ተጠያቂ የሚያደርጉ የህገ መንግስቱን መሠረታዊ መርሆችና ድንጋጌዎች እንደዚሁም በህገ

መንግስቱ ዕውቅና ጥበቃ የተሰጣቸውን የግለሰቦችም ሆነ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች መብትና ነፃነት የሚጥስ ኃላፊነት የጎደለው ውሣኔ የሚሰጡ የመንግስት ባለሥልጣናት የሰጧቸው ውሣኔዎቻቸው ህገ መንግስታዊ ባለመሆናቸው ተፈፃሚነት እንዳይኖረው ስልጣን ባለው አካል በመወሰን ብቻ ሣይሆን ባለስልጣናቱ ለፈፀሙት የመብት ጥሰትና የወንጀል ድርጊት ተጠያቂ የሚደርግ የተሟላ የወንጀል የህግ ማዕቀፍ ሲኖርና ህጉን ተግባራዊ ለማድረግ ሲቻል ነው፡፡

የህገ መንግስቱ የበላይነትና ልዕልና ለማስፈን የሚችለው በህገ መንግስቱ ጥበቃና ዋስትና የተሰጣቸው የግለሰቦችና የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት የሚጥስ ተግባራትን የሚፈፅሙ የተፈጥሮ ሰዎች የፖለቲካ ድርጅቶች የንግድ ማህበሮች እና ሌሎች ማህበሮች እንደዚሁም ባለሥልጣኖቻቸው በወንጀል ተጠያቂ የሚሆኑበት የተሟላ የህግ ማዕቀፍና ህጉን የሚተገብር የወንጀል የፍትህ ሥርዓት ሲኖር ነው፡፡ ከህገ መንግስቱ መሠረታዊ መርሆች ድንጋጌዎችና እሴቶች ጋር የሚቃረኑ ልማዳዊ ድርጊቶች በአገሪቱ ግዛት ክልል ተፈፃሚነት እንዳይኖራቸው በማድረግ የህገ መንግስቱን የበላይነት ለማረጋገጥ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚጥሱና ጉዳት የሚያስከትሉ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚፈፅሙ ሰዎች በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችል የወንጀል የህግ ማዕቀፍ ሲኖርና ህጉ በተግባር ላይ ማዋል ሲቻል ነው፡፡

የህገ መንግስቱ የበላይነት እና ልዕልና በተሟላ ሁኔታ ተፈፃሚ የሚሆነው አገሪቱ የዓለም አቀፍ ደረጃ የገባቻቸውን ግዴታዎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሚጥሱና በአገሪቱ ግዛት ክልል ጥበቃና ከለላ ማግኘት ያለባቸው የሌሎች አገር መንግስታት ክብር መብትና ጥቅም ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች መብትና ጥቅም በመጣስ ወንጀል የሚፈፅሙ ድርጊቶች በወንጀልነት የሚደነግግ የወንጀል የህግ ማዕቀፍ ሲሟላና የህግ ማዕቀፍ ተግባራዊ ለማድረግ ሲቻል ነው፡፡

በኢፌዲሪ የወንጀል ህግ በህገ መንግስቱና በህገ መንግስታዊ ሥርዓት ላይ የሚደረጉ በተፈጥሮ ወይም ህግ ወለድ ሰዎች የሚፈፀሙ የሽብር የአመፅ ወንጀሎች በዝርዝር በመደንገግ ከህገ መንግስቱ ሥርዓት ውጭ ሥልጣን ለመያዝና መንግስት ስልጣን በሀይልና በአመፅ ለመገልበጥ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ከባድ ቅጣት የሚያስከትሉ መሆናቸውን ይደነግጋል፡፡ ዓለም አቀፍ ህግጋትንና አገሪቱ የገባቸውን ዓለም አቀፍ

ስምምነት  በመጣስ በሌሎች አገሮች ክብር ጥቅምና መብት ላይ የሚፈፀሙ ድርጊቶችን የወንጀል ተጠያቂነትየሚያስከትሉወንጀሎችመሆናቸውን በግልፅ ደንግጓል፡፡

የህገ መንግስቱ ዕውቅና እና ጥበቃ የተሰጣቸውን መብቶች የሚጥሱ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚፈፅሙ ሰዎች በወንጀል ተጠያቂ የሚያደርጉ ድንጋጌዎች በማካተት የወንጀል ህጉ በህገ መንግስታዊ ሥርዓትና በአገራዊ ደህንነት ላይ ወንጀል ድርጊቶችን ለመፈፀም የሚደረጉ ሙከራዎች እና የወንጀል ድርጊቶች ብቻ ሣይሆን እነዚህን ወንጀሎች ለመፈፀም የተደረጉ ግዙፍነት ያላቸው የመሰናዳት ተግባራትንና ግዙፍነት የሌላቸውን የመሰናዳት ተግባራት መፈፀም በወንጀል ህግ አንቀፅ 26 ከተደነገገው ጠቅላላ መርህ በልዩ ሁኔታ የወንጀል ኃላፊነትን የሚያስከትሉወንጀሎች መሆናቸውን በግልፅ ደንግጓል፡፡ የወንጀል ህጉበህገመንግስታዊ ሥርዓትማስከበር ዓላማ ያደረጉት ድንጋጌዎች በማካተት የታወጀ ነው፡፡ የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ እነዚህን የህገ መንግስቱን የበላይነት ልዕልና ለማረጋገጥ ዓላማ ያላቸውን የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች በተሟላ ሁኔታ  ተግባራዊ በማድረግ የህገ መንግስቱን የበላይነትና ልዕልና ለማረጋገጥ የበኩላቸውን ኃላፊነት ለመወጣት የማያቋርጥ ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. በህገ መንግስታዊ ሥርዓቱ እና በመንግስትና በአገራዊ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ከሌሎች ወንጀሎች የሚለዩባቸው መሠረታዊ ባህሪዎች አሉ ብለው ያስባሉ? ለምን?
2. በህገ መንግስትና በአገራዊ ደህንነትና ጥቅም ላይ ወንጀል ለመፈፀም የሚደረጉ ግዙፍነት ያላቸውን ግዙፍነት የሌላቸው የመሰናዳት ተግባራት የወንጀል ኃላፊነትና ቅጣት የሚያስከትሉ መሆናቸውን በወንጀል ህጉ መደንገጉ የህገ መንግስቱን የበላይነትና ልዕልና ከማረጋገጥ አንፃር ተገቢነት አለው ብለው ያስባሉ? ለምን?

### 1.3 የመንግስት ሰብዓዊ መብትን የማክበር የማስከበር ግዴታና የወንጀል ህግ

ሰብአዊ መብቶችና  ነፃነቶች ከሰው  ልጅ ተፈጥሮ  የመነጩ  የማይጣሱና የማይገፈፉ መሆናቸውን የህገ  መንግስቱ አንቀፅ 10(1) መሠረታዊ  መርህ ሆኖ ተደንግጓል፡፡ በአገሪቱ  የዜጎች፣ የብሔር ብሔረሰቦችና የህዝቦች  ሰብዓዊና  ዴሞክራሲዊ  መብቶች የሚከበሩ  ስለመሆኑ  በመሠረታዊ መርህነት የተደነገገ ከመሆኑም በላይ በማንኛውም

ደረጃ የሚገኝ የፌዴራል መንግስትና የክልል ህግ አውጭ ሕግ አስፈፃሚና የዳኝነት አካል በህገ መንግስቱ ምዕራፍ ሶስት በተካተቱ የሰብዓዊ መብትና መሠረታዊ ነፃነቶች ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ ያለባቸው ስለመሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 13 (1) ተደንግጓል፡፡

በህገ መንግስቱ ምዕራፍ ሶስት የተዘረዘሩት ሰብዓዊ መብቶች እና መሰረታዊ ነፃነቶች ድንጋጌዎች በተናጠል ብቻቸውን ሣይሆን ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ህግጋት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ዓለም አቀፍ ሰነዶችና መርሆች ጋር በተጣጣመ መንገድ መተርጎም እንዳለባቸው ህገ መንግስቱ በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር መንግስት በህገ መንግስቱ ዕውቅና እና ጥበቃ የተሰጣቸውን ሰብዓዊ መብቶችና መሠረታዊ ነፃነቶች አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ልምድ ህግጋት፣ አገራቱ ካፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው የተባበሩት መንግስታትና የአፍሪካ ህብረት ያወጧቸው የሰብዓዊ መብት ሰነዶችና መርሆች ጋር በሚጣጣም መንገድ መተርጎምና ተግባራዊ የማድረግ ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡

መንግስት በህገ መንግስቱና በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ህግጋትና ስምምነቶች ይዘታቸው፣ የተፈፃሚነት ወሰናቸውና ባህሪያቸው የተዘረዘሩትን የሰብዓዊ መብቶች በአገሪቱ በተሟላ ሁኔታ እንዲከበሩና እንዲተገበሩ ለማድረግ በዋነኛነት አራት ጠቅላላና መሠረታዊ ግዴታና ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑህገመንግስመንግስቱናበዚህ ዙሪያ ከተደረጉ ጥናቶች ለመረዳት ይቻላል፡፡

**ይኸውም፡-**

- የመንግስት ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር ግዴታ፣
- የመንግስት ሰብዓዊ መብቶችን የማስከበርና የመጠበቅ ግዴታ፣
- የመንግስት ሰብዓዊ መብቶችን የማሟላትና
- ሰብዓዊ መብቶችን የማቀላጠፉ ግዴታዎች ናቸው፡፡

(ሀ) ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር ግዴታና የወንጀል ህግ

የመንግስት ሰብዓዊ መብት የማክበር ግዴታ ከዝቅተኛ እርከን እስከ ከፍተኛው እርከን ድረስ ያሉ የፌዴራልና የክልል ህግ አውጭ ህግ አስፈፃሚና የዳኝነት አካላት፣

የመንግስት ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች በህገ መንግስቱ ዕውቅና ጥበቃ የተሰጣቸውን መብቶች ከመጣስ በመታቀብ ሰብዓዊ መብቶች በማክበር የዕለት ከዕለት ተግባራቸውን የሚያከናውኑ መሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ መንግስት በየደረጃው ያሉ የመንግስት ባለሥልጣናት እና የመንግስት ሠራተኞች ያላቸውን ሥልጣንና ኃላፊነት መከታ በማድረግ ሰብዓዊ መብት ከመጣስ እንዲታቀቡ ለማድረግ የሚቻልበት አንደኛው መንገድ የመንግስት ሥልጣንና ኃላፊነት በመጠቀም የሚፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥስቶችን በወንጀልነት የሚፈርጅ የወንጀል ህግ በማውጣትና እና የወንጀል ህጉን ተፈፃሚ ማድረግ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር የወንጀል ህጉ በመንግስትና በዜጎች መካከል ባለው የቀጥታ ግንኙነት (ቨርቲካል ሪሌሽንሺፕ) የመንግስት ሥልጣንና ኃላፊነት አላግባብና ከህግ ውጭ በመጠቀም የሚፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥስቶችን የወንጀል ተጠያቂነትና ሀላፊነት የሚያስከትሉ ድርጊቶች መሆናቸውን በመደንገግና የህጉን ድንጋጌ በተሟላ ሁኔታ በወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ እንዲፈፀም በማድረግ መንግስት ሰብዓዊ መብት የማክበር ግዴታውን ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚችልበት በአሳማሚ ቅጣት የታጀበ አንደኛው መንገድ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የወንጀል ህጉ የመንግስት ባለሥልጣናት አላግባብ ሥልጣናቸውን በመጠቀምና የተሰጣቸውን የሥራ ኃላፊነት ባለመወጣት የሚፈፅሟቸውን የመብት ጥስቶች በወንጀልነት በመፈረጅና የወንጀል ቅጣት በመጣል መንግስት በህገ መንግስቱና በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ህግጋት ያለበትን ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር ግዴታና ኃላፊነት መውሰድ ያለበትን አንደኛውን እርምጃ የወሰደ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ሆኖም የህጉ መኖር ብቻውን ህጉ በተግባር ላይ ስለማዋል ማረጋገጫ ሊሆን ስለማይችል የዚህ አይነት ዓላማና ግብ ያላቸውን የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ሊያሳኩት የሚፈልጉትን ግብ ከግምት ውስጥ ባስገባ መንገድ መተርጎምና ተፈፃሚ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

(ለ) <u>ሰብዓዊ መብቶችን የማስከበርና የመጠበቅ ግዴታ እና የወንጀል ህግ</u>

በህገ መንግስቱና በሰብዓዊ መብት የቃል ኪዳን ስምምነቶች የተደነገጉ መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች በመንግስት አካላትና ባለሥልጣናት ሠራተኞች ብቻ ሣይሆን በማናቸውም የተፈጥሮ ሰውና ህግ ወለድ ሰው መከበር አለባቸው፡፡ በተፈጥሮ ሰዎች የጎንዮሽ የእርስ በርስ ግንኙነት አንዱ የሌላውን መብት የሚጥስባቸው የተለያዩ

ገፅታዎች አሉ፡፡ መንግስት ሰብዓዊ መብቶችን ማክበሩና የመንግስት ባለሥልጣናት ሠራተኞች ሰብዓዊ መብት ጥሰው በሚገኙ ጊዜ ተጠያቂ የሚሆኑበት ሥርዓት በመዘርጋቱ ብቻ በአገሪቱ ግዛት ክልል ሰብዓዊ መብቶችና መሠረታዊ ነፃነቶች ገቢራዊነት ማረጋገጥ አይቻልም፡፡

በህገ መንግስቱና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ህግጋት ዋስትና እና ጥበቃ የተሰጣቸው መብቶች በተሟላ ሁኔታ ሊከበሩ የሚችሉት ሰዎች ባላቸው የዕርስ በርስ የጎንዮሽ ግንኙነት አንደኛው የሌላውን መብት እንዲያከብሩ ለማስገደድ ሲቻል ነው፡፡ ይኸም በመሆኑ መንግስት በጎንዮሽ ባሉ የሰዎች ግንኙነት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው እና የህግ ወለድ ሰዎች የሌላውን መብትና ነፃነት እንዳይጥሱ የመጠበቅና ሰብዓዊ መብትን የማስከበር ግዴታ አለበት፡፡ መንግስት ሰብዓዊ መብቶችን የማክበርና የማስከበር ግዴታ የሚወጣው አስፈላጊውን የህግ የአስተዳደርና ሌሎች እርምጃዎች በመውሰድ እንደሆነ በተለያዩ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ተደንግጓል፡፡

መንግስት በግዛት ክልሉ ውስጥ የሚኖሩና የዜጎችን በህይወት የመኖር መብት የአካል ደህንነት መብት የንብረት ባለቤት የመሆን መብት እና ሌሎች መብቶችና ነፃነቶችና ማስከበር ግዴታውን የሚወጣው መብቶቹን የሚጥሱ ድርጊቶችን የወንጀል ተጠያቂነትና ኃላፊነት የሚያስከትሉ መሆናቸውን በወንጀል ህጉ በመደንገግ መሆኑን ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ ቃል ኪዳን ስምምነት አፈፃፀም የሚከታተለው የሰብዓዊ መብት ኮሚቴ በተለያየ ጊዜ በሰጠው ሙያዊ አስተያየት ተገልጿል፡፡ በነባራዊ ዕውነታው የሰብዓዊ መብቶችን ጥስቶችን (ክሪሚናልናይዝ) ማድረግ መንግስት ሰብዓዊ መብቶችን የመጠበቅና የማስከበር ግዴታውን የሚፈፅምበት አይነተኛው መንገድ መሆኑን በንድፈ ሀሳባዊ ትንታኔዎች ሳይሆን ተግባራዊ ማስረጃዎችን በማቅረብ ለማስረዳት ይቻላል፡፡

መንግስት በሰዎች መካከል ባለው የጎንዮሽ ግንኙነት አንደኛው የሌላውን መብት እንዳይጥስ የመከላከልና የጥበቃ ሥራ የመሥራትና የሰብዓዊ መብት ጥስቶችን በወንጀል የሚያስቀጡ መሆኑን በዝርዝር በመደንገግና በወንጀል የሚያስጠይቁ የሰብዓዊ ቅጣት ጥስት የፈፀሙ ግለሰቦች እና ህግ ወለድ ሰዎች ተጠያቂ እንደሆኑና ተገቢውን ቅጣት እንዲቀጡ ማድረግ በህገ መንግስቱና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ህግጋት የተጣለበትን ሰብዓዊ መብቶች የመጠበቅና የማስከበር ግዴታውን የሚወጣበት አይነተኛው መንገድ መሆኑንመብቶቹን የሚጥሱ ድርጊቶችን ወንጀሎች መሆናቸውን በግልፅ ደንግጓል ፡፡

ከዚህ አንፃር ስናየው የተለያዩ ወንጀሎችን የፈፀሙ ሰዎች በአድረሻቸው ባለመገኘታቸው ምስክሮች ባለመቅረባቸውና ውጤታማ ምርመራ በማድረግ አጥጋቢ ማስረጃ ባለመሰባሰቡ ምክንያት በወንጀል ተጠያቂ ሳይሆኑ በሚቀርባቸው ጉዳዮች መንግስት ሰብዓዊ መብቶችን የማስከበር ግዴታና ኃላፊነቱን በመወጣት በኩል ድክመት ያለበት መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ስለሆነም የወንጀል የፍትህ ስርዓት የውድቀት መጠኑን መቀነስና የውጤታማነት መጠኑን በማሳደግ ሰብዓዊ መብቶችን የማስከበር ግዴታውን በተሟላ ሁኔታ እንዲወጣ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ አለበት፡፡

## ሐ. <u>ሰብዓዊ መብቶችን የሚሟላትና የማፋጠን ግዴታ፣እና የወንጀል ህግ</u>

መንግስት ሰብዓዊ መብቶችን አስመልክቶ ያለበትን ግዴታ የሚወጣው ሰብዓዊ መብቶችን በማክበርና በማስከበር ብቻ አይደለም፡፡ መንግስት በየወቅቱ እየጨመረ የሚሄድ በጀት በመመደብ የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን በመገንባት የኢኮኖሚ ማህበራዊና የባህል መብቶችን የማሟላት ግዴታ እንዳለበት ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 89 ድንጋጌዎችና አገሪቱ ካጸደቀችው ዓለም አቀፋ የኢኮኖሚ ማህበራዊና የባህል መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መንግስት ለኢንቨስትመንት ለስራ ፈጠራ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ፖሊሲን በማውጣትና ህጎችን በመቅረጽ የዜጎችን ስራ የማግኘት መብት የማፋጠን (ፋሲሊቴት) የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

መንግስት ከፍተኛ በጀት በመመደብ የኤሌክትሪክ፣ የስልክ የመንገድ መሰረት ልማት በመገንባት የዜጎቹን ፍላጎት ለማሟላት የሚያደርገው ጥረት ከፍተኛ ነው፡፡ መንግስት ሌሎች የትምህርት የጤና አገልግሎት እና የንጹህ ውሃ አገልግሎት ለሁሉም ለማዳረስ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ሰብዓዊ መብቶችን የማሟላት ግዴታውን ለመወጣት አይችልም፡፡ መንግስት ከፍተኛ በጀት በመመደብ የዘረጋቸው መሰረተ ልማት አውታሮች የትምህርት የጤናና ንጹህ ውሃ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት የሚያበላሹ የሚበክሉና የሚያፈርሱ የሽብር ወንጀሎችና ሌሎች ተራ የወንጀል ድርጊቶችን መከላከልና አጥፊዎች በህግ ተጠያቂ ማድረግ ሰብዓዊ መብቶችን የሚሟላት ግዴታውን በተሟላ ሁኔታ መወጣት የሚያደርገውን ጥረት የሚያግዘው እርምጃ ነው፡፡

የወንጀል ህጉ የህዝብ አገልግሎት ሰጭ የመሰረተ ልማት አውታሮች የትምህርት የጤና የውሃና ሌሎች ተቋማት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ላይ አሳማሚ ቅጣት የሚያስከትሉ ወንጀሎች መሆኑን በግልጽ በማወጅ ሰብዓዊ መብቶችን የሚሟላት ግዴታውን ለመወጣት ለሰራቸው መሰረታዊ ልማቶች የህግ ጥበቃ መስጠት ይችላል፡፡

የወንጀል የፍትህ ስርዓቱ ህጉን በተሟላ መንገድ በማስፈጸም የህብረተሰቡን አገልግሎት የማግኘት መብት ማስከበርና ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ከዚህ አንፃር የወንጀል ህጉ ከህገ መንግስቱ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## መ. <u>ለሰብዓዊ መብት ጥሰትና ጥብቅ የወንጀል ተጠያቂነት</u>

መንግስት ህገ መንግስቱና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ህግጋት ያለበትን ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር፣ ሰብአዊ መብቶችንና የማስከበርና የማሟላት ግዴታና ኃላፊነቱን ለመወጣት ሰብዓዊ መብቶቹን የሚጥሱ የተለያዩ ድርጊቶች ወንጀል መሆናቸውን የሚዘረዝር የወንጀል ህግ ማወጅ አስፈላጊ መሆኑንና ወንጀሉ ህጉም ተፈጻሚ መሆን እንዳለበት ከላይ ተገልጿል፡፡ ከላይ የተገለጸው አጠቃላይ ሁኔታ እንዳለ ሆኖ አገሪቱ ካለፈችባቸው የታሪክ ሂደቶችና በጅምላና በተቀነባበረ መንገድ ሲፈጸሙ የቆዩ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ህገ ወጥ እስር ቶርቸር ያለ ፍርድ ግድያ በመፈፀም ወንጀሎች በቂ ትምህርት በመውሰድ አሁን ባለው ህገ መንግስታዊ ስርዓት እንዳይፈጸሙ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት ጥሰቶቹ በተፈጸሙም ጊዜ ፈጻሚዎቹን ያለምንም የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ገደብ ተጠያቂ እንዲሆኑ ለማድረግና በይቅርታና በምህረት ከተጠያቂነት የማይታለፉ መሆኑን ለማረጋገጥ ህገ መንግስቱ ግልጽ ድንጋጌ ደንግጓል፡፡

የህገ መንግስቱ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 1 ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነትና በጦርነት ጊዜ በቆሰሉና በተማረኩ ወታደሮች በሲቪል ህዝብና የሲቪል ተቋሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን የሚደነግጉት የጄነቭ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ፕሮቶኮሎችና ሌሎች ስምምነቶች እና በኢትዮጵያ ህግ ለወንጀልነት የተደነገጉትየወንጀል ህጉ የይርጋ የጊዜ ገደብ የማይገድባቸውና ማንኛውም አካል በምህረት ወይም በይቅርታ ሊያልፏቸው የማይችሉ እንደሆኑ ደንግጓል፡፡

- በሰው ልጅ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (crimes against humanity)
- የሰው ዘር የማጥፋት ወንጀል (genocide)

- ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ መውሰድ/ (summary execution)
- በአስገዳጅ ሰውን መሰወር (forced disappearance)
- ኢሰብዓዊ የድብደባ ድርጊቶች (torture)

የሚፈጽሙ ሰዎች ላይ የሚቀርብ የወንጀል ክስ በይርጋ እንደማይታገድና በማናቸውም አካል ውሳኔ በምህረት ወይም በይቅርታ የማይታለፍ መሆኑን በግልጽ በመደንገግ ለእነዚህ ወንጀሎች ከሌሎች ወንጀሎች በተለየ ሁኔታ ጥብቅ የወንጀል ተጠያቂነትን ደንግጓል፡፡

ከዚህ አንፃር ህገ መንግስቱን የወንጀል ህግ ስለ ወንጀል ክስ የይርጋ ገደብ ስለ ምህረትና ይቅርታ የተደነገጉት ድንጋጌዎችና ከዚያ በኃላ በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ የወጡ የይቅርታና የምህረት አዋጆች ከእነዚህ ወንጀሎች አንዱን በፈጸመው ሰው ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መሆኑን ደንግጓል፡፡ የወንጀል የፍትህ ስርዓቱ በዓለም አቀፍ የሰብዐዊ መብት ህግጋትና በህገ መንግስቱ ጥብቅ ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ መሆናቸው የተደነገጉት ወንጀሎች ከመፈጸማቸው በፊት ለመከላከል ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እነዚህ ወንጀሎች ሲፈጸሙ ህገ መንግስቱ የደነገገውን ጥብቅ ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ትኩረት ሰጥተው ተግባርና ግዴታቸውን መወጣት አለባቸው፡፡

የወንጀል ህጉ ዝርዝር ድንጋጌዎችም የእነዚህን ወንጀሎች ዝርዝር ይዘት የሚደነግጉ እና የሚያስቀጡትን ቅጣት አይነትና መጠን የሚወስኑ መሆን አለባቸው፡፡ ከዚህ አንጻር አዲሱ የወንጀል ህግ በህገ መንግስቱ ጥብቅ ተጠያቂነት ያስከትላሉ የተባሉትን ወንጀሎች በተሟላ ሁኔታ የሚዘረዝር ነው ወይ? የሚለው ጥያቄ በትኩረት መታየት አለበት፡፡ ከዚህ አንጻር የወንጀል ህጉ፣

- ዓለም አቀፍ ህጎችን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በማለት በዝርዝር የደነገጋቸውን ወንጀሎች እና ሌሎች ሰውን አስገድዶ መስወርና በሰው አካል ላይ ጉዳት ስለማድረስ የተደነገጉ ድንጋጌዎች ወንጀሎቹ በዓለም አቀፍ ህግጋት ያላቸውን ይዘት የሚካተት መሆኑን መመርመር ያስፈልጋል፣
- ከዚህ በተጨማሪ የወንጀል ህጉ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሰው ልጅ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች /ክረይምስ አጌንስት ሂማኒቲ) ተብለው የሚፈረጁ ድርጊቶችን ራሱን የቻለ ወንጀል በማድረግ የሚዘረዝርና ቅጣት የሚደነግግ ሆኖ አናገኘውም፡፡

በአጠቃላይ በወንጀል ህጉ በአገላለጽ የሚታዩ ጉድለቶችም ሆኑ በግልጽ በወንጀልነት ያልተደነገጉ ህገ መንግስቱ ጥብቅ የወንጀል ተጠያቂነት እንደሚያስከትሉ በልዩ ሁኔታ የደነጋገቸው ወንጀሎች ባህሪና ይዘት በመረዳት አጥፊዎች ሊጠየቁበት የሚችሉበትን የህግ ማዕቀፍ መወሰንና የህግ ማዕቀፉን ተግባራዊ ማድረግ ህገ መንግስታዊ አደራ ኃላፊነት በህገ መንግስቱ ተጥሎበታል፡፡ በወንጀል ህጉ ሊደረጉ የሚገባቸውን ማሻሻዎች ለህግ አውጭው የማመላከት ግዴታ አለበት፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. መንግስት ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር ግዴታውን ለመወጣት በማሰብ የደነገጋቸው የወንጀል የህግ ድንጋጌዎች ጠቅላላ ባህሪና ይዘት ያብራሩ?
2. መንግስት ሰብዓዊ መብቶችን የማስከበር ግዴታውን ኃላፊነት ለመወጣት በማሰብ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች ጠቅላላ ባህሪና ይዘት ይግለጹ?

## 1.4 <u>ህገ መንግስትና የወንጀል ህግ መርሆች</u>

ህገ መንግስት የወንጀል የህግ ማዕቀፎች ማለትም መሰረታዊ የወንጀል ህግ (ሰብስታንቲቪሎው) የወንጀል የስነ ስርዓትና የማስረጃ ህግ ይዘትና ቅርጽ የሚወሰኑና ገዥ የሆኑ የወንጀል ህግ መርሆችን ይደነግጋል፡፡ ህገ መንግስቱ ህግ አውጭው በዝርዝር የሚያውጃቸው የወንጀል ህግማዕቀፎች ህገ መንግስታዊ መርሆቹ ላይ የተመሰረቱና ከህገ መንግስቱ ጋር የሚጣጠሙ መሆናቸውን በማረጋገጥ ህጎቹን እንዲያውጅ የሚያስገድዱ ገዥ ድንጋጌዎችን ይደነግጋል፡፡ ህገ መንግስታዊ የወንጀል መርሆችን በማስቀመጥ በአገሪቱ ወጥተው ስራ ላይ የሚውሉ የወንጀል የህግ ማዕቀፎች ህገ መንግስታዊ እንደሆኑ (ኮንስቲቲዩሽና ክረሚናል ሎው) እንዲኖር ለማድረግና ህገ መንግስታዊ ያለሆነ የህግ ማዕቀፍና ድንጋጌ ህገ መንግስታዊነቱ ስልጣን ባለው አካል እንዲመረመር መሰረት የሚሆኑ ድንጋጌዎችን ይደነግጋል፡፡ ይኸም የኢፌዴሪ ህገ መንግስት በአገሪቱ የህገ መንግስት የበላይነትና ልዕልና ለማስፈን እና ህገ መንግስታዊ ገደብ ያለበት የመንግስት ስልጣን እንዲኖር ለማድረግ ከሚጠቀምባቸው ስልቶች አንደኛው ነው፡፡

የኢፌዲሪ ህገ መንግስትም የፌዴራልንም ሆነ የክልሎችን ስልጣን የሚገድቡ እና በፅኑ ሊከበሩና ሊተገበሩ የሚገባቸው መሰረታዊ የወንጀል ህግ መርሆች በህገ መንግስቱ

ምዕራፍ ሶስት ውስጥ በተለያዩ ድንጋጌዎች ስር ዝርዝራቸው እናገኛቸዋለን፡፡ በዚህ ክፍል ሁሉንም ሳይሆን፣

- የህጋዊነት መርህና የወንጀል ህግ ተፈጻሚነት
- በአንድ ወንጀል በድጋሜ ያለመጠየቅና ያለመቀጣት መርህ
- የእኩልነት መርህ
- የሰብዓዊነት መርህና ኢሰብዓዊ አያያዝና ቅጣት መከልከል

የሚሉት መርሆች በህገ መንግስቱና በወንጀል ህጉ የተካተቱበትን አግባብና የእነዚህ ህገ መንግስታዊ መርሆች ይዘት ትርጉምና ጠቀሜታ በአጭሩ እንመለከታለን፡፡

### 1.4.1 <u>የህጋዊነት መርህና የወንጀል ህግ ተፈጻሚነት</u>

የህጋዊነት መርህና የወንጀል ህግ ወደ ኃላ የማይሰራ መሆኑን የሚደነግገው መርህ ተያያዥነት ያላቸው ቢሆንም ሁለቱም አንድና ተመሳሳይ አይደሉም ህገ መንግስቱ በአንቀጽ 22 "የወንጀል ህግ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ" በሚል ርዕስ ስር የደነገገ ሲሆን ይህ ድንጋጌ ከላይ የተገለጹትን ሁለት ተያያዥነት ያላቸው ጽንሰ ሀሳቦች የሚደነግግ ነው፡፡ ስለዚህ ድንጋጌው በውስጡ የህጋዊነትን መርህ እና የወንጀል ህግ ወደኃላ የማይሰራ መሆኑን የሚደነግግ መሆኑን መገንዘብና የድንጋጌው መልዕክት ከዕርሱ የሰፋ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

#### ሀ. <u>የህጋዊነት መርህ</u>

የህጋዊነት መርህ" Nulla ponena sine lege" ከሚለው የላቲን ቃል የተወሰደ በአሁኑ ወቅት የህጋዊነት መርህ በበርካታ አገሮች የወንጀል የፍትህ ስርዓት የሚመሩበትና ዓለም አቀፍ ጥብቅና ዕውቅና ያለው መርህ ነው፡፡ የህጋዊነት መርህ መሰረታዊ ይዘት ማናቸውም ሰው የተከሰሰበትን ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም ድርጊቱን አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑን የሚደነግግ ህግ ከሌለ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆንና ሊቀጣ አይገባውም የሚል ነው፡፡ አንድን ሰው ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት አንድ ድርጊት ፈጽመሀል ወይም መፈጸም የሚገባህን አልፈጽምክም ብሎ ለመክሰስና በወንጀል እንዲቀጣ ለማድረግ የሰውየውን ድርጊት ወይም ተዓቅቦ በወንጀልነት የሚፈርጅና የወንጀል ቅጣት የሚደነግግ አስቀድሞ የታወጀ ህግ መኖር አለበት፡፡ የህጋዊነት መርህ አስቀድሞ የተደነገገ የህግ ክልከላ ሳይኖር የወንጀል ተጠያቂነት ሊኖር አይገባም የሚለውን ሀሳብ ያራምዳል፡፡

የህጋዊነት መርህ በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 የመጀመሪያው ፓራግራፍ “ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ በህግ ካልተደነገገ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም” በማለት በግልጽ ደንግጓል፡፡ የህገ መንግስቱ ድንጋጌ አንድ ድርጊት መፈጸም ወንጀል መሆኑንና የወንጀል ቅጣት የሚያስከትል መሆኑ በህግ አስቀድሞ ካልተደነገገ አንድ ሰው ወንጀል ፈጽመሀል ብሎ መክሰስና ለቅጣት የማይቻል መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡

ይኸ ህገ መንግስታዊ መርህ መንግስት የወንጀል ተጠያቂነትና ኃላፊነት የሚያስከትሉ የአገር የመንግስትን የህብረተሰብን እና የኗሪዎችን ሰላም ደህንነት ስርዓት መብትና ጥቅም የሚጥሱ ድርጊቶችን ይዘትና የሚያስከትሉትን የወንጀል ቅጣት አይነትና መጠን የሚዘረዝር ህግ የማውጣትና ለህብረተሰቡ አስቀድሞ የማሳወቅ ግዴታ ያለበት መሆኑን አካትቶ የያዘ ነው፡፡ የህጋዊነት መርህ ወንጀልን ከመከላከል አንፃርና የወንጀል ህግ ግብ ከማሳካት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

መንግስት የወንጀል ኃላፊነት ቅጣት የሚያስከትሉ ድርጊቶችን ወይም አልድርጊቶችን በህግ ሲደነግግና ሲያውጅ ህብረተሰቡ ወንጀል የሆነውንና ወንጀል ያልሆነውን ጥፋት ለመለየት ይችላል፡፡ ማንኛውም ሰው ድርጊቱን ከመፈጸሙ በፊት ደጋግሞ እንዲያስብና ወንጀል ከመፈጸም ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ በማድረግ ወንጀልን ይከላከላል፡፡ የወንጀል ህጉ ወንጀል እንዳይፈጸም የመጀመሪያው የመከላከያ መንገድ ስለ ወንጀሎችና ስለቅጣታቸው አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ መስጠት መሆኑን የወንጀል ህግ አንቀጽ 1 ሁለተኛው ፓረግራፍ ይደነግጋል፡፡ የህጋዊነት መርህ አስቀድሞ ህጉን ሳይወጣ አንድ ሰው መክሰስና መቅጣት የማይቻል መሆኑን በመደንገግ በመንግስት ላይ ግዴታ ይጥላል፡፡

ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ የህጋዊነት መርህ በዳኞች (ፍርድ ቤቶች) ስልጣን ላይ ገደብ የሚጥልበት ገፅታ አለው፡፡ ይኸውም ዳኞች አንድን ድርጊት ወይም አለድርጊት በህግ ክልከላ በተደረገበት ድርጊት ጋር ተመሳሳይ ነው በማለት ወንጀልነቱ በግልጽ ያልተደነገገውን ድርጊት ወይም አልድርጊት በፈጸሙ ሰዎች ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሳለፍ የማይችሉ መሆናቸውን አካትቶ የያዘ መርህ ነው፡፡ በፍታብሔር ህጉ ዳኞች በማመሳሰል ህግ መተርጎምና መወሰን የሚችሉ ሲሆን በወንጀል ጉዳይ የህጋዊነት

መርህ በማመሳሰል ወንጀል መፍጠር አይችልም የሚለውን ሀሳብ የሚያካትትና ዳኞች በግልጽ ወንጀልነቱ ያልተደነገገው ድርጊት ወይም አልድርጊት ያልፈጸመን ሰው መቅጣት የሌለባቸው መሆኑ ይደነግጋል፡፡

ከላይ የገለጽናቸውን መሰረታዊ ሀሳቦች ያካተተውና በህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 የመጀመሪያው ፓረግራፍ የተካተተው የህጋዊነት መርህ ዝርዝር ይዘት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጎ እናገኘዋለን፡፡ ሆኖም የህገ መንግስቱ መሰረታዊ መርህና ተፈጻሚነት አሰመልክቶ የሚነሱና የሚያከራክሩ ነጥቦች እንዳሉ መገንዘብ ይገባል፡፡

የመጀመሪያው በህገ መንግስቱ ድንጋጌ “ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በህግ ካልተደነገገ በስተቀር” የሚለው አገላለጽ አስመልክቶ የሚነሳው ጥያቄ ነው፡፡ ምን ዓይነት ህግ? የሚለውን ነጥብ በተመለከተ “በህግ ካተደነገገ በስተቀር”? የሚለው አገላለጽ የወንጀል ህጉ በግልጽ ባይደነገግም በሌሎች አዋጆች ወይም ደንቦች ድርጊቱ ወይም አለደርጊቱ ወንጀል መሆኑ ከተደነገገና ቅጣት ከተመለከተ አዋጅን ወይም የደንቡን ተፈጻሚ መሆን የለባቸው መሆኑን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 3 የተደነገገ በመሆኑ ለችግሩ ግማሽ መፍትሄ ይሰጣል፡፡

ሆኖም አንድ ድርጊት በህገ መንግስቱ ወንጀል መሆኑን የወንጀል ተጠያቂነትን እንደሚያከትል ተገልፆ በወንጀል ህጉና በሌሎች አዋጆች በወንጀልነት ባይደነገግ ድርጊቱን የፈጸመ ሰው በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል ወይስ አይሆንም?

አንድ ድርጊት በዓለም አቀፍ የልምድ ህግና አገሪቱ በፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነት ወንጀል መሆኑ ተደንግጎ በወንጀል ህጉ ወይም በሌላ አዋጅ ወንጀል መሆኑ ሳይደነገግ ቢቀር ድርጊቱን የፈጸመው ሰው በወንጀል ይጠየቃል ወይስ አይጠየቅም? የሚሉት ነጥቦት በሚገባ መመርመርና ምላሽ ማግኘት ያለባቸው ናቸው፡፡

ከላይ የተገለጹት መሰረታዊ ነጥቦች በእኛ አገር ከነበሩ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ማየት ያስፈልጋል፡፡ በቀይ ሽብር ወንጀል የተከሰሱ ባለስልጣናት የወንጀል ህጉ በግልጽ ባይሽርም በፀረአብዮተኞች ላይ ነፃ እና አብዮታዊ እርምጃ መውሰድ የሚፈቅድ አዋጅ በደርግ ታውጆ ስለነበር በድርጊታችን በህጉ ስለሆነ በወንጀል ልንጠየቅ አይገባም የሚል መከራከሪያ አንስተው ነበር፡፡

በሌላ በኩል የኤፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 28 በሰብዓዊ ፍጡር ላይ የሚፈጸም ወንጀል የይርጋ የጊዜ ገደብ የማይገድበው በማናቸውም አካል በይቅርታ ወይም በምህረት የማይታለፍ ወንጀል እንደሆነ በግልጽ ደንግጓል፡፡ ሆኖም የወንጀል ህጉ በሰብዓዊ ፍጡር ላይ የሚፈጸም ወንጀል ዝርዝር ይዘት ምን እንደሆነ አይደነገግም፡፡ ከዚህ አንፃር ዓለም አቀፍ ደረጃ ወንጀል ናቸው የተባሉ ድርጊቶች መፈጸም በዓለም አቀፍ ህግ መሰረት ተጠያቂ እንደሆነ የወንጀል ክስ ቢቀርብ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 "በህግ ካልተደነገገ በስተቀር" የሚለውን አገላለጽ ያሚላል? ወይስ አያሚለም? የሚሉት ነጥቦች በዝርዝር ማየት ይጠይቃል፡፡

ለ. <u>የወንጀል ህግ ወደ ኃላተመልሶ የማይሰራ መሆኑ</u>

ከህጋዊነት መርህ ጋር ተያያዥነት ያለው ሌላው መርህ የወንጀል ህግ ወደ ኃላ ሄዶ ህጉ ከመውጣቱ በፊት ሊሰራ አይገባውም የሚለው ነው፡፡ ይኸ መርህ የወንጀል ህግ ህግ ሆኖ ከወጣ በኃላ በሚፈጽሙ ድርጊቶች ወይም አለድርጊቶች ላይ ብቻ ተጠቃሽ እንደተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው መሆኑን "prospective application of criminal law" የሚመለከት ነው፡፡ ህጋዊነት መርህ ተግባራዊ ሊሆንና ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚችለው መሰረታዊ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች /substantive criminal law/ ከመውጣታቸው በፊት በተፈጸሙ ድርጊቶች ወይም አለድርጊቶች ላይ ተፈፃሚ እንዳይሆኑ የሚከለክል የህግ ገደብ ነው፡፡ የዚህ መርህ ይዘትና ተግባራዊ ተፈጻሚነት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 ሁለተኛው ፓራግራፍና በህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጎ እናገኛዋለን፡፡

የወንጀል ህጉ  መርህ አንድ የወንጀል ድርጊት የፈጸመ ሰው ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ የነበረው የወንጀል ህግ ከሚደነግገው ቅጣት የከበደ ቅጣት የሚደነግግ አዲስ የወንጀል ህግ ወይም ሌላ አዋጅ ወይም ደንብ ወጥቶ ስራ ላይ በዋለበት ጊዜ ተከስሶ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝም እንኳን ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ ስራ ላይ የነበረው የወንጀል ህግ ከሚደነግገው ቅጣት በላይ ሊቀጣ እንደማይገባው በመደንገግ የመንግስትን ስልጣን የሚገድብ ነው፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 ሁለተኛ ፓረግራፍ "እንዲሁም ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ ከነበረው ቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም ሰው ላይ አይወስንም" በሚል አገላለጽ የወንጀል ህግ ወደኃላ ተመልሶ የማይሰራ መሆኑን ደንግጓል፡፡

የህገ መንግስቱ ድንጋጌ በመጀመሪያ ህግ አውጭው የወንጀል ኃላፊነትና ቅጣት የሚያስከትሉ አዋጆችን ሲያውጅ አዋጅ ከመጽደቁ በፊት ለተፈጸመ ድርጊቶች ተፈጻሚነት ያላቸው መሆኑን በመደንገግ አዋጆቹን ከመውጣታቸው በፊት ለተፈጸሙ ጉዳዮች ተፈጻሚ ማድረግ የማይቻል መሆኑን ግልፅ የሚያደርግና የህግ አውጭውን ስልጣን የሚገደብ ድንጋጌ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የወንጀል ክስ የማቅረብና የመሟገት እንዲሁም ሙግት፣ የፍርድ ሂደት፣ የመስማት፣ ፍርድ የመስጠት ስልጣን ያላቸው የፍትህ አካላት በልዩ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር አንድ የወንጀል ህግ ከመውጣቱ በፊት በተፈፀሙ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን መጥቀስና ውሳኔ መስጠት የማይችሉ መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡

የወንጀል ህግ ወደኃላ ተመልሶ መስራት የለበትም የሚለው መሰረታዊ የወንጀል ህግ መርህ መሰረታዊ ግቡ የህጋዊነት መርህ እንዲከበር ማድረግና ተከሳሾች ወንጀሉን ከፈጸሙ በኃላ በሚወጡ የህግ ማዕቀፎች በሚደነገጉ ከባድ ቅጣቶች እንዳይቀጣ መከላከልና መጠበቅ ነው፡፡ ስለዚህ መርሁ የተከሳሾችን መብትና ጥቅም ለማስከበርና የመንግስትን ስልጣን ለመገደብ ታስቦ የተፀነሰና በብዙ አገሮች የወንጀል ህግ ማዕቀፎች ተካትቶ ስራ ላይ የዋለና በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ህግጋት በተለይም በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሁሉ አቀፍ መግለጫና በዓለም አቀፉ የስቭልን የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት የተደነገገ ነው፡፡

ይኽ መሰረታዊ መርህ ይዘት ከተነሳበት መሰረታዊ ግብና ሊጠብቀው እና ሊከላከለው ከሚገባው መብትና ጥቅም በመነሳት መርሁ ተፈጻሚ የማይሆንበት አንድ ልዩ ሁኔታ አለ፡፡ የወንጀል ህግ ወደኃላ ተመልሶ መስራት የለበትም የሚለው ጠቅላላ መርህ ተፈጻሚ የማይሆንበት ልዩ ሁኔታ የተከሳሹን መብትና ጥቅም ማዕከል ያደረገ ነው፡፡ ይኸውም ድርጊቱ ከተፈጸመ በኃላ የወጣ ህግ ለተከሳሹ ጠቀሚ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ድርጊቱ ከተፈጸመ በኃላ የወጣው ህግ የሚደነግገው ቅጣት ዝቅተኛ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ለተከሳሹ የሚጠቅመውን እና ዝቅተኛ ቅጣት የሚደነግገውን ህግ ተፈጻሚ የማድረግ ግዴታና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ ህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 2 ከላይ የተገለጸውን መሰረተ ሀሳብ በሚያካትት ሁኔታ የወንጀል ህግ ወደኃላ ተመልሶ የሚሰራባቸውን ልዩ ሁኔታዎች ደንግጓል፡፡

በህገ መንግስቱ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ ሁለተኛ ፓረግራፍ የተደነገገው መርህና መርሁ ቀሪ የሚሆንበት ልዩ ሁኔታ አስመልክቶ በአንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ድንጋጌ በሚዘረዝር ሁኔታ የወንጀል ህጉ በአንቀጽ 5 እና አንቀጽ 6 ተፈፃሚነት ያላቸውን ደንቦች ደንግጓል፡፡

የመጀመሪያው ከህጋዊነት መርህ ጋር ተያያዥነት ያለውና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ነው፡፡ ድንጋጌው ድርጊቱ በኤፌዲሪ የወንጀል ህግ መሰረት ወንጀል ሆኖ በተፃፈውና 1949 በወጣው የወንጀል መቅጫ ህግ እና በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ ከመውጣቱ በፊት በነበሩ አዋጆች እንደ ወንጀል ካልተቆጠረና ድርጊቱም የተፈጸመው የወንጀል ህጉ ከመጽናቱ በፊ ከሆነ ሊያስቀጣ የማይቻል መሆኑን የሚደነግገው ነው፡፡ ይኸ ድንጋጌ የህጋዊነት መርህን የሚያጠናክርና የህጋዊነት መርህ ተፈፃሚነት ወሰን የሚያመለክት ነው፡፡ ስለሆነም ከዚህ በፊት በነበሩ የህግ ማዕቀፎች በወንጀልነት ያልተፈረጁና ያልተደነገጉ ድርጊቶች በአዲሱ የወንጀል ህግ በወንጀልነት ተደንግገው ሲገኙ ድርጊቱ በወንጀል ህጉ በወንጀልነት የተደነገገ መሆኑን ብቻ ሣይሆን ድርጊቱ የተፈፀመው የወንጀል ህጉ ከመውጣቱ በፊት ከሆነ የተፈፀመበትን ጊዜ በትኩረት መመርመርና ህጉን ተፈፃሚ ማድረግ የሚገባን መሆኑን የሚደነግግነው፡፡

ሁለተኛው በተሻረው ህግ እንደ ወንጀል የተቆጠረ ድርጊት የወንጀል ህጉ ከመፅናቱ በፊት የተፈፀመ በሆነ ግዜ በወቅቱ ስራ ላይ በነበረው የወንጀል ህግ መሠረት ሊወሰን እንደሚገባው የሚደነግገው የወንጀል ህጉ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 2 ሲሆን ይኸም የህገመንግስቱን መሠረታዊ መርህ የሚያጠናክር ነው፡፡

ሶስተኛው በህገ መንግስቱ አንቀፅ 22 ንዑስ 2 የተደነገገው ልዩ ሁኔታ ተግባራዊ ተፈፃሚነት እስከምን ድረስና በምን መንገድ መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ በተሻለለው የወንጀል ህግ ማዕቀፎች በሥራ ላይ በነበሩበት ጊዜ የተፈፀመ ወንጀል ሲኖርና የወንጀል ህጉ ያንን ድርጊት እንደ ወንጀል ያልፈረጀው እና በወንጀልነት ያልደነገገው ሲሆን በጉዳዩ ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባው አዲሱ የወንጀል ህግ መሆን እንዳለበትና ድርጊቱ ሊያስከስስም ሆነ ሊያስቀጣ የማይችል መሆኑን ሥራ ላይ በነበረው የወንጀል ህግ መሰረት ክስ ተጀምሮ እንደሆነ መቋረጥ እንደሚገባው የወንጀል ህጉ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 3 ደንግጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 6 የህገ መንግስቱ አንቀፅ 22 ንዑስ አንቀፅ 2 ተፈፃሚነት የወንጀል ህጉ እንዲፀና ከተደረገ በኋላ አድራጊው የወንጀል ህጉ ከመውጣቱ በፊት ላደረገው ወንጀል ሲፈረድበት ወንጀሉን በፈፀመበት ጊዜ ስራ ላይ ከነበረው ሕግ ይልቅ የኋኛው ሕግ ቅጣት የሚያቀልለት ሲሆን በወንጀል ህጉ የተመለከተው ቅጣት ይፈፀምበታል፡፡ ፍርድ ቤቱ ይኸ ሕግ የተሻለ መሆኑን የሚወስነው በእያንዳንዱ ጉዳይ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች በመመዘን ነው በማለት ደንግጓል፡፡

ህገ መንግስቱ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለውን የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ መስራት የለበትም የሚለውን መርህና ይኸ መርሕ ቀሪ የሚሆንበትን ልዩ ሁኔታ በአንቀፅ 22 ደንግጓል፡፡ የወንጀል ህጉም ይህንን ህገ መንግስታዊ መርሕ የሚዘረዝሩት ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ደንቦችን በአንቀፅ5 እና በአንቀፅ 6 ደንግጓል፡፡ ሆኖም አሁንም ቢሆን የህገ መንግስቱን ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆንባቸውን ሁኔታዎችና የወንጀል ህግ አንቀፅ 6 ድንጋጌዎች ትርጉምና ተፈፃሚነት አስመልክቶ እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ድረስ የሚያከራክሩ ጉዳዮች አሉ፡፡ ይኸውም፣

- *የመጀመሪያው አንድ ሰው ወንጀሉን ሲፈፅም ፀድቆ ስራ ላይ ባልነበረ የሥነሥርዓት እና የማስረጃ ህግ መሠረት መዳኘት ይገባዋል ወይ? ህግ አውጭው የሚያወጣው የወንጀል ሥነሥርዓት እና የማስረጃ ህግ ማዕቀፎች ሕጎቹ ከመውጣታቸው በፊት የወንጀል ድርጊት በፈፀመ ተከሳሽ ላይ ተጠቃሽና ተፈፃሚ መሆን ይችላሉ ወይስ አይችሉም? ከሚለው ነጥብ ጋር የተያያዘ ነው፡፡*
- ሁለተኛው ፍርድ ቤቱ የተከሳሹን ጥፋተኝነት ከመወሰኑ በፊት ክርክሩ በሚታይበት ሂደት የዋስትና እና ሌሎች ተዛማጅ ጥያቄዎች በተከሳሾች ሲቀርቡለት ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ በጉዳዩ ተፈፃሚ መሆን ያለበት ወንጀሉ ሲፈፀም ሥራ ላይ የነበረው ሕግና በክሱ የተጠቀሰው የህግ ድንጋጌ ነው ወይስ ተከሳሹ ወደፊት ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ ሊቀጣ ይችላል ተብሎ የሚታሰበው አዲሱ የወንጀል ህግ ድንጋጌ ነው የሚለው ነው፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ የህጋዊነት መርህና የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሠራ መሆኑ በህገ መንግስቱ ተደንግጓል፡፡ የወንጀል ህጉ እና ሌሎች የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትሉ የህግ ማዕቀፎች ሥራ ላይ ስናውል የዚህን ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ መሠረታዊ ግብ እና ከድንጋጌው ይዘት ጋር በሚጣጣም መንገድ መተርጎምና ተፈፃሚ

በማድረግ ለህገ መንግስታዊ መርሁ ተገዥ መሆን ህገ መንግስቱን የማክበር ግዴታችንን መወጣት ህገ መንግስታዊ መርሁን በማስፈፀም ህገ መንግስቱን የማስከበር ግዴታና ኃላፊነታችንን መወጣት ይገባናል፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. በህገ መንግስቱ በምህረትና በይቅርታ የማይታለፍና የይርጋ የጊዜ ገደብ የማይገድበው ወንጀል መሆኑ የተደነገገው በሰብዓዊ ፍጡር ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች (crimes against humanity) እና በዘር ማጥፋት ወንጀል(genocide) መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት አስብለው ያስባሉ? ለምን?
2. በሰብዓዊ ፍጡር ላይ የሚፈፀም ወንጀልና በጦር ወንጀሎች መካkል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድነው ብለው ያስባሉ? ለምን?
3. ወንጀል መሆኑ በህገ መንግስቱ የተገለጠውን በሰብዓዊ ፍጡር ላይ የሚፈፀም ወንጀል ዝርዝር ይዘት በወንጀል ህጉ ተደንግጓል ብለው ያስባሉ? ለምን?
4. በወንጀል ህጉ በዝርዝር ባይገለፅም በህገ መንግስቱ ወንጀል መሆኑን የተገለፀ ድርጊት በፈፀሙ ሰዎች ላይ በተመሣሣይ ሁኔታ የተደነገጉ የወንጀል ቅጣት ህግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንዲሆንባቸው ክስ ቢቀርብ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 22 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገውን የህጋዊነት መርህ ይጥሳል ብለው ያስባሉ ?ለምን?
5. በኢፌዲሪ የወንጀል ህግ በወንጀልነት ያልተዘረዘሩ ነገር ግን በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብትና በዓለም አቀፍ የወንጀል ህግ ዓለም አቀፍ ወንጀል መሆናቸው የተደነገጉ ድርጊቶችን የፈፀሙ ሰዎች በዓለም አቀፍ ህግ መሠረት እንዲቀጡ የሚጠይቅ ክስ ዐቃቤ ህግ ቢያቀርብ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 22/ለ/ ድንጋጌዎች የሚጥስና ጉዳይ መታየት የሌለበት ነው ብለው ያስባሉ? ለምን?
6. በህገ መንግስቱ አንቀፅ 28 ድንጋጌዎች መሠረታዊ ዓላማና ግብ ምንድን ነው? በዚህ ድንጋጌ በከባድ ወንጀልነት የተገለፀና በወንጀል ህጉ በወንጀልነት ያልተደነገጉ ወንጅሎች አሉን ?
7. የወንጀል የሥነ ሥርዓት ሕግና የማስረጃ ህግ ወደኋላ ተመልሶ የሥነሥርዓት ሕጉ ከመውጣቱ በፊት ለተፈፀሙና በዳኝነት በመታየት ላይ ላሉ ጉዳዮች ተፈፃሚ መሆን የለባቸውም የሚለው ክርክር ህገ መንግስታዊ መሠረት አለው ብለው ያስባሉ? ለምን?

8. ወንጀል በማመሳሰል መፍጠርና ማለትም በወንጀል ህጉ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 3 እና የወንጀልን ህግ በመተርጎም ማለትም በወንጀል ህጉ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 4 መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
9. ፍርድ ቤቱ አዲሱ የወንጀል ህግ ከመውጣቱ በፊት በተፈፀመ ድርጊት ለተከሰሰው ተከሳሽ ላይ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው አዲሱ የወንጀል ህግ ነው ወይስ ድርጊቱ ሲፈፀም ሥራ ላይ የነበረው ህግ የሚለውን በማመዛዘን የሚመርጠው በተከሳሽ ላይ የጥፋተኝነት ውሣኔ ከሰጠ በኂላ ነው ወይስ ዓቃቤ ህግ ክሱን ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በክርክርና በሙግት ጊዜ ጭምር የሚለውን ነጥብ ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 22 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ከወንጀል ህጉ አንቀፅ 6 አንፃር እንዴት ይተረጉሙታል/ይመልሱታል?

### 1.4.2 በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ህግጋት የተደነገገውና የኢፌድሪ ህገ መንግስት በመሠረታዊ የወንጀል ህግ መርህነት የደነገገው ሌላው መርህ አንድ ሰው በአንድ የወንጀል ድርጊት ክስ ቀርቦበት የመጨረሻ በሆነ ውሣኔ ጥፋተኝነቱ ተረጋግጦ በተቀጣበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና መከሰስና መቀጣት የለበትም የሚለው ነው፡፡ ይኸ መርህ መንግስት አንድ ጊዜ ክስ አቅርቦበት ተከራክሮ የመጨረሻ ፍርድ በተሰጠበት ድርጊት በሌላ ጊዜ ተከሳሹን በድጋሚ ለመክሰስና ለማስቀጣት የማይችል መሆኑን በመደንገግ ሰዎችን በተደጋጋሚ ከሚቀርብ የወንጀል ክስ ስጋት ውስጥ እንዳይወድቁ ለመከላከል ለዜጎች የተረጋጋ ሰላማዊ ኑሮ ዋስትና እና ጥበቃ የሚያሰጥ ነው፡፡

ይህንን ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው መርህ ህገ መንግስቱ በአንቀፅ 23 "ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነ ሥርዓት መሠረት ተከስሶ የመጨረሻ በሆነ ውሣኔ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም" በማለት ደንግጓል፡፡

አንድ ሰው በወንጀል ህግና በወንጀል ሥነሥርዓት ተከስሶ የመጨረሻ ፍርድ በተሰጠበት ጉዳይ ጥፋተኛ ሆኖ ተቀጥቷል ወይም በነፃ ተለቋል የሚለው መከራከርያ በመጀመሪያ የክስ መቃወሚያነት የሚያቀርብ መብት መሆኑን የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 የተደነገገ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ያቀረበውን ማስረጃ የክስ መቃወሚያ

በመመርመር ውሣኔ መስጠት ያለበት መሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 131 ተደንግጓል፡፡ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 23 መሰረታዊ ግብና ዓላማ አንድ ሰው ተከስሶ ጥፋተኛ ተብሎ በተቀመጠበት ወይንም በነፃ በለቀቀበት ድርጊት በተለያየ የወንጀል ርዕስ እና በተለያየ ጊዜ ተደጋጋሚ ክስ ከማቅረብና ተከሳሹን ከመጠየቅ ለመገደብና ለተከሳሽ ከወንጀል ክስ ስጋት ነፃ ማድረግና የተረጋጋ ህይወት እንዲመራ ዋስትና እና ጥበቃ መስጠት ነው፡፡

ይኸ መሠረታዊ ነጥብ እንዳለ ሆኖ በህገ መንግስቱ የተደነገገው ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት በዕለት ከዕለት የክስ አቀራረብ የሙግትና የፍርድ ሥራ አሰጣጥ ከሚታዮ ስህተቶችና ከሚፈጠሩ ችግሮች አንፃር እንዴት መተርጎምና ተፈፃሚ መሆን ይገባዋል የሚለው ነጥብ አከራካሪ መሆኑ የሚሸሽግ አይደለም፡፡ የአፈፃፀም ስህተቶቹ በክስ አቀራረብ ወይም ፍርድ በሚወስነው አካል የሚፈፀሙ የተለያዮ ገፅታዎች ያላቸው ሲሆኑ ሁሉንም በንድፈ ሀሳብ መልክ ለመዘርዘር የማይችል በመሆኑ ካጋጠሙ ተጨባጭ ጉዳዮች በመነሳት ሠልጣኞቹ የሚከተሉት ነጥቦች ከድንጋጌው ጋር በማገናዘብ እንዲመረመሯቸው አቅርቤያቸዋለሁ፡፡

- ዐቃቤ ህግ በመጀመሪያ ከፍተኛ ቅጣት እና ኃላፊነት በሚያስከትል የወንጀል ድንጋጌ ተጠያቂ የሚሆን ሰው በከባድ ስርቆት መከሰስ የሚገባውን በስርቆት ወንጀል ክስ አቅርቦ ማስረጃ አሰምቶ ተከሳሽ ጥፋተኛ ተብሎ ከተቀጣ በኃላ በዚያው የወንጀል ድርጊት በሌላ ጊዜ ከባድ ስርቆት ወንጀል ፈፅሞል የሚል ክስ ቢያቀርብ የህገመንግሥቱ አንቀፅ 23 በመጥቀስ ተከሳሹ የሚያቀርበው የመጀመሪያ ክስ ተቃውሞ ተቀባይነት ይኖረዋል ወይስ አይኖረውም?
- በግ መስረቁ ተጠቅሶ በቀበሌው አስተዳደር የተከሰሰ ተከሳሽ ከተከላከለ በኃላ ጥፋተኛ ተብሎ በሶስት ወር እሥራት እንዲቀጣ ወሰነበት፡፡ በውሣኔውም ይግባኝ ጠይቆ ወረዳ ፍርድቤት ቢያቀርብ ፀናበት ፡፡ ተከሳሹ ቅጣቱን ከፈፀመ በኂላ በዚያው ጉዳይ የወረዳው ዐቃቤ ህግ የወንጀል ህግ ጠቅሶ ክስ አቀረበበት፡፡ ምን ይበይናሉ? ለምን?
- ዐቃቤ ህግ ሥልጣን ያለው ፍርድቤት በተከሳሹ ላይ የወንጀል ክስ አቅርቦ ተከሳሹ የዕምነት ክህደት ቃል ከሰጠ በኃላ ዐቃቤ ህግ ለሶስት ቀጠሮ ማስረጃ እንዲያቀርብ ፍርድቤቱ በተደጋጋሚ ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ ዐቃቤ ህግ ምስክሮቹን ስላላቀረበ በአራተኛው

ቀጠሮ ፍርድቤቱ ዐቃቤ ህግ ማስረጃ በማቅረብ የተከሳሽን ጥፋተኝነት ስላላስረዳ ተከሳሽ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር141መሠረት በነፃ ለቅቄዋለሁ የሚል ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ ዐቃቤ ህግ ይግባኝ በማለት ትዕዛዙን አላሻረም፡፡ ከሶስት ወር በኋላ ምስክሮቹ ተገኙዐቃቤ ህግ ክሱን ለማንቀሳቀስ በተፈለገበት ጊዜ ተከሳሽ የህገመንግስቱን አንቀፅ 23 በመጥቀስ ተቃውሞ ምን አይነት ትእዛዝ ወይም ብይን ይሰጣሉ?ለምን ?

- ተከሳሽ ላይ በሰው መግደል ወንጀል የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሣኔ በፍርድ ቤቱ ሥር ነገር ሥልጣን አለመኖር በይግባኝ ወይም በሰበር ከተሻረ በኋላ ዐቃቤ ህግ በዚያው ጉዳይ ሌላ ክስ ስልጣን ያለው ፍ/ቤት አቀረበ፡፡ በዚህ ጉዳይ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 23 ሊጠቀስና ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል?
- በተከሳሽ የተጭበረበረ ማስረጃ በማቅረብና የዐቃቤ ህግን ማስረጃዎች በመደለል ወይም በማስፈራራት ነፃ የወጣ መሆኑን የሚያረጋግጥ እርግጠኛ ማስረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ ከሰጠ ከአንድ ዓመት በኋላ ተገኘ ፡፡ ዐቃቤ ህግ ፍርዱ እንደገና እንዲታረም ለመጠየቅ ይችላል? በወንጀል ጉዳይ ዐቃቤ ህግ ፍርድ እንዲታረም የሚያቀርበው ጥያቄ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 23 እንዴት ያዩታል?
- በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው አይነት ድንጋጌ ያለው የወንጀል ሥነሥርዓት ሕግ ቢፀድቅ ህገመንግስቱ አንቀፅ 23 ጋር ይጣጣማል ብለው ያስባሉ ? ለምን?
- ከላይ የተገለፁትና ሌሎች ያልተነሡ በርካታ ሁኔታዎች የህግ መንግስቱን አንቀፅ 23 አፈፃፀም እና አተረጓጎም የሚመለከት የሚነሡ አከራካሪ ነጥቦች በመሆናቸው እና ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ነው ፡፡

ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 23 አቀራረፅና ይዘት ለመረዳት የሚቻለው አንድ ሰው ያቀረበውን የወንጀል ክስ በአንድ ጉዳይ ደግሞ ያለመከሰስና ያለመቀጣት መብት የሚጥስ ነው ብሎ ለመከራከርና ተፈፃሚ ማድረግ የሚቻለው፣

- ➢ ተከሳሹ በመጀመሪያ በወንጀል ህግና ሥነሥርዓት ሕግ መሠረት የተከሰሰ ሲሆን
- ➢ ተከሳሹ በተከሰሰበት ወንጀል መጨረሻ በሆነ ፍርድ ጥፋተኛ ሆኖ ከተቀጣ ወይም በነፃ የተለቀቀ እንደሆነ ነው፤፤

ሆኖም እነዚህ መስፈርቶች ከተግባራዊ የዕለት ከዕለት የፍርድ ሥራ ሒደት መተርጎም ቀላል እንዳይሆንና የዚህ አይነት አከራካሪ ጉዳይ ሲያጋጥም የፌዴራል ጠቅላይ

ፍርድቤት ሰበር ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉምና ህገመንግስታዊ ድንጋጌው ሊያሳካው የሚፈልገውን ግብና ዓላማ መሠረት በማድረግ መፍታት ያስፈልጋል፡፡
ከዚህ ህገመንግስታዊ መርህ ጋር አብሮ መታየት ያለበት የወንጀል ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 184 ነው ፡፡ ምክንያቱም አንድ በድርጊቱ ከዚህ በፊት ተከሳሽ የመጨረሻ ፍርድ ተሰጥቶ ተቀጥቶበታለሁ ወይም በነፃ ተለቅቄበታለሁ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወምያ ያቀረበው ተከሳሽ ፍርድቤቱ ተቃውሞውን ውድቅ ካደረገበት ይግባኝ ማቅረብ እንደማይፈቅድለት የመጨረሻ  ውሳኔ እስኪሰጥ መጠበቅ እንዳለበት የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 184 ይደነግጋል ፡፡ ይኽ የሥነሥርዓት ሕግ ድንጋጌ ተከሳሹ ህገ መንግስታዊ መብቱን በወቅቱ ተከራክሮ ለማስከበር እድል የሚሰጥ ነው? የሚለው ሀሳብ መታየት አለበት፡፡

የህገ መንግስቱ አንቀፅ 23 ትርጉምና የተፈፃሚነት ወሰን አስመልክቶ የሚነሱ አከራካሪ ጉዳዮች በህግ መንግስቱ አንቀፅ13 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ኢትዩጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ቃልኪዳን ስምምነት ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ  የህገ መንግስቱ አንቀፅ 23 ተፈፃሚነት ወሰን ለመረዳት መመርመር ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 23 በአንድ በኩል መንግስት በአንድ ድርጊት በተለያየ የወንጀል ዕርስና የህግድንጋጌ በመጥቀስ ወይም ተመሳሳይ የወንጀል ህግ ድንጋጌ በመጥቀስ ተከሳሹ ተከስሶ በፍርድቤት በተሰጠ የመጨረሻ ፍርድ ነፃ ያወጣውን ወይም የተቀጣውን ሰው እንዳይጠይቅ ነው፡፡ ተከሳሹ በወንጀል ክስና ጭንቀት ሥጋት እንዳይሸማቀቅ የመንግስትን ስልጣን የሚገድብ ተከሳሹ በወንጀል ተከስሶ በነፃ በተለቀቀበት ወይም በተቀጣበት ጉዳይ ላይ ሌላ የወንጀል ክስና ተጠያቂነት ይመጣብኛል ከሚል ስጋት ተላቅቆ የተረጋጋ ህይወት እንዲኖር የማድረግ ዓላማና ግብ ነው፡፡ በሌላ በኩል የህገ መንግስቱ ድንጋጌ በወንጀል ተከስሰው የመጨረሻ ፍርድ ሣያገኙ በተከሳሽ መጥፋት በምስክሮች መቅረት ክሱ ሥልጣን በሌለው ፍርድ በማቅረብ የዐቃቤ ህግ ክሱን በማንሳቱ የዐቃቤ ህግ ክስ የተሚላ ባለመሆኑና ተከሳሽም ባለመቅረቡ እና በሌሎች ምክንያቶች ክርክሩ በመቋረጡ ምክንያት ወንጀል የፈፀሙ ሰዎች ከወንጀል ኃላፊነትና ተጠያቂነት ለማምለጥ የህገ መንግስቱን መርሆዎችን መሸሸጊያ እንዳያደርጉት ለመግለፅ በሚያስችል አግባብ  የተደነገገ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡

## <u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. የወንጀል ክሱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑ ተገልጾ ከተዘጋ በኃላ ዐቃቤ ህግ በዚያው ጉዳይ ሌላ የወንጀል ክስ ማለትም የይርጋው ጊዜ ረጅም የሆነ ድንጋጌ በማጥቀስ ክስ ቢያቀርብ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 23 ተፈፃሚነት ይኖረዋል ብለው ያስባሉ? ጉዳዩን ለማብራራት ዐቃቤ ህግ በመጀመሪያ ተከሳሽ የሰረቆት ወንጀል ፈፅሟል በማለት የወንጀል ክስ በተከሳሽ ላይ አቀረበ ፡፡ ተከሳሹ የወንጀል ክስ ማቅረብያ ጊዜው አልፎል በማለት ተከራከረ፡፡ ፍርድ ቤቱ የወንጀል ክስ የይርጋ የጊዜ ገደብ አልፏል በማለት ትዕዛዝ ሰጥቶ መዝገቡ ተዘጋ ፡፡ ከዚህ በኂላ ዐቃቤ ህግ ተከሳሽ ከባድ የስርቆት ፈፅሟል በማለት በዚያው ጉዳይ ክስ አቀረበ ተከሳሹ የህገመንግስቱን አንቀፅ 23 እና የሥነሥርዓት ህጉን 130 በመጥቀስ ተከራከረ፡፡ ምን ይበይናሉ?
2. ከላይ ከአንድ እስከ ዘጠኝ በተደረደሩት ሁኔታዎች ከህገመንግሥቱ አንቀፅ 23 ድንጋጌ አንፃር እንዴት አያችሁት፡፡

### 1.4.3 <u>የእኩልነት መርህ</u>

### (ሀ) የእኩልነት መርህ መሠረታዊ ይዘትና ተፈፃሚነት

በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ሌላው የወንጀል ህግ መሠረታዊ መርህ የእኩልነት መርህ ነው፡፡ የእኩልነት መርህ የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ህግ የመጀመሪያ መርህ ብቻ ሳይሆን ሰብአዊ መብት የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ክቡርነት የመነጨ መሆናቸው አንደኛው መግለጫ ነው፡፡ የእኩልነት መርህን ለማስከበር ማንኛውንም የዘር መድሎ ለማስወገድ የቃል ኪዳን ስምምነት ድንጋጌዎችና በእያንዳንዱ የሰብአዊ መብት ስምምነት አድሏዊ አሰራርን የሚያወግዱ እና የእኩልነት መርህን የሚያራምዱ ድንጋጌዎች አካትተዋል፡፡ ህገ መንግስቱ ይህንን የእኩልነት መርህ በአንቀፅ 25 በመደንገግ በሰዎች መከከል ልዩነት ሣያደርግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር በብሔረሰብ በፖለቲካ በማህበራዊ አመጣጥ በሀብት በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሣይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው ባመለት በአንቀፅ 25 ደንግጓል ፡፡

ይኽ መንግስታዊ መርህ በመጀመሪያ ደረጃ የሰዎችን በዘር በብሔረሰብ በፖለቲካ በማህበራዊ አመጣጥ በሀብት በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት

የሚያደርጉና አድሎአዊ ይዘት ያላቸው ህጎች ህግ አውጭዎች ሊያወጣ እንደማይገባውና በህግ ፊት ሁሉም ሰዎች በእኩልነት መታየት እንዳለባቸው የሚደነግግ ነው፡፡ በህገ መንግስቱ የተፈቀዱና ወደኃላ የቀሩ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ወይም የሴቶችን የእኩልነት መብት ለማረጋገጥ ታስበው የሚሰጡ ድጋፎችን ህጋዊ መሠረት ለመሥጠት ከሚወጡ ሕጎች በስተቀር ሌሎች ህጎች ሁሉም ሰዎች በእኩል ሁኔታዎች መነሻ በማድረግ አድላዊ የሆነ የህግ ማዕቀፎች ሊታወጅ የማይገባ መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡

ሁለተኛው ነጥብ ህጎች በሁሉም ሰዎች መብትና ነፃነት እኩል ጥበቃና ዋስትና የሚሰጡና ህጎቹም ተግባራዊ ሲሆንና ሲፈፀሙ በሁሉም ሰዎች ላይ በእኩል ደረጃ ሊፈፀሙ የሚገባቸው መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ የወንጀል ህጉ ይህንን መሠረታዊ መርህ መሠረት በማድረግ የተደነገገና ተፈፃሚ የሚሆን በመሆኑ በአንቀፅ 4 የመጀመሪያው ፓራግራፍ በግልፅ ደንግጓል፡፡

የወንጀል ህጉ በሕግ ፊት እኩል መሆን በሚል ርእስ ሥር የወንጀል ህግ የሰውን የማህበራዊ ኑሮ ደረጃን የዘርን የብሔርን የብሔረሰብን የቀለምን የፆታን የቋንቋን የሓይማኖትን ልዮነት ሳያደርግ በሁሉም በእኩል ተፈፃሚ ይሆናል በማለት በአንቀፅ 4 በመጀመሪያው ፓራግራፍ ይደነግጋል፡፡ በህገ መንግስቱና በወንጀል ህግ የተደነገገው የእኩልነት መርህ በወንጀል ህጉ በድርጊት ወይም በአለድርጊት (ተዓቅቦ) ቢፈፅሙ የወንጀል ተጠያቂነትና ኃላፊነት ያስከትላሉ ተብለው ከተዘረዘሩ ወንጀሎች አንደኛውን ወይም ከአንድ በላይ የሆነ ወንጀል የፈጸመ ማናቸውም ሰው የወንጀል ስራው የዘር የሐይማኖት የብሔር የማሕበራዊ የብሔር ብሔረሰብ የማሕበራዊ አመጣጥ የፖለቲካ አቋም የኢኮኖሚ አቋም እናሌሎች ከግለሰብ ማንነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ሣይገቡ በወንጀል ህግ መሰረት ሊከሰስና በእኩል ደረጃ ሊጠየቁ እንደሚችል የሚደነግጉ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በወንጀል ህጉ የተዘረዘሩ ወንጀሎች በተፈጸሙ ጊዜ መንግስት የወንጀሉ ሰለባ የሆነውን ሰው ግላዊ ማንነት ምክንያት ልዮነት ሣያደርግ የወንጀል ምርምር በማከናወን ማስረጃ በማቅረብ ወንጀል የሠራውን ተጠያቂ የሚያደርግ ግዴታና ኀላፊነት ያለበት መሆኑን የሚደነግጉ ናቸው፡፡ ከላይ የተገለፀው የድንጋጌዎቹ መሰረታዊ ይዘት እንደተጠበቀ ሆኖ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 25 የተደነገገው ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት እና በወንጀል ህጉ አንቀፅ 4 የተደነገገው

የወንጀል ህግ በሁሉም ላይ እኩል ተፈፃሚ የመሆን መርህ የህጎቹን መሠረታዊ ይዘት ብቻ ህጎቹ መደንገጋቸው ብቻ ሣይሆን ህጎቹ በተግባራዊ አፈፃፀማቸው በእኩል ደረጃ ተግባራዊ መሆን አለባቸው፡፡

ይኸ ደግሞ የፍትህ አካላቱን ከአድሏዊ አሠራር የፀዳ አገልግሎት እና በገለልተኛነት ኃላፊነታቸውን ከመወጣት ጋር የጠበቀና ተጨባጭ የሆነ ግኙኝነት ያለው ነው፡፡ በህግ ፊት እኩል የመሆን መርህ ከላይ ከገለፃቸው በተጨማሪ ሁሉም ሠዎች በፍርድ ቤቶችና በሌሎች ፍርድ ሰጭ አካላት ፊት በእኩልነት የመታየት መብትና ነፃና ገለልተኛ በሆነ ፍርድ ቤት ፍትሕ የሆነ ዳኝነት የማግኘት መብትን የሚያካትት እንደሆነ ዓለም አቀፍ የሲቪል የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ዳኞች ሥራቸውን ከማናቸውም ግለሰብ ወይም አካል ተፅኖ ነፃ ሆነውና ህጎችን መሠረት በማድረግ የዳኝነት ሥራቸውን የሚወጡ መሆናቸውን ዳኞች ከማናቸውም መድሎ ነፃ እና ገለልተኛ ሆነው የዳኝነት ተግባራቸውን የማከናወን ግዴታንና ኃላፊነታቸውን የህገ መንግሰቱ አንቀፅ 79 ንዑስ አንቀፅ 2እና 3 ድንጋጌዎች መሠረት ለማከናወን ካልቻሉ በህግ ፊት በእኩልነት የመታየትና እኩል የህግ ጥበቃ እና ዋስትና የማግኘት መብት በተሟላ ሁኔታ ሊረጋገጥ አይችልም፡፡ ከዚህ አንፃር የፍትህ አካላት ያላቸውን ከባድ ኃላፊነት መረዳትና ህገ መንግስታዊ መርሁን ተፈፃሚ ለማድረግ በትኩረት መሥራት አለባቸው፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. የወንጀል ህጉን ግብና ዓላማ መሠረት በማድረግ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 41 እንደዚሁም በወንጀል ህግ ከአንቀፅ 52 እስከ አንቀፅ 56 የተደነገጉትን ሁኔታዎች መነሻ በማድረግ ዳኞች የቅጣት መጠንና የቅጣቱን አፈፃፀም አስመልክቶ የተለያዮ ውሣኔ ይሰጣሉ፡፡ ይኸ ከህገ መንግስቱ የእኩልነት መርህ የሚቃረን ነው ብለው ያስባሉ ? ለምን?
2. የህገ መንግስቱ አንቀፅ 25 እና የወንጀል ህጉ አንቀፅ 4 ሁለተኛው ፓራግራፍ የተደነገጉ ጉዳዮች በማጣጣም ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል? ለምን

3. የወንጀል ህጉ ተፈፃሚነት  አስመልክቶ በህገ መንግስቱ የተደነገጉ ልዮ ሁኔታዎች አሉ ብለው ያስባሉ? በዓለም አቀፍ ህግ የተደነገጉትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ልዮ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው፡፡
4. የህገ መንግስቱ አንቀፅ 25 መሠረታዊ ግብና ዓላማ እንደዚሁም ሁለቱ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ በሚሆኑበት ጊዜ ጥንቃቂ ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ምንድ ናቸው?
5. የአንዲት አገር አምባሳደር በኢትዮጵያ ውስጥ እያለ የሰው መግደል ወንጀል መፈፀሙ ቢረጋገጥ አምባሳደሩን በቁጥጥር ስር መዋል፤ በወንጀል መክሰስና ጥፋተኛ ብሎ እንዲቀጣ መወሰን በሌላ አነጋገር የወንጀል ህጉን ከማናቸውም ዜጋ ጋር በእኩል ደረጃ ተፈፃሚ ማድረግ ይቻላል? ለምን?

### 1.4.4. <u>የሰብዓዊነት መርህና ኢሰባዓዊ ቅጣትና አያያዝ ስለመከልከሉ፡፡</u>

በተለያዩ ሀገሮች የወንጀል የህግመፅቀፎች በመሠረታዊ መርህነት የተደነገጉ መሰረታዊ መርህ የሰብኣዊነት መርህ ነው፡፡ ይኽ መርህ ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወንጀል ፈፅመሀል ተብሎ በተጠረጠረበት በተከሰሰበትና ጥፋተኛ ሆኖ ቅጣት በሚወሰንበት ጊዜ በሰብዓዊ ፍጡርነት ዕውቅና እና ጥበቃ ሊሰጠው የሚገባው መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ ማናቸውም ሰው በየትኛውም ሥፍራ ሰው መሆኑ በህግ ፊት ዕውቅናና እና ጥበቃ ሊሰጠው የሚገባው መሆኑ በዓለም አቀፍ የሰባዓዊ መብት  ህግ የተደነገገ ሲሆን የህገ መንግስቱ አንቀፅ 24(2) መንኛውም ሰው በማናቸውም ሥፍራ በሰብዓዊነቱ እውቅና የማግኘት መብት ያለው መሆኑን ይደነግጋል፡፡

ይኸ መሰረታዊ መርህ መንግስት በግዛት ክልሉ ውስጥ የሚገኝ አንድ ሰብዓዊ ፍጡር የፈፀመው ወንጀል ከባድ ሰብዓዊና ቁሣዊ  ውድመት ያስከተለ የሰውየው ወንጀል አፈፃፀም በተለያየ ሁኔታ ጨካኝና ነውረኛ መሆኑን በመመዘን ተፈጥሯዊ ሰብዓዊ ክብሩን ለመግፈፍና በእንሰሳትነት ወይም በሌላ ግዙፍነት ያለው ቁስነት ሊፈረጅና ሊመድበው የማይችል መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡

መርሁ መንግስት የሚደነግገው የወንጀል ቅጣት የሰውን ተፈጥሯዊ ክቡርነት የሚገስስ መሆን የሌለበት መሆኑንና ፍርድ ቤቶች የሚወስኑት የቅጣት ውሣኔ ሰብዓዊ ፍጡርነትን እውቅና የሰጠና ያከበረ መሆን ያለበት መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ይኸም መርህ ከህገ መንግስቱ አንቀፅ10(1) ጋር ተጣምሮ መታየት አለበት፡፡

ሁለተኛው መርህ ከመጀመሪያው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አንድ ሰው ምንም ያድርግ ምንም ከሰብዓዊና ተፈጥሮዊ ክቡርነቱ ዝቅ በማድረግ እንደ እንስሳ ወይም ልዩነት ያለው ቁስ መቁጠርና መገሰሰ የማይቻል ከሆነ በወንጀል ተጠርጥሮ ሲያዝ ሲከሰሰና የወንጀሉ ጥፋተኛ ሆኖ ቅጣት ሲወሰንበትና የተፈረደበትን ቅጣት ሲፈፀም ለሰብዓዊና ተፈጥሮዊ ክቡርነቱን ዕወቅና የሚሰጥ ሁኒታ መፈፀመ አለበት የሚለው ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ኢሰብዓዊና ጭካኔ የሞላበትና አዋራጅ አያያዝ ዓለምአቀፍ ክልከላ ከተደረገበትና በዓለም አቀፍ ወንጀልነት ከተፈረጀ ዓመታት ተቆጥራዋል፡፡

ህገ መንግስቱ ማንኛውም ስው ጭካኔ ከሞላበት ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት እንዳለው በአንቀፅ 18 ንዑስ አንቀፅ 1 ይደነግጋል፡፡ ይኸ ህገ መንግስታዊ መርህ ህግ አውጭው የሚያውጀው የወንጀል ህግና የሚደነግገው ቅጣት ጭካኔ የሞላበት ኢሰብአዊ የሆነና ክብሩን የሚያዋርድ መሆን የሌለበት መሆኑን ህገ መንግስቱ ከመፅደቁ በፊት ሲሠራባቸው በነበሩ ህጎች የተደነገጉ የዚህ አይነት ቀጣቶች መሻርና ማስወገድ ያለበት መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ በሌላ በኩል ቅጣት የሚወስኑና ህጉን ተፈፃሚ የሚያደርጉት አካላት ማናቸውም ጭካኔ የሞላበት ኢሰብዓዊ የሆነ የተያዘውን ወይም በፍርድ የተቀጣውን ሰው ሰብዓዊ ክብር ከሚያዋርድ ማናቸውም ተግባር ከመፈፀም የመታቀብ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡

ይኸንን መርህ ተፈፃሚ ለማድረግ ህገ መንግስቱ በአንቀፅ 19(5)በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በግልፅ በሚደንገግ እንዲሁም ህገ መንግስቱ በአንቀፅ 28 በይቅርታ ወይም በምህረት ሊታለፍ የማይችል ጥብቅ የወንጀል ተጠያቂነትን በመደንገግ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጓል፡፡ ወንጀሉ በተደራጀ መንገድ በክልል መንግስታት አካላት ወይም ባለስልጣናት ተሣትፎ ሲፈፀም የፌደራል መንግስት ጣልቃ የሚገባበት እና ወንጀል ሠራዎች ለፍርድ የሚቀርቡበት ሥርዓት የፌዴራል መንግስት በክልሎች ጣልቃ ስለሚገባበት ሁኔታ የህገ መንግስቱ በአንቀፅ 55 ንዑስ አንቀፅ 16 ይደነግጋል፡፡

ከዚህ አንፃር የወንጀል ህግ በይዘቱም ሆነ ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ የሰውን ተፈጥሮዊ ክብር የሚገስስ፣ ጭካኔ የሞላበት ኢሰብዓዊ የሆነና ክብሩን የሚያዋርድ መሆን የለበትም፡፡ ይህ በተያዙና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች መብት ጭምር እንደሆነ በህገመንግስቱ

አንቀፅ 18 ንዑስ አንቀፅ 1 የህገ መንግስቱ አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ከህገ መንግሰቱ አንቀፅ 10(1) ጋር በማጣመር በማንበብ ለመረዳትና ለመገንዘብ ይችላል፡፡ ከዚህ አንፃር ይህንን ድንጋጌ በማክበርና በማስከበር በኩል ከፍተኛ ኃላፊነት ያለባቸው የፍትህ አካላት መሆናቸውን በመገንዘብ የወንጀል ህጉ ስንተረጎምም ሆነ ሰናስፈፅም የሰብዓዊነት መርህን መሠረት በማድረግ ተግባራዊ ማድረግ ይገባናል፡፡

በህገ መንግስቱ አንቀፅ 18 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገጉ በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ያለመያዝ መብት፣ በኃይል ተገድዶ ወይም ግዴታን ለሟሟላት ማንኛውንም ሥራ እንዲሠራ ያለመገደድ መብትና በሰው መነገድ የተከለከለ መሆኑ ከሰው ልጅ ተፈጥሮዊ ክብርነት የሚሰጠው ዕውቅና እና ጥበቃ ጋር የተያያዘ ናቸው፡፡ ስለሆነም የወንጀል ህጉ ድርጊቶቹን በወንጀልነት መፈረጅና ቅጣት መደንገግ ያለበት ሲሆን የፍትህ አካላትም ህጉን በአግባቡ በማስፈፀም መብቱን የማስከበር ግዴታ እና ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ከዚህ አንፃር የወንጀል ህጉ በዓለምአቀፍ ወንጀልነት ከተፈረጀ ረዥም ዘመናት ያስቆጠረውን ሰውን በባርነትና በግዴታ አገልጋይነት የመያዝና በሰው የመነገድ ወንጀል በተሟላ ሁኔታ በወንጀልነት የሚደነግግና አጥጋቢ ቅጣት የሚጥል ስለመሆኑ መመርመር ያስፈልጋል ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የፍትህ አካላት ያለውን የህግ ማዕቀፍ ተግባራዊ በማድረግ በሰው የመነገድ ልዩ ባህሪ በመነሳት በብዛት የወንጀሉ ሰለባ የሚሆኑ በተለያዩ በህፃናቶችና በሴቶች የመነገድ ወንጀልን ለመከላከል ለመግታትና ወንጀል ፈፀሚዎቹ በህግ ተጠያቂ ለማድረግ የሚያደረጉት እንቅስቃሴ የችግሩን ክብደትና እስከ ውጤት ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባና አጥጋቢ ነው ብሎ ለመደምደም የሚቻል መሆኑን መመርመር የህገ መንግስቱን አንቀፅ 18 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 18 አንቀፅ 3 ከማክበርና የማስከበር ያላፊነታችን ጋር በተያያዘ ሁኔታ መታየት ያለበት ነው፡፡

የወንጀል ህጉ አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገው የስብዓዊ ተፈጥሮዊ ክቡርነት መርህ በማናቸውም ጊዜና ቦታ የማይገስስና የማይገፈፍ መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ10(1)የተደነገገው መሠረታዊ መርህ ነፀብራቅ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አንቀፅ 18 ድንጋጌ የወንጀል ህጉን ቅርፅና ይዘት በመወሰንና የፍትህ አካላት ተግባርና ኃላፊነታቸው ሲወጡ ሊከተሉት የሚገባውን የሥራ ዲስፒሊንና ባህሪ ከመወሰን በኩል ከፍተኛ ድርሻ ያለው ድንጋጌ ነው፡፡ ይህንን ድንጋጌ ተከትሎ የተደነገጉት አንቀፅ 19(5) እና ሌሎች ህገ

መንግስታዊ ድንጋጌዎች በማክበርና በሚያስከብር ሁኔታ የዕለት ከዕለት ኃላፊነታችንን የመወጣት እንቅስቀሴችን ህገመንግስታዊ ማድረግ ከሁሉም በላይ ከፍትህ አካላት የሚጠበቅ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. የሞት ቅጣት ተፈፃሚ የሚሆኑባቸው ወይም ወደእድሜ ልክ የተቀየረላቸው መሆኑን ሣያውቁ ለረዥም ጊዜ የሚጠብቁ ፍርድኞች ኢሰብዓዊ ለሆነ አያያዝ ተጋልጠዋል ብሎ ለመደምደም ይቻላል? ለምን?
2. 1949 ወጥቶ ሲሠራበት የቆየው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ተካትቶ የነበረና በኢፌ.ደ.ሪ የወንጀል ህግ እንዳይካተት የተደረገው የወንጀል ቅጣት አለን ? ምክንያቱን ምንድን ነው?
3. አንድ ሰው በወንጀል ተጠርጥሮ ከተያዘ በኃላ ወደ ፖሊስ ጣቢያ አልሄድም በሚልበት ጊዜ ህግ አሰከባሪው የሚወሰደው እርምጃ እና የህገ መንግስቱ አንቀፅ 18 ንዑስ አንቀፅ1 እንዴት ሊጣጣም ይችላል?ምን የጥንቃቄ እርምጃዎች በህግ አስከባሪው በኩል መደረግ አለበት?
4. በሰዎች የመነገድ ወንጀል በተለይም በሴቶች እና ህፃናት የመነገድ ወንጀልን ለመከላከል አጥፊዎችን ለህግ ለማቅረብ በአካባቢያችሁ የተወሰዱእርምጃ አለ? ምንምን ናቸው?

## 1.5 <u>ህገ መንግስታዊ የሥነ ሥርዓት መብቶች እና የወንጀል ህግ</u>

ህገ መንግስት ከላይ የተገለፁትን የወንጀል ህጉን ቅርፅና ይዘት ገዥ የሆነ መርሆችንና ድንጋጌዎችን ከመደንገጉ በተጨማሪ መንግሥት አንድን ሰው በወንጀል ጠርጥሮ ሲይዘው፣ የወንጀል ምርመራና ብርበራ ተግባራትን ሲያከናውን የወንጀል ክስ አቅርቦት ሲከራከርና  የወንጀል ፍርድ ሲሰጥ ማክበርና ማስከበር የሚያገባውን ሥነ-ሥርዓታዊ መብት በመደንገግ በአገሪቱ ሊታወጅና ሊሠራበት የሚገባውን የሥነ-ሥርዓት የማስረጃ የህግ ማዕቀፍ ይዘትና ቅርፅ ገዢ የሆኑ ድንጋጌዎችን ያሰቀምጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ህግ አስከባሪው ሥነ-ሥርዓታዊ መብታቸውን በሚጥስበት ጊዜ የተያዙ የተከሰሱና በፍርድ የተሰሩ ሰዎች አቤቱታ አቅርበው መብታቸው እንዲከበር ለማድረግ የሚቻሉበትን ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

በወንጀል ተጠርጥረው የተያዙ የተከሰሱና በፍርድ የተሰሩ ሰዎች ሥነ-ሥርዓታዊ መብትን ዓለም አቀፍ ይዘት እና ዕውቅና ጥበቃ የተሰጣቸው ናቸው በተለይም ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ የቃል ኪዳን ስምምነት በአንቀፅ 9 እና በአንቀፅ 14 ስምምነቱን ፈራሚ አገሮች በአገራቸው የህግ ማዕቀፍ ሊያካትቷቸው እውቅና እና ጥበቃ ሊሰጧቸው የሚገቡ መብቶችን በመዘርዘር ይደነግጋሉ፡፡ የሥነ ሥርዓታዊ መብቶች ዓላማና ግብ በማንኛውም ሰው በሰብአዊ ፍጡርነቱ የተጎናፀፈውን ነፃነት አላአግባብና ከህግ ውጭ በመንግስት እንዳማይጣስ ዕውቅና እና ጥበቃ መስጠት ነው፡፡ የሥነ ሥርዓታዊ መብቶች መሠረታዊ ይዘት ከመዘርዘራችን በፊት ስለ ነፃነት መብት በጥቅሉ በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሠነዶችና በህገ መንግስቱ የተሰጠውን ዕውቅና እና ጥበቃ በአጭሩ ማየት ይገባል፡፡

### 1.5.1. ነፃነት መብቶችና ሥነ ሥርዓታዊ መብቶች በጠቅላላው

በዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶችና ቃል ኪዳን ስምምነትና በሌሎች ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ህግጋት እና በህገ መንግስቱ አንቀፅ 19ና አንቀፅ 20 እና በሌሎች ድንጋጌዎች የተካተቱት የሥነሥርዓታዊ መብቶች መሠረታዊ ዓላማ መንግሰት ያለ በቂ ምክንያትና ህጋዊ ሥርዓት የአንድን ሰው የነፃነት መብት እንዳይገድብ ዋስትና እና ጥበቃ መስጠት ነው፡፡ የብዙ አገሮች ህገ መንግስት የአንድ ሰው በህይወት የመኖር የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት ከሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ክቡርነት የመነጨ ሊደፈሩና ሊገሠሡ የማይችሉ መብቶች መሆናቸውን በመግለፅ ይደነግጋሉ፡፡

ከዚህ በላይ የአማርኛ ቁንቋ ነፃነት የሚለው ቃል እጅግ ሰፊ ይዘትና ትርጉም ያለውን የእንግሊዘኛው' liberty 'የሚለውን ቃልና ለመግለፅ እንጠቀምበታለን፡፡ የነፃነት መብት /liberty/ በይዘቱ አንድ ሰው የሌላውን ሰው ወይም የሌሎችን ሰዎች መብትና ነፃነት የማይነካ ወይም የማይገፋ የፈለgውን ማናቸውንም ድርጊት የመፈፀምና ሀሳብን የመግለፅ መብት የሚያካትት ነው፡፡ ስለዚህ ከቦታ ወደ ቦታ የመዘዋወር ነፃነት፣ ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት፣ የእምነትና የሃይማኖት ነፃነት፣ በመረጠው የሥራ መስክ የመሥራት ነፃነት፣ የመረጃነት ነፃነት፣ እና ሌሎችም በርካታ ነፃነቶች የነፃነት መብት በሚለው ሰፊ ይዘትና ትርጉም ባለው የመብቶችን ስብስብ በሚገለፀው ፅንሰ ሀሳብ የሚጠቃለሉ ናቸው፡፡

አንዳንድ ፀሀፊዎች እስካሁን ወጥተው ሥራ ላይ በዋሉ ህጎችና የሰብዓዊ መብት ሰነዶች የተዘረዘሩ መብቶች በአራት መሠረታዊ ነፃነቶች አጠቃልሎ መግለፅ የሚቻል መሆኑን በሁለተኛው ዓለም ጦርነት የዩስኤሜሪካ ኘሬዝዳንት የነበሩትን ኘሬዝዳንት ሩብቨልት አነጋገር መሠረት  በማድረግ ይገልፃሉ ፡፡ ኘሬዚዳንቱ አገላለፅ አራቱ መሰረታዊ ነፃነቶች ከፍርሃት ነፃ መሆን ከመቸገር (ከመከጀል ነፃ መሆን)፣ የእምነት የሀይማኖት ነፃነት እና ሀሳብን የመግለፅነፃነት  ናቸው፡፡

የነፃነት መብት በባህሪው ፍፁማዊ መብት አይደለም፡፡  የአንድ ሰው በፈለገው መንገድ ሀሳቡን የመግለፅና የፈለገውን የመፈፀም መብት ህጋዊ ዕውቅና እና ጥበቃ የሚሰጠው የሌላውን ሰው ወይም የሌሎችን ሰዎች መብትና ነፃነት እስካልነካ  ድረስ ብቻ ነው፡፡ የአንድ ሰው እጅን  የመዘርጋት  ነፃነት የሚከበረው የሌላውን ሰው አፍንጫ ወይም አካል አስካልነካ ድረስ መሆኑንና  መብትና ግዴታ  የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች መሆናቸው መረዳት ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ አንፃር ሥነሥርዓታዊ መብቶች መንግስት ያለ በቂ ምክንያቶች ህጋዊ ሥርዓት ህገ መንግስታዊ ዕውቅና እና ጥበቃ የተሰጠውን የነፃነት መብቶች እንዳይገደብና የሰውን ነፃነት የሚገድብ እርምጃ በሚወስድበት ጊዜ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ ሊከተላቸው የሚገቡ መሠረታዊ ሥርዓቶችና ሊፈፅማቸው የሚገቡ ሁኔታዎችን ይደነግጋል፡፡ ህገ መንግስቱ መሠረታዊ ሥርዓቶች በመደንገግ በአገሪቱ የህግ የበላይነትና ልዕልና የከበረ የወንጀል የምርመራ የክስ የሙግት የፍርድ ሒደት እንዲረጋገጥ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው በህገ መንግስቱ የተደነገጉ መብቶች መንግስት ህገ መንግስታዊ ዕውቅና እና ጥበቃ የተሰጠውን  መብት መንግስት ያለ አግባብ እና ህገዊ ሥርዓት እንዳይገደብ  የምርመራ የክስና የፍርድ ሒደቱ ሊያከብራቸው

- የቀረበባቸውን ክስ  የመረዳትና የክሱን የክሱን ኮፒ የማግኘት
- በተከሰሱበት ጉዳይ ከፍርድ በፊ እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት
- በተከሰሱበት ጉዳይ በምስክርነት እንዲቀርብ ያለመገደድ መብት
- የቀረበባቸውን ማስረጃ የመመልከትና ምስክሮቻቸውን የመጠየቅ መብት
- የመከላከያ ማስረጃ  እንዲቀርብላቸው የመጠየቅ መብት
- በመረጡት የህግ ጠበቃ የመወከል መብት
- በመንግስት ወጭ ነፃ የጠበቃ ድጋፍና ግልጋሎት የማግኘት መብት

- በመንግስት ወጭ የክርክሩ ሒደት እንዲተረጎምላቸው የመጠየቅ መብት የሚያካትት መሆኑን ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 19 እና 20 እና ሌሎች ተያያዥነት ያቸላው ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ያቻላል ፡፡

### 5.1.2 አንድ ሰው ሲያዝ ሊከበሩ የሚገቡ ሥነሥርዓታዊ መብቶች

(ሀ) ተጠርጥሮ የተያዘበት ምክንያት የመረዳት መብት

ከላይ እንደተገለፀው የነፃነት መብት ሊገሰስና ሊገፈፍ የማይችል ከሰው ልጅ ተፈጥሮዊ ክብርነት የመነጨ መብት ነው፡፡ የነፃነት መብትን ለመገደብ የሚቻለው በህግ በተደነገገ ሥርዓትና ህጋዊ ሥርዓትን በማሟላት መሆን እንደሚገባ የህገ መንግስት አንቀፅ 17 በግልፅ ይደነግጓል፡፡ መንግስት የአንድን ሰው ነፃነት ሊገድብ የሚችልበት ህጋዊ ሥርአት ሰውየው በአገሪቱ የወንጀል ህግ በተደነገጉት ድንጋጌዎች አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑትን በመተላለፍ በድርጊት ወይም በመታቀብ የአገርን የመንግስትን የህብረተሰቡን ወይም የግለሰብን ሰላም ደህንነት መብት ወይም ጥቅም የሚጎዳ የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል የሚል ጥርጣሬ ሲያድርበት ነው ፡፡

መንግስት ወይም መንግስት ወክሎ የሚይዘው አካል (ፖሊስ) በአካባቢው ወንጀል ስለመፈፀሙ መረጃ ሳይደርሰውና ተጠርጣሪው ተፈፀመ የተባለውን ወንጀል ፈፅሞ ሊሆን ይችላል ብሎ ለመጠርጠር መነሻ የሚሆኑና ምክንያታዊ ጥርጣሬ የሚፈጥሩ ሁኔታዎች ሣይኖሩ ከምንም ተነስቶ የአንድ ሰው ህገ መንግስታዊ የነፃነት መብት በግምትና በዘፈቃደ የሚገድብ እስር እንዲፈፅም የህገ መንግስቱ አንቀፅ 14 እና አንቀፅ 17 ድንጋጌዎች የሚፈቅዱ አይደሉም፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው የተያዘው ሰው መሠረታዊ መብትም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡

የህገ መንግስቱ አንቀፅ 19 ወንጀል ፈፅመዋል በመባል የተያዙ ሰዎች የቀረበባቸውን ክስና ምክንያቶች ወዲያውኑ በሚገባቸው ቋንቋ እንዲነገራቸው መብት አላቸው በማለት ይደነግጋል ፡፡ የህገ መንግስቱ ድንጋጌ አገላለፅ በዓለም አቀፍ ሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 2 ጋር ተመሣሣይነት ያለው ነው፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 19 ንኡስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ድንጋጌ ማንም የማሰር ሥልጣን ያለው አካል ተጠርጣሪውን በምን ወንጀል እንደጠረጠረውና ለምን እንደጠረጠረው ለመግለፅና ለማስረዳት የሚያስችል በቂ ምክንያት ከሌለው አንድን ሰው መያዝ የሌለበት

መሆኑን ተጠርጣሪው የተጠረጠረበትን ወንጀል ይዘት ብቻ ሳይሆን የጥርጣሬው ምክንያቶችን በዝርዝርና ሊረዳው በሚችለው ቋንቋ የመናገር መብት ያለው መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ የህገ መንግስቱ ድንጋጌ ፖሊስ አንድ ሰው አንድ የወንጀል ድርጊት የፈፀመ መሆኑን የሚጠረጥርበት ምክንያት ከሌለው ሰውየውን መያዝ የማይችል መሆኑን ወንጀል ፈፅመዋል በመባል የተያዙ ሰዎች "ከሚለው" የህገ ምንግስቱ አገላለፅ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ድንጋጌው ፖሊስ አንድ ሰው ወደፊት ወንጀል ሊፈጽም የሚችል ስለመሆኑ መረጃ ደርሶኛል በሚል በህግ ተጠያቂ የሚያደርግ የወንጀል መሰናዶ ወይም የወንጀል ሙከራ የፈፀመ ስለመሆኑ መረጃ ያለገኘበትን ሰው በቁጥጥር ስር እንዲያውል የሚፈቅድ አይደለም፡፡ ህገ መንግስቱ አንድ ሰው ለመያዝ በህግ የሚያስጠይቅ ወንጀል ፈፅሟል የሚል ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሊኖር ይገባል፡፡ ይህንንም ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 19(1) ድንጋጌ ብቻ ሣይሆን የህገ መንግስቱ አንቀፅ 19(3) የመጨረሻው ፓራግራፍ "ወዲያውኑ ፍርድቤት እንዲቀርበ በተጠረጠሩበት ወንጀል ለመታሰር ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ ሊገለፅላቸው መብት አላቸው" በማለት የሚደነግግ መሆኑን በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ህገ መንግስቱ አንድ ሰው የተጠረጠረበትን ወንጀል እና የተያዘበትን ምክንያት የማወቅ መብት እንዳለውና ያለበቂ ምክንያታዊ ጥርጣሬ አንድ ሰው ህገ መንግስታዊ ነፃነት በመገደብ እስር መፈፀም የማይችል መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡ ህገ መንግስት አንድ ሰው ወደፊት በሚፈፀም ወንጀል ሊሣተፍ ይችላል በሚል ጥርጣሬ ለማሰር እንደማይችል (preventive detention) የማይፈቅድ መሆኑን ወይም አንድ ሰው ወንጀል ሊፈፅምብህ ይችላል ብሎ ለማሠር (protective detention) የማይችል መሆኑን የሚደነግግ ድንጋጌ ነው ፡፡

ምክንያቱም ወንጀል ፈፅመዋል ወይም በተፈፀመ ወንጀል ተሣታፊ ሆነዋል የሚል በቂ ምክንያት ሣይኖረው ፖሊስ አንድ ሰው በpreventive detention ሆነ በprotective detention እስር ፈፅሞ ቢገኝ የተያዙት የሰው የአካል ነፃነታቸው እንዲከበር ለፍርድቤት የማመልከትና የአካል ነፃነት መብታቸው የሚከበርበትን ሥርዓት ህገ መንግስቱ በአንቀፅ 19(4) የደነገገ መሆኑን ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 19(1) እና አንቀፅ 19(3) የመጨረሻው

ፓራግራፍ ጋር አጣምሮ በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር ስንመለከተው የነፃነት መብት ህገ መንግስቱ ከፍተኛ ዋስትና ጥበቃ ከሚሰጣቸው መብቶች አንደኛው መብት መሆኑንና ፖሊስ ይህንን መብት አንድ ሰው ወንጀል ለመፈፀሙ ምክንያታዊ ጥርጣሬ የሚያሳድር ሁኔታ ሣይኖረውና መያዝ የሌለበት በመሆኑና የያዘበትን ምክንያቱን ለተጠርጣሪው የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል ፡፡

ይኸም የአገሪቱ ሰዎች ያለ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ፖሊስ በፈለገው ጊዜ ሊይዘንና ሊያስረን ይችላል ከሚል ስጋት ነፃ ሆነው እንዲኖሩ ዋስትና የሚሰጥ ነው ፡፡ ይህንን ድንጋጌ ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓተው ሕግ አንቀፅ 11 እና አንቀፅ 12 አንቀፅ 18 ጋር ተጣምሮ መታየት ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም ወንጀል ተፈፅሟል በማለት አቤቱታው የሚያቀርቡ ሰዎች ወንጀል የተፈፀመ ስለመሆኑና ተጠርጣሪው ለወንጀሉ ተጠያቂ ስለመሆኑ ታዓማኒነት ያላቸው ጠቃሚ መረጃዎች ማቅረብ ያለባቸው መሆኑና ሀሰተኛ ጥቆማ ከጠቆሙ በወንጀል ህጉ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች መሰረት ተጠያቂነት የሚያስከትሉ መሆኑን የሥነ ሥርኣት ሕግ ድንጋጌዎቹን ከአንቀፅ 25 ጋር በጣምራ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከላይ የተደነገገውን የህገ መንግስቱ አንቀፅ19(1) አንድ በወንጀል የሚጠረጠር ሰው የመያዝ ሥልጣን ያለው አካል ሊፈፅማቸው የሚገቡ ግዴታዎች ባይፈፅምና ተጠርጣሪውን የያዘበትን ወንጀልና የተያዘበትን ምክንያት ባይገለፅለት ውጤቱ ምን ይሆናል የሚል ጥያቄ ምላሽ የሚያስፈልገው ነው፡፡

በህገ መንግስቱ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ተጠርጣሪውን የያዘው ፖሊስ የተጠረጠረበትን ወንጀልና የተያዘበት ምክንያት በፖሊሱ ያልተገለፀት የተያዘ ሰው በህግ መንግስቱ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት ፍርድ ቤት ሲቀርብ የያዘው ፖሊስ የጠረጠረበትን ወንጀልና የተያዘበትን ምክንያት መረዳት የሚችል መሆኑን ህገ መንግስቱ አንቀፅ 19(3) የመጨረሻው ፓራግራፍ ለመረዳት እንችላለን ፡፡

ስለዚህ የተያዙ ሰዎች በመርማሪው ፖሊስ ፍርድ ቤት በሚቀርብበት ጊዜ የተጠረጠሩበትን ወንጀል ምን እንደሆነ በእስር የሚቆይበት ምክንያት ያለ መሆኑን በመግለፅና በማስረዳት ህገ መንግስታዊ መብታቸው ማክበርና ማስከበር የጊዜ ቀጠሮ ጉዳይ የሚያየው ፍርድቤት ግዴታና ኃላፊነት ነው፡፡

የጊዜ ቀጠሮ ጉዳይ የሚያየው ፍርድቤት ተጠርጣሪውን የያዘው ፖሊስ ለተጠርጣሪው የተያዘበትን ወንጀልና ምክንያት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 19(1) መሠረት አልገለፀለትም በሚል ምክንያት የተከፈተውን የግዜ ቀጠሮ መዝገብ ማዘጋትና ተጠርጣሪው ከእስር እንዲለቀቅ ትዕዛዝ እንዲሰጥ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 19(3) ድንጋጌ የሚፈቅድ አይደለም፡፡ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 19(1) በፖሊስ የተከበረ ሆነ አልሆነ ፍርድቤቱ ተጠርጣሪው የተጠረጠረበትን ወንጀልና በእስር የሚቆይበትን ምክንያት ያለመሆኑን ለተጠርጣሪው በመግለፅና የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ ይህንን ግዴታና ኃላፊነቱን ለመወጣት መጣር አለበት፡፡

### (ለ) ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት

የህገ መንግስቱ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 3 አንድ ሰው ያለ ፍርድ ቤት ዕውቅና እና ትዕዛዝ ህግ አስከባሪ አካላት አስረው ለመቆየት የሚቻሉት ወደ ፍርድ ቤት ለመድረስ ጉዞው የሚፈጀው ጊዜ ሣይጨመር እጅግ ቢበዛ ለአርባ ስምንት ሠዓት ብቻ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ የተጠርጣሪው ፍርድ ቤት መቅረብ ተጠርጣሪው የሚያዝበት ህጋዊ ምክንያት ምን እንደሆነ ፖሊስ እንዲያስረዳ ተጠርጣሪው ተይዞ በሚቆይበት ጊዜ የአካል ደህንነት መብቱ የተከበረ መሆኑንና የተጠርጣሪው በእስር መቆየት ምርመራ ሥራውን ለማከናወን አስፈላጊ መሆን አለመሆኑን ለመወሰንና በተጠርጣሪው በኩል የሚቀርቡ አቤቱታዎችና የመብት ጥያቄዎች ሰምቶ ለመወሰን አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አንድ ሰው ሲያዝ በተፋጠነ ሁኔታ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት ያለው መሆኑ መደንገጉ ለነፃነት መብት ህገ መንግስቱ  የሚሰጠው ጥበቃና ዋስትና አንደኛው መገለጫ ነው፡፡

እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ ፖሊስ ተጠርጣሪውን ይዞ ፍርድ ቤት ከቀረበ በኃላ፡-

- በዓለም አቀፍ ወይም የወንጀል ህግ በወንጀልነት በማያስጠይቅ ድርጊት ፈፅሟል በሚል ጥርጣሬ የያዘው መሆኑን ቢገለፅ፣
- ፖሊስ የሰጠው ምክንያት ፍርድ ቤት የቀረበውን ሰው ለመጠርጠር የሚያስችል ወንጀል ስለመፈፀሙ በቂ መረጃ የማይሰጥ ቢሆን፣
- የወንጀል ምርመራውን ለማጣራት የተጠርጣሪው በእስር መቆየት አስፈላጊ አይደለም የሚል መደምደሚያ ላይ ሲደርስ፣ፍርድ ቤቱ ሁል ጊዜ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 59 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ተጠርጣሪው ዋስ እንዲጠራ ማድረግ ይገባዋል ወይ? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

(ሐ) አካልን ነፃ የማውጣት መብት

ፖሊስ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 19(1) መሠረት ተጠርጣሪው የተጠረጠረበትን ወንጀልና የተያዘበትን ምክንያት ካለመግለፅ በተጨማሪ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 19 (3) መሠረት ፍርድ ቤት ባያቀርበው ምን አይነት የእርምት እርምጃ ይወሰዳል የሚለው ሌላው የሚነሣው ጥያቄ ነው፡፡ አንድ አስፈፃሚ ወይም ህግ አስከባሪ አካል ተጠርጣሪውን ሊቀርብ የሚችልበት ፍርድ ቤት በአቅራቢያው እያለ ከአርባ ስምንት ሠዓት በላይ ፍርድ ቤት ሣያቀርብ ከቀረ እስሩ ህጋዊ መሆኑ ይቀራል፡፡ ስለዚህ ህጋዊ ያልሆነ እስር (illegal arrest) ተድርጎ እንደሚወሰድ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 4 ይደነግጋል፡፡ ይኸም በመሆኑ የተያዘው ሰው በማናቸውም ሰው አማካኝነት በሚያቀርበው አቤቱታ ፍርድ ቤቱ ያለህጋዊ ምክንያት የነፃነት መብቱን የገደበው አካል ፍርድ ቤት ይዞ ቀርቦ ለምን እንደያዘው እንዲያስረዳና የአካል ነፃነት መብቱ እንዲከበርለት መጠየቅ የሚቻል መሆኑ አቤቱታው የሚቀርብበት ሥርዓትም ከፍታብሔር ሥነ ሥርዓት 177-179 እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

አካልን ነፃ የማውጣት ጥያቄ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጥያቄው እንደቀረበለትና ፖሊስ ከአርባ ስምንት ሠዓት በላይ በራሱ ስልጣን ተጠርጣሪውን ይዞ መቆየቱን እንዳረጋገጠ ወዲያውኑ ፖሊስ ተጠርጣሪውን እንዲለቅ ሀልጊዜ ትዕዛዝ መስጠት የለበትም፡፡ ፍርድ ቤቱ ፖሊስ ህገ መንግስቱን ባለማክበር ተጠርጣሪውን ይዞ መቆየቱን ብቻ ሣይሆን የተጠርጣሪውን የአካል ነፃነት መብትና ተጠርጣሪው ፈፅሞታል ተብሎ የተጠረጠረበትን ወንጀልና ምክንያት አስመልክቶ ተጠርጣሪው ይዞ የመጣው አካል የሚሰጠውን መግለጫ በመስማት የተጠርጣሪው የአካል ነፃነት እንዲከበርና ከእስር እንዲለቀቅ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ቢሰጥ ፍትህን የሚያስተጓጉል የሚሆን ሆኖ ባገኘው ጊዜ፣ ከዚያ በኋላ ምርመራውን ለማጣራት የሚያስችል የጊዜ ቀጠሮ ሊሰጥ የሚገባው መሆኑን የህገ መንግስቱ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 4 ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

የህገ መንግስቱ አንቀፅ 19(4) ድንጋጌ መሠረታዊ ዓላማ ተጠርጣሪዎች ህገ ወጥ እስር በፍርድ ቤት ታይቶ የአካል ነፃነታቸውን ማስከበር ሆኖ በሌላ በኩል ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ሥር የዋለው አካል ወይም የፖሊስ አዛዥ ወይም የፖሊስ አባል ከአርባ ስምንት ሠዓት በላይ ተጠርጣሪውን ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማሠሩ ምክንያት በአገር

በመንግስት በህዝብ እና በግለሰቦች ሰላም ደህንነት መብትና ጥቅም ላይ ከባድ ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የተያዘው ተጠርጣሪ በሥነ ሥርዓት ግድፈት ምክንያት ቢለቀቅ የሚደርሰውን ጉዳት ማመዛዘን እንደሚገባው በግልፅ አስቀምጧል፡፡

የተከሳሽ መለቀቁ የፍትህ መጓደል የሚያደርስ ሲሆን ተጠርጣሪው ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ሥር ያዋለው አካል በፈፀመው የሥነ ሥርዓት ግድፈትና የህግ ጥሰት ላይ ከማተኮር ይልቅ ከዚያ በኋላ እስሩ ህጋዊ ሆኖ ምርመርው የፍርድ ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገበት እንዲቀጥል ማድረግ እንደሚገባ ህገ መንግስቱ በአንቀፅ 19(4) ይደነግጋል፡፡ አንቀፅ 19(4) የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ የተከሳሽን መብት የመንግስትንና የጠቅላላውን ህዝብ ሰላምና ደህንነትና የወንጀሉ ሰለባ የሆኑ ሰዎች መብት በማመዛዘን ተግባርና ኃላፊነቱን መወጣት እንዳለበት የሚያመለክት አግባብ ደንግጓል፡፡

ሌላው ከዚህ ጋር መታየት ያለበት ተጠርጣሪው የተያዘበት ወንጀል ለፍርድ ቤቱ ከተገለፀለት በኋላ የተጠርጣሪው በእስር መቆየት ወንጀሉን ለመርመር አስፈላጊ የማይሆን ሆኖ ካገኘውና ተጠርጣሪው ፈፅሞታል የተባለው ወንጀል በህግ በዋስትና መብት እንዳይፈታ የማያስከለክል ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤቱ በተጠርጣሪውን በአንቀፅ 19 (6) እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 59(1) መሠረት ዋስ እንዲፈታ ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡ በዋስ የመለቀቅ መብት በአገራችን ህገ መንግስታዊ ዋስትና እና ጥበቃ የተሰጠው መብት ነው፡፡ ፍርድ ቤት ትዕዛዙን ከመስጠቱ በፊት የምርመራው ሥራው ላይ የሚያሣድረውን ተፅዕኖ የሚኖረውን ጥቅምና የሚያስከትለውን ጉዳት ማመዛዘን መቻል አለበት፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. በአርባ ስምንት ሠዓት ውስጥ አንድ ተጠርጣሪ ፍርድ ቤት መቅረብ ያለበት መሆኑ በህገ መንግስቱ መደንገግ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ምንድን ነው?
2. ፖሊስ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 28 መሠረት በዋስ ወይም ያለ ዋስ ሊለቀው የሚገባውን ተጠርጣሪ የጊዜ ቀጠሮ ፋይል በማስከፈት ፍርድ ቤት ይዞ ቀረበ፡፡ ዕርስዎ በችሎቱ የተሰሙት ዳኛ ቢሆኑ ምን አይነት ትዕዛዝ ይሰጣሉ?
3. ሆነ ብሎ የሰው መግደል ወንጀለ ፈፅሟል የተባለ ተጠርጣሪ ላይ ምርመራ ለማጣራት ጊዜ እንደሰጠው ፖሊስ የጊዜ ቀጠሮ ፋይል አስከፈተ፡፡ የጊዜ ቀጠሮ ፋይል የያዘው

ፍርድ ቤት ለአስር ጊዜ ያህል የአስር ቀን ጊዜ ቀጠሮ ሰጠ፡፡ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ጊዜ ቀጠሮ ሲጠናቀቅ ፖሊስ የምርመራ መዝገቡ ይዞ በመቅረብ የምርመራው ሂደት የደረሰበትን ደረጃ ያጋጠመውን ችግር ለማስረዳት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ የጊዜ ቀጠሮ ለመስጠት የማይችል መሆኑን በመግለፅ የጊዜ ቀጠሮ ፋይሉን በመዝጋት ተጠርጣሪው ለታሠራበት ማረሚያ ቤት በፅሑፍ አሳወቀ፡፡ ማረሚያ ቤቱ ፍርድ ቤት የመፍቻ ትዕዛዝ አልሰጠም በሚል ምክንያት አንድ ወር በእስር ካቆየው በኋላ ተጠርጣሪው ያለ ህጋዊ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ታሥሮ የሚገኝ መሆኑን በመግለፅ ፍርድ ቤቱ የአካል ነፃነቱን የማውጣት መብት እንዲያስከብርለት አመለከተ፡፡ ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 19(4) ድንጋጌ አንፃር እንዴት ይፈቱታል? ምን አይነት ትዕዛዝ ይሰጣሉ? ለምን?

4. ዐቃቤ ህግ የምርመራ መዝገቡ ከደረሰው በኋላ ለክስ ማቅረቢያ በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 109 ከተሰጠው አስራ አምስት ቀን በላይ በማቆየቱ የምርመራ መዝገቡን አይቶ ተገቢውን ውሳኔ ባለመስጠቱ በህገ ወጥ መንገድ ታሥሬአለሁ የሚል አቤቱታ ቢቀርብልዎ ምን አይነት ትዕዛዝ ይሰጣሉ? ለምን?

### 5.1.3 የተጠረጠሩ ሰዎችዝምየማለትመብትቃል እንዳይሰጡያለመገደድና በራሳቸው ላይ ያለመመስከር መብት፣

#### (ሀ) ያለመናገር ማናቸውንም ቃል ወይም ማስረጃ እንዲሰጥ ያለመገደድ መብት

በወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው ያለመናገር ህገ መንግስታዊ መብት ያለው መሆኑ በአንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 2 የመጀመሪያው ፓራግራፍ የተደነገገ ሲሆን የተጠረጠሩ ሰዎች የተከሳሽነት ቃል በፈቃዳቸው የሚሰጡ ከሆነ የሚናገሩት ማናቸውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብባቸው የሚችል ስለመሆኑ ማስገንዘቢያ የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን የህገ መንግስቱ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 2 ይደነግጋል፡፡ የተጠርጣሪ ያለመናገር መብት በምርመራ ጊዜ ብቻ ሳይሆን የወንጀል ክስ ቀርቦ ከተነበበ በኋላ ለፍርድ ቤት የዕምነት ክህደት ቃል እንዲሰጡ ሲጠይቁ ዝም የማለት መብት ያላቸው መሆኑንና የተጠርጣሪው ወይም የተከሳሽ ዝምታ ወንጀሉን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም ተብሎ ሊያዝ እንደሚገባ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 19(2) ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 27 እና አንቀፅ 133 በማጣመር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

የተጠርጣሪ ወይም የተከሳሽ ያለመናገር መብት የወንጀል ምርመራ የትኩረት ማዕከል ተከሳሹ የሚሰጠውን ቃል ማግኘት መሆን የሌለበት መሆንና መርማሪው አካል ከተከሳሽ ስለወንጀሉና ስለ ወንጀሉ አፈፃፀም ፍንጭና መረጃ ሊያገኝ የሚችለው ተከሳሹ ወዶና ፈቅዶ ቃሉን ሲሰጥ ብቻ እንደሆነ በመደንገግ፣ መርማሪ አካላት ቃልህን መስጠት አለብህ በማለት በሚፈጠሩ የመገደድ አሰራሮች ምክንያት ሊፈጠር የሚችል የመብት ጥሰት ከምንጩ የሚያደርቅ ድንጋጌ ነው፡፡ ተጠርጣሪው ቃሉን የሚሰጥ ከሆነ ቃሉ በማስረጃነት የሚቀርብ መሆኑ አስቀድሞ ማስገንዘቢያ ሊሰጠው እንደሚገባ ህገ መንግስቱ ይደነግጋል፡፡

- አከራካሪው ጉዳይ የድንጋጌው ይዘት ሳይሆን የድንጋጌው መጣስ የሚያስከትለው ውጤት ነው፡፡ መርማሪው አካል ተጠርጣሪው የሚናገረው ማናቸውም ቃል ማስረጃ ሆኖ ለፍርድ ቤት የሚቀርብበት መሆኑን ሣይናገር የተጠርጣሪውን ቃል የተቀበለው መሆኑ ቢረጋገጥ የተከሳሽነት ቃሉ በማስረጃነት ተቀባይነት አለው ወይስ የለውም? የማስረጃው ታዓማኒነት እንዴት ይታያል? መርማሪው ህገ መንግስታዊ ድንጋጌውን ሣያከብር የተገኘውን ማስረጃ በፍርድ ሂደት ያለው ውጤት ምንድን ነው? የሚለው ነው፡፡

ማናቸውም ሰው የዕምነት ቃል እንዲሰጥ ያለመገደድ መብት ያለው መሆኑና በመገደድ የተገኘ ማስረጃ ወይም የዕምነት ቃል ተቀባይነት የሌለው መሆኑን የህገ መንግስቱ አንቀፅ 9(5) ላይ ደንግጓል፡፡ ህገ መንግስቱ አንቀፅ 9(5) ደንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ “የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምኑ አይገደድም፡፡ በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም” የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ይኽ ድንጋጌ በዓለም አቀፍ ደረጃ ማናቸውንም ጭካኔ የሞላበት ኢሰብዓዊና አዋረጅ የሆነ አያያዝና ቅጣት ለማስቀረት ከተደረገው የቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 15 ድንጋጌ ጋር ተመሳሳይና ለቃል ኪዳን ስምምነት ህገ መንግስታዊ ዕውቅና የሚሰጥ ነው፡፡ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 19(5) በህገ መንግስቱ አንቀጽ 14 እና አንቀጽ 16 ጥበቃ እና ዋስትና የተሰጠው የአካል ደህንነት መብት በመድፈርና እና በህገ መንግስቱ አንቀጽ 18(1) የተደነገገውን ከማናቸውም ጭካኔ ከሞላበት ኢሰብዓዊ የሆነ ክብሩን የማያዋርድ አያያዝ የመጠበቅ መብትን

በመጋፋት መርማሪው አካል አንድ ሰው የእምነት ቃል ከተቀበለ ፍርድ ቤቶች በማስገደድ የተገኘውን ማስረጃ መቀበል የሌለባቸው መሆኑን የሚደነግግ ነው፡፡

ከላይ የተገለጹት መሰረታዊ ነጥቦች እንዳለ ሆኖ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 19(5) “በማስገደድ” የተገኘ ማስረጃ ወይም በእንግሊዘኛው “Any evidences obtained under coercion shall not be admissible” በማለት አገላለጽ የተጠቀመ በመሆኑ

- አንድ ሰው ተገድዶ ወይም (under coercion) ነው የእምነት ቃል የሰጠው የሚባለው ምን ምን ሁኔታዎች ሲፈጽሙ ነው?
- አንድ ሰው የእምነት ቃል እንዲሰጥ የማስገደጃ መንገዶች ምንድን ናቸው?
- አንድ ሰው ተገድዶ የእምነት ቃል የሰጠ መሆኑን ሲገልጽ መርማሪው አካል አልተገደደም በማለት ይከረከራል ተካሳሹ ተገድዶ የእምነት ቃል የሰጠ መሆኑን የማስረዳት ሸክም ያለበት ማንኛውም ወገን ነው?
- ማስረጃ ተቀባይነት የለውም “inadmissible” የሚለው አባባል ከማስረጃ ታዓሚኒነትና የማስረጃ ክብደት ከሚሉት ጽንሰ ሀሳቦች በምንድን ነው የሚለየው? የሚሉትን ነጥቦ በትኩረት ማየት ይጠይቃል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 5 የመጀመሪያው ፓራግራፍና የመጨረሻው ፓረግራፍ የቃላት አጠቀቀምና የሀሳብ አገላለጽ የተካተቱ መሰረተ ሀሳቦች ምንድ ናቸው? የሚለውን ነጥብ በዓለም ዙሪያ አከራካሪ የሆነ ጉዳዮች በተለይም በማስገደድ በተገኘ እምነት ቃል መነሻ በማድረግ ከተገኘ ግዙፍነት ያላቸው ተጨማሪ ማስረጃዎች መገኘት (corroborative evidence) ጋር ተያያዦ የሚነሱ ጥያቄዎች አንጻር ማየት ይጠይቃል፡፡

ጉዳዩን በዝርዝር ለማስቀመጥ በሰው መግደል ወንጀል የሚጠረጠር ተጠርጣሪ በፈቃዱ የእምነት ቃል ለማስጠት ፍላጎት የሌለው መሆኑን የተገነዘበው መርማሪ በብረት ድስት ሙሉ ዘይት ካፈላ በኃላ ተጠርጣሪውን እውነቱን የማትናገር ከሆነ ይህንን የፈላ ዘይት ሰውነትህ ላይ አፈሰዋለሁ በማለት ዘይቱን እግሩ ላይ ማፍሰስ ሲጀምር ተጠርጣሪው ሚችን የገደለው መሆኑ የሚችን አስከሬን ቆፍሮ እንደቀበረው ሚችን የገደለበት ጩቤ/ቢለዋ የሚች ልብስና ከሚች የወሰደውን ገንዘብ ከእህቱ ቤት ከእህል ጎተራ እንዳስቀመጠው ተናግሮ መርማሪው ይህንን የተከሳሽ ቃል በመጠቀም የሚችን አስከሬን የሚች ልብስ ሚች በሬ ሸጦ ይዞት የነበረው 5000 ሺ ብር ደም የነካው ጩቤ በዕምነት

ቃሉ መሠረት አገኘ፡፡ ጩቤው ሲመረመር የተከሳሽ የእጅ አሻራና የሟች ደም የነካ መሆኑ በሳይንሳዊ ምርመራ ተረጋጋጠ፣ ዓቃቤ ህግ በተከሳሹ ላይ ክስ ሲያቀርብ ተከሳሹ የሰጠውን የተከሳሽነት ቃል ሳይሆን የሟች አስከሬን ተቀብሮ መገኘቱን የሚያሳይ ቪዲዮ፣ የሟች ልብስ፣ ሟች የተገለበትን ጩቤ ሳይንሳዊ ማስረጃና ሌሎች የአካባቢ ሁኔታ ማረጃዎችን አቀረበ፡፡ የተከሳሽ ጠበቃ የሟች አስከሬን የተገኘበትን ቦታ የሚያሳየው ቪዲዮ ደም የነካ የሟች ልብስ ገንዘቡና ጩቤው ከተከሳሽ እህት ጎተራ መገኘቱን የሚያሳየው ማስረጃ እና ግዙፍነት ያላቸው ማስረጃዎች በሙሉ ተከሳሽ ተገድዶ የሰጠው የእምነት ቃል ውጤት በመሆናቸው በማስገደድ የተገኙ ማስረጃዎች ናቸው፣ ስለዚህ ተቀባይነት ሊኖራቸው አይገባም በማለት የህገ መንግስቱን አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 5 በመጥቀስ ተቃወመ፡፡ እርስዎ ጉዳዩን የያዙት ዳኛ ቢሆኑ የተከሳሹን የእምነት ቃል መሰረት በማድረግ መርማሪው ያገኛቸውን ግዙፍነት ያላቸው ማስረጃዎችና እነርሱ ተመርምረው የተገኛውን ሳይንሳዊ ማስረጃ ተቀባይነት አስመልክቶ ምን አይነት ብይን ይሰጣሉ? ለምን?

### (ለ) ራስን ወንጀለኛ የሚያደርግ ጉዳይ በምስክርነት ያለማቅረብ መብት

ማንም ሰው በተከሰሰበት ጉዳይ በምስክርነት እንዲቀርብ ከመገደድና በራሱ ላይ ያለመመስከር መብት ያለው መሆኑ መንግስት ከተከሳሹን በማስረጃነት የሚጠቅም ማናቸውም ማስረጃ የሚያገኘው ተከሳሹ ፈቃደኛ ሲሆን ብቻ ነው ከሚለው መርህ ጋር ተያያዥነት ያለው ቢሆንም የራሱ የሆነ ምክንያትና መነሻ አለው፡፡ በፍትሐብሔር ጉዳይ ተከሳሽ በፍትሐብሔር ቃለ መሀላ እንዲፈፅምና ስለተከሰበበት ጉዳይ እንዲመሰክር የሚደረግበት ሁኔታ ያለ ቢሆንም በወንጀል ጉዳይ ራሱን ወንጀለኛ እና ጥፋተኛ የሚያደርግ የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ ተከሳሽ ሊገደድ የማይገባው መሆኑን ከህገ መንግስት አንቀፅ 20(3)ተደንግጓል፡፡

በወንጀል ጉዳይ በምስክርነት ቀርበው ቃላቸውን እንዳይሰጡ የማይገደዱ ምስክሮች “previledge witnesses” በማለት የተለያዩ አገሮች የህግ ጥበቃና እና ዋስትና የሚሰጡ ሲሆን ከነዚህ መካከል ማንም ሰው ራሱን ጥፋተኛ የሚያደርግ የምስክርነት ቃል ያለመስጠት መብት አለው የሚለው አንደኛው ነው፡፡ የድንጋጌው መልዕክት ግልፅ በመሆኑ ብዙ ትርጉም የሚያስፈልገው አይደለም:: ሆኖም የዚህ ድንጋጌ አፈፃፀም

አስመልክቶ የሚነሱ የተለያዩ አከራካሪ ጉዳዮች በመሆኑ የሚከተሉት ሁኔታዎች በመመርመር ከጋራ መግባባት ላይ መድረስ ያስፈልጋል፡፡

- አቶ “A” አቶ ”B” ገድሏል የሚል ክስ ቀርቦበት አቶ “C” ወንጀሉን አቶ“A” ሲፈፅም አይቻለሁ በማለት የምስክርነት ቃሉን ለመስጠት ፍርድ ቤት ቀረበ፡፡ አቶ “C” ዓቃቤ ህግ ባቀረበበት ዋና ጥያቄ ምላሽ ከሰጠ በኋላ የአቶ ”B” ተከላካይ ጠበቃ የሚያቀርበው የመስቀለኛ ጥያቄ አቶ “A” የገደለው ተከሳሹ አቶ ”B” ሳይሆን ምስክሩ አቶ “C” መሆኑን የሚያመላክቱ ፍሬ ጉዳዮች በአቶ “C” መገለፅ ጀመሩ፡፡ ሆኖም አቶ “C” ከዚህ በኋላ የሚሰጠው መልስና ምስክርነት እኔን ወንጀለኛ የሚያደርግ በመሆኑ እኔን ወንጀለኛ የሚያደርግ የምስክርነት ቃል ከመስጠት የመጠበቅ መብት አለኝ ለተከሳሽ ተከላካይና ጠበቃ ጥያቄም ሆነ ለዓቃቤ ህግ ድጋሚ ጥያቄና ለፍርድ ቤቱ ማጣሪያ ጥያቄ መልስ አልሰጥም በማለት በፍርድ ቤቱን ጠያቂ በማሳወቅ ምስክርነት ቃሉን መስጠቱን በማቋረጥ ዝም አለ፡፡ የተከሳሹ ተከላካይ ጠበቃ በበኩሉ አቶ “C” የሚሰጠው መልስ ለጉዳዮ ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ በመሆኑ የምስክርነት ቃሉን ሊሰጥ ይገባል የሚል ክርክር አቀረበ፡፡ ይህንን ጉዳይ ለመወሰን አግባብነት ያላቸው ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች የትኞቹ ናቸው፡፡ በጉዳዮ ምን አይነት ብይን ይሰጣሉ?
- በዋና ወንጀል አድራጊነት ሳይሆን በሌላ ሁኔታ በወንጀል ተካፋይ የሆኑ ሰዎች ለምሳሌ በወንጀሉ አነሳሽ ወንጀሉ ከተፈፀም በኋላ ተከሳሽን በመርዳት ወንጀል የተከሰሰ ሰው ስለ ዋናው ወንጀል ፈፃሚ የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ ሲጠይቅየህገ መንግስቱ አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ 3 ሊነሳ የሚችል ነውን?

በተለይ ዓቃቤ ህግ በአንድ መዝገብ ሳይሆን በተለያየ ክስና መዝገብ ሰዎቹ በሚከሰሱበት ሁኔታ ተፈፃሚነት አለው ወይስ የለውም?

- የህገ መንግስቱ አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ 3 ሁለተኛው ፓራግራፍ አገላለፅ በወንጀል ዋና አድራጊነትና ግብረአበርነት የተከሰሱ ሰዎች መካከል አንዱ ወይም ሁለቱ በምስክርነት ሲጠሩ እንደመከራከሪያ የሚነሳና ተፈፃሚነት ያለው ነው የሚለው በትክክል ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?
- ከላይ የተገለፁት ሁኔታዎች ህገ መንግስቱን በመጥቀስ የምስክርነት ቃላችንን እንድንሰጥ መገደድ የለብንም የሚሉትን መከራከሪያዎች የሚያሳይ ሲሆኑ

ይህንን ወንጀል በመፈፀም የዋና ወንጀል አድራጊነት በግብረአበርነት በሌላ የወንጀል ተካፋይነት ከተጣራባቸው ሰዎች መካከል ዐቃቤ ህግ የተወሰኑትን ከወንጀል ክስ ነፃ በማድረግ በምስክርነት ያቀርባል፡፡ የተከሰሱት ሰዎች በበኩላቸው በመጀመሪያ ዓቃቤ ህግ በጋራ ወንጀል ከፈፀምነው መካከል ግማሾችን ከስሶ ተመሳሳይ ማስረጃ የተገኘባቸውን በሌሎቹ ላይ የወንጀል ክስ አለማቅረቡ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 25 እና የወንጀል ህጉን አንቀፅ 4 የሚጥስ ነው ስለዚህ ሊመሰክሩብን አይገባም የሚል፣ መቃወሚያ ያቀርባሉ፡፡

- ከዚህ በተጨማሪ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ 3 ሁለተኛው ፓራግራፍ የተደነገገው መብት ወንጀል የፈፀሙ ሰዎች አንደኛው በሌላው ላይ እንዳይመሰክር የማይፈቅድ ተደርጎ መተርጎም አለበት የሚል ክርክር የሚያቀርቡ አሉ፡፡ እርስዎ ጉዳዩን የሚያዩት ዳኛ ቢሆኑ

1. በጉዳዩ ምን አይነት ብይን ይሰጣሉ?
2. ወንጀሉ የሙስና ወንጀል ወይም ሌላ አይነት ወንጀል ቢሆን በሚሰጡት ብይን ልዩነት ይኖረዋል?

3.ከሙስና ወንጀሎች ውጪ በሆኑ ወንጀሎች ዓቃቤ ህግ በጋራ ወንጀል ከፈፀሙ ሰዎች መካከል የተወሰኑትን ከወንጀል ክስ ነፃ የሚያደርግበትና በምስክርነት የሚያቀርብበት ህጋዊ ሥልጣንና ኃላፊነት አለው ብለው ያስባሉ? ለምን

4.የተከሳሹ በራሱ ላይ ምስክር ሆኖ ከመጠየቅ የመጠበቅ መብቱን ለመተውና የምስክርነት ቃል ለመስጠት ቢጠይቅ ምን አይነት ብይን ይሰጣሉ፡፡

### 1.5.4 በተጠረጠረበት ጉዳይ ወይም የሚከሰስ ወይም የማይከሰስ ለመሆኑ በአጭር ጊዜ ውሳኔ የማግኘት መብት፣

ወንጀል ፈፅሟል በሚል ጥርጣሬ የተያዘ ሰው በህገ መንግስቱ አንቀፅ 19 ከተደነገጉት ድንጋጌዎች እና በወንጀል ሥነ ስርዓት ሕጉ መሰረት የወንጀል ምርመራ ከተከናወነና ከተጠናቀቀ በኋላ ፈፅሞታል ተብሎ በተጠራጠረበት ወንጀል የተደረገው ምርመራ ታይቶና ተመርምሮ አፋጣኝ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡ አንድ ሰው ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ ተጠርጥሮ ምርመራ ከተከናወነና ማስረጃ ከተሰበሰበ በኋላ መወሰን የሚገባው ቁልፍ ጉዳይ ሰውየው በወንጀል መከሰስና ወደ መደበኛው የክስና የሙግት ሂደት መግባት አለበት ወይስ ተጠርጣሪው በወንጀል መከሰስ የለበትም የሚለው ነው፡፡

በወንጀል የፍትህ ስርዓት የዕለት ከዕለት ተግባራዊ እንቅስቃሴ አንድ ሰው በወንጀል መከሰስ አለበት ወይም በወንጀል ሊከሰስ አይገባውም የሚለው ውሳኔ እጅግ በጣም ወሳኝና ከባድ ነው፡፡ ይኸም በመሆኑ የተለያዩ አገሮች በተለይ በከባድ ወንጀሎች ምርመራ የተገኘውን የዓቃቤ ህግ ማስረጃ በመመዘን ዐቃቤ ህግ ክሱን ለመቀጠል የሚችል መሆን አለመሆኑን ተከሳሹ ለፍርድ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ የህግ ሥርዓታቸው መሠረት በግራንድ ጁሪ(በሸንጎ) በአሜሪካ ወይም በመርማሪ ዳኛ(ፈረንሳይ) የሚወሰንበት ሁኔታ አለ፡፡

በእኛ አገር የህግ ሥርዓት የፖሊስን የምርመራ መዝገብ በመመርመርና የተሰበሰበውን ማስረጃ በመመዘን

- ተከሳሹ በወንጀል የማይከሰስ ስለመሆኑ፣
- ተከሳሹ በወንጀል መከሰስ ያለበት መሆኑ፣
- ወይም ጉዳዮ ተመልሶ ተጨማሪ ምርመራ መደረግና ማስረጃ መሰብሰብ ያለበት መሆኑን የመወሰን ሥልጣን ያለው በፌዴራልም ሆነ በክልል የዓቃቤ ህግ ነው፡

ህገ መንግስቱ በአንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ 1 የተከሰሱ ሰዎች ጉዳያቸው በአፋጣኝ መታየት ያለበት መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ምርመራ ተጣርቶ የደረሰው ዓቃቤ ህግ የምርመራ መዝገቡን በፍጥነት በማየት ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ የሚያስገድድ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ በአንቀፅ 19 ሆነ በአንቀፅ 20 አልተደነገገም፡፡ ስለዚህ ዐቃቤ ህግ የምርመራ መዝገቡን አይቶ የተፋጠነ ውሳኔ የመስጠት ግዴታ ህግ አውጭው በሚያወጣው ህግ እንጂ ከህገ መንግስቱ የሚመነጭ አይደለም፡፡ ህግ አውጭው ከፈለገ የአስራ አምስት ቀን የክስ ማቅረቢያ ጊዜ እንደፈለገው ማስረዘም ወይም ማሳጣር ይቻላል በማለት የሚከራከሩ ሰዎች አሉ፡፡

ሆኖም በዚህ ጉዳይ የዐቃቤ ህግ ግዴታ ተጠርጣሪው የተጠረጠረበት ወንጀል የሚያስከሰስበት ወይም የማይከሰስ መሆኑን ለማወቅና የህገ መንግስቱ አንቀፅ 37 ከተደነገገው ፍትህ የማግኘት መብት ጋር በተገናዘበ መታየት አለበት፡፡ አንድ ተጠርጣሪ በወንጀል መከሰስ ወይም አለመከሰስ የሚለውን ነጥብ አይቶ ውሳኔ የመስጠት የዐቃቤ ህግ ሥልጣን በመሆኑ ዐቃቤ ህግ የተጠርጣሪውን ፍትህ የማግኘት መብት ማክበርና አፋጣኝ ውሳኔ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ ከዚህ አንፃር ህግ አውጪው የዐቃቤ ህግ

የተፋጠነ ውሳኔ የመስጠትና በተከሳሹ ላይ የወንጀል ክስ የማቅረብና ወይም የወንጀል ክስ ሊቀርብ አይቻልም ብሎ የሚወስንበትን የጊዜ ገደብ በፈለገው መንገድ በህግ ማራዘም ይቻላል የሚለው መከራከሪያ ህገ መንግስቱ ከሰብዓዊ መብቶች ከሰጠው ጥበቃ አንፃር መታየት አለበት፡፡

በሌላ በኩል ዓቃቤ ህግ ክስ ለማቅረብ ወይም ላለማቅረብ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባትና የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚያከብርና በሚያስከብር መንገድ የመወሰን ግዴታና እና ኃላፊነት አለበት፡፡ ይኸም ማለት፣

- ተጠርጣሪው የተጠረጠረበት ጉዳይ በአገሪቱ የወንጀል የህግ ማዕቀፍ በወንጀልነት የተፈረጀና የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ድርጊት መሆን አለመሆኑን በማጣራት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 22 የተደነገገው የህጋዊነት መርህ ማክበርና ማስከበር የህጋዊነትን መስፈርት መሟላቱን ማረጋገጥ፣
- በወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር ህገ መንግስታዊ መብት አለው፡፡ ይኸ መብት ቀሪ ሊሆን የሚቻለው ጥፋት የሆነ የወንጀል ድርጊት መፈፀሙን በማስረጃ የሚደነግግ ነው፡፡ ስለዚህ ዓቃቤ ህግ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ህግ በሚደነግጉት መሠረት ተጠርጣሪው ወንጀል ለመፈፀሙ የማስረዳት ሸክሙን ለመወጣት የሚያስችል ማስረጃ መኖሩን ካላረጋገጠ በስተቀር የወንጀል ክስ ማቅረብ የለበትም፡፡

ከዚህ አንፃር ዐቃቤ ህግ ማስረጃ ሳይኖር ክስ ከማቅረብና የተከሳሹ የነፃነት መብት እንደገደብ ማድረግ የሌለበት መሆኑን የማስረጃ መስፈርት መሟላቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ይኸም ማለት ዐቃቤ ህግ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ስርዓት ሕግ ጉጥር 42(1) ሀ ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ 3 ድንጋጌ አንፃር በማገናዘብ ውሳኔ መስጠት ግዴታ አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዐቃቤ ህግ በይርጋ የጊዜ ገደብ ያለፈባቸውን ጉዳዮች በመዝጋትና ሌሎች የሥነ ስርዓት ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነቱን መጠቀምና የህገ መንግስቱን አንቀፅ 17 የማክበርና የማስከበር ግዴታውን መወጣት አለበት፡፡ ይኸ ግልፅ ቢሆንም በዐቃቤ ህግ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚነሱ አከራካሪ ሁኔታዎች በአንድ ክልል በተፈጠረው እውነተኛ ታሪክ ላይ ተመስረቶ ማየትና ማቅረብ ይቻላል ፡-

- 1990 አቶ ከበደ ሴት ልጃቸውን ለመዳር በጋን ጠላ ለማስጠመቅ ከቤታቸው ግቢ ዳስ በማሰራት ላይ እያሉ ወንድወሰን ደመላሽና ድፋባቸው የተባሉ ወንድማማ ቾች አቶ ከበደን ለመግደል የሩምታ ተኩስ ተኮሱባቸው፡፡ አቶ ከበደ ድፍድፍ የያዘ ጋን ተገን በማድረግ ያፀፋ ተኩስ መታኮስ ጀመሩ፡፡ የተኩስ ልውውጥ በሚደረግበት ጊዜ አቶ ከበደ ድፋባቸውን ደረቱን በአንድ ጥይት መቱት ወንድወሰንም የግራ እግሩን በአንድ ጥይት አቆሰሉት፡፡ ደመላሽ እግሩ የቆሰለውን ወንድወሰንን ተሸክሞ ሸሽቶ መኪና መንገድ ከደረሰ በኂላ በመኪና ወንድሙን ሀኪም ቤት ካስገባ በኂላ ፖሊስ ጣቢያ ሄዶ አቶ ከበደ ድፋባቸው የተባለውን ወንድሙን መግደሉንና ወንድወሰን የተባለውን ለመግደል አስቦ በተኮሰው ጥይት ታፋውን በፅኑ ያቆሰለው መሆኑን ገልጾ አመለከተ፡፡ ፖሊስ አቶ ከበደን በቁጥጥር ሥር በማዋል ምርመራ ሲያጣራ በአቶ ከበደና በእነ ወንደወሰን መካከል ለረዥም ጊዜ የቆየ ደም መመላለስ ጥላቻ የነበረ መሆኑና በዕለቱ አቶ ከበደ ልጁን ከመዳሩ በፊት ለመግደል ከአስር ኪሎ ሜትር በላይ ተጉዘው መጥተው በአቶ ከበደ ላይ የእሩምታ ተኩስ እነ ወንድወሰን የከፈቱ መሆናቸውን አቶ ከበደ በአፀፋው መተኮሱንና ለአምስት ደቂቃ ያህል የተኮስ ልውውጥ በኂላ ድፋባቸው ተመትቶ መውደቁንና ወንድወሰንም እግሩ ላይ መመታቱን ደመላሽ የወንድወሰንን እግር በሽርጥ ካሰረ በኂላ ይዞት መሄዱን በወቅቱ በቦታው የነበሩ አስር ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል በማያያዝ የምርመራ መዝገቡን ለዐቃቤ ህግ አቀረበ፡፡

የምርመራ መዝገብ የደረሰው የዞኑ ዐቃቤ ህግ አቶ ከበደ የፈፀመው ራሱን የመከላከል ተግባር እንደሆነና አቶ ከበደን ከስሶ ጥፋተኛ ለማስባል የሚችል ማስረጃ የለም በማለት አቶ ከበደን በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ ቁጥር 42(1)ሀ መሠረት ከእስር እንደለቀቁ ወሰነ፡፡ አቶ ደምመላሽ የዞኑ ዐቃቤ ህግ አላአግባብ መዝገቡን ዘግቶ ተከሳሹን ለቀቀ የሚል አቤቱታ አቀረቡ፡፡ የክልሉ ፍትህ ቢሮ የዓቃቤ ህግ መመሪያ ዐቃቤ ህግ ተከሳሹ የፈፀመው ራሱን የመከላከል ተግባር ነው በማለት በወ.መ.ሥ.ወ.ሕ ቁጥር 42(1)ሀ መሠረት ክስ አላቀርብም የማለት ሥልጣን የለውም፡፡ ይኸ ስልጣን የፍርድ ቤት ነው ስለዚህ አቶ "ከበደ" 1949 በወጣው 524 (ለ) እንዲከሰሱ መሪ ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ በዚህ ጉዳይ መነሻ በክልሉ ውስጥ ለሚገኙ ፍትህ ጽ/ቤቶች ተከሳሽ ድርጊቱን የፈፀመው በህግ ይቅርታ የሚሰጡ ህጋዊ መከላከል በአስገዳጅ ሁኔታና መገደድና የመሳሰሉት ምክንያት መሆኑን በፖሊስ የተሰበሰበው ማስረጃ የሚያስረዳ ቢሆንም ዓቃቤ ህግ መዝገቡን በመ.መ.ሥ.ሥ

ሕግ ቁጥር 42(1)ሀ መዝጋትና ውሳኔ መስጠት የማይችልና ይህንን የማድረግ ሥልጣን የሌለው በመሆኑ እንደዚህ አይነት ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ክስ እንዲቀርብ የሚል መመሪያ ተላለፈ፡፡

1. በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 42(1)ሀ ዓቃቤ ህግ ተከሳሹን ጥፋተኛ ሊያስብል የሚችል ማስረጃ የሌለ ነው ብሎ ሲያምን " The public prosecutor is of opinion that there is not sufficient evidence to justify aconviction" የሚለውን ድንጋጌ ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀፅ3 እና ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 14 እና ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 17 ጋር በማገናዘብ ሲተረጎም የዞኑ ዓቃቤ ህግ አቶ ከበደ ክስ ላለማቅረብ የሰጠው ውሳኔ ስህተት ነበር ብለው ያስባሉ?
2. በምርመራ የተሰበሰበው ማስረጃ ተጠርጣሪው ድርጊቱን የፈፀመውን በወንጀል ህግ በአንቀፅ 68፣በአንቀፅ 69፣በአንቀፅ 71፣በአንቀፅ 75 ወይም በአንቀፅ 74 መሠረት መሆኑን የሚያስረዳ ሆኖ እያለ ዓቃቤ ህግ ፍርድ ቤቱ መርምሮ በነፃ ይልቀቀው በሚል ምክንያት ብቻ የወንጀል ክስ ማቅረብ አለበት ብለው ያስባሉ? ለምን ?
3. የዓቃቤ ህግ ህገ መንግስቱን የማክበርና የማስከበር ሥልጣንና ኃላፊነቱን እንዴት መወጣት ይገባዋል ብለው ያስባሉ? ለምን ?
4. ዓቃቤ ህግ የምርመራ መዝገቡን በፍጥነት መርምሮ ውሳኔ የመስጠት ህገ መንግስታዊ ግዴታና ኃላፊነት አለበት ብለው ያምናሉ?

### 1.5.5 በመደበኛ ፍርድ ቤት በአጭር ጊዜ ፍትህ የማግኘት መብት፣

አንድ ተከሳሽ ሲከሰስ በመደበኛ ፍ/ቤት በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ በግልፅ ችሎት ጉዳዩ የመስማት መብት አለው። የህገ መንግሥቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 1 የተከሳሽ በመደበኛ ፍርድ ቤት በግልፅ ችሎት ጉዳይ የመታየት መብት ያለው መሆኑን ይደነግጋል።ይኸውም፡-በህገ መንግሥቱ አንቀፅ 78 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት መደበኛ ሥርዓት የማይከተል ልዩ ፍርድ ቤት የማይቋቋም መሆኑን መደንገጉን ግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዓለም አቀፉ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 ተከሳሽ ነፃ ገለልተኛና ብቃት ባለው ፍርድ ሰጭ አካል የመዳኘት መብት ያለው መሆኑን ከሚደነግገው ድንጋጌ ጋር በሚጣጣም መንገድ ለመግለፅ '' በመደበኛ ፍርድ ቤት '' የሚለውን አገላለጽ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል።

የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች እንደሆነና ዳኞች ከማናቸውም አካል ወይም ግለሰብ ተፅዕኖና ጣልቃገብነት ነፃ ሆነው ኃላፊነታቸውን እንደሚወጡ የህገ መንግሥቱ አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀፅ 2 እና 3 የተደነገገ በመሆኑ ህገ መንግሥቱ በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች ነፃ ገለልተኛና የዳኝነት አገልግሎት ለመስጠት ብቃት ባለው በመደበኛ ፍርድ ቤት ጉዳያቸው የመታየት መብት ያለው መሆኑን የሚደነግግ ነው። የተከሰሱ ሰዎች በልዩ ሁኔታ ጉዳዩ በህግ መታየት ያለበት ካልሆነ በስተቀር በግልፅ ችሎት የመዳኘት የክሱን ኮፒ የማግኘት እና ዝርዝር የመረዳት ምስክር የመጠየቅና የቀረበባቸውን ማስረጃ የማየት መብት እንዳላቸው በህገ መንግሥቱ አንቀፅ 20 /2/ እና 20 /4/ ተደንግጓል። የተከሰሰ ሰው የመከላከያ ማስረጃዎቹ እንደቀርቡለትና እንዲሰሙለት የመጠየቅ መብት አለው።

የተከሰሰ ሰው በመረጠው ጠበቃ የመወከልና መንግሥት ወጭ በጠበቀ የመወከል መብት ያለው መሆኑ በህገ መንግሥቱ አንቀፅ 20/5/ ይደነግጋል። እነዚህ የህገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች በክርክርና በሙግት ሂደት ተከሳሽና ከሳሽ እኩል እውቀት እና እድል ማለትም እኩል የሆነ የሚል ሚዛን ሊኖራቸው ይገባል /equality of arms/ ሊኖር ይገባል። አንደኛው ማለት በተለይ ከሳሽ የተሻለ የክርክር ብቃት ስለ ክሱ የተሻለ እውቀት ስላለው በክርክሩ አሸናፊ መሆን የለበትም።ከሳሽና ተከሳሽ  ስለ ክሱ ስለማስረጃው ተመጣጣኝ የሆነ ዕውቀት ኖሯቸውና እኩል የሆነ የማስረጃ የማቅረብ መብት ኖሯቸው ዕውነቱን ለማስረዳት እና ለማረጋገጥ በመቻላቸው ብቻ አንደኛው ረቺ አንደኛው ተረቺ መሆን አለበት የሚለውን መርህ ተፈፃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ ናቸው። ከዚህ አንፃር ተከሳሹ ስለ ክሱ እንዲገነዘብ ክሱ ደርሶት መከራከሪያውንና መከላከያ ማስረጃውን እንዲያዘጋጅ የዐቃቤህግን ማስረጃ በመመልከትና በመጠየቅ ዕውነቱ እንዲያወጣ እንዲያደርግና የሙያ ድጋፍና ግልጋሎት እንደሁኔታው በራሱ ወጭ ወይም በመንግሥት ወጭ እንዲያገኝ ማድረግ የፍርድ ይዘቱ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች እኩል የሆነ ሚዛንና የሙግት አቅም እንዲኖራቸው ለማድረግ አስፈላጊ ነው።

የተከሰሰ ሰው በፍርድ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ የተሰጠው ፍርድ ተፈፅሚል የሚለውን የህግና የፍሬ ጉዳይ ስህተት በይግባኝ እንዲታረም የማድረግ መብት ያለው መሆኑን ህገ መንግሥቱ ይደነግጋል። ከዚህ አንፃር ይግባኝ በወንጀል ጉዳዩች ህገ መንግሥታዊ ዋስትና የተሰጠው መብት ነው።

ከላይ በተደነገጉት ህገ መንግሥታዊ መብቶች አንፃር በተግባራዊ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችና ሊሰጣቸው የሚገቡ መፍትሄዎች ዙሪያ ለመወያየት መነሻ የሚሆኑ ነጥቦች ስንመለከት፡-

- ዐቃቤ ህግ ተከሳሽ የሰው መግደል ወንጀል ፈፅሟል በማለት ክስ አቀረበ:: የዐቃቤህግ ለክሱ በማስረጃነት ሶስት የዓይን ምስክሮች ያሉት መሆኑን ስምና አድራሻቸውን ጠቅሶ አቅርቦ ነበር፡፡ ሆኖም የዐቃቤህግ ምስክሮቹ በአድራሻቸው ሊገኙ ስላልቻሉ ለፖሊስ የሰጡት ምስክርነት ቃል በማስረጃነት ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ ውሣኔ ይስጥልኝ በማለት አመለከተ፡፡ ተከሳሹ በበኩሉ በህገ መንግሥቱ አንቀፅ 20/4/ መሠረት ምስክሮቹን ያልጠየቅናቸው በመሆኑ በማስረጃነት ምስክሮች ለፖሊስ የሰጡን ቃል ሊያያዝ አይገባውም የሚል ተቃውሞ አቀረበ? ምን ዓይነት ውሣኔ ይሰጣሉ?
- ለቀዳሚ ምርመራ ፍርድ ቤት የተሰጠ የምስክሮች ቃል በሚቀርብበት ጊዜ ተከሳሽ ህገመንግሥቱ አንቀጽ 20/4/ በመጥቀስ ተከሳሾች የሚያቀርቡትን ተቃውሞ እንዴት ያዩታል?
- በወረዳ ፍ/ቤት እና በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የመንግሥት ተከላካይ ጠበቃ አለመኖሩ የህገ መንግሥቱን አንቀጽ 20 /5/ አንፃር እንዴት ያዩታል?
- በከፍተኛ ፍ/ቤት ከባድ ውንብድና ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የተከሰሰ ተከሳሽ ተከላካይ ጠበቃ ሣይቆመለት ብቻውን  ጥፋተኛ ተብሎ በሞት ፍርድ እንዲቀጣ ተወሰነ፡፡ እርስዎ ይህንን ውሣኔ በይግባኝ አይተው እንዲያርሙ የተሰየሙ ዳኛ ቢሆኑ ከህገመንግሥቱ ድንጋጌዎች አንፃር ምን ዓይነት ውሣኔ የሰጣሉ? ለምን?

### 1.5.6የሴቶችና የህፃናት መብት እና የወንጀል ህግ

በሴቶች ላይ የሚደርሱ አካላዊና ሥነ ልቦናዊ ጥቃቶች ወንጀል በማድረግና የወንጀል ቅጣት በመደንገግ የሴቶችን ህገ መንግሥታዊ መብት ከማስከበር አንፃር የወንጀል ህጉ የማይተካ ድርሻ አለው። የወንጀል ህጉ የሴቶችን የሥነ ተዋልዶ መብት ከማስከበር አንፃር አስገድዶ መድፈር ጠለፋ፣ እና ሌሎች የወንጀል ተግባር በመቅጣት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል።

ህፃናትን አስመልክቶ በህገ መንግሥቱ የተረጋገጠላቸውን መብቶች የወንጀል ህጉ በህፃናት ላይ የሚደርስ አካላዊ ቅጣት የጉልበትና የወሲብ ብዝበዛ በወንጀልነት ከመፈረጅ የወንጀል ቅጣት በመደንገግ የህፃናት መብት ለማስከበር የወንጀል ሕጉ ጠቀሜታ አለው። ከዚህ በተጨማሪ እድሜያቸው ህፃን በሚለው ዓለም ዓቀፉ ትርጉም ውስጥ የሚካተቱ ወጣት አጥፊዎች እና በሽግግር እድሜ ክልል ያሉ ሰዎች ወንጀል ፈጽመዋል ተብለው ሲከሰሱ የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ ሊመራባቸው የሚገቡ ልዩ የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች በመደንገግና የሚወሰኑ የቅጣት ዓይነቶችን በማስቀመጥ ለህፃናቶች ልዩ ጥብቅና ይሰጣሉ።

በሌላ በኩል በሴቶች ህፃናት ላይ ሊፈፀሙ ጐጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን በወንጀልነት በመፈረጅና የወንጀል ቅጣት በመደንገግና ህጉን ተፈፃሚ በማድረግ የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ የሴቶች እና ህፃናት ህገ መንግሥቱ የሚሰጠውን መብትና ጥበቃ የማክበርና የማስከበር የወንጀል ሕጉና የፍትህ ሥርዓቱ ጥረት ማድረግ ይገባዋል። ከዚህ አንፃር በቀላሉ የወንጀል ሰለባ የመሆን እድላቸው እና ለአደጋ ተጋላጭነታቸው ከፍተኛ የሆኑትን ህፃናትና ሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች በልዩ ሁኔታ በማጥናት ወንጀሎቹን ለመከላከል አጥፊዎቹንም ለፍርድ ለማቅረብ የሚያስችል ስልት በመቀየስ ውጤታማ እንቅስቃሴ ካልተደረገ በሴቶችና በህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ለፖሊስ ሪፖርት ሳይደረጉ የሚቀሩበት ሁኔታ ያለ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

### 1.6 የወንጀል ህግ የማውጣት እና የዳኝነት ሥልጣን ማከፋፈል

ህገ መንግሥቱ ከወንጀል ሕግ ጋር የሚያያይዘው ሌላው ጉዳይ የወንጀል ህግ የማወጣት ስልጣንና የተፈፀሙ ወንጀሎች አይቶ የመወሰን ስልጣን ለፌዴራልና ለክልል መንግሥታት የሚያከፋፍል መሆኑ ነው። በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት መሠረታዊ የሆነውን የወንጀል ሕግ የማውጣት ስልጣንና ኃላፊነት የፌዴራል መንግሥት ሲሆን ክልሎች ፌደራል ባወጣው የወንጀል ህግ የማይታቀፉ ጉዳዩች የወንጀል ህግ የመደንገግ ሥልጣን አላቸው።

ከዚህ አንፃር ክልሎች የክልል የመንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የክልሉን የገቢ ግብር አዋጅ በመተላለፍ በሚፈፀሙ ወንጀሎችና ሌሎች የክልሉ ምክር ቤት የሚያወጣቸውን ህጐች በመተላለፍ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የመደንገግና ቅጣት የመጣል ሥልጣን ኃላፊነት ያላቸው ለመሆኑ ህጋዊ መሠረቱ ህገ

መንግሥቱ ሆኖ እናገኘዋለን። በሌላ በኩል ህገ መንግሥቱ የዳኝነት ስልጣን በክልል እና በፌደራል ደረጃ የሚያዝ መሆኑን ይደነግጋል። ሆኖም በፍትሐብሄርም ሆነ በወንጀል ጉዳይ የትኛው ነው የፌደራል የዳኝነት ስልጣን የትኛው ነው የክልል የዳኝነት ሥልጣን በሚለው ነጥብ ዙሪያ ህገ መንግሥቱ ግልፅ መልስ አይሰጥም። ሆኖም አዋጅ ቁጥር 25/88 እና በተከታታይ የተደረጉት ማሻሻያዎች የፌደራል የወንጀል የዳኝነት ስልጣን እና የክልል የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ገልፀዋል።ከዚህም አንፃር ህገ መንግሥቱ የወንጀል ህግ የመደንገግ ሥልጣንና የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ለፌዴራልና ለክልል መንግሥት በማከፋፈል መሠረታዊ ህግ በመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል።

## *ማጠቃለያ*

ህገ መንግሥቱ የወንጀል ህግ ማዕቀፎችን ቅርፅና ይዘት በመወሰንና የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ አሠራርና አደረጃጀት በመወሰን በኩል ያለው ድርሻ ከላይ በተገለፀው መንገድ ብቻ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም። የወንጀል ህጉ በህገ መንግሥቱ እውቅና እና ጥበቃ የተሰጣቸውን እያንዳንዱን መብት ከማስከበር አንፃር ያለውን ሚና ለመዘርዘር ብንሞክር ይዘቱ እጅግ ሰፊ እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል። ስለዚህ በዚህ ጽሁፍ የተገለፁት ጉዳዩች ጠቅለል ባለ ሁኔታ በህገ መንግሥቱና በወንጀል ሕግና የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ ያለውን ትስስር ለማሣየትና ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ነጥቦችን ብቻ ለማቅረብ የተዘጋጀ በመሆኑ በዕለት ከዕለት የሥራ እንቅስቃሴያችን የወንጀል ህጉ ድንጎጌዎች እና የወንጀል የሥነ ሥርዓት ህግ ተግባራዊ ስናደርግ የህገ መንግሥቱን ራዕይ ዕውን ማድረግና የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ከማክበርና ከማስከበር አንፃር የተጣለብንን ተልዕኮ መወጣት ይኖርብናል።

ይህንን ለማድረግ የህገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ሲፀድቁ ሊያሳኩት የሚፈለገውን ግብና ዓላማ አስመልክቶ የህገ መንግሥት ጉባዔ አባላት ያደረጉትን ውይይትና የሰጡትን ውሣኔ እንደዚሁም ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ህግጋት ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት የቃል ኪዳን ስምምነቶች መርሆችና ሰነዶች ይዘት በዝርዝር ለማወቅ የማያቋርጥ ጥረት ማድረግ ይገባናል።

# ምዕራፍ ሁለት

# ከውል ውጭ በሚደርስ ኃላፊነት ህግ የህገመንግስቱ መሰረታዊ መርሆዎች

## 2.1. ስለ ህገ መንግስትና ከውል ውጭ የኃላፊነት ህግ በጠቅላላው

ህገ መንግስቱ የኗሪዎችንና የዜጎችን የሲቪል የፖለቲካ የኢኮኖሚ የማህበራዊ እና የባህል መብቶችና የብሔር ብሔረሰብና ህዝቦችን መብቶች በምዕራፍ ሦስት ይደነግጋል፡፡ ህገ መንግስቱ ዕውቅና እና ጥበቃ የተሰጣቸው የግለሰብና የቡድን ወይም የወል መብቶች ዜጎች ከመንግስት ጋር ባላቸው የቀጥታ ግንኙነት (ቨርቲካል ሪሌሽንሽፕ) እና በዜጎች መካከል በሚኖር የዕርስ በርስ ግንኙነት (የጎንዮሽ ወይም ሆሪዞንታል ሪሌሽንሺፕ) በግለሰቦች በህግ ወለድ ሰዎች ወይም በመንግስት ባለሥልጣናት በመንግስት ሠራተኞችና የእነዚህ ንብረት በሆኑ ቁሣዊ ሀብቶች ጉዳት የሚደርስበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡

መንግስት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 1 የተጣለበትን ሰብዓዊ መብቶችን የማክበርና የማስከበር ግዴታና ኃላፊነት ከሚወጣባቸው መንገዶች አንደኛው የተለያዩ የመብት ጥሰቶችን በወንጀልነት መፈረጅና መብቶቹን በቸልተኝነት ወይም ሆነ ብሎ በመጣሳቸው ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ ሰዎች በወንጀል ተጠያቂ እንዲሆኑና እንዲቀጡ ማድረግ ነው፡፡ የወንጀል ተጠያቂነት የአጠቃላዩን ማህበረሰብ ሠላምና ደህንነት ማስከበር ዋና ዓላማው ያደረገ ሲሆን አጥፊው በወንጀል በመቀጣቱ ለተጎጂው የሚደርሰው የገንዘብ ድጎማ የለም፡፡ ከወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ በአጥፊው ላይ ከሚወስደው እርምጃ በተጨማሪ መንግስት ሰብዓዊ መብቶችን የማክበርና የማስከበር ህገ መንግስታዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚችለው በአንድ ሰው ላይ ለደረሰው በኃላፊነት ተጠያቂ የሚሆኑ የተፈጥሮ ወይም የህግ ሰዎች በፍትሐብሄር ተጠያቂ የሚሆኑበትና የጉዳቱ ሰለባ የሆኑ ሰዎች ካሣ የሚከፍሉበት አሠራርና ሥርዓት በመዘርጋት ነው፡፡

በአንድ የተፈጥሮ ወይም ህግ ወለድ ሰው ህጋዊ ጥበቃና ዋስትና የተሰጠው መብት ላይ ጉዳት ያደረሰ ወገን በፍትሐብሄር ተጠያቂ ከሚሆንበት የህግ ማዕቀፎች አንደኛው ከውል ውጭ ኃላፊነት የሚያስከትሉ ሁኔታዎችንና ለደረሰው ጉዳት የካሣ አከፋፈል ሥርዓት በዝርዝር የሚደነግገው ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት ህግ ነው፡፡ በወንጀል ጉዳይ ከፍርድ በፊት ጥፋተኛ ነው በተብሎ ያለመገመት መብት እንዳለ ሁሉ

በፍትሐብሄር ጉዳይም ማንኛውም ሰው ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ አይደለም ተብሎ የመገመት (presumption of non-liability) ሊኖር የሚገባው መሆኑ እየተሠራበት ያለና ተቀባይነት ያለው መርህ ነው፡፡ የአገራችን ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት ህግ ይህንን መርህ የሚከተል ስለመሆኑ ከፍታብሔር ህጉ አንቀፅ 2141 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም፡-

1. አንድ ሰው ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት በፈፀመ ጥፋት በሌላው ሰው መብትና ጥቅም ጉዳት ማድረሱ በማስረጃ የተረጋገጠበት በሆነ ጊዜ፣
2. በአንድ ሰው የሚያከናውነው አደገኝነት ባለው ተግባር ወይም አንድ ሰው አደገኛ የሆኑ ንብረቶች ባለቤት መሆኑ ሲረጋገጥና አደገኝነት ያላቸው ንብረቶች በሌላው ሰው መብትና ጥቅም ጉዳት ማድረሣቸው በማስረጃ ሲረጋገጥ፣
3. በአንድ ሰው መብትና ጥቅም ላይ ጉዳት ያደረሰን ሰው የመቆጣጠርና የማስተዳደር ኃላፊነት ያለበት ሌላው ሰው ሲሆን በህግ በኃላፊነት የሚያስጠይቅ ሁኔታ መኖሩ ሲረጋገጥ ከውል ውጭ ለደረሰው ጉዳትና የመካስ ኃላፊነት የሚኖርባቸው መሆኑ በእኛ አገር የህግ ሥርዓት ብቻ ሣይሆን በሌሎች አገሮች የህግ ማዕቀፎች ተደንግጎ እናገኘዋለን፡፡

ስለሆነም የጉዳቱ ሰለባ የሆነው ሰው ከላይ ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ሦስት በተዘረዘሩት ምክንያቶች የደረሰበትን ጉዳት የመካስና የመተካት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በማቅረብ ካስረዳ፣ ለጉዳቱ ኃላፊ የሆነው አካል ያደረሰውን ጉዳት የመተካትና የመካስ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

በአጭሩ ከውል ውጭ ለሚደርስ ኃላፊነት ለጉዳቱ ኃላፊና ተጠያቂ የሆኑ ሰዎች ለተጎጅው ተገቢውን ካሣ እንዲከፍሉ የሚያደርግ የህግ ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ መንግስት በህገ መንግስቱ የተጣለበትን ሰብዓዊ መብቶችን የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት የሚወጣበት አንደኛው መንገድ ነው፡፡ ይኸ ሥርዓት መንግስት አካላት ወይም ባለሥልጣናትና ሠራተኞች ግልፅ የሆነ ህግ በመጣስ በሌላው መብት ላይ ጉዳት ሲያደርሱ ወይም መንግስት በኃላፊነት በሚያከናውናቸው አደገኝነት ያላቸው ኢካኖሚያዊ ተግባራት እና የመንግስት ንብረት የሆኑ የአደገኝነት ባህሪ ያላቸው ንብረቶች በሌላው ሰው መብትና ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሰው በተገኙ ጊዜ ለጉዳቱ በኃላፊነት የሚጠየቅበትንና ለተጎጅው ካሣ የሚከፍልበትን ሥርዓት በመዘርጋት

ተግባራዊ የሚሆንበት የህግ ክፍል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት የሚዘረዝር የህግ ማዕቀፍ በህገ መንግስቱና አገሪቱ ባፀደቃቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዓዊ መብት ስምምነቶች እውቀና እና ጥበቃ የሰጣቸው መብቶች ለማስከበር የሚችልና ለጉዳቱ ኃላፊነት ያለበት ሰው በፍታብሔር ተጠያቂ ሆኖ ጉዳቱን እንዲክስ ለማድረግ የሚያስችልና የተሟላ መሆን አለበት፡፡

ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት ህግ የሚያስፈፅሙና የሚተረጎሙ አካላት የህጉ ድንጋጌዎች ህገ መንግስቱ ይዘት የተነሣውን ሰብዓዊ መብቶችን በተሟላ ሁኔታ የማስከበር ግብ ሊያሣካ የሚችልና ለጉዳቱ ኃላፊ የሆነው ሰው ለመብት ጥስቱ ተጠያቂ በሚሆንበትና ተገቢውን ካሣ ለተጎጅው እንዲከፍል በሚያስችል ሁኔታ ህገ መንግስታዊ ግዴታና ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት ህግ መሠረታዊ ዓላማ በአንዱ ወይም በሌላ መልኩ የሰው መብት በመጣስ ጉዳት ያደረሠ አካላት በፍታብሔር ተጠያቂ እንደሆኑ በማድረግ ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ ማድረግና መብታቸው የተጣሰባቸው ሰዎች ለደረሰበት ጉዳት ተመጣጠኝ የሆነ ካሣ እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም በህገ መንግስቱና ከውል ውጭ በሚደርስ ኃላፊነት ህግ መካከል ከፍተኛ የሆነ ትስስርና ቁርኝት ያለ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## 2.2. <u>የመንግስት አሠራር ግልፅነትና ተጠያቂነትና ከውል ውጭ የሚደርስ የኃላፊነት ህግ</u>

### 2.2.1. <u>የመንግስት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ተጠያቂነት</u>

የመንግስት አሠራር ግልፅነት ተጠያቂነት መሠረታዊ የህገ መንግስቱ መርህ መሆኑ በአንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 1ና ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡ መንግስት በተለያዩ አካላት በየደረጃው ለህብረተሰቡ  የሚሰጠው አገልግሎት አገልግሎቱን በሚሰጥበት ጊዜ የሚከተላቸው የአሠራር ሥርዓቶችና አገልግሎቱን የሚሰጥበት ሁኔታ ለህዝብ በህግና በሌሎች መንገዶች ግልፅ የማድረግ ሀላፊነቱንም በግልፅ ማከናወን እንዳለበት ህገ መንግስቱ ደንግጓል፡፡  ከዚህ በተጨማሪ ማንኛውም የመንግስት ኃላፊ ወይም የህዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ የሚሆን መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ 2 በግልፅ ተደንግጓል፡፡

አንድ የመንግስት ኃላፊ ወይም የመንግስት ሠራተኛ የተሰጠውን ኃላፊነት በማጓደልና በሌላው ሰው መብት ላይ ጉዳት የሚያደርስ ጥፋት ሲፈፀም ተጠያቂ የሚሆንበት ሥርዓት አንደኛው ሀላፊው ወይም የመንግስት ሠራተኛው ለጥፋቱ በፍታብሔር ተጠያቂ እንዲሆን ማድረግና ለተጎጅው ካሣ የሚከፍልበት የህግ ማዕቀፍ ማሟላት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከት፣

- አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የሥራ ኃላፊ ጠቅላላውን ማህበረሰብ እንዲያገለግል ያገኘውን ስልጣን ለግል ጥቅሙ ወይም የተለየ ሰው ጥቅም የዋለው እንደሆነ፣
- የመንግስት ሠራተኛ ወይም የሥራ ኃላፊ በህግ በትክክል ተገልፆ የተመለከተውን ልዩ ድንጋጌ፣ ደንብና ሥርዓት በመጣስ በሌላው ሰው ላይ ጉዳት አድርሶ እንደሆነ ለጉዳቱ በጥፋተኝነት እንደሚጠየቅ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2033 እስከ ፍታብሔር ህግ ቁጥር 2036 ድንጋጌዎች በማየት በመገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት ህግ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2138 ለጉዳቱ በኃላፊነት ሊጠየቁ አይችሉም ከተባሉ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት፤ በፓርላማ አባላትና በዳኞች በሌሎች ህጎች ከፍታብሔር ተጠያቂነት ህጋዊ ከለላ የተሠጣቸው የመንግስት ሹማምትና ኃላፊዎች ውጭ ያሉ ሠራተኞች እና የመንግስት ኃላፊዎች ሥልጣናቸውን አላግባብ መጠቀም፤ ግልፅ የሆነውን የህግ ድንጋጌ በመጣስ ለፈፀሙት ጥፋት በኃላፊነት የሚጠየቁበትንና ጉዳቱን የሚክሱበት ሥርዓት በመደንገግ ህገ መንግስቱ የደነገገውን የተጠያቂነት መርህ ተፈፃሚ የሚሆንበት የህግ መሠረት ይጥላል፡፡

## የመወያያ ጥያቄ

1. የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2138 ንዑስ አንቀፅ (ለ) ለወረዳ ምክርቤት አካላት ለብሔረሰብ ዞን ምክር ቤት አባላት በፍታብሔር እንዳይከሰሱ ህጋዊ ከለላ ይሰጣል ብለው ያስባሉ? ለምን?
2. የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2138 ንዑስ አንቀፅ (ለ) ለክልል ምክር ቤት አባላት በፍታብሔር መከሰስ ህጋዊ ከለላ ይሰጣል ብለው ያስባሉ? ለምን?

3. የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2138 ንዑስ አንቀፅ (ሐ) ለማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች በፍታብሔር ከመከሰስ ህጋዊ ከለላ ይሰጣል ብለው ያስባሉ? ለምን?
4. የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2138 ድንጋጌዎ አሁን ካለው የፌደራል ሥርዓትና የመንግስት ሥልጣን በቀጥተኛው የአስተዳደር እርከን ወደታች ለማውረድ በተወሰደው እርምጃ አንፃር እንዴት መተርጎምና ሥራ ላይ መዋል አለበት ብለው ያምናሉ? ለምን?
5. የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2139 ልዩ ድንጋጌ መሠረታዊ ዓላማና ግብ ምንድነው?

### 2.2.2. <u>የመንግስት አካላት ተጠያቂነትና ከውል ውጭ የሚያደርስ ኃላፌነት ህግ</u>

የመንግስት አሠራር ግልፅነት ተጠያቂነት በየደረጃው ያሉ የመንግስት አካላት ሠራተኞቻቸውንና ኃላፊዎቻቸው ተግባርና ኃላፊነታቸውን በግልፅ በተደነገገው ህግ አሠራር መሠረት የሚሰጡ መሆኑን ውጤታማ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ይጠይቃል፡፡ በየደረጃው ያሉ የመንግስት አካላት ይህን ሀላፊነታቸውን በአግባብ መወጣት ይገባቸዋል፡፡ የመንግስት ሹም ወይም ሠራተኛ በራሱ ጥፋት በሌላው ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነና ጥፋቱን የፈፀመው የመንግስቱን ሥራ በሚሠራበት ወቅት በሆነ ጊዜ ተጎጂው መንግስትን የመጠየቅ መብት የሚኖረው ስለመሆኑ በፍታብሔር ሕግ አንቀፅ 2126 እስከ አንቀፅ 2128 ያሉትን ድንጋጌዎች በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይኸም የመንግስት ሹም ወይም ሰራተኛ በሥራው ምክንያት ለሚያጠፋው ጥፋት ግለሰቡ የመንግስት ሹም ወይም ሠራተኛ ብቻ ሣይሆን አሠሪው የመንግስት አካል የፍታብሔር ተጠያቂነትና የጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመደንገግ የመንግስት አሠራር ግልፅነት ተጠያቂነት ህገ መንግስታዊ መርህ ያጠናክራል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የተለያዩ ንብረቶች በባለቤትነት በመያዝ ለዕለት ከዕለት ሥራቸው ይጠቀማሉ የመንግስት አካላት ለቢሮ አገልግሎት የሚውል ህንፃ ለትራንስፖርት የሚገለገሉባቸው መኪኖች ሞተር ሣይክሎች የመሣሠሉት ንብረቶች ባለሀብት በመሆን ይጠቀማሉ፡፡ ይኸም በመሆኑ እነዚህ ንብረቶቻቸው በሌላው ሰው ላይ ጉዳት በሚያደርሱበት ጊዜ የመንግስት አካላት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 394 መሠረት እንደ አንድ ሰው የሚቆጠርና በፍታብሔር ህግ

ቁጥር 2089 በተደነገገው መሠረት የጉዳቱ ሰለባ ለሆኑ ሠዎች ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ተደንግጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ መንግስት ለልማቱ ወሳኝ ሚና እንዳላቸው በተለያዩና አደገኛነት ያላቸው ተግባራት ለምሳሌ የኤሌትሪክ ሀይል ማመንጫዎንና መስመሮችን ሌሎች ተመሣሣይ ተግባራትን ያከናውናል፡፡ ስለዚህም የመንግስት የልማት ድርጅቶች እንደማንኛውም የንግድ ድርጅቶችና ማህበር የሚያከናውኑት አደገኛ ተግባራት ምክንያት ጉዳት ካደረሱ ከላይ በተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎች መሠረት ተጠያቂ የሚሆኑና ካሣ የሚከፍሉ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይኸም መንግስት በሰዎች ላይ ጉዳት በሚያደርስ መንገድ ንብረቶቹን እንዲጠቀምና አደገኝነት ያላቸው የመሠረተ ልማት አውታሮችን እንዲዘረጋ በማስገደድ የመንግስት አሰራር ተጠያቂነትን ያጠናክራል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ በተለያየ ደረጃ የሚገኝ የመንግስት አካላት በቂ ባልሆነ ምክንያት በሌላው ሰው የሥራ ድካም በሆነ ሀብት አላግባብ የተጠቀመ ሆኖ በተገኘ ጊዜ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2162 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት ተጠያቂ የሚሆን መሆኑና በዚህ ምክንያት ባለሀብቱ ለደረሰበት ጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመደንገግ ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት ህግ በህገ መንግስቱ የመንግስት አሠራር ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሁም የህገ መንግስቱን የበላይነትና ልዕልናን በማረጋገጥ መንግስት በህግ ተገዥ ሆኖ የሚተዳደርበትን ሥርዓት ያጠናክራል፡፡

## <u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. የአንድ ክልል የእርሻ ምርምር ተቋም ድርቅ የሚቋቋም ከፍተኛ ምርት የሚሰጥ የገብስ ዝርያ ያገኘ መሆኑን ዝርያውም በገበሬዎች ማሣ ተሞክሮ ጥሩ ውጤት እንዳስገኘ በመግለፅ ዘሩ አንድ ሺ ለሚሆኑ ገበሬዎች እንዲሠራም አደረገ፡፡ ሆኖም የተሠጠውን ምርጥ ዘር የዘሩ ገበሬዎች የእርሻ ማሣ የተዘራው ገብስ ምንም አይነት ፍሬ ሣይሰጥ ቀረ፡፡ ጉዳዩ እንደገና ሲጠና የእርሻ ምርምር ግኝት ለአንድ ጊዜ ብቻ እንጅ በድጋሜ በሚዘራበት ጊዜ ፍሬ የሌለው እና ጉድለት ያለበት መሆኑ ተረጋገጠ፡፡ ምርጥ ዘሩን የዘሩት አንድ ሺ ገበሬዎች በህብረትና በተናጠል የጉዳት ካሣ ጥያቄ ለማቅረብ ክስ አቀረቡ፡፡ ለጉዳቱ በመጀመሪያ ጥፋተኛውና በኃላፊነት የሚጠየቀው ማን ነው? የእርሻ ምርምር ተቋርጦ ለጉዳቱ በኃላፊነት ተጠያቂ የሚሆንበትና ካሣ የሚከፍልበት ህጋዊ መሠረት አለ ብለው ያስባሉ? ለምን?

2. የመንግስት ሹም ወይም ሠራተኛ በሥራው ላይ ለፈፀመው ጥፋት የመንግስት አካል ካሣ ከከፈለ በኋላ መልሶ የመንግስት ሹም ወይም ሠራተኛ የሚጠይቅበት የህግ መሠረት አለን?

## 2.3. ህገ መንግስታዊ ጥበቃ የተሰጣቸው መብቶችና ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት ህግ

ህገ መንግስት ጥበቃና ዋስትና የሰጣቸው መብቶችና ነፃነቶች በርካታ መሆናቸውን ከህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ህገ መንግስቱ ዕውቅና እና ጥበቃ ከሰጣቸው መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች፡-

- በህይወት የመኖር መብት፣
- የአካል ደህንነትና ማንኛውም ጭካኔ ከሞላበት ኢሰብዓዊ ከሆነ አያያዝ፣ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት፣
- የነፃነት መብት እና የቤተሠብ መብት፣
- የክብርና የመልካም ሥም መብት፣
- የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት፣
- የንብረት ባለቤትነት መብት

በመጣስ ለሚደርሱ ጉዳዮች፣ የተፈጥሮ ወይም የህግ ሰዎች ተጠያቂ የሚሆኑበትንና ከተጠያቂነት ነፃ የሚሆኑበትን ሁኔታ በፍታብሔር ህጉ ከአንቀፅ 2038 እስከ አንቀፅ 2065 የሚደነግግ ሲሆን፣ ይኸም በጎንዮሽ ግንኙነት በፍታብሔር ተጠያቂነት የሚያስከትሉ ጥፋቶችን ጥፋት ካልሆኑት ለመለየትና በህገ መንግስቱ ዕውቅና እና ጥበቃ የተሰጣቸው መብቶች የተፈፃሚነት ወሰን ለመረዳትና የፍታብሔር ህጉን ድንጋጌዎች ለመተርጎም ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

በተግባራዊ አፈፃፀም ሂደት ከላይ የተገለፁትን መብቶች በቸልተኝነት ወይም ሆነ ብለው በመጣስ ጉዳት ያደረሱ ሰዎችን ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ መሆናቸውን በመወሰን በኩል የጎላ ችግር አይታይም፡፡ በርካታ ችግሮችና ስህተቶች የሚታዩት ለጉዳቱ ኃላፊ ነው የተባለው ሰው ለጉዳቱ ሰለባ ለሆኑ ሰዎች የሚከፍሉትን የካሣ መብት በመወሰን በኩል ነው፡፡

የፍታብሔር ህጉ ከህገ መንግስታዊ ሥርዓት ጋር በሚጣጣም መንገድ ያልተሻሻሉ መሆናቸው ለችግሩ መከሰት አንደኛው መንስኤ ሲሆን በሌላ በኩል ዳኞች እነዚህን የካሣ መጠን አወሳሰን የሚደነግጉ ድንጋጌዎች የህገ መንግስቱን የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ግብና ዓላማ ሊሣካ በሚችል መንገድ ድንጋጌዎቹን እየተረጎሙ ውሣኔ አለመስጠታቸው በትኩረት ሊታይና ልንወያይበት የሚገባው አይነተኛ ችግር ነው፡፡ ከዚህ አንፃር እስካሁን እስከ ሰበር ድረስ ቀርበው ታይተው በተወሰኑ ጉዳዮች የሚታዩ ችግሮችን ጠቅለል አድርጎ በፈርጅ በፈርጅ ማቅረቡ የችግሩን መንስኤና እና ክብደት ለመረዳት ይጠቅማል በሚል እምነት እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ፡፡

1. የመጀመሪያው ችግር የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2095 ድንጋጌ በመተርጎም ተፈፃሚ ከማድረግ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የሚታዩ ችግሮች በተለያየ መንገድ ለመግለፅ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ወላጆች የወደፊት ጧሪና ቀባሪ የሆኑ ልጆቻቸው በአደጋ ምክንያት ህይወታቸውን ሲያጡ የሚሰጠው ውሳኔና የሚከሰተው ሁኔታ ነው፡፡ ለአብነት የአርባ ዓመት አዛውንት የሆኑ ሽማግሌ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ የሆኑ የአስራ አራት ዓመት ልጃቸው በመኪና በመገጨቱ ህይወቱ ያልፋል፡፡ የልጁ አባት ልጃቸው በህይወት በነበረበት ጊዜ በአርሻ ሥራና ከብቶችን በማሠማራት ያደርገው የነበረው አስተዋፅኦ በመሞቱ ምክንያት መቋረጡን እና ልጃቸው በህይወት ቢኖር ኖሮ ወደፊት በጉልበቱና በዕውቀቱ ሠርቶ ይጦራቸው የነበረ መሆኑን በመግለፅ ለደረሰባቸው ጉዳት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2091 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2092 መሠረት ካሣ እንዲከፈላቸው አመለከቱ፡፡

ተከሳሹ ለጉዳቱ ኃላፊ መሆኑን አምኖ ነገር ግን ሟች የሆነው የአስራ አራት ዓመት ህፃን ለአባትና ለእናቱ በመጦሪያ መልክ የሚሰጠው ነገር ስለመኖሩ በማስረጃ አልተረጋገጠም፡፡ ስለዚህ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2095 መሠረት በመተዳደሪያ ረገድ የደረሰባቸው ጉዳት ያለ መሆኑን ያላስረዱ ስለሆነ ተከሳሹ ከሳሽ ልጃቸው በመሞቱ ምክንያት ያደረሰበትን የሞራል ጉዳት ካሣ ብር 1000 /አንድ ሺ ብር/ ይክፈል የሚሉ ውሣኔዎች በተመሣሣይ ጉዳዮች በተለያየ ደረጃ ባሉ ፍርድ ቤቶች ተሰጥተዋል፡፡

የዚህ አይነት ውሣኔ መንግስት በህይወት የመኖር መብት ከሰጠው ዕውቅና እና ጥበቃ ጋር የሚጣጣም ነው ብለው ያስባሉ?

➢ የሟች አባት ህፃን ልጃቸው በመሞቱ ምክንያት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2091 መሠረት ሊታሰብ የሚችል የቀረባቸው ጥቅም የለም ብለው ያስባሉ?

➢ የሟች አባት ህፃን ልጃቸው በመሞቱ ምክንያት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2092 መሠረት ሊታሰብ የሚችልና ወደፊት ልጃቸው በህይወት ቢኖር ሊያገኙት የሚችሉት ጥቅም የለም ብለው ያስባሉ? ለምን?

➢ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2095 ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2091 እና 2092 እንደዚሁም ከፍታብሐር ህግ ቁጥር 2102 ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 14 እና አንቀፅ 15 ዓላማና ግብ ሊያስከብር በሚችል መንገድ መተርጎምና ሥራ ላይ ማዋል ይቻላልን? ለምን?

2. ሌላው ጉዳይ በጋብቻ ተሣሥረው ከሚኖሩ ባልና ሚስቶች አንዳቸው በሞት አደጋ ሲለዩ ሌላኛው የትዳር ጓደኛ ካሣ እንዲከፈለው ሲጠይቅ የሚሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ በተለይ ሚስት በሞት አደጋ በምትለይበት ጊዜ ባል በመጦሪያ ወይም መተዳደሪያ ረገድ የደረሰበት ጉዳት የለም በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2095 በመጥቀስ የሞራል ካሣ ብር 1000 /አንድ ሺ ብር/ ብቻ ለጉዳቱ ኃላፊ የሆነው ሰው እንዲከፈል ይወሰናል፡፡

   ➢ ሚስት በቤት ውስጥ የምግብ እና ሌሎች ዝግጅቶችን በማድረግና ሥራዎችን በመሥራት ለባሏ የምትሰጠው ጥቅም በመሞቷ  ምክንያት አልተቋረጠም ብሎ ለመወሰን ይቻላል?

   ➢ ይህንን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2092 እና ከፍታብሐር ህግ ቁጥር 2102 እና በህይወት የመኖር መብት ከተሰጠው ጥበቃና ዋስትና አንፃር እንዴት አጣጥሞ መተርጎምና ሥራ ላይ ማዋል ይቻላል?

3. አንድ ሰው የአካል ጉዳት ሲደርስበት ሥራ የሌለው በሆነ ጊዜ አካሉ መጉደሉ ቢረጋገጥም ሥራ ያልነበረው ሥለሆነ የቀረበት እርግጠኛ ጥቅም የለም፡፡ ለወደፊትም የተቋረጠ ጥቅም ያለ ስለመሆኑ አላስረዳም ስለዚህ ከሞራል ካሣ 1000 /አንድ ሺ ብር/ ውጭ ሊከፍለው የሚገባው ካሳ ያለም በሚል መንገድ የሚሰጡ ውሳኔዎች አሉ፡፡

   ➢ ስራ ያሌለው ሰው አካሉ ላይ በደረሰበት ጉዳት የቀረበት ጥቅምና ያደረሰበት ጉዳት የለም? የሚለው መደምደሚያ ህገ መንግስታዊ ዋስትና እና ጥበቃ ከተሰጠው ከአካል ደህንነት መብት ጋር የሚጣጣም ነው ብለው ያስባሉ? ለምን?

➢ አካል ጉዳት የደረሰበት ሰው የቀረበትን ጥቅምና አካሉ በመጉደሉ ምክንያት በእለት ከእለት ኑሮው ውስጥ የሚደርስበትን ኪሳራ በርትእ መወሰን ይቻላል ብለው ያስባሉ? ለምን?

4. መተዳደሪያ ስራ የለው ሰው በአደጋ ምክንያት የአካል ጉዳት ሲደርስበትና 5% የቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የአካል ጉዳቱ ያስቀረበት ጥቅም እና ወደፊትም የሚያቀርበት ጥቅም የለም ተብሎ ውሳኔ ቢሰጥ ተገቢ ነው ብለው ያስባሉ?

5. አስር ፐርሰንት ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰበት ሰው መቶ ፐርሰንት የመሥራት ችሎታን የሌለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በሀኪም ቦርድ ተሰጥቶታል፡፡ የካሳው መጠን መወሰን የለበት በየትኛው ማስረጃ መሰረት መሆን አለበት ብለው ያስባሉ ለምን?

ከላይ የተገለጹት ሁኔታዎች ለአብነት የተነሱበት ዋናው ቁም ነገር ህገ መንግስታዊ ዋስትና እና ጥበቃ የተሰጣቸው መብቶች በተፈጥሮ ወይም በህግ ሰው ተጥሰው በሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት መድረሱ በተረጋገጠ ጊዜ የጉዳቱ ኃላፊ የሆነውን ሰው ነፃ የሚያወጡ አማራጮችን ነው መከተል ያለብን? ወይስ ህገ መንግስታዊ መብቱ ለማከበርና ለተጎጅው ተመጣጣኝ ካሳ ለማስከፈል የሚችል የህግ አተረጓጎም? የሚለው ህገ መንግስቱን ከማክበርና ከማስከበር ኃላፊነታችን ጋር በማያያዝ ማየትና መመርመር ያስፈልጋል፡፡

### 4.4 የሰብዓዊ መብት ጥሰትና ጥሰቱን የማስቀረትና የመንግስት ካሳ የመክፈል ኃላፊነት

ከላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት አካላት የግለሰቦችን ወይም በአንድ አካባቢ የሚኖር ማህበረሰብ መብት ጥሰት ፈጽመዋል የሚለው አቤቱታ በአህጉራዊ ድርጅት በአፍሪካ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን እና በሚመለከታቸው አካላት በማረጋገጥ ውሳኔ ቢሰጥ የመንግስት ግዴታና ኃላፊነት ሁለት መልክ ይኖረዋል፡፡ የመጀመሪያው የመብት ጥሰቱ እንዲቆም ማድረግ ሲሆን ሁለተኛው መብቱ ለተጣሰበት ሰው ወይም የህብረተሰብ ክፍል ካሳ መክፈል በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት በልምድ የዳበረ ውጤታማ የመብት የጥሰት ማረሚያ (effective remedy) መሆኑን የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የአፍሪካ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና ሌሎች አህጉራዊ ተቋማት አሰራሮች በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ መንግስት ወንጀልን በመከላከልና የወንጀል ሰለባ የሆኑ ሰው ወይም ማህበረሰብ መብት ለመጠበቅ በማይቻልበት ሁኔታ የተጎጅውን መብት ለመከላከልና ለመጠበቅ ባለመቻሉ ብቻ ለተጎጅው ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት የሚለውን ሀሳብ የሚያራምዱና የወንጀል ሰለባ ለሆኑ ሰዎች የሚከፈል የካሳ ፈንድ እና ይህንን የሚያስፈጽም ተቋም ያቋቋሙ አገሮች አሉ፡፡ ይህንን በተመለከተ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር 1985 ዓ.ም ዓለም አቀፍ መግለጫ ወጥቷል፡፡ በአንድ ብሄር ብሄረሰብና ህዝብ ወይም በአንድ ህብረተሰብ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች በወቅቱ ለመከላከል ካልተቻለ ለወንጀሉ ሰለባዎች ካሣ መክፈል አንደኛው መንገድ ነው፡፡ ይህንን ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 13 /2/ ጋር እንዴት ያዩታል?

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በዓለም አቀፉ የሲቭልና የፓለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 5 በህገ ወጥ መንገድ የነፃነት መብቱን የተገሰሰበትና በህገ ወጥ መንገድ የታሰረ ሰው ካሳ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በሌላ በኩል ከተከሰሰ በኃላ የፍትህ መጓደል /miscarrage of justice) የደረሰበት መሆኑን የተረጋገጠ ሰው ካሳ የማግኘት መብት ያለው መሆኑ በሲቪልና የፓለቲካ መብቶች የቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 5 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ከውል ውጭ የሚመጣ ኃላፊነት ግለሰቦችን ወይም አንድን የመንግስት መሥሪያ ቤት ብቻ ሣይሆን አገርን እንደአገር በግዞት ክልሏ ውስጥ ለተፈጸመ የሰብዓዊ መብት ጥሰት በዓለም አቀፍ ወይም በአህጉር ደረጃ ተጠያቂ የሚያደርግና የመብት ጥሰት የተፈጸመበት ሰው በአገር ደረጃ እንዲካስ የሚያስገድድ የህግ ማዕቀፎችና ዓለም አቀፍ አሰራሮች አሉ፡፡ ስለሆነም ይህንን ዓለም አቀፍ ተጠያቂነት የማስቀሪያ መንገዱ አንደኛው የአገር ውስጥ የሰብዓዊ መብት ጥሰቱን ለማስቆምና ጉዳቱን ለመካስ የሚያችል አሰራር በማጎልበት መብታቸው የተጣሰባቸው ሰዎች የሚካሱበት አስተማማኝ ሥርዓት መዘርጋት በመሆኑ ህገ መንግስታዊ ተልዕኳችንን ከዚህ አንጻር ማየት ከውል ውጭ የሚያደርስ ኃላፊነት ህግ ሰፋ ባለ ሁኔታ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሰረታዊ መርህና እና ሌሎች የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ግብና ዓላማ ለማሳካት በሚችል መንገድ መተርጎምና ስራ ላይ ለማዋል ሚዛናዊና ፍትሐዊ የሆነ እንቅስቃሴ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

## የመወያያ ጥያቄ

1. በአገር ደረጃ በግዛት ክልሏ ውስጥ ለተፈጸመ የሰብዓዊ መብት ጥሰት በኃላፊነት የምትጠይቅበትና ለተጎጅው ካሳ እንዲከፍል የምትገደድበት ስርዓት አለ ብለው ያስባሉ? ለምን?
2. አሁን ባለው የኢትዮጵያ የህግ ስርዓት አንድ ሰው በዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብት የቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ4 መሰረት በማድረግ መንግስት ካሳ እንዲከፍለው ለመጠየቅ ይችላል? አንድ ሰው illegal arrest /ህገ ወጥ እስር/ ተፈጽሞበታል ለማለት ምን ምን ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው? ይህንን ሁኔታ ከፍተብሔር ህግ ቁጥር 2042 ድንጋጌዎች ጋር እንዴት ይያዛል፡፡
3. አሁን ባለው የኢትዮጵያ የህግ ስርዓት አንድ ሰው ዓለም አቀፉ የሲቪልና የፓለቲካ መብቶች የቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ14 ንዑስ አንቀጽ5 መሰረት የፍትህ መጓደል ደርሶብኛል በማለት መንግስት ካሳ እንዲከፍለው ለመጠየቅ ይችላል? በአንድ የፍርድ ሂደት የፍትህ መጓደል (miscarriage of justice) ተፈጽሟል የሚባለው ምን ምን ሁኔታች መከሰታቸው ሲረጋገጥ ነው?
4. ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች በመጥቀስ መብቴ ተጥሶብኛል ጉዳት ደርሶብኛል የሚል የአገሪቱ ዜጋ ወይም ሌላ ሰው ካሳ እንዲከፈለው እርስዎ በሚያስችሉበት ፍርድ ቤት ክስ ቢያቀርብ ምን ዓይነት ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ይሰጣሉ?
5. ከውል ውጭ የሚያደርስ ኃላፊነት ህግ ከህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች እና ህገ መንግስታዊ ግቦች ጋር ለማጣጣም ምን ዓይነት ማሻሻያ ሊደረግለት ይገባል ብለው ያስባሉ?

## ማጠቃለያ

ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት ህግ አገሪቱ እንደ አገር፣ የመንግስት አካላት የመንግስት ባለስልጣኖችና የመንግስት ሰራተኞች ሰብዓዊ መብት የማክበር ግዴታና ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ለሚደርስ ጉዳት እንዲዚሁም በጎንዩሽ ግንኙነት የተፈጥሮ ወይም የህግ ሰው የሌላውን ሰው መብት በመጣስ ለሚደርሰው ጉዳት በፍ/ብሔር ተጠያቂና ኃላፊ የሚሆኑበትን ስርዓት በመደንገግ የህገ መንግስቱን ርዕይ

እውን ለማድረግና ህገ መንግስታዊ ግቦችን በማሳካት በኩል ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ ያበረክታል። ከዚህ አንጻር የህጉን ድንጋጌዎች ለሰብዓዊ መብት ከፍተኛ ጥበቃና ዋስትና የሚሰጠው የኢፌዲሪ ህገ መንግስት ጋር በማጣጣም መተርጎምና ስራ ላይ የማዋል ከባድ ተልዕኮና እና ኃላፊነት በፍትህ አካላት ላይ የወደቀ መሆኑን በመረዳት ተገቢውን እንቅስቃሴ ማድረግ ይገባናል።

# ምዕራፍ ሦስት

# በንብረት ህግ የህገመንግስቱ መሰረታዊ መርሆዎች

## 3.1. ስለንብረት ህግ እና ህገ መንግስት በጠቅላላው

ንብረት የሚለው ቃል በማናቸውም በተፈጥሮ ሰው ወይም ህግ ወለድ ሰው በግል ወይም በጋራ በባለቤትነት ሊያዝ ወይም ሊከማች የሚችል ዋጋ ወይም ጥቅም የሚሰጥ ማናቸውም ነገር ለመግለፅ የምንጠቀምበት ቃል ነው። አንድ ነገር ንብረት ነው የሚባለው ለሰው ሊጠቅም የሚችልና ዋጋ ያለው ሲሆንና በተፈጥሮ ወይም በህግ ወለድ ሰው በባለቤትነት ሊያዝ የሚችል ሆኖ ሲገኝ ነው። ማናቸውም የሰው ልጅ በተለያየ መንገድ ሊገለገልባቸውና ሊጠቀምባቸው የሚችልና በተለያየ መንገድ ለሶስተኛ ወገን ሊያስተላልፋቸው የሚችላቸው ባለቤታቸው ሊሆንባቸው የሚቻለውና በተፈጥሮ ፀጋ የተገኙ ወይም ሰው ሠራሽ የሆኑ ግዙፍነት ያላቸውና ግዙፍነት የሌላቸውን ነገሮች ንብረት በሚለው ሰፊ ፅንሰ ሀሳብ የሚጠቃለሉ ናቸው። ይኸውም ማለት ለሰው ልጅ ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጡ ነገር ግን በማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም ህግ ወለድ ሰው በባለቤትነት ሊያዙ የሚችሉ በተፈጥሮ የሚገኙ በማናቸውም ሰው ባለቤትነት የማይያዙ ፀሐይ፤ ጨረቃ እና የመሳሰሉት ለሰው ለጅ ጠቀሜታ የሚሰጡ ነገሮች ንብረት በሚለው ፅንሰ ሀሳብ የማይጠቃለሉ ናቸው።

የተለያየ ባህሪ ገፅታና ጥቅም ያላቸው ንብረቶች የባለቤትነት መብት ምንጭና መሠረት አስመልክቶ በተለያየ ጊዜ የተለያየ አሠራር እንደነበረ በአስተሳሰብ ሂራመድ እንደቆየ በዚህ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች ያሣያሉ። የግል ንብረት ባሌቤትነት ማቆጥቆጥና ማደግ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የንብረት ባለቤትነት ባለይዞታነትና ሌሎች ተዛማጅ መብቶች አስመልክቶ የተለያዩ ይዘት ያላቸው ደንቦችና የህግ ማዕቀፎችን በማውጣት

ሥራ ላይ ሲያውል እንደኖረ ጥንታዊ የሆኑትን የሀሙራቢ ህግ፣ የሶሎን ህግና ሌሎች የጥንታዊ ሰው ህጎች ዙሪያ ጥናት ያደረጉ ሙሁራን ይገልፃሉ፡፡

በመካከለኛው ዘመንና እስከ አለንበት ክፍለ ዘመን የንብረት ባለቤት የመሆን መብት በተመለከተ የተለያዩ አስተሳሰቦች ሲራመዱ ቆይተዋል፡፡ የመጀመሪያው የንብረት ባለቤት የመሆን መብት ማናቸውም ሰው ሆኖ በመፈጠሩ ብቻ የሚጎናፀፈው መብት ነው፡፡ በህይወት የመኖር መብት፣ የነፃነት መብትና የንብረት ባለቤት የመሆን መብት ምንጫቸው ሰው ሠራሽ ህግ ሣይሆን የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ክብርነት በመሆኑ የማይገሠሥና የማይገፈፍ መብት ነው፡፡ የህግ ሚና ለመብቶቹ ዕውቅና እና ጥበቃ መስጠት ነው የሚለው አስተሳሰብ የሚያራምዱና ለግል ንብረት ባለቤትነት መብት ህገ መንግስታዊ ዕውቅና እና ጥበቃ የሚሰጡ በርካታ አገሮች አሉ፡፡ በሌላ በኩል የግል ንብረት ባለቤትነት የአንዲት አገር ንብረት በጥቂት ግለሰቦች እጅ እንዲከማች በማድረግ ብዙሀኑን ህዝብ ለብዝበዛና ጭቆና ያጋልጣል፡፡ ስለዚህ ማናቸውም የምርት መሣሪያና ንብረት በወል ወይም ህብረት መያዝና በመንግስት በባለቤትነት መያዝ አለበት የሚለውን አስተሳሰብ የሚያራምድ የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም የሚከተሉ አገሮች ነበሩ፡፡

በእነዚህ ሁለት መሰረታዊ ልዩነት ያላቸው አስተሳሰቦች ከነበራቸው ተፅዕኖ ምክንያት ማናቸውም ሰው በግሉ ወይም በሌሎች ጋር በጋራ በመሆን የንብረት ባሌቤት የመሆን መብት ያለው መሆኑን ማንም ሰው በዘፈቀደ ያለ ህጋዊ ሥርዓት የንብረት ባለቤትነት መብቱ እንደማይገፈፍ በሰብዓዊ መብቶች ሁለንተናዊ መግለጫ አንቀፅ 17 የተደነገገ ቢሆንም የንብረት ባለቤት የመሆን መብት በዓለም አቀፍ የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት ወይም በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ የማህበራዊ የባህል መብቶች ስምምነት ሣይካተት ቀርቷል፡፡ በዚህ ምክንያት የንብረት ባለቤትነት መብት ከላይ የተገለፀውን ድንጋጌ በሚዘረዝር መንገድ መሠረታዊ ይዘትና መብቱ የሚገደብበትና ቀሪ የሚሆንበት ሁኔታ በሌሎች ዓለማቀፍ ስምምነቶች መስፈርት ሣይወጣለት ቀርቷል፡፡

የንብረት ህግ የሚለው ቃል በአንዲት አገር በንብረትነት የሚያዙና ህጋዊ ዕውቅና እና ጥበቃ የተሰጣቸው ንብረቶች በግል ወይም ከሌሎች ጋር በማህበር ወይም በወል የሚያዝበትን መብቱ ሙሉ በሙሉ እና በከፊል ለሌሎች ሰዎች የማተላለፍበትንና በተለያዩ መንገድ ሊሠራባቸው የሚችልበትን ሁኔታ የንብረት ባለቤት ወይም ይዞታን

ስለማስረዳትና ሌሎች ከንብረት ባሌቤትነት መብት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች በዝርዝር የሚደነግግ የህግ ክፍል ነው፡፡

ህገ መንግስት በአንድ በኩል ህገ መንግስታዊ ዋስትናና ጥበቃ ሊሰጣቸው የሚገቡ የንብረት ባሌቤትነት መብት የንብረት ባለይዞታ የመሆንና የመጠቀም መብት በመደንገግ ለንብረት ባሌቤትነት መብት ዕውቅና እና ጥበቃ ይሰጣል፡፡ ህገ መንግስት የግል ንብረት ሊሆኑ የሚችሉ ንብረቶችና የግል ንብረት ሊሆኑ የማይችሉና የመንግስትና የሕዝብ ሐብት መሆን ህገ መንግስታዊ ጥበቃ ማግኘት ያለባቸውን ንብረቶች ግልፅ ያደርጋል፡፡ እንደዚሁም መንግስት ለህዝብ ጥቅም የግለሰብ ንብረቶችን ሲያስለቅቅ ማሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎችና መስፈርቶች ይደነግጋል፡፡ በሌላ በኩል በአገሪቱ ወጥተው ሥራ ላይ መዋል ያለባቸው የንብረት መብት የህግ ማዕቀፎች መሠረት የሚሆኑ ገዥ አስተሳሰቦችንና መርሆችን በመደንገግ በንብረት ህጉ ቅርፅና ይዘት በመወሰን ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

ከዚህ አንጻር በፍታብሔር ህጉና በሌሎች አዋጆች ሥራ ላይ የዋሉ የንብረት የህግ ማዕቀፎች መሠረታዊ ባህሪና ይዘት በመወሰን በኩል በኢፌድሪ ህገ መንግስት ከፍተኛ አስተዋፆኦ ያበረከተ ሲሆን ስለ ግል ንብረት ባለቤትነት የግል ንብረት ባሌቤት ለመሆን የሚያስችሉ ህጋዊ ሁኔታዎች መሠረታዊ መርሆችን ይደነግጋል፡፡ ህገ መንግስቱ በመንግስትና የሕዝብ ንብረት እንደሆኑ በመደንገግ ህገ መንግስታዊ ጥበቃና ዋስትና ሊሰጣቸው ስለሚገቡ ንብረቶች እና የሕዝብና የመንግስት ንብረት በሆኑ ሀብቶች ላይ ግለሰቦች ሊኖራቸው የሚገባው የይዞታና የመጠቀም መብት ገዥ የሆኑ መርሆችን ይደነግጋል፡፡ ህገ መንግስቱ ከላይ የተገለፁትን ሁለት መሠረታዊ ተግባራት ማለትም ለግል ንብረት ባለቤትነት መብት ህገ መንግስታዊ ዕውቅና እና ጥበቃ በመስጠትና በአገሪቱ ሊወጡና ሥራ ላይ ሊውል የሚገባቸውን የንብረት ህግ ማዕቀፎች ቅርፅና ይዘት የሚወስኑና ገዥነት ያላቸውን ድንጋጌዎች የያዘ የአገሪቱ የበላይ ህግ ነው፡፡

## 3.2. <u>የንብረት ባለቤትነትና ህገ መንግስት</u>

የግል ንብረት ባለቤትነት አስመልክቶ የኢፌድሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 40 እና በሌሎች ድግጋጌዎች ዋስትና እና ጥበቃ ሰጥቷል፡፡ ህገ መንግሰቱ በአንቀፅ 40 ንዑስ

አንቀጽ 1 "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ወይም መሆኗ ይከበርለታል ወይም ይከበርላታል" በማለት በመጀመሪያው ፖራግራፍ ይደነገጋል፡፡

ይህ የህገ መንግስቱ ድንጋጌ የግል ንብረት ባለቤትነት ህገ መንግስታዊ ዕውቅና እና ጥበቃ የተሰጠው ለኢትዮጵያ ዜጋ ነው የሚል እድምታ ያለው የሚመስል ነው፡፡ ሆኖም ድንጋጌው ለንብረት ባለቤትነት መብት በአገሪቱ የኢንቨስትመት ህግ መሠረት የአክስዮን ማህበር በኢትዮጵያ ውስጥ በማቋቋም ወይም በኢትድጵያ እንዲመዘገብ በማድረግ የንግድ ድርጅትና ኩባንያ አቋቁመው ለሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች መብት ዕውቅና እና ጥበቃ የሚሰጥ መሆኑን የህገ መንግስቱን አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 1 የመጀመሪያው ፖራግራፍ ድንጋጌ ከህገ መንግሰቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 2 ጋር በማጣመር በማየት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚህም ምክንያት የህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 2 "የግል ንብረት" በማለት ህገ መንግስት ጥበቃና ዋስትና የሚሰጠው ኢትዮጵያዊ ዜግነት ላላቸው የተፈጥሮ ሰዎች ንብረት ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ህግ መሠረት ህጋዊ ህልውና የተሰጣቸው ኢትዮጵያዊ ማህበራት የሚጨምር መሆኑን ህገ መንግስቱ በግልፅ የሚደነግግ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም በኢትዮጵያ ህግ መሠረት የተቋቋመና የተመዘገበ የተለያየ የንግድ ማህበራት የአክሲዮን ባለቤት የሆኑ የውጭ አገር ዜጉች የንግድ ድርጅቱ ኢትዩጵያዊ ህገ ዜግነት ያለው በመሆኑ የንብረት ባለቤት የመሆን መብት የሚከበርለት መሆኑንና መብቱም ህገ መንግስታዊ ጥበቃና ዋስትና የተሰጠው መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይኸም ማለት የውጭ ዜጎች በንግድ ድርጅቱ ያላቸው የአክሲዮን ድርሻና ግዙፍነት የሌለው ሀብት ህገ መንግስቱ ዕውቅና እና ጥበቃ የሚሰጥ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

በሌላ በኩል የህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ድንጋጌ አገላለፅ የውጭ አገር ዜጎች በመንግስት ፈቃድ ያፈሩት የማይንቀሳቀስና የሚንቀሳቀስ ንብረትና በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ አገር ዜጎች በግላቸው ያፈሯቸው የሚንቀሣቀሱና የማይንቀሣቀሱ ንብረቶች ምንም አይነት የህግ ዋስትና እና ጥበቃ አይሠጣቸውም ማለት አይደለም፡፡ የውጭ አገር ዜጎች የንብረት ባለቤትነት መብት አግባብነት ባላቸው የፍታብሔር ህግ ድንጋጌዎች የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎች የንብረት ባለቤትነት መብት በፌደራሉ አዋጅ ቁጥር 270/1994 እና ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ባወጣው ደንብ ቁጥር 101/1996 እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው የህግ ማዕቀፎች ዋስትና እና ጥበቃ ተሰጥቶቷል፡፡ የውጭ አገር ዜጎችና የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎች በአገሪቱ ህግ መሠረት ያፈሩትን የግል ንብረት ባለቤትነት መብት የሚጋፋ ማናቸውም ድርጊት እንዲወገድ ወይም መብታቸው እንዲከበር ለፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ስልጣን ላለው አካል የማቅረብና ፍትህ የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 37 ተደንግጓል፡፡

ከዚህ አንፃር የህገ መንግስቱ አንቀፅ 37 ለማናቸውም ሰው ማለትም፣

- ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው የተፈጥሮ ሰዎች፣ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ላላቸው የንግድ ማህበሮች፣
- የኢትዮጵያ ተወላጅ ያልሆኑ የውጭ ዜጎችና የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎች የንብረት ባለቤትነት መብት ጥበቃና ዋስትና የሚሰጥ ሆኖ እናገኘዋልን፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የዳኝነት ሥልጣን ለፍርድ ቤቶች ብቻ መሆኑንና ፍርድ ቤቶች ከማናቸውም አካል ወይም ባለሥልጣን ጣልቃ ገብነት ነፃና ገለልተኛ ሆነው ሥራቸውን የሚያከናውኑ መሆኑና የዳኞችን ግላዊ ነፃነት የሚያረጋግጡ ድንጋጌዎች በህገ መንግስቱ አንቀፅ 79 የደነገገ መሆኑ ለግል ንብረት ባለቤትነት መብት ዋስትና እና ጥበቃ የሚሰጡና ህገ መንግስታዊ መሠረት የሚጥሉ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

ህገ መንግስቱ ግለሰቦች በተናጠል ብቻ ንብረት ባለቤት እንዲሆኑ ዕውቅና እና ጥበቃ የሚሰጥ ሰነድ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ህገ መንግሰቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 1 ንዑስ አንቀፅ 2 አገላለፅ አግባብ ባላቸው ሁኔታዎች በሕግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤት እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ማህበረሰቦች በንብረቱ ላይ ያላቸው የወል ወይም የጋራ የንብረት ባለቤትነት ህገ መንግስታዊ ዕውቅና እና ጥበቃ የሚሰጥ ነው፡፡ ህገ መንግስቱ ለባልና ለሚስት የጋራ ንብረት ባለቤትነት መብት በአንድ ላይ የንብረት ባለቤት የሆኑ ሰዎች በአንድ ንብረት ላላቸው የጋራ የባለቤትነት መብትና በአገሪቱ ግዛት ክልል የሚኖሩ ሰዎች ማህበረሰቦች በአካባቢው ልማድና ባህል መሠረት በአንድ ንብረት ላይ ያላቸው የውል የባለቤትነት መብት ህገ መንግስታዊ ዋስትና አና ጥበቃ የተሰጠው መሆኑን ለመገንዘብ ይችላል፡፡

ህገ መንግሰቱ ለግል ለጋራና ለውል የንብረት ባለቤትነት ህጋዊ ዕውቅና ጥበቃ በመስጠት የተወሰነ አይደለም፡፡ ህገ መንግስቱ ዕውቅና እና ጥበቃ የሰጠው በምን መንገድ ለተገኘ ንብረት እንደሆነ በአንቀፅ 40 ንዑስ እንቀፅ 2 ደንግጓል፡፡ ህገ መንግስቱ ማንኛውም ኢትዮጵያ ዜጋ በማህበር ወይም ከሌሎች ጋር በጋራ ያፈራው ንብረት ዋስትና እና ጥበቃ የሚሰጠው ንብረቱ፣

- በጉልበታቸው ሠርተው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነ ወይም ተጨባጭነት የሌለው ሀብት ሲሆን፣
- የመፍጠር ችሎታቸውን ተጠቅመው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነ ወይም ተጨባጭነት የሌለው ሀብት፣
- በካፒታሉ ያፈራው ተጨባጭና ተጨባጭ ያልሆነ ሀብት ሲሆን፣
- ወይም ከላይ በተገለው መንገድ የንብረቱ ባለቤት ከሆኑ ሰዎች በህጋዊ መንገድ የባለቤትነት መብት የተላለፈለት የሆነ እንደሆነ መሆኑን በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 2 ተደንግጓል፡፡

ይኸም ማለት በህገወጥ መንገድና በወንጀል ሥራ አንድ ሰው ላገኘው ንብረት የንብረት ህገ መንግስቱ ዕውቅና እና ጥበቃ የማይሰጥ መሆኑን ለመገንዘብ ይችላል፡፡

### 3.3 የግል ንብረት ባለቤት መብት መሠረታዊ ይዘትና ባለመብቱ ላይ ስለሚጣሉ ገደቦች

የህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ድንጋጌዎች ለግል ንብረት ባለቤትነት የሚከበር ስለመሆኑ በግልፅ የሚያውጅ ከመሆኑ በተጨማሪ በአገሪቱ ውስጥ፣

- በግል የባለቤትነት የሚያዙ ዋና ዋና ሀብቶች፣
- በግል ባለቤትነት መብት የሚረጋገጡባቸውን ንብረቶች አይነትና ባህሪ፣
- የተለያዩ የንብረት ባለቤትነት መብቶችን፣
- የንብረት ባለቤት የሆኑ ሰዎች በንብረታቸው ላይ ያላቸውን ስልጣንና የባለቤትነት መብታቸው ሊገደብ የሚቻልበትን ሁኔታ፣
- መንግስት ለጠቅላላው ህዝብ ጥቅም የግለሰቦችን ንብረት ለመውሰድ ስለሚችልበት ሁኔታ በመደንገግ የግል ንብረት ባለቤትነት መብት መሠረታዊ ይዘትና መብቱ በዕለት ከዕለት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኑሮ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ይደነግጋል፡፡

### 3.3.1 በግል ንብረት የማይሆኑ ሀብቶች

በህገ መንግስቱ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው የተፈጥሮና የህግ ሰዎች በአገሪቱ ውስጥ ከሚገኙት ሀብቶች በባለቤትነት ለመያዝ የሚችሉትንና በባለቤትነት ለመያዝ የማይችሉትን ለመለየት በሚያስችል ግልፅ ድንጋጌ ደንግጓል፡፡ በአገሪቱ ግዛት ክልል አንድ የተፈጥሮ ወይም ህግ ወለድ ሰው የመብትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት መሆን አይችልም፡፡ ህገ መንግስቱ መሬት ግለሰቦች ሀብትና ንብረት በነበረበት ረዥም ዘመን በአብዛኛው የአገሪቱ ዜጋ ላይ የደረሰውን ግፍና በደል ግምት ውስጥ በማስገባትና የመሬት ጥያቄ አገሪቱ ባሳለፈችው ፖለቲካ ኢኮኖሚ ሂደት ውስጥ ቁልፍ የህዝብ ጥያቄ በመሆኑን በማገናዘብና መሬትና የተፈጥሮ ሀብት የህዝብና በመንግስት ንብረት እንዲሆን ህዝቡ ከፍተኛ ትግል በማድረጉ በአዋጅ ቁጥር 31/67 እና በአዋጅ ቁጥር 47/67 የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት የመንግስትና የህዝብ ሀብት እንዲሆን መሠረታዊ እርምጃ በደርግ ተወስዷል፡፡ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና ሀብት የባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ብቻ ነው፡፡ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ንብረት ነው በማለት በአንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 3 ደንግጓል፡፡

ድንጋጌው በአገሪቱ ግዛት ክልል ማናቸውም የተፈጥሮ ወይም የህግ ሰው የመሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለንብረት መሆን እንደማይችል ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 1 ለግል ንብረት ባለቤትነት መብት በህገ መንግስቱ የተሰጠው ዕውቅና እና ጥበቃ መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን የማይጨምር መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 3 የተፈጥሮም ሆኑ የህግ ሰዎች በመሬት ላይ የሚኖራቸው መብት የይዞታና መሬቱን የመጠቀም ከመንግስት ጋር በሚያደርጉት ስምምነት የተፈጥሮ ሀብት በማውጣትና በማምረትና ፕሮሰስ በማድረግ የመጠቀም መብት እንደሆነ የሚደነግግ ነው፡፡ የአገሪቱ ዜጎች እና ባለሀብቶች የመሬት ባለይዞታ የሚሆኑበት ሁኔታ ራሱን ችሎ በሰፊው የሚታይ በመሆኑ ወደ ዝርዝሩ መግባት አያስፈልግም፡፡

የህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 3 መሬትና የተፈጥሮ ሀብት የግል ንብረት ሊሆኑ የማይችሉ መሆኑን ከመደንገጉ ጋር ተያይዞ ያስቀመጠው አንድ ህጋዊ ገደብ አለ፡፡ ይኸውም የመሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት መሆናቸው የተረጋገጠላቸው

መንግስትና የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መሬትና የተፈጥሮ ሀብትን ሙሉ ባለቤትነት መብት ለግለሰብ ወይም የንግድ ድርጅት ወይም ማህበር በሽያጭ ወይም በለውጥ ሊያስተላልፉ የማይችሉ መሆናቸውን ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ህገ መንግስቱ የመሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤቶች ናቸው በማለት የገለፃቸውን ህዝብና መንግስት የባለቤትነት መብት ላይ ህገ መንግስታዊ ገደብ ይጥላል፡፡ የአንድ ንብረት ባለቤት የሆነ ሰው ንብረቱን መሸጥ መለወጥ መቻሉ የባለቤትነት መብት ዋናው መገለጫ ነው፡፡ ሆኖም መሬት መንግስትና ህዝብ መሸጥ መለወጥ የማይችሉ ስለመሆኑ መደንገግ ያስፈለገበት መሠረታዊና ዋና ምክንያት ምንድን ነው የሚለውን በጥልቀት መመርመርና መረዳት ያስፈልጋል፡፡

በህገ መንግስቱ ከተደነገጉት በተጨማሪ በግለሰብ ወይም በህግ ወለድ ሰዎች ባለቤትነት ሊያዙ የማይችሉ ሐብቶች እንዳሉ ከተለያዩ የህግ ማዕቀፎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከነዚህም መካከል በፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 1129 እንደተንቀሳቃሽ ንብረት የሚቆጠሩ የኤሌክትሪክ ኃይል ማሰራጫ መስመሮች የቴሌፎን የቴሌክስና የፋክስ አገልግሎት ማሰራጫ የስልክ መስመሮች እና ኔትወርክ መስመሮች በአገሪቱ በመንግስት እንጅ በግል ባለቤትነት አይያዙም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአደንዛዥ ዕፅ እና መርዛማ ነገሮችን የጦር መሣሪያ ያለመንግስት ፈቃድ ህጋዊ ባለቤት መሆን የማይቻል ንብረቶቹን ይዞ መገኘት የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑን በማየት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀንፅ 1 “የህዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላው ሁኔታ በህግ እስካልተወሰነ ድረስ” የሚለው አገላለፅ መንግስት የህዝብ ጥቅም መነሻ በማድረግ ለግለሰብ ባለቤትነት የማይሆኑ ንብረቶች ወይም የንብረቱ ባለቤት መብት ላይ በህግ በግልፅ በማወጅ ገደብ የሚጥል ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር አንድ ሰው የንብረት ባለቤት ለመሆን የሚቻልባቸው ሀብቶችና በንብረት ባለቤትነት መብቱን በመጠቀም ሂደት የሚጣሉበት ህጋዊ ገደቦች መኖራቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## <u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. መሬትና የተፈጥሮ ሀብት በግል ንብረትነት አይያዙም፡፡ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት የማይሸጥ የማይለወጥ የመንግስትና የህዝብ ሀብት ነው ብሎ ህገ መንግስቱ የደነገገበት መሠረታዊ ምክንያት ምንድን ነው?

2. መሬትና የተፈጥሮ ሐብት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሄር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ሀብት መሆኑ በህገ መንግስቱ መደንገጉ ተገቢ ነው ብለው ያስባሉ? ለምን?
3. በሀገሪቱ እየተሰራባቸው ባሉ የህግ ማዕቀፎች በግል ንብረትነት የማይያዙ ከመሬትና ከተፈጥሮ ሀብት ውጭ ያሉ ሌሎች ግዙፍነት ያላቸው ንብረቶች ይዘርዝሩ? ንብረቶቹ በመንግስት ብቻ በባለቤትነት እንዲያዙ የተደነገገበት ምክንያት ምንድን ነው?
4. አንድ ሰው በይዞታው በመገኘታቸው በወንጀል ኃላፊና ተጠያቂ የሚሆንባቸው ግዙፍነት ያላቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ የወንጀል ህጉና ሌሎች የህግ ማዕቀፎች መሠረት በማድረግ ይዘርዝሩ፡፡ እነዚህን ነገሮች በባለቤትነት ወይም በሌላ መንገድ መያዝ በወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ወንጀል ሆኖ የተደነገገበት መሠረታዊ ምክንያት ምንድን ነው?

## <u>3 3.2 የንብረት ባለቤትነት መብት ዓይነቶች</u>

ህገ መንግስቱ የተለያዩ ዓይነት የባለቤትነት መብቶች ዕውቅና እና ጥበቃ ይሰጣል፡፡

- የመጀመሪያው የጋራ ባለቤትነት መብት (joint ownership) የሚለው ነው፡፡ ህገ መንግስቱ በህግ በሚፈቅደው መሠረት ሰዎች በአንድ ንብረት ላይ የጋራ ባለሀብት ሊሆኑ እንደሚችሉ በአንቀፅ 40 በንዑስ አንቀፅ 1 አና ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ አንድ ንብረት የብዙ ሰዎች ሀብት በሚሆንበት ጊዜ እያንዳንዱ በንብረት ላይ ያለው ድርሻ በውል የሚወሰን ስለመሆኑ፣ ውል ከሌለ እኩል መብት እንዳላቸው እንደሚወሰን የጋራ ባለሀብቱ የራሱን ድርሻ ማስያዝ ለመሸጥና ለመለወጥ እንደሚቻል እና የጋራ ባለሀብቱ ገንዘብ አበዳሪዎች ድርሻቸውን መያዝ የሚችሉ መሆኑንና የጋራ የንብረት ባለቤትነት መብት ዋናው መገለጫ ነው፡፡ ይህ ማለት ሁለት ሰዎች እኩል አዋጥተው አንድ ህንፃ ሰርተው የጋራ ባለሀብት ቢሆኑ የአንደኛው ባለሀብት በህንፃው ላይ ያለውን ድርሻ ለማወቅ ለመሸጥ ለመለወጥ ወይም ለመያዝ የሚቻል እንደሆነና ከሁለታቸው አንዳቸው በማንኛውም ጊዜ ንብረቱን ለመካፈል ለመጠየቅ የሚችሉ መሆናቸው የጋራ ባለሀብትነት መሠረታዊ ባህሪ ሲሆን ይህንን አስመልክቶ የፍትሐብሄር ህጉ በአንቀፅ 1256 — 1277

ዝርዝር ደንቦችን ደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር የጋራ ባለሀብት የሆኑ ሰዎች የንብረት ባለቤትነት መብት በህገ መንግስቱ እውቅና እና ጥበቃ የተሰጠው መሆኑን መገንዘብ እንችላለን፡፡

- ህገ መንግስቱ ከጋራ ንብረት ባለቤትነት ባለፈ በህግ እውቅና ያለው ግንኙነት በመመስረታቸው የራሱ ልዩ ባህሪ ያለው የጋራ (የወል) የንብረት ባለቤትነት ስርዓት እውቅና እና ጥበቃ ይሰጣል፡፡ ህገ መንግስቱ ጋብቻ የመፈፀምና ቤተሰብ የመመስረት መብት በአንቀፅ 34 እውቅና እና ጥበቃ የሰጠ ሲሆን በአንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 2 "በህግ በተለየ የጋራ ባለቤት እንደሆኑ የተፈቀደላቸው" የሚል አገላለፅ ባልና ሚስት በጋብቻ ጊዜ ያፈሩት የጋራ ሐብት (common property)ዋስትና እና ጥበቃ ይሰጣል፡፡ የባልና የሚስት የጋራ ንብረት በመሠረታዊ ባህሪ ከጋራ ንብረት ባለቤትነት (joint ownership) የሚለይበት ሁኔታ አለ፡፡ ከዚህ አንፃር የፌዴራልም ሆነ የክልሎች የቤተሰብ ህግ ማዕቀፎች በጋብቻ በተፈራ የጋራ ንብረት (common property) የሚሰጡት ጥበቃ እና ዋስትና በዝርዝር ማየትና ከህገ መንግስቱ ድንጋጌ ጋር የሚጣጣም መሆኑን መመርመር ያስፈልጋል፡፡
- ህገ መንግስቱ በማህበር በመደራጀት የንብረት ባለቤት መሆን የሚቻል መሆኑን እና በኢትዮጵያ ውስጥ የተመዘገቡ የተለያዩ ማህበሮች ማለትም የፖለቲካ ድርጅቶች የሲቪል ማህበሮች የንግድ ድርጅቶች የንብረት ባለቤትነት መብት ህገ መንግስታዊ እውቅና እና ጥበቃ የተሰጣቸው መሆኑን ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 1ና ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡
- ህገ መንግስቱ በህግ የአንድ ንብረት በውል እንዲይዙና የወል ባለቤት እንደሆኑ የተፈቀደላቸው ማህበረሰቦች በንብረቱ ላይ የሚኖራቸው የወል ባለቤትነት መብት ዕውቅና እና ጥበቃ የተሰጠው መሆኑን በአንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ ስንመለከተው ህገ መንግስቱ የግለሰብ ኢተዮጵያዊያን የንብረት ባለቤትነት፣ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው የህግ ሰዎች፣ ማህበሮችና የንግድ ድርጅቶች የንብረት ባለቤትነት፣ የግለሰቦች የጋራ የንብረት ባለቤት የመሆን መብትና የባልና የሚስት የጋራ ንብረት ባለቤትነት መብት በህግ የተፈቀደላዠው ማህበረሰቦች የወል የባለቤትነት መብት ዕውቅና እና ጥበቃ ይሰጣል፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. የጋራ ንብረት ባለቤትነበት (joint ownership) እና በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ባለቤትነት መብት (common property) መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው፡፡
2. ህገ መንግስቱ በውጭ አገር ለተቋቋሙና በኢትዮጵያ ህግ መሠረት ተመዝግበውና ፈቃድ ተሰጥቷቸው ለሚሠሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የንብረት ባለቤትነት መብት ዕውቀና እና ጥበቃ ሰጥቷል ብለው ያስባሉ? ለምን?
3. የውጭ አገር ዜጎች የአክሲዮን ባለድርሻ የሆኑበት በኢትዮጵያ ውስጥ የተመሠረተና የተመዘገበ "የአክሲዮን ማህበር" የንብረት ባለቤት የመሆን መብት በህገ መንግስቱ ዕውቅና እና ጥበቃ ተሰጥቶታል ብለው ያስባሉ? ለምን?
4. የፖለቲካ ድርጅቶች እና ሌሎች የሲቪል ማህበሮች የንብረት ባለቤት የመሆን መብት አላቸው? ለምን?

### 3.3.2 የንብረት ባለቤት የሆነ ሰው ወይም የሆኑ ሰዎች ስላላቸው ሥልጣንና ስላለባቸው ኃላፊነት

የንብረት ባለቤት ወይም ባለቤቶች በንብረታቸው ላይ ያላቸው መብት ከሌሎች መብቶች ሁሉ የሠፋና በንብረቱ ላይ ከፍተኛ የማዘዝ ሥልጣን የሚያጎናፅፍ እንደሆነ በርካታ ፀሐፊዎች ይስማሙበታል፡፡ የንብረት ባለቤትነት መብት-

- ንብረቱን የመጠቀም
- የንብረቱን ፍሬ ወይም አላባ የመሰብሰብ
- ንብረቱን የመሸጥ የመለወጥ በመያዣነት የማስያዝ እና የባለቤትነት መብቱን ሌላ ሰው የማስተላለፍ፣
- የሌሎች ሰዎችን መብት በማይነካ ሁኔታ ንብረቱን የማውደም ወይም የንብረት ባለቤትነት መብቱን የመተው
- ሦስተኛ ወገኖች እና ማናቸውም ሰው በንብረቱ እንዳያዝ ወይም እንዳይጠቀሙ የማስወገድ ወይም የመፋለም መብትና መብቱ ቋሚነት ያለውና የማይቀያየር መሆኑን የሚያጠቃልል መሆኑ በበርካታ አገሮች የንብረት ህግ ማዕቀፎች የተደነገገ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በእኛም አገር እየተሰራበት ያለው የፍታብሄር ህግ የንብረት ህግ ድንጋጌዎች የንብረቱ ባለቤት የሆነ ሰው ከላይ የተገለፁት ሰፊ መብቶች ያሉት መሆኑን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1204 እስከ ፍታብሄር ህግ ቁጥር 1206 ተደንግጓል። ህገ መንግስቱ ለግል ንብረት ባለቤትነት መብት ዕውቅና እና ጥበቃ ሲሰጥ መንግስት የህዝብ ጥቅም ለመጠበቅ ዓላማ ያደረገ ህግ በማውጣት እስካልገደበው ድረስ ወይም ባለንብረቱ መብቱን ሲጠቀም የሌሎች ዜጎችን መብት እስካልተቃረነ ድረስ የንበረቱ ባለቤት ንብረቱን የመያዝ፣ የመጠቀም ንብረቱን የመሸጥ የማውረስና በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብት ያለው መሆኑን በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 1 እና በህገ መንግስቱ በአንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 7 ተደንግጓል።

በህገ መንግስቱ ዕውቅና የተሰጠው የባለቤትነት መብት ባለንብረቱ መንግስትን ጨምሮ በሌላ በማናቸውም ወገን ከህግ ውጭ ከንብረቱ ላይ ያለመፈናቀል መብት ያለውና የተከበረ መሆኑንና ማናቸውንም ሰው በህግ አግባብ የመፋለም መብትን አጠቃልሎ ሊይዝ የሚችል መሆኑን የህገ መንግስቱን አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 7 ድንጋጌዎች ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 37 ጋር በማጣመር ለመገንዘብ ይቻላል። የንብረቱ ባለቤት የሆነ ሰው በህገ መንግስቱና በሌሎች የህግ ማዕቀፎች መሠረት በንብረቱ ለመጠቀም የንብረቱን አላባና ፍሬ ለመሰብሰብ ንብረቱን ለመሸጥ ለመለወጥና ለማስያዝ ለማስተላለፍ እንዲሁም ሌሎች ሰዎች በመብቱ ጣልቃ እንዳይገቡ የመፋለም መብት ያለው ሲሆን፤ በተመሣሣይ ሁኔታ የንብረት ባለቤት ሊያከብራቸው የሚገቡ ግዴታና ኃላፊነቶች አሉበት።

- መብቱን ሲጠቀም መንግስት ለአጠቃላዩ ህብረተሰብ ጥቅም በማሰብ በህግ የደነገጋቸውን ገደቦች እና ሁኔታዎች ማክበርና ለህጉ ተገዥ የመሆን፣
- መብቱን ሲጠቀም በሌሎች ዜጎች መብትና ነፃነት በማይጋፋና በእነርሱ ላይ ጉዳት ወይም ሁከት በማይፈጥር ሁኔታ መጠቀምና የሌሎች ሰዎች በህግ የተረጋገጡ መብቶች ማክበር፣
- ንብረቱ የሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች የጋራ ንብረት በሆነ ጊዜ የጋራ ንብረትን በሙሉ ለመሸጥ ለመለወጥ ለማስያዝና ለማስተላለፍ በህግ መሟላት አለባቸው ተብለው የተደነገጉ ቅድመ ሁኔታዎችን የማሟላት፣

- ንብረቱ የባልና የሚስት የጋራ ንብረት በሆነ ጊዜ ስለባልና ሚስት የጋራ ንብረት አስተዳደር የተደነገጉ ሁኔታዎችን የማሟላት፣
- የወል ንብረት በሚሆን ጊዜ የማህበረሰብ የወል ንብረት አጠቃቀም አስመልክቶ የተደነገጉ ህጎችን የማክበር፣
- ንብረቱን ለመሸጥ ለመለወጥ በመያዣነት ለማስያዝና ለሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ በህግ የተደነገገውን ፎርም የሚሟላ ህጋዊ ተግባር የመፈፀም፣
- ባለንብረቱ ሦስተኛ ወገኖችን ለመፋለም መብቱን በሚጠቀም ጊዜ ባለቤትነቱን የማስረዳት እና በህግ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ክሱን የማቅረብ፣
- እና ሌሎች በህግ የተጣሉበትን ንብረትን የማስመዝገብ፣ የግብርና ሌሎች ክፍያዎችን የመክፈል ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡

የንብረት ባለቤት የሆነ ሰው መብቱን ለማስከበርና መብቱን ሲጠቀም ሊያከብራቸው የሚገቡ ግዴታዎች በባለቤትነት እንደያዛቸው ንብረቶች ባህሪና አይነት የሚለያይ ነው፡፡ ስለሆነም በንብረቶቹ ባህሪና አይነት በአጭሩ ስንመለከት፣ ህገ መንግስቱ አንቀፅ 42 ንዑስ አንቀጽ 2 ጥበቃና ዋስትና የሰጣቸውን መብቶች በተለያየ መንገድ የሚፈርጅ ሲሆን ህገ መንግስቱ የንብረቶችን፣

- ተጨባጭነት ያላቸው (tangible) ንብረቶች
- ተጨባጭነት የሌላቸው ንብረቶች (non-tangible) በማለት ይከፍላቸዋል፡፡

ተጨባጭነት ያላቸው ንብረቶች የሚባሉት ግዙፍነት ያላቸውን የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀስ ንብረት (ህንፃ ወይም ቤት) የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ግዙፍነት የሌላቸው ተላላፊ የንግድ ሰነዶች የአክሲዮን ድርሻ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት "ቢል ኦፍ ሌድንግ" እና የመሣሰሉትንና የአእምሮ ሥራና ፈጠራ ውጤቶች የሆኑ የቅጅ መብት የንግድ ምልክትና የፓተንት መብትን የሚያጠቃልል ነው፡፡

ከነዚህ የተለያየ ባህሪ ካላቸው ንብረቶችና የመብት መጠየቂያ ሰነዶች አንፃር የሚነሱና የማያከራክሩ ሁኔታዎች እጅግ በጣም በርካታ ናቸው፡፡ የሚከተሉትን ሁኔታዎች በማየት አከራካሪ ነጥቦች ላይ የጋራ መግባባት መድረስ የሚያስፈልግ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ለአብነትም፣

- ወ/ሮ እናኑ ቤቷን ለአቶ አለሙ በብር 50,000 (ሀምሳ ሺ. ብር) ሸጠች፡፡ አቶ ዓለሙ ብር 30,000 (ሰላሳ ሺ. ብር) ከፍሎ የቤቱን ይዞታ ከወ/ሮ እናኑ ተረክቦ ለሁለት ዓመት ያህል ከገዛው ቤት ከኖረ በኋላ ቀሪውን 20,000 (ሀያ ሺ. ብር) አልከፈለኝም በሚል ምክንያት ዘመዶቿን ሰብስባ የአቶ አለሙን ዕቃ ከቤት ግቢ ውጭ በማውጣት እሸጠችው ቤት ገብታ መኖር ጀመረች፡፡ የቤቱ ባለሀብትነት ከወ/ሮ እናኑ ወደ አቶ አለሙ አልተዛወረም፡፡ አቶ አለሙ የሁከት ይወገድልኝ ክስ በወ/ሮ እናኑ ላይ አቀረበ፡፡ ወ/ሮ እናኑ የቤቱ ባለሀብት ስለሆንኩኝ አቶ ዓለሙ በወ/ሮ እናኑ ላይ የሁከት ይወገድ ክስ የማቅረብ መብት የለውም በማለት ተከራከረች፡፡ አቶ ዓለሙ የሁከት ይወገድልኝ ክስ በወ/ሮ እናኑ ላይ ማቅረብ ይችላል? ህገ መንግስታዊ ጥበቃ የተሰጠው መብት ያለው ማን ነው? አቶ ዓለሙ በምን ሁኔታ መብቱን ለማስከበር ይችላል?
- አቶ ደምሴ የአቶ አበበን ቤት በተከራይነት እንደያዙ አቶ አበበ አገር ጥሎ በመሰደዱ ለሀያ አመት ያህል ያለማንም ጠያቂና ተቆጣጣሪ የአቶ አበበን ቤት ይዞ ቆየ፡፡ አቶ አበበ ከስደት ተመልሶ አቶ ደምሴ የሀያ ዓመት ኪራይ እንዲከፍለው ቤቱንም እንዲለቅለት ክስ አቀረበ አቶ ደምሴ የአቶ አበበ የባለቤትነት ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1677(3) እና 1845 በመጥቀስ ተከራከረ፡፡ አቶ አበበ በማይንቀሣቀስ ንብረት ባለቤትነታቸውን ለማስከበር በአቶ ደምሴ ላይ ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍ አለው ብለው ያስባሉ? ለምን? አቶ አበበና አቶ ደምሴ የሚከራከሩበት ንብረት የሚንቀሳቀስ ንብረት ቢሆን አቶ ደምሴ ክርክር ዋጋ ይኖረዋል?
- አቶ ከበደ በአዲስ አበባ ከተማ በማህበር ተደራጅተው የሠሩት ቪላ ቤት በሀሰተኛ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርና ካርታ በመያዝ በተጭበረበረ ሁኔታ አቶ ስዩም የቤቱ ባለቤት ነኝ በማለት ለወ/ሮ ድንቄ በውልና ማስረጃ ሸጡት፡፡ አቶ ስዩም የአቶ ከበደን ቤት ለወ/ሮ ድንቄ በሸጠበት ጊዜ የአቶ ከበደ ቤት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ለሦስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ በፍርድ ቤት የተሰጠ የዕግድ ትዕዛዝ ከቤቱ ማህደር ጋር ተያይዞ ነበር፡፡ አቶ ከበደ ቤታቸው መሸጡን ሲሰሙ ቤቱን የቤቱ እርግጠኛ ባለቤት ሣይሆን በተጭበረበረ ካርታና ፕላን አቶ ስዩም የሸጠውና ቤቱም የዕግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት መሆኑን የሚመለከተው አስተዳደር በአግባቡ ማህደሩን መርምሮ ሣያረጋግጥ የቤቱን ባለሀብትነት ለወ/ሮ ድንቄ በማስተላለፍ ለወ/ሮ ድንቄ የቤቱ

ባለሀብት መሆኗን የሚያረጋግጥ የባለቤትነት ማስረጃና ካርታ ፕላን በክፍሉ መሬት አስተዳደር መምሪያ መሰጠቱ ተገቢ ስላልሆነ የአስተዳደሩ መሥሪያ ቤት ለወ/ሮ ድንቂ የሰጠውን የባለቤትነት ማስረጀና ካርታና ፕላን እንዲሰረዝ አመለከቱ፡፡ ለስድስት ወር ያህል ውሣኔ ባለማግኘታቸው አቶ ከበደ ወ/ሮ ድንቂ የባለቤትነት መብት ከሌለውና ቤቱን ለመሸጥ ከማይችል ሰው የገዙ መሆናቸውንና ወ/ሮ ድንቂ ሲገዙ የቤቱን ማህደር የተያያዙ መረጃ ቢያዩ ኖሮ ከስህተት ላይ እንደማይወድቁ በመግለፅ እንደዚሁም ቤቱ የተሸጠው የፍርድ ቤት ዕግድ ትዕዛዝ ተጥሶ መሆኑን በማብራራት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 (1) መሠረት የንብረት ባለቤትነት መብታቸው እንዲከበር የክፍሉ አስተዳደር ለወ/ሮ ድንቂ የሰጠው የባለቤትነት የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ ለፍርድ ቤት ውሣኔ በመስጠት የባለቤትነት መብታቸውን እንዲያስከብርላቸው ክስ አቀረቡ፡፡

- ፍርድ ቤት ጉዳዩን አከራክሮ የመወሰን ስልጣን አለው ብለው ያስባሉ? ለምን?
- በጉዳዩ የሚሰጡት ውሣኔ ምንድን ነው ውሣኔውን ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 37 እና አንቀፅ 40 ድንጋጌ አንፃር እንዴት ያዩታል?

- የንብረት ባለቤት የሆነ ሰው ንብረቱን የማስያዝ መብት ያለው መሆኑ የሚታወቅና ግልፅ ጉዳይ ነው፡፡ የአክሲዮን ድርሻ ግዙፍነት የሌለው ንብረት (non-tangible) ንብረቶች ከሚባሉት አንደኛው ነው፡፡ ለመሆኑ የሚንቀሣቀሱ ግዙፍነት ያላቸው ንብረቶች ማስያዝ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 2828(2) የተጠቀሰው መሥፈርት የአክሲዮን ድርሻን በመያዣነት ለማስያዝ በሚደረጉ ውሎች ላይ ተፈፃሚት አላቸው ብለው ያስባሉ? ለምን?

## 3.4 የመሬት ባለይዞታነትና መሬትን የመጠቀም መብት

መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የመንግስት ሀብት መሆኑን የሚደነግገው የህገ መንግስቱ ድንጋጌ ከመሬት ባለይዞታነትና መሬትን ከመጠቀም መብት ጋር የተያያዙ አራት መሠረታዊ መብቶችን ጥበቃና ዋስትና ሰጥቷል፡፡ እነሱም፡-

- ✓ የአርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘት መብተና ከይዞታ መሬታቸው ያለመነቀል መብት፣

- ✓ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርበቶ አደሮች በነፃ የማግኘት መብትና ከይዞታ መሬታቸው ያለመፈናቀል መብት፣
- ✓ የግል ባለሀብቶች በህግ በሚወሰን ክፍያ መሬት ባለይዞታ የመሆንና መሬትን የመጠቀም መብት፣
- ✓ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ መሬት ላይ ለገነባው ቋሚ ንብረት (የማይንቀሳቀስ) ንብረትና ላደረገው ቋሚ መሻሻል ንብረቱን የመሸጥ የመለወጥና የማስያዝ እና የማውረስ መብት ያለው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 4 እስከ ንዑስ አንቀፅ 7 የተደነገጉት እነዚህ መብቶች የየራሳቸው ልዩ ባህሪ እና ይዘት ያላቸው ናቸው፡፡ ህገ መንግስቱ መሬት በነፃ የማግኘት መብት ያላቸው በገጠር ኗሪ የሆኑ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች መሆናቸውን በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ህገ መንግስቱ ማናቸውም የከተማ ኗሪ የሆነ ሰው በነፃ መሬት የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ አይደነግግም፡፡ ይኸውም በከተሞች አካባቢ ያለውን የመሬት እጥረት፣ የከተሞች ወደ ጎን ማደግና መስፋት መንገድ ውሀ መሬት ስልክና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማት ለማዳረስ የሚፈጥረውን ችግር እና በዋነኛነት ከተሞች ወደ ላይ፣ ፎቅ ቤቶችን በመገንባት ለብዙ ሰዎች መኖሪያነት የሚያገለግሉ ከንግድ ሥራና የጽ/ቤት እና ሌሎች አልግሎት ሰጭ ተቋማት እንዲኖሩ ለማድረግ የሚከተሉትን የዕድገት አቅጣጫ የሚመለከት ነው፡፡ ይህንን ለማድረግ ለኢንቨስትመንት የሚሆን ገንዘብ ያላቸውና ባለሀብቶች በከተማም ሆነ በገጠር በሊዝ ኪራይ ክፍያ መሬት የማግኘትና መሬት የመጠቀም መብት ያላቸው መሆኑን ህገ መንግስታዊ ዕውቅና የሰጠ መሆኑን ለመገንዘብ እንችላለን፡፡

ከዚህ አንፃር የከተማ ኗሪዎች በማህበር በምሪትና በሌሎች መንገዶች የመኖሪያ መብት ለመሥራት መሬት የማግኘት መብታቸው እያንዳንዱ ክልል እና የከተማ አስተዳደር በሚያወጣው ህግ የሚወሰንና በህገ መንግስቱ አንቀፅ 25 መሠረት መስፈርቱን ያሟሉ ሰዎች በእኩል ደረጃ የመስተናገድና አገልግሎት የማግኘት መብት አንፃር የሚታይ ነው፡፡ ህገ መንግስቱ በነፃ መሬት የማግኘት መብት ዕውቅና እና ጥበቃ የሰጠው፣ የኑሮ ህልውናቸው የመሬት ባለይዞታ ከመሆን ጋር ለተያያዘው በአርሶ አደሮች ከፊል አርብቶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ብቻ ነው፡፡

### 3.4.1 ባለሀብቶች መሬት በክፍያ የማግኘት መብት፣

ለባለሀብቶች የመሬት ባለይዞታ የሚሆኑበት ሥሪት ዋነኛው የሊዝ ሥሪት መሆኑን ህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 6 ይደነግጋል፡፡ ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም የህግ ሰው በከተማም ሆነ የገጠር መሬት በህግ የተደነገጉ መሥፈርቶችን በማሟላት መሬት በሊዝ የመያዝና የመጠቀም መብት ያለው መሆኑን ህገ መንግስቱ አመላካች በሆነ መነገድ ደንግጓል፡፡ ይህንን ህገ መንግስታዊ መብት ተፈፃሚ ለማድረግ የፌዴራል መንግስት ከተጨባጭ ሁኔታዎች እና በሊዝ አፈፃፀም የሚነሱ ችግሮችን ሊፈቱ የሚችሉ የህግ ማዕቀፎች ደንግጓል፡፡ የፌዴራል መንግስት የከተማ ቦታ በሊዝ ስለማያዝን እንደገና ለመደንገግ አዋጅ 272/1974 የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ 456/97 ያወጀ ሲሆን ክልሎችም ከራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፌዴራሉን አዋጅ መሠረት ያደረገ የሊዝ ደንብ እና ክልላዊ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ በማውጣት እየተገበሩት ይገኛሉ፡፡ የአዋጆቹን ዝርዝር ይዘት በዚህ ፅሁፍ መዘርዘርና ማካተት የማይቻል በመሆኑ ከንብረት መብትና ከተሰጠው ጥበቃና ዋስትና አንፃር ዋናዋናዎቹን ብቻ ስንመለከት፣

- የገጠር መሬት በኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችና ህጎች መሠረት የመጠቀም መብት ባለሀብቶች እንደሚኖራቸው አዋጅ ቁጥር 456/97 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 4 የሚደነግግ ሲሆን ይኸውም መብት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ፣ በክልሎች ህግ የሚደነገግ ስለመሆኑ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 2 ይደነግጋል፡፡
- ከዚህ ጋር በተያያዘ የገጠር መሬት በሊዝ የተከራየ ባለሀብት የመጠቀም መብቱን በዋስትና ማስያዝ እንደሚችልና በአንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 4 ተደንግጓል፡፡

በሌላ በኩል የከተማ መሬት በሊዝ የተከራየ ማንኛውም ሰው ቦታውን ለተፈቀደለት አገልግሎት የሊዝ ዘመኑ እስኪጠናቀቅ የመጠቀም፡

- የሊዝ መብቱን ማስተላለፍና በዋስትና የማስያዝ፣
- ለህዝብ ጥቅም በሊዝ የያዘውን ይዞታ እንዲለቅ ሲደረግ ተገቢውን ካሣ የማግኘት መብት፣

- አቤቱታ የማቅረብ ይግባኝ ለከተማ ቦታ ማስለቀቅ ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ እና በካሣ መጠን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 272/1994 ተደንግጓል፡፡

ከዚህ አንጻር በከተማም ሆነ በገጠር በሊዝ መሬት የተከራዩ ሰዎች በህገ መንግሥቱ እውቅና የተሰጠው መብታቸው ተፈጻሚነት የሚያረጋግጡ የሕግ ማዕቀፎች የወጡ ሲሆን፣ መሬት የመንግሥትና የሕዝብ ሆኖ ባለበት ሁኔታ ግለሰቦች በህግ ለተደነገገ ዘመን፣ የመሬት ባለይዞታና ተጠቃሚ የሚሆኑበትንና መብታቸውን በማስያዝ ወይም ለማስተላለፍ የሚችሉበትን ሁኔታ ይደነግጋል፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄ</u>

1. የክልላችሁ የሊዝ ደንብና በክልሉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ አንድ ባለሀብት የከተማና የገጠር መሬት በሊዝ የመከራየትና የመሬት ተጠቃሚ የመሆን መብት ምን ምን ሁኔታዎችን ያጠቃልላል?
2. የከተማ ነዋሪ የሆኑ የአገሪቱ ዜጎች ለመኖሪያ ቤት መሥሪያ የሚሆን መሬት በነፃ የማግኘት መብት በህገ መንግሥቱ እውቅና እና ጥበቃ ያልተሰጠበት ምክንያት ምንድን ነው?
3. የሕገ መግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረታዊ ዓላማ ምንድን ነው ብለው ያስባሉ?
4. አንድ ሰው ሕግ በሚያዘዉ መሠረት የከተማ ቦታ ባለይዞታ ሆኜ እያለሁ አስተዳደሩ ይህንን የሚያረጋግጥ የይዞታ ማስረጃ አልሰጥም ስለአለኝ የይዞታ መብቱ ተረጋግጦ የይዞታ የምስክት ወረቀት እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ለፍርድ ቤት የሚያቀርበው ጥያቄ በዳኝነት ሊታይ የሚችል /justicable/ ጉዳይ ነው? ከህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች አንፃር እንዴት ያዩታል?

### 3.4.2. <u>አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች በነፃ መሬት የማግኘትና ከይዞታቸው ያለመፈናቀል መብት</u>

ሕገ መንግሥቱ የአርሶ አደሮችና የአርብቶ አደሮች በነፃ መሬት የማግኘት የመሬት ባለይዞታ የመሆንና ያለመነቀል መብት ወጥ በሆነ ሁኔታ ለማረጋገጥ የሚችል የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ እንዲያወጣና ክልሎች የፌዴራል መንግሥት ያወጣውን

ሕግ መሠረት በማድረግ ዝርዝር የሕግ ማዕቀፎችን በማውጣትና አስፈጻሚ አካላትን በማደራጀት በክልሉ ውስጥ ያለውን መሬት የማስተዳደር ሥልጣን ያላቸው መሆኑ በግልጽና በማያሻማ ቋንቋ ይደነግጋል፡፡

የፌዴራል መንግሥት በሕገ መንግሥቱ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የመጀመሪያውን የፌዴራል የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ በ1989 ዓ.ም. አውጥቷል፡፡ የመጀመሪያው አዋጅ 89/1989 ሲሆን የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራተጂ ከተነደፈ በኋላ ፖሊሲውን በአግባቡ ሊያስተገብር በሚችል መልኩ አዋጁን ማሻሻል በማስፈለጉ አዋጅ ቁጥር 456/97 ተሻሽሏል፡፡ ይኸ የሕግ ማዕቀፍ፣

- ❖ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ በነፃ መሬት የማግኘት መብት ለማረጋገጥ የአርሶ አደሩን ከይዞታው ያለመፈናቀል መብት ጥበቃ ለመስጠት፣
- ❖ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ከይዞታቸው ማፈናቀል የሚያስፈልግበት በቂ ምክንያት ሲኖር መሬቱን ለማልማት ያወጡትን ወጪና በመሬቱ ላይ ላለሙት ቋሚ ንብረትና ሰብል በቂ ካሣ እንደዚሁም ከይዞታቸው የተፈናቀሉ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች በመፈናቀሉ ምክንያት ለሚደርስባቸው የሚያገኙበትን ሁኔታ በዝርዝር በመደንገግ ሕገ መንግሥቱን መሠረታዊ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሕግ መሠረት ጥለዋል፡፡

የፌዴራል የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/97 በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ በማናቸውም የገጠር መሬት ላይ ተፈጻሚነት ያለው የሕግ ማዕቀፍ ሲሆን አዋጁ ሁለት ዓይነት ባሕሪይ ያላቸው ድንጋጌዎች የያዘ ነው፡፡ እነርሱም፣

- ❖ ሁሉም ክልሎች ሊያከብሯቸውና ሊተገብሯቸው የሚገቡ አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎች
- ❖ ክልሎች ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ ውሳኔ ሊሰጡባቸው የሚገቡ ፈቃጅ የሕግ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 456/97 መሠረት ሁሉም ክልሎች የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ዝርዝር የሕግ ማዕቀፎችን ሲያወጡና የሕግ ማዕቀፎቹን ሲያስፈጽሙ የሚከተሉትን መሠረታዊ መብቶች የማክበር ግዴታ አለባቸው፡፡

- ❖ በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ አርሶ አደር ከፊል አርብቶ አደርና አርብቶ አደሮች የገጠር መሬት በነፃ እንዲያገኙ ማድረግ፣

❖ ሕፃናት አካለ መጠን እስኪደርሱ በሞግዚታቸው አማካኝነት የገጠር መሬት የመጠቀም መብታቸውን ማረጋገጥ፣

❖ ሴቶች የገጠር መሬት በነፃ የማግኘትና የመጠቀም መብት ማረጋገጥ፣

❖ አርሶ አደር ከቤተሰቡ የመሬት ይዞታ በስጦታ ወይም በውርስ የማግኘት መብት ማረጋገጥ፣

❖ ኢንቨስተሮችና ሌሎች ድርጅቶች የገጠር መሬት የመጠቀም መብት ለማረጋገጥ የሚችል አሠራር መከተል፣

❖ የገጠር መሬት በግልና በወል መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ስለመያዙ የተሟላ መረጃ መዝግቦ መያዝና ኘላን መስጠት፣

❖ የአርሶ አደሮች ከፊል አርብቶ አደሮችና አርብቶ አደሮች በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ያለምንም ጊዜ ገደብ ማረጋገጥ፣

❖ የገጠር መሬት ባለ ይዞታ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መሬቱን በመንግሥት እንዲለቅ ሲደረግ በመሬቱ ላይ ላደረገው ማሻሻያና ላፈራው ንብረት ተመጣጣኝ ካሣ የማግኘት መብቱን ማረጋገጥና ተለዋጭ መሬት እንዲያገኝ ማድረግ፣

❖ አርሶ አደሮች በማይፈናቀሉበት መልኩ በይዞታ የያዙትን መሬት የማከራየት መብት ማረጋገጥ፣

❖ የገጠር መሬት በሊዝ የተከራየ ባለ ሀብት መሬቱን የመጠቀም መብቱን እንደዋስትና የማስያዝ መብቱን ማረጋገጥ፣

❖ የገጠር መሬት ሽግሽግ ለማድረግ መሠረት የሚሆኑ ደንቦችን መከተል፣

❖ የገጠር መሬት አጠቃቀም እቅድ ማውጣትና ማስፈጸም፣

❖ የመሬት ተጠቃሚዎች ግዴታቸውን እንዲወጡ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ክልሎች የመሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም የሕግ ማዕቀፎች ሲወጡም ሆነ ሕጎችን ሲያስፈጽሙ በጥብቅ ሊያከብሯቸው የሚገቡ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 456/97 መሠረት ክልሎች የራሳቸውን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ በሕግ ሊያወጡባቸውና በተለያየ መንገድ ሊያስፈጽሟቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በተመለከተ፡-

❖ አርሶ አደር ሆኖ መሬት በነፃ የማግኘት መብት ያለው ምን መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን መወሰን፣

- በገጠር የሚገኝ መሬት በግል ይዞታ የሚያዝ የውልና የጋራ መሆናቸውን መለየትና መከለል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሠወልና የጋራ መሬት ይዞታዎችን ወደ ግል ይዞታ ማዛወር የሚቻልበትን ሥርዓት መዘርጋት፣
- የገጠር መሬት በሊዝ የያዙ ኢንቨስተሮች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት የመሬት ባለይዞታነትና መሬትን የመጠቀም መብት ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ መወሰን፣
- አርሶ አደሮች በኪራይ ሊያስተላልፉ የሚችሉትን የይዞታ መጠንና ኪራዩ ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ መወሰን፣
- የኪራይ ውል የሚመዘገብበትን ሁኔታ መወሰንና ማመቻቸት፣
- የመስኖ መሬት ሽግሽግና የመሬት ሽግሽግ ለማካሄድ የሚያስችሉ ደንቦች ማውጣት፣
- የገጠር መሬት አነስተኛ ወለል መጠን መወሰን፣
- የመሬት ይዞታን አስመልክቶ የሚነሳ ክርክር የሚፈታበትን ሁኔታና ሥልጣን ያላቸውን አካላት በሕግ መደንገግ፣
- የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ሕግን የሚያስፈጽም አካል ማደራጀት ናቸው፡፡

ክልሎች ይህንን ለመተግበር የሚያስችል የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅና ደንብ አውጥተው ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌውን በማስፈጸም ላይ ይገኛሉ፡፡

<u>መወያያ ጥያቄ</u>

1. የክልላችሁ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅና ደንብ ከአዋጅ ቁጥር 456/97 ከአስገዳጅ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣሙ ናቸው?
2. አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር በገዛ መሬቱ የመጠቀም መብት ተግባራዊ ለማድረግ የፌዴራልና በክልል የሕግ ማዕቀፎች ምን ምን መንገዶችን ይጠቀማሉ?

### 3.4.3 በመሬት ላይ በተደረገ ቋሚ መሻሻልና ቋሚ ንብረት ላይ ባለቤት ስለመሆን

ሕገ መንግሥቱ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት የመንግሥትና የሕዝብ ንብረት መሆናቸውን ቢያውጅም ማንኛዉም በገጠርም ሆነ ከተማ የሚኖር ኢትየጵያዊ በሕጋዊ መንገድ መሬት በነፃ ወይም በሊዝ ሥርዓት አግኝቶ በመሬቱ ላይ የሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ቋሚ መሻሻል ያለው የባለቤትነት መብት የማይቀንስና የባለቤትነት መብቱ ሙሉ መብት መሆኑንና ይኸም መብት መሸጥ፣ መለወጥ የማውረስና የመሬት ተጠቃሚነቱ

ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም ካሣ የመጠየቅ መብቱን የሚያካትት መሆኑን በአንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 6 ይደነግጋል፡፡

ይኸም መንግሥት የመሬት ባለሀብት ሲሆን ከመንግሥት በኪራይ ወይም በነፃ መሬት በሕጋዊ መንገድ አግኝተው ገንዘባቸውንና በጉልበታቸው ቋሚ ንብረት የገነቡ በመሬቱ ላይ ቋሚ መሻሻል ያደረጉ ሰዎች በመሬቱ ላይ ባፈሩት ንብረት ሙሉ የባለቤትነት መብት ያላቸውና የባለቤትነት መብታቸው መሬቱ የመንግሥት በመሆኑ የማይቀነስባቸው ስለመሆኑ ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 6 ይደነግጋል፡፡ ይኸም መሬትን ከጉልበትና ከካፒታል ጋር በማጣመር የተፈጠረ የማይንቀሳቀስ ሀብት ''real property'' ከመፈጠር አንፃር የመሬት ባለቤትነት የመንግሥትና በሕዝብ መሆኑ እንቅፋት እንደማይሆን የሚያረጋግጥ ድንጋጌ ነው፡፡ ይህንንም በርካታ ፀሐፊዎች ''Real Property rights is a combination of interest in land and improvement there to" በማለት በርካታ ጸሐፊዎች ይገልጻሉ፡፡ በገጠር አርሶ አደሩ የመኖሪያ ቤት የሚሠራበት የተለየ ቦታ / የጓሮ ቦታ/ ወይም ጎጆ መውጫ ቦታ በማለት የሚከለልና የሚሰጥ ሲሆን በከተማም ከከተማው ካለው ካርታና ኘላን በመነሳት ለግለሰብ መኖሪያ ቤት፣ ለቢሮ፣ ለንግድና ሪልስቴት ኢንቨስትመንት የሚሆኑ መሬቶች ይከለላሉ፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ኢትየጵያዊ የተፈጥሮ ወይም ሕገ ወለድ ሰው በሕጋዊ መንገድ በተፈቀደለት ቦታ ላይ በገነባው ቋሚ ንብረት ወይም በመሬቱ ላይ ላደረገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት ያለው መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የንብረቱ ባለቤትነት መብቱ ምን ምን ሁኔታዎችን እንደሚያጠቃልል በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 6 ተደንግጓል፡፡

ከዚህ አንፃር በመሬታቸው ላይ ላደረጉት የመሻሻልና በገጠርና በከተማ በሕጋዊ መንግድ በመሬት ላይ የተፈሩ ቋሚ ንብረቶችና የተደረጉ ቋሚ መሻሻሎች ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት ሕገ መንግሥታዊ ጥበቃና እውቅና የተሰጠው መሆኑን መገንዘብና መብቱን ማክበርና ማስከበር ያስፈልጋል፡፡

## <u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 የመጨረሻው ፖራግራፍ እና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 6 መካከል ልዩነት አለ ብለው ያስባሉ? ለምን?

2. በህገ ወጥ መንገድ በእርሻ መሬት ላይ የመኖሪያ ቤት የገነባ አርሶ አደር ወይም ከመንግሥት በሊዝ ሳይከራይ ወይም በነፃ ቦታውን በይዞታ እንዲይዝ ሳይፈቀድለት ለከተማነት ከተከለለ ክልል ውስጥ ይኖሩ ከነበሩ አርሶ አደሮች መሬት ገዝቶ ቤት የገነባ ሰው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 6 የተደነገገው መብት አለው ብለው ያስባሉ? ለምን?
3. በሕገ መንግሥቱ በመሬት ላይ የተደረገ "ቋሚ መሻሻል" የሚለው በመሬት ላይ የተተከሉ ረዥም ዓመት የሚቆዩ እንደ ወይራ፣ ማንጎ፣ ብርቱካን ቡና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል? ለምን?

## <u>3.5</u> መንግሥት የግል ንብረት ለሕዝብ ጥቅም ስለሚወሰድበት ሁኔታ

የግል ባለቤትነት መብት ሕገ መንግሥታዊ እውቅና እና ጥበቃ ተሰጥቶታል፡፡ ሆኖም ይኸ መብት ምንም ዓይነት ገደብ የማይደረግበት ፍፁም መብት አይደለም ሕገ መንግሥቱ መንግሥት የአንድን የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ ሰው ንብረት የሚወሰድበት /ቴኪንግ ክሎዝ/ ያካተተ ነው፡፡ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 8 መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን የያዘ ነው፡፡ የመጀመሪያው መንግሥት የአንድን ግለሰብ ንብረት ለሌላ ግለሰብ ጥቅም እና የሌላ ግለሰብ ፍላጐት ለማሟላት ለመውሰድ የማይችል መሆኑ ነው፡፡ መንግሥት የአንድን ግለሰብ ንብረት የሚወስደው ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ነው፡፡ "የሕዝብ ጥቅም" ከማይንቀሳቀስ ንብረት አንጻር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ሕዝቦች በመሬት ላይ ያላቸውን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥና ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ልማትን በቀጣይነት ለማጎልበት አግባብ ያለው አካል ለከተማ መዋቅራዊ ኘላን ወይም በልማት እቅድ መሠረት የሕዝብ ጥቅም ነው ብሎ የሚወስነው መሆኑ በሕግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

ሁለተኛው መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም የአንድ ሰው ንብረት ሲወስድ ተመጣጣኝ ካሣ መክፈል ያለበት መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በፌዴራልና በአዲስ አበባ አስተዳደር አንድ ቤት ወይም ቋሚ ንብረት አካባቢው ለሕዝብ ጥቅም ሲፈለግ ካሣ የሚከፈልበት

አዋጅና ደንብ፣ ያወጣ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የፌዴራል መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትና ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 455/1997 ደንግጓል፡፡ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚችል ደንብ አውጥቷል፡፡

- የካሣ አከፋፈሉም በመሬቱ ላይ የሚገኘውን ንብረት እና በመሬቱ ላይ ላደረገው ቋሚ መሻሻል፣
- አርሶ አደሩ ከመሬቱ በመፈናቀሉ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት ለማካካስ የሚችል የመፈናቀያ ካሣ ክፍያ፣
- የከተማ ነዋሪ ከሆነ መጠኑ በከተማው አስተዳደር የሚወሰን የቤት መምሪያ ምትክ ቦታ እና የንብረቱን ግምት ጋር የሚሰጠው መሆኑንና
- የሊዝ ዘመኑ ከማለቁ በፊት መሬቱ ሲለቀቅ ለቀሪው የሊዝ ዘመን የሚጠቀምበት ተመጣጣኝ ምትክ ቦታ እንደሚሰጠው በአዋጅ ቁጥር 455/97 ከአንቀፅ 7 እስከ አንቀፅ 8 ያሉትን ድንጋጌዎች በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ህገ መንግስቱ የፌደራልም ሆነ የክልል መንግስት የግል ንብረት የባለቤትነት መብት ጣልቃ መግባት የሚችሉት “ለህዝብ ጥቅም” አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት ብቻ መሆኑንና ይህንንም ሲያደርጉ ለንብረቱ ተመጣጣኝ ካሣ የመክፈል ኃላፊነትና ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ይደነግጋል፡፡ “የህዝብ ጥቅም” መስፈርት ህገ መንግስቱ ጥበቃና ዋስትና ከሰጠው ከግል ንብረት ባለቤትነት መብት ጋር መመዛዘን አለበት፡፡ ከዚህ አንፃር በጥንቃቄ መታየትና መመርመር ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ መንግስት ቋሚ ንብረቶችን ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚወስድበት እና ይዞታ የሚያስለቅቅበት ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 455/97 ትርጉም የሰጠበት ሲሆን በትርጉሙ ውስጥ-

- ይዞታውና ንብረቱ መለቀቁ ለቀጥታ ህዝቦች በመሬት ላይ ያላቸውን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ሲሆን ወይም
- ይዞታውና ንብረቱ መለቀቁ በተዘዋዋሪ መንገድ ህዝቦች በመሬት ላይ ያላቸውን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ሲሆንና
- ይዞታውና ንብረቱ መለቀቁ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ልማትን በቀጣይነት የሚያጎለብት አግባብ ባለው አካል በዕቅድና በፕላን ተደግፎ የፀደቀ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 5 ይደነግጋል፡፡

ስለዚህ ንብረቱ አስቀድሞ በተዘጋጀው ዕቅድና ፕላን መሠረት ለህዝብ ጠቃሚ ናቸው ተብለው የተያዙ ሥራዎችን ለመሥራት አስፈላጊ መሆኑን ማረጋገጥ የሚጠይቅ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የአንድን ሰው ንብረት ማለት ቤት ጎረቤቱ የተሻለና ያማረ ቤት ለመስራት ስለጠየቀ ብቻ መንግስት ንብረቱን ለመውሰድ አይችልም፡፡ መንግስት የአንድን ሰው የባለቤትነት መብት ጣልቃ የሚገባው የንብረቱ መወሰድ የከተማውን ወይም የአካባቢውን ማህበራዊና ኢኮኖሚ ልማት ለማረጋገጥ የተያዘው ዕቅድና ፕሮግራም ለማስፈፀም ምቹ ሁኔታን የሚፈጥርና የህዝብ ጥቅም ለማረጋገጥ የሚቻል መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መሆን እንደሚገባው የህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 8 ድንጋጌ ለማስፈፀም ከወጣው አዋጅ ቁጥር 455/97 የሚደነግጉ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## የመወያያ ጥያቄ

1. ለንብረቱ የሚከፈለው ካሣ ተመጣጣኝ ካሣ ማለት ምን ማለት ነው፡፡
2. በክልላችሁ የክልሉ መንግስት አንድን ቦታና ቤት ለልማት ሥራ ሲወስድ ካሣ ለመክፈል የሚያስችለው ክልላዊ የህግ ማዕቀፍ አለን?
3. በአካባቢያችሁ በመንግስት ለተወሰደ ንብረት ካሣ በአይነትና በገንዘብ የሚከፈልበትን ሁኔታ የሚደነግግ የክልል ህግ ወይም የከተማ አስተዳደር ደንብ አለን?
4. ምትክ የእርሻ ቦታ ወይም ምትክ የቤት መስሪያ ቦታ የማግኘት መብት ህገ መንግስታዊ ዋስትና እና ጥበቃ ተሰጥቶታል ብለው ያስባሉ? ለምን?
5. ህገ መንግስቱ ለንብረት ባለቤትነት መብት ብቻ ሣይሆን ለመሬት ባለይዞታነትና መሬትን የመጠቀም መብት ዕውቅና እና ጥበቃ ሰጥቷል ብለው ያስባሉ? ለምን?

## ማጠቃለያ

ህገ መንግስቱ ለግል ንብረት ባለቤትነት መብት እና መሬት ባለይዞታና የመሬት ተጠቃሚ የመሆን መብት ህገ መንግስታዊ ዕውቅና ጥበቃ የሚሰጡ ድንጋጌዎችን ያካተተ መሆኑን የህገ መንግስቱን አንቀፅ 40 ድንጋጌዎች በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ የፍትህ አካላት በፍትሐብሔር ህጉ ስለ ይዞታ፣ ስለ አላባ ጥቅም፣ ስለ መያዣ እና ስለ ንብረት ባለቤትነት የተደነገጉ ድንጋጌዎች ሌሎች የህግ ማዕቀፎች ከዚህ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችና ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 37 ከተደነገገው ፍትህ የማግኘት መብት ጋር ባገናዘበ መንገድ መተርጎምና ሥራ ላይ በማዋል በህገ መንግስቱ አንቀፅ 13/1/ የተደነገገውን የንብረት ባለቤትነት መብት የማክበርና የማስከበር ግዴታቸውን መወጣት

አለባቸው፡፡ ከዚህ አንፃር የንብረት ባለቤትነት እና የመሬት ይዞታና ተጠቃሚነት መብት ጋር ተያያዥነት ያላቸው በርካታ ጉዳዮች እንደየባህሪያቸውና ህገ መንግስቱን ግብና ዓላማ ሊያሣካ በሚችል መንገድ እልባት በመስጠት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት ለማስመስዝገብ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለውን ለግል ንብረት ባለቤትነት መብት ተገቢውን ጥበቃ መስጠት እና የሚፈጠሩ ችግሮችን በተፋጠነ ሁኔታ መፍታት ይጠበቅብናል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## በውርስ ህግ የህገመንግስቱ መሰረታዊ መርሆዎች

### 4.1 ንብረትን የማውረስ መብት በጠቅላላው

የሰው ልጅ ንብረቱን የማውረስ መብት የህግ ጥበቃና ዋስትና ከተሰጠው ረዥም ዘመን ተቆጥሯል፡፡ ሆኖም ንብረቱን በውርስ የማስተላለፍ መብት ዋስትና ጥበቃ ያገኘው በህገ መንግስት ነው ወይስ ከሌሎች ህጎች የሚለው ነጥብ በሌሎች አገሮች አከራካሪ ነጥብና ዳኞችም የሚለያዩበት ጉዳይ ነው፡፡

በኢፌዲሪ ህገ መንግስት በአገራችን ይኸ አከራካሪ ነጥብ ሊሆን በማይችልበት ሁኔታ ግልፅ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 7 የንብረት ባለቤት የሆነ ሰው ንብረቱን የመሸጥ የማውረስ የመሸጥ የመለወጥና በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብት ያለው መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ህገ መንግስቱ ለንብረት ባለቤትነት መብት ዕውቅና እና ጥበቃ የሰጠው የንብረቱ ባለቤት በህይወት ዘመኑ ባለበት ጊዜ እንዲሸጥ እንዲለወጥና ለሦስተኛ ወገን እንዲያስተላለፍ ብቻ ሣይሆን ባለቤቱ በሞት በሚለይበት ጊዜ በመውረስ ለማስተላለፍ ያለውን መብት ጭምር ነው፡፡

በህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀፅ 7 የተረጋገጠው የማውረስ መብት እንዴት ይተረጎማል የሚለው መታየት አለበት፡፡ በአገራችን የህግ ሥርዓት የሚች ውርስ

- ሙሉ በሙሉ ያለ ኑዛዜ
- ሙሉ በሙሉ በኑዛዜ
- በከፊል በኑዛዜና በከፊል ያለ ኑዛዜ

ሊደረግ የሚችል መሆኑ በፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 829 በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ በህገ መንግስቱ ዕውቅና እና ጥበቃ የተሰጠው በሦስቱ የአወራረስ ሥርዓቶች የትኛው ነው? የሚለው ህገ መንግስቱን ዓላማና ግብ መሠረት በማድረግ መተርጎምና የባለቤትነት መብት በማያጣብብ መንገድ ሥራ ላይ ማዋል ይገባል፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄ</u>

አንድ ሰው እሱ ከሞተ በኃላ ስለ ንብረቱ ሁኔታ የመወሰን ተፈጥሯዊና ህግ መንግስታዊ መብት አለው ብለው ያስባሉ? ለምን?

<u>የአወራረስ ሥርዓት በኢትዮጵያና ህገ መንግስት፣</u>

የውርስ ህግ አመጣጥና እድገት ከግል ንብረት አመጣጥና እድገት ጋር የጠበቀ ግኑኝነት እንዳለው ከላይ ተገልፆል፡፡ ከዚህ መሠረታዊ ነጥብ ተነስተን በኢትዮጵያ የነበረውንና አሁን ያለውን የአወራረስ ሥርዓት ስንመረምር፣ በፊትም ጊዜ ሆነ አሁን፣ አገሪቱ አንድ የወጥ የሆነ የአወራረሥ ሥርዓት የውርስ ደንቦች የሌሏት መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያ የተለያዩ ማህበረሰቦች ባህልና ልማዳዊ ደንቦች፣ የተለያዩ ሀይማኖቶች የአወራረስ ደንቦችና በዘመናዊ መልክ የተቀረፀ የፍትሐብሔር ህግ የውርስ ደንቦች ጎን በጎን ተፈፃሚ ለማድረግ የተለያዩና በርካታ የውርስ አወራረስ ሥርዓቶች በልምድና በህግ ዕውቅና የሰጠች አገር ናት፡፡

ህገ መንግስቱ የአገሪቱ ያወራረስ ሥርዓት በመወሰን ረገድ ያሣደረውን አስተዋፅኦ ለመረዳት በኢትዮጵያ ሲሠራባቸው የኖሩና እየተሠራባቸው ያሉ የሟች ውርስ አወራረስ ደንቦች በሶስት የተለያዩ ታሪካዊ ወቅቶች አንፃር መመርመር ያስፈልጋል፡፡ እነርሱም፣

- 1952 የፍትሐብሔር ህጉ ከመውጣቱ በፊት የሟች ውርስ የአወራረስ ሥርዓት ላይ ተፈፃሚነት የነበራቸው የውርስ ደንቦች፣
- 1952 ዓ.ም የፍትሐብሔር ህጉ ከወጣ በኃላ እስከ ነሐሴ1987 ተፈፃሚነት የነበራቸው የውርስ አወራረስ ደንቦችና
- ከነሐሴ ወር 1987 ዓ.ም በኃላ በአገሪቱ እየተሠራባቸው ያሉ የአወራረስ ሥርዓቶች ናቸው፡፡

ሀ. 1952 በፊት የነበሩ ያወራረስ ሥርዓቶች፣

1952 ዓ.ም የፍትሐብሔር ህጉ ከመውጣቱ በፊት በአገሪቱ፣ የሚች ውርስ የሚኖሩበትን ማህበረሰብ ልምድና ባህላዊ ደንቦች፣ የክርስትና ሀይማኖት ተፅዕኖ ያለበትን የፍትሐነገስት ድንጋጌዎች እና የሼሪዓ ህግን መሠረት በማድረግ የሚፈፀሙ፣ የተለያየ ይዘት ባህሪና ውጤት የነበራቸው የውርስ አወራረስ ሥርዓቶች እንደነበሩ በዚህ መስክ የተጠኑ ጥናቶች ያሣያሉ፡፡ ስለዚህ የፍትሐብሔር ህጉ ፀድቆ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ባህላዊና ልማዳዊ የአወራረስ ደንቦች፣ የፍትሐነገስቱ የአወራረስ ደንቦች እና የሼሪዓ የአወራረስ ደንቦች ጎንበጎን ይሠራባቸውና ህጋዊ ውጤትም የነበራቸው መሆኑን እንረዳለን፡፡

## ለ. የፍትሐብሄር ህጉ ከታወጀ በኋላ የነበሩ የአወራረስ ሥርዓቶች፣

ህግ አውጭው የፍትሐብሔር ህጉን ሲያውጅ፣ በአገሪቱ አንድና ወጥ የሆነ የአወራረስ ሥርዓትና የውርስ ህግ እንዲኖር በማሰብ ስለውርስ ዝርዝር ድንጋጌዎችን አውጇል፡፡ ህግ አውጪም በአገሪቱ ያሉ የውርስ አወራረስ ሥርዓቶች በፍትሐብሔር ህጉ የውርስ ድንጋጌዎች ብቻ የማስፈፀም ፍላጎት የነበረው መሆኑን፣ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3347 አንቀፅ 1 "ግልፅ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር በዚህ በፍትሐብሔር ህግ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮች ከዚህ በፊት በልምድ ወይም ተፅፈው ይሠራባቸው የነበሩ ደንቦች ሁሉ በፍትሐብሔር ህግ ስለተተካ ተሽረዋል" በማለት በግልፅ በማስቀመጥ፣ የውርስ አወራረስ አስመልክቶ ሲሠራባቸው የነበሩ፣ ልማዳዊ ደንቦች ሀይማኖታዊ ህግጋትና የተሻሩና በፍትሐብሔር ህጉ የተተኩ መሆኑን አውጇል፡፡ በወቅቱ የነበረው ህግ አውጭ አንድ ወጥነትና ተፈፃሚነት ያለው አንድ የውርስ ህግ እንዲኖር በማሰብ አንድ የአወራረስ ሥርዓት ለማስፈን የሞከረ ቢሆንም ይህንን ህግ ተግባራዊ ለማድረግ አልቻለም፡፡

ምክንያቱም የፍትሐብሔር ህጉ የውርስ ህግ ድንጋጌዎች በሁሉም ማህበረሰብ ተቀባይነት አለማግኘታቸውና የተለያዩ ማህበረሰቦች የፍትሐብሔር ህጉ ከመጣ በኃላ ባህላቸውንና ልማዳዊ የአወራረስ ደንቦቻቸውን መሠረት በማድረግ የሚችን የአወራረስ ሥርዓት ተፈፃሚ ማድረግ መቀጠላቸው መንግስቱም የፍትሐብሔር ህጉን ከዳር እስከዳር ተፈፃሚ ለማድረግ አቅም ያልነበረው በመሆኑና በአዋጅ ቁጥር 62/1936 የተቋቋሙት የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ሙስሊሙ ህብረተሰብ ባቀረበው አቤቱታ መሠረት የፍትሐብሔር ህጉ ፀድቆ ሥራ ላይ ከዋለ በኃላ በሸሪዓ መሠረት የሙስሊሙን

ህብረተሰብ የጋብቻ፣ የልጆች አስተዳደግ፣ የዋቅፍ ስጦታና የውርስ ጉዳይ ዳኝነት ማየታቸውን እንዲቀጥሉ በፍትህ ሚኒስትር በተፃፈ ደብዳቤ መሠረት ሥራቸውን ያለማቋረጥ መቀጠላቸውን ስናይ ህግ አውጭው አንድ ወጥ የውርስ አወራረስ ሥርዓት ለመዘርጋት በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3347 ንዑስ አንቀፅ 1 ያወጀው ግልፅ ድንጋጌ፣ በአገሪቱ ያወራረስ ሥርዓት ምንም አይነት ተግባራዊ ለውጥ ያላስከተለ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም 1952 ዓ.ም የኢ.ፌ.ድ.ሪ. ህገ መንግስት ሥራ ላይ እስከ ዋለበት ነሐሴ 1987 ዓ.ም ድረስ፣ በኢትዮጵያ የሚች የውርስ አወራረስ ሥርዓት እንደየሁኔታው ውርስ ልማዳዊ የውርስ ደንቦችን፣ የሸሪዓ የውርስ ደንቦችንና የፍትሐብሔር ህጉ የውርስ ድንጎጌዎች መሠረት በማድረግ ሲፈፀም የቆየ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

ስለዚህ ሁለተኛው የኢትዮጵያ የአወራረስ ሥርዓት ዘመን መንግስት በግልፅ ድንጋጌ በፍትሐብሔር ህጉ የውርስ ህግ ደንቦች ውጭ ያሉትን ልማዳዊና ሀይማኖታዊ የአወራረስ ደንቦች የሻረበትና ህጋዊ ዕውቅና የነሣበት በተግባር ግን የሚች ውርስ ባህላዊና ልማዳዊ ደንቦች በሸሪዓ እና የፍትሐብሔር ህጉ የውርስ ህግ ድንጋጌዎች ሲፈፀም የኖረበት የእድገት ደርጃ እንደሆነ ለማየት ይቻላል፡፡ ይኸ ዘመን ህግ አውጭው በመርህ ደረጃ ያወጀው ድንጋጌ በወረቀት ላይ ንድፍ ሀሳብ ብቻ ሆኖ የቀረበት ህብረተሰቡ ደግሞ ልማዳዊና ሀይማኖታዊ የአወራረስ ደንቦችን ተግባራዊ በማድረግ የህግ አውጭውን አንድና ወጥ የሆነ የአወራረስ ሥርዓት የመዘርጋት ፍላጎት ማህበራዊ ተቀባይነትና ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን በተግባር ያሣየበት ዘመን ነው፡፡

### ሐ. የአወራረሥ ሥርዓት በኢፌዲሪ ህገ መንግስት

ስለ ኢትዮጵያ የአወራረስ ስርዓት ስናነሳ በሶስተኛ ደረጃ የሚታየው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ፀድቆ ስራ ላይ ከዋለ በኂላ ያለው የአወራረስ ስርዓት ነው፡፡ ህገ መንግስቱ የግል መብቶችን በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮች በተከራካሪዎቹ ፈቃድ በባህላዊ ወይም ኃይማኖታዊ ፍርድ ቤት የመዳኘት መብትን በአንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5 ደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤትና የክልል ምክርቤት ለህገመንግስቱ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የሀይማኖት እና የባህል ፍርድቤቶችን ሊያቋቁሙ ወይም ዕውቅና ሊሰጡ እንደሚችሉ ከመደንገጉም በላይ ህገመንግስቱ ከመጽደቁ በፊት ዕውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ

የኃይማኖትና የባህል ፍርድ ቤቶች በህገመንግስቱ መሰረት ዕውቅና አግኝተው የሚደራጅ መሆኑን በአንቀጽ 78 ንዑስ አንቀጽ 5 በግልጽ ደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት የፌዴራል ሼሪዓ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 188/1992 መሠረት ተጠናክሮ ስራውን የቀጠለ ሲሆን ክልሎችን የክልል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን የማጠናከሪያ አዋጆችን በማወጅ ስራቸውን እንዲቀጥሉ አድርገዋል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመዝነው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ፀድቆ ሥራ ላይ ከዋለበት ነሐሴ 1 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ባህላዊና ልማዳዊ የአወራረስ ደንቦች፣ ሀይማኖታዊ የአወራረስ ደንቦች ህገ መንግስታዊ ዕውቅናና ጥበቃ አግኝተው ከፍታብሔር ህጉ የውርስ ህግ ድንጋጌዎች ጉንበጉን እየተተገበሩ ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ አሁን ያለው የአወራረስ ስርዓቶች ስንመለከት ሁለት መሠረታዊ እና ልዩ ባህሪያት ያሉት ነው፡፡ የመጀመሪያው በእኩል ደረጃ ህገመንግስታዊ ዕውቅናና ጥበቃ በተሰጣቸው

- ❖ ባሕላዊና ልማዳዊ የውርስ አወራረስ ደንቦች
- ❖ ሀይማኖታዊ የውርስ አወራረስ ደንቦችና
- ❖ በፍታብሔር ህጉ የውርስ ድንጋጌዎች መሠረት የሚፈፀሙ

የኢፌዲሪ ህገ መንግስት የወሰዳቸውን መሠረታዊ ዕርምጃዎች ስንመለከት የመጀመሪያው የተለያዩ አይነት ባህሪ እና ውጤት ያላቸው የአወራረስ ሥርአቶች በአገሪቱ ውስጥ ተግባራዊ እየሆኑ መሆናቸው ሲሆን፣ ሁለተኛው በሟች የውርስ አወራረስ ሒደት ሥርዓት ሲፈፀም የሚነሱ ክርክሮች ተፈፃሚነት ያላቸውን የአወራረስ ደንቦች የመምረጥ መብት ሙሉ በሙሉ የተከራካሪዎች መሆኑ ነው፡፡ እዚህ ላይ መታየት ያለበት ከተከራካሪዎቹ አንደኛው በልማዳዊ ወይም ሀይማኖታዊ የአወራረስ ደንቦች መሰረት ለመዳኘት ፈቃደኛ ካልሆነ ጉዳዩ በፍታብሔር ህጉ የውርስ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት የሚፈፀም መሆኑን ነው፡፡ ዜጐች የፍታብሔር ህጉን የውርስ ደንቦች ተፈፃሚነት የሚያስቀሩት ጉዳዩ በባህላዊ ወይም ኃይማኖታዊ የአወራረስ ደንብ እንዲፈፀም ሙሉ በሙሉ ሲስማሙና ፈቃደኛ ሲሆኑ ብቻ ነው፡፡

### 4.2.1 የተለያየ አይነትና የውርስ አወራረስ ደንቦች መኖራቸው ያለው ጠንካራና ደካማ ጐን

ከላይ እንደተገለፀው በአገሪቱ አንድ ወጥ የሆነ የአወራረስ ሥርዓት ኖሮ የማያውቅ ሲሆን አንድና ወጥነት ያለው የአወራረስ ሥርዓት ለመዘርጋት የተደረገው ሙከራም ተግባራዊ ውጤት አላስገኘም፡፡ ይህም በመሆኑና ህገመንግስቱ ባህልን፣ ሃይማኖትን መሰረት ለሚያደርጉ የአወራረስ ደንቦች ዕውቅናና ጥበቃ ሰጥቷል፡፡ ይህም ዜጐች በፈቃዳቸውና በፍላጎታቸው የህብረተሰባቸው ባህላዊ የውርስ ደንቦች ወይም ኃይማኖታዊ የውርስ ድንጋጌዎች መሰረት የሚች ውርስ የሚያስፈፅሙበት እድል የሚሰጥ በመሆኑ፣ ዜጐች የግል ጉዳያቸው በመረጡት መንገድ የመጠየቅና የመዳኘት መብታቸውን ያረጋግጣል፡፡ ይኸ ሊመሰገን የሚገባው የህገ መንግስቱ ጠንካራ ጎን እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ከአንድ በላይ የሆኑ የውርስ አወራረስ ስርዓቶች በአንዲት አገር ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ሲሞከር የአንዱ የአወራረስ ሥርዓት ደንቦች ከሌላው የሚለያዩበት ሰፊ ሁኔታ ስለሚኖርና ከሚች ወራሾች መካከል የተወሰኑትን በአንደኛው የአወራረስ ስርዓት ሌሎቹ ደግሞ በሌላ የአወራረስ ሥርዓት መሰረት የሚች ውርስ እንዲፈፀም ለማድረግ የየበኩላቸውን ጥያቄ ስለሚያቀርቡና በሌሎች ምክንያቶች የሚፈጠረው የተለያዩ የውርስ ደንቦችና የአፈፃፀም ግጭት ምክንያት የሚፈጠሩ ችግሮች አሉ፡፡ በኢትዮጵያ ተፈፃሚነት ያላቸው ባህላዊ የአወራረስ ሥርዓቶች ብዛታቸውን፣ ይዘታቸውን ለመለየት የሚያስችል ወጥ ጥናት ባለመደረጉ በእርግጠኝነት ብዛታቸውን፣ ይዘታቸውንና የአፈፃፀም ሒደታቸውን ከሌሎች ኃይማኖታዊና የፍታብሔር ህግ የውርስ ድንጋጌዎች ጋር በማነፃፀር ለመግለጽ አይቻልም፡፡ ሆኖም የተለያዩ የብሔር ብሔረሰቦች ጎሳዎችና ማህበረሰቦች የየራሳቸው ባህላዊ የውርስ አወራረስ ደንቦች እንዳላቸውና እነዚህም በይዘትም ሆነ በአፈፃፀም የተለያየ ይዘትና ባህሪ እንዳላቸው በተለያየ ጊዜ ከተደረጉ አጫጭር የዳሰሳ ጥናቶች ለመረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም በኢትዮጵያ ተግባራዊ እየሆኑ ባሉ የባህል አወራረስ ደንቦች መካከል ያለው ልዩነትና አንድነት እንደዚሁም እያንዳንዱ ባህላዊ የውርስ አወራረስ ሥርዓት እየተሰራባቸው ካሉት የፍትሐብሔር ህጉ እና የሸሪዓ የውርስ ድንጋጌዎች ያላቸውን አንድነት እና ልዩነት በንጽጽር ለማቅረብ አይቻልም፡፡ በአንጻሩ ጉን በጎን የሚተረጉሟቸው እና የሚያስፈጽሟቸው ፍርድ ቤቶች ተቋቁመው እየተሰራባቸው ባሉት የፍትሐብሔር ሕግ የውርስ ደንቦችና በሸሪዓ የውርስ ደንቦች መካከል ያለውን

መሰረታዊ የይዘት ልዩነትም በአፈፃፀም ሒደት እየተከሰቱ ያሉ መሠረታዊ ችግሮች ማየት በአገራችን የተለያዩ ባህላዊ ኃይማኖታዊና የፍትሐብሔር ህግ የተደነገገውን የአወራረስ ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ ሒደት ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚገቡ መሰረታዊ ጉዳዮች ለመረዳት ጠቀሜታ ስለሚኖረው በአጭሩ ማየት ይጠይቃል፡፡

**የሸሪዓና የፍትሐብሔር የውርስ ደንቦች መካከል የሚታየው መሠረታዊ ልዩነትና በአፈፃፀም የሚታዩ ችግሮች**

**ሀ) በሸሪዓና በፍትሐብሔር ህጉ መሰረታዊ የፖሊሲ ሐሳብ ልዩነቶች**

የሸሪዓም ሆነ የፍትሐብሔር ህጉ የውርስ ደንቦች መሰረታዊ ግብ የሟችን ውርስ ለወራሾቹ ማስተላለፍ ቢሆኑም በይዘታቸው አንዳንድ መሰረታዊ ልዩነቶች አሏቸው፡፡ ይህም ልዩነት ሁለቱ ህግጋት መካከል የተካተቱ የፖሊሲ ሀሳብ ልዩነት ነፀብራቅ ነው፡፡ ከልዩነቶቹ ጥቂቶቹን ስንመለከት፣

- የፍትሐብሔር ሕጉ የሟች ወራሾች ከሟች በሀይማኖትና በእምነት መለየታቸው የወራሽነት መብታቸውን አያሳጣቸውም፡፡ በሌላ በኩል ሟች ሙስሊም ከሆነ የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ያልሆኑ ወራሻቹ በሟች ውርስ እንዳይሳተፉ የሸሪዓ የውርስ ደንቦች ይከለክላሉ፡፡
- የፍትሐብሔር ህጉ የሟች ሴትና ወንድ ወራሾች በጾታቸው ምክንያት የተለያየ ድርሻ እንዲወስዱ አያስገድድም፡፡ በእኩል የዝምድና ደረጃ እስካላቸው ድረስ እኩል ድርሻ ያገኛሉ፡፡ በሸሪዓ የሟች ሴት ልጆች ከሟች ውርስ አንድ ሶስተኛ የሚሰጣቸው ሲሆን ወንዶች ሁለት ሶስተኛ ይወስዳሉ፡፡
- በሸሪዓ ሚስት ባሏን የመውረስ መብት ያላትና ከባሏ ውርስ አንድ ስምንተኛ የማግኘት መብት ያላት ሲሆን በፍትሐብሔር ህግ መሰረት ሚስት ባሏን የመውረስ መብት የላትም፡፡
- የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ህግ ሟች ከወራሾቹ አንዱን በኑዛዜ የመንቀል መብት ያለው መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን በሸሪዓ ሟች ወራሾቹን በኑዛዜ የመንቀል መብት የለውም፡፡
- በፍትሐብሔር ህጉ ሟች በኑዛዜ ንብረቱን ለሶስተኛ ወገን የማስተላለፍ መብት ያለው ሲሆን በሸሪዓ አንድ ሰው በኑዛዜ ሊያስተላልፍ የሚችለው የንብረቱን አንድ ሶስተኛ ብቻ ነው፡፡

### ለ) በአፈፃፀም የሚታዩ ችግሮች

በሁለቱ ህጐች መካከል ያሉት እነዚህ እና ሌሎች መሰረታዊ ልዩነቶች ሟች ሙስሊም በሆነ ጊዜና የሟች ወራሾች የሌላ ኃይማኖት ተከታይ ወይም ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ በሆኑ ጊዜ ወይም ሟች በጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታና ነጠላ የኑዛዜ ስጦታ ንብረቱን ባከፋፈለ ጊዜ በሸሪአ ተጠቃሚ የሚሆኑት ወራሾቹ በሸሪዓ መሠረት ውርሱ እንዲፈፀም ሌሎች ደግሞ በፍትሐብሔር ህጉ መሰረት ታይቶ እንዲወሰን በየበኩላቸው የወራሽነት ማረጋገጫ ለማግኘትና ውርሱን ለመካፈል ክስ የሚያቀርቡበትና የአንድ ሰው ውርስ ጎን በጎን በሁለት ፍርድ ቤቶች የሚታይበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀፅ 5 ይህንን ችግር ዘለቄታ መፍትሔ ለመስጠት ታስቦ የተደነገገ ሲሆን ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን ለማጠናከር አዋጅ ቁጥር 188/1992 ታውጇል፡፡ በተለያዩ ክልሎችም የክልል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ማጠናከሪያ አዋጆች ታውጀዋል፡፡ እነዚህ የህግ ማዕቀፎች ከመውጣታቸው በፊት የነበሩ በርካታ ችግሮችን ለመፍታት እንደሚረዱ የሚስተባበል ባይሆንም አሁንም ቢሆን፣

- በህግ ማዕቀፎቹ ድንጋጌዎች ግልፅ አለመሆንና በአንድ አንድ ጉዳዮች ክፍተት ያለባቸው በመሆኑ የተነሳና
- መደበኛው ፍርድ ቤት እና የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ህግን በመተርጎምና በማስፈፀም ሒደት የየራሳቸው ችግር ያለባቸው በመሆኑ

ሁለቱን የውርስ ህግጋት በማስፈፀም በኩል በርካታ ችግሮች እንደሚፈጠሩና ችግሮቹ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አልፈው የህገመንግስት አጣሪ ጉባኤና የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመነጋገሪያ አጀንዳ እየሆኑ መሆኑን አንዳንድ ጉዳዮችን አንስቶ ማየት ይቻላል፡፡

በዚህ በኩል በህግ አተረጓጎምና አፈፃፀም ያሉ ችግሮችን ለመረዳት

- በአንሻ መሐመድና ከድጃ በሽር
- በወ/ሮ ፈንታየ መሐመድና ወ/ሮ እናትነሽ ከተማ መካከል የተደረጉ ክርክሮችንና በየደረጃው የተሰጡ ውሳኔዎች መመርመሩ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

በአጠቃላይ በአገራችን እየተሰራባቸው ያሉ በርካታ ባህላዊና ኃይማኖታዊ የአወራረስ ሥርዓቶች ከፍትሐብሔር ህጉ የአወራረስ ደንቦች ጋር ጎን በጎን ሥራ ላይ በሚውሉበት ጊዜ የሚከሰቱትን ችግሮች መሰረታዊ ባህሪ፣ ችግሮቹ የሚፈቱበትን የህግ አግባብ በመረዳት ለተግባራዊ እንቅስቃሴ ዝግጁ ለመሆን ስልጠናዎች በአካባቢያችን ያሉትን ባህላዊ ኃይማኖታዊ የአወራረስ ሥርዓቶች መሰረታዊ ደንቦች እና የአፈፃፀም ሥርዓት ላይ ስልጣኖቹ በየአካባቢያቸው የዳሰሳ ጥናት በማድረግ በጥናቱ ግኝት ላይ የጋራ ውይይት እንዲያደርጉ ማድረግ የላቀ ጠቀሜታ ስላለው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነጥብ ነው፡፡

## <u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. የአንዲት አገር ፖሊሲና ስትራቴጂ በውርስ ህግ ውስጥ የሚካተትበትና የሚንፀባረቅበት አግባብ አለ ብለው ያስባሉ? እንዴት?
2. የውርስ ህግ አንድ ሰው በህይወት በነበረበት ጊዜ ያለው የንብረት ባለቤት የመሆን መብት ከሞት ከተለየም በኋላ ተፈፃሚነት የሚያደርግ ከንብረት ባለቤትነት መብት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ የህግ ክፍል እንደሆነ የሚገልፁ ጸሐፊዎች አሉ፡፡ የውርስ ህግ መሠረታዊ ግብና ዓላማ ምንድን ነው?
3. የሟች ውርስን በማስፈፀም በኩል በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ የተቋቋሙ መደበኛ ፍርድ ቤቶችና በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ላይ የተጣለ የህግ ገደብ አለ ብለው ያስባሉ? ለምን?
4. ባህላዊ የአወራረስ ደንቦች ኃይማኖታዊ የአወራረስ ደንቦች እና የፍትሐብሔር ህጉ የውርስ ደንቦች ጎን በጎን ሥራ ላይ መዋላቸው ምን አይነት ጠቀሜታ እና ጉዳት ይኖራቸዋል ብለው ያስባሉ? ያብራሩ፡፡
5. አንድ ሙስሊም ወንድ ከዚህ ዓለም በሞት ይለያል፡፡ የሟች ሚስት በሸሪዓ መሠረት ሟች ያገባት ህጋዊ ሚስት መሆኗን አጣርቶ ማስረጃ እንዲሰጣት በአካባቢዋ ላለው የናኢባ ፍርድ ማመልከቻ ታቀርባለች፡፡ ይህ ማለት የጋራ ንብረት አከፋፈል በሸሪዓ መጣራት እንዲከናወን በአዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ስምምነት ሰጥታለች ማለት ነውን? ለምን?
6. ወ/ሮ ከድጃ ዑመርና አቶ ሰማን አበጋዝ በሸሪዓ ሕግ መሠረት ተጋብተው ሃያ ዓመት ከኖሩ በኋላ ባልየው ከዚህ ዓመት በሞት ይለያል፡፡ በዚህ ወቅት ሴትዮዋ በሸሪዓ

መሠረት ከሟች ጋር ጋብቻ ፈጽማ የነበረች የሟች ሕጋዊ ሚስት መሆኗን ለማረጋገጥ ለሸሪዓ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርባ ሸሪዓ በሚፈቅደው መሠረት የተገባች የሟች ሚስት መሆኗን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ይሰጣታል፡፡ በሌላ የፌደራልና የክልሉ የቤተሠብ ሕግ ጋብቻ የሚቋረጥበት አንደኛው ምክንያት ከተጋቢዎቹ አንደኛው በሞት ሲለይ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ጋብቻው ሲፈርስ ደግሞ የጋራ ንብረታቸው እኩል ተከፍሎ የሟች ድርሻ ለወራሾቹ የሚስት ድርሻ ደግሞ ለራሷ እንደሚሆን የቤተሠብ ሕጉ ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡

ወ/ሮ ከድጃ ዑመር የሸሪዓ ፍርድ ቤት የሟች ሚስት ስለመሆኗ አረጋግጦ የሰጣትን ማስረጃ በማያያዝ የሟች ወራሾች ግማሽ ንብረቷን እንዲያካፍሏት የሥረ ስልጣን ላለው መደበኛ ፍርድ ቤት ክስ ስታቀርብ የሟች ወራሾች ሚስት ስለመሆኗ ማስረጃ እንዲሰጣት ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ያመለከተች ስለሆነ የንብረት ክፍያውም ጉዳይ መታየት ያለበት በመደበኛው ፍርድ ቤት ሣይሆን ጉዳዩን በመጀመሪያባየው የሸሪዓ ፍርድ ቤት በኩል መሆን አለበት በማለት ተቃወሙ፡፡ ይህንንም የሚሉት የንብረት ክፍያው በሸሪዓ ሕግና በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በኩል ቢታይ በሸሪዓው ሚስት ባሏን መውረስ ስለምትችል በሸሪዓ ሕግ መሠረት ከንብረቱ የምታገኘው አንድ አራተኛውን እንጅ ግማሹን ባለመሆኑ ነው፡፡

ሀ. እርሰዎ ጉዳዩን የያዙት ዳኛ ቢሆኑ

የንብረት ክፍፍሉን አስመልክቶ ወ/ሮ ከድጃ ዑመር የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 34/5/ እና የፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር በወጣው አዋጅ 188/1992 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘትና በሸሪዓ ሕግ መሠረት ጉዳዩ እንዲታይ ፈቃድ ሰጥታለች ብለው ጉዳዩን በሸሪዓ ፍርድ ቤት እንድታቀርብ ይወስናሉ? ለምን?

ለ. ወ/ሮ ከድጃ ዑመር የአቶ ዑስማን አበጋዝ ልጅ ብትሆንና የሟች ልጅና ወራሽ መሆኗን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሸሪዓ ፍርድ ቤት እንዲሰጣት አመልክታ የወራሽነት ማስረጃውን ከወሰደች በኋላ የውርስ ንብረት ክፍፍሉን በተመለከተ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ ባትሆንና የውርስ የንብረት ክፍፍሉ በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ መሠረት እንዲፈፀም ብትጠይቅ ጥያቄዋ ተቀባይነት ማግኘት አለበት ብለው ያስባሉ? ወራሽነትን እንዲያረጋግጥ ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ማመልከቻ ማቅረብ የውርስ ንብረት ክፍያ ስርዓቱን የሸሪዓ ፍርድ ቤት አይቶ እንዲወስን ፈቃደኝነትን መግለጽን ያሣያል ብለው ያስባሉ? ለምን?

# ክፍል አምስት

# በቤተሰብ ሕግ የህገ መንግስቱ መሰረታዊ መርሆዎች እና አቅጣጫዎች

## ጠቅላላ

የቤተሰብ ህግ በመሰረቱ የጋብቻ ምስረታን፣ ህጋዊ የጋብቻ ውጤትን የጋብቻ መፍረስን መለያየትን አባትነትን፣ጉድፈቻን የቤተሰብ መደጋገፍ ግዴታን እና የመሳሰሉ ጉዳዮችን የሚመለከት የህግ ክፍል ነው። ይህ በሰዎች መሀከል የደም ዝምድናን ወይም ጋብቻን መሠረት በማድረግ የሚፈጠር ትስስር በየትኛውም አለማችን በሚገኝ የህብረተሰብ ክፍል ውስጥ ይኖራል። በዚህ መልኩ የተሳሰረ ቡድን የህብረተሰቡ መሠረታዊ መነሻ ነው። ቤተሰብም ለአባሉ የተለየ ጥበቃ፣ ወዳጅነት እና ዋስትና (Security) የሚሰጥ ከመሆኑ በላይ ሰው ከህብረተሰቡ ጋር እንዴት ተቀላቅሎ መኖር እንዳለበት የሚማርበት (Socialization) ተቋም ነው። በተለያየ ቦታ የተለያየ ተግባር ቢኖረውም ለቤተሰብ ቤተሰባዊ የሆነ ፍቅር (emotional support) መስጠትና ልጅን ባግባቡ በማሳደግ ለጉልምስና ማብቃት የጋራ ኃላፊነቶች (ተግባራት) ተደርገው ይወሰዳል። ቤተሰብ ይህ አጠቃላይ ተግባር ይኑረውም እንጅ በቅርፁ ከቦታ ቦታ ይለያያል። አንዳንድ አካባቢ ቤተሰብ የሚባለው አባት፣ እናት እና ልጅን ብቻ (nuclear family) ሲሆን በሌላ ቦታ ደግሞ ከዚሁ በላይ ሌሎች እንደ አያት እና ዘመዶችን (extended family) ይጨመርበታል። በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ልጆች ከአንደኛው ወላጃቸው ጋር የሚኖሩበት ቤተሰብ (Single parent family) አለ። ይህም የፍቺ፣ ያለመጋባት፣ የመፋታት፣ አንደኛው ወላጅ በሞት የመለየት ውጤት ሊሆን ይችላል። ብቸኛው ወላጅ ሌላ ተቃራኒ ፆታ ያለው ሰው ሲያገባ የአንጀራ ልጅ ቤተሰብ (Step family) ልጅ አልባ ቤተሰብ (childrenss family) ወዘተ የቤተሰብ አይነቶች ናቸው።

ቀደም ሲል በነበረው ዘመን ቤተሰብ እጅግ ከመለጠጡ የተነሳ አሁን ኒዮክሌር ቤተሰብ የምንላቸው ሁለት እና ከሁለት በላይ ቤተሰቦች በአንድነት ይኖሩ ነበር። አላማው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማግኘት ነበር። ወንዶች በአደንና ፍራፍሬ ለቀማ ሴቶች ደግሞ በቤት ውስጥ ስራም ተወስነው የቆዩት ለዚሁ እንደነበረም ፀሐፊዎች ይገልፃሉ። በችግር ጊዜ የህፃናት ሞት (infanticide) መበርከት እና መስራት የማይችሉ ደካሞች (infirm)

ከቤት መባረራቸው የዚሁ ኢኮኖሚያዊ የስራ ክፍፍል ውጤት ነበር። ይህ ቤተሰብ አባታዊ (patriarchal) እንዲሆን ያደረገ ነው። የኋላ ኋላ የቤተሰብ ትስስር ኃይማኖታዊ እየሆነ የመጣ ሲሆን ከተሐድሶ ዘመን (16th Reformation) በኋላ ይህ ትስስር ቤተሰብ ከኃይማኖት ውጪ የሲቪል (የፍታብሔር) ጉዳይም ሆኗል። አሁን ያለንበት ዘመን የኢንዱስትሪ እና ከተሞች መስፋፋትን አልፎ ግሎባላይዜሽን (እንደ አንዳንዶች ደግሞ postglobalization) ላይ የደረሰ ሲሆን ቤተሰብን አስመልክቶ ካሉ ለውጦች ሁሉ የቤተሰብ አወቃቀር (በተለይ ኒዩክለር መሆኑ) እምብዛም የተለወጠ አይደለም። ትውልድን መተካት እና ለቤተሰብ አልባ በተለይ ህፃናት እና ታዳጊዎች ቤተሰባዊ ፍቅር (affection and emotional support) ሰጥቶ ማሳደግ አሁንም እምብዛም ያልተቀየረ የቤተሰብ ተግባር ነው። ባለንበት ዘመን ኢኮኖሚያዊ፣ ኃይማኖታዊ፣ ትምህርታዊ ተግባራት እና መሰል ተግባራት ከሞላ ጎደል በሌላ ተቋማት ሲሸፈሉ (ወይም ሲታገዙ) ይታያል። ይህ በቀድሞ ዘመን የቤተሰብ ብቸኛ ኃላፊነት ነበር።

በጥቅሉ አሁን ባለንበት ዘመን የቤተሰብ ህግ የምንለው የቤተሰብ አባላት (አባት፣ እናት፣ ልጅ፣ ...) መካከል ያለን መብት እና ግዴታ የሚመለከት ህግ ነው። ከፍ ሲል እንደተገለፀው ቤተሰብ ረዥም ታሪክ ያለው ሲሆን ህጉም በተመሳሳይ ረዥም ታሪክ ያለው ነው። ይሁን እንጅ በዚህ መልኩ ከመጣ ህግ ውስጥ የጋብቻ ምስረታን የተመለከተው ከሞላ ጎደል እምብዛም ለውጥ ያልተደረገበት ነው። በተቀረው የቤተሰብ ህግ ላይ ግን በበርካታ ሀገራት መሠረታዊ ለውጥ ተደርጎባቸዋል። ይህ ለውጥ በተለይ በ3ት ምክንያቶች የመጣ ሲሆን እነርሱም፡

1. ፍቺን ነፃ ማድረግ (liberalization of divorce)
2. በቤተሰብ ጉዳይ ላይ ውሣኔ በመስጠት እና ንብረት በሚመለከት፣
3. በማንኛቸውም ጉዳይ ላይ የወንዶች እና ሴቶች እኩልነት እንዲሁም፣
4. በጋብቻ እና ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልዶች መሀከል ያለውን የመብት ልዩነት በማስቀረት ማመሳሰል (assimilation) ’

ወደ ሀገራችን ህግ ስንመለስ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ 10 ስር ሰብአዊ መብቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ መሆናቸውን ይደነግጋል። የሰብዓዊ መብቶች ምንጭ ሰው መሆን እንጅ የግድ ወንድ ወይም ሴት መሆን አይደለም። በዚህ መሠረት ማንኛውም ሰው (ወይም ኢትዮጵያዊ) በህገ መንግስቱ የተቀመጡ መብቶችን በእኩልነት

የማግኘት መብት አለው፡፡ በዚህ መልኩ ከተቀመጡት መብቶች ውስጥ የጋብቻ የግል እና የቤተሰብ መብት አንዱ ነው (አንቀጽ 34) ይህ መብት የማግባት እና ቤተሰብ የመመስረት መብትን ያካትታል፡፡ በጋብቻ እና ቤተሰብ መብት ረገድ ህገ መንግስቱ ለእኩልነት የተለየ ትኩረት ይሰጣል፡፡ በአንቀጽ 25 ስር የፆታ ልዩነት ሳይደረግ ሰው የእኩልነት መብት የተጎናፀፈ መሆኑ ሲደነግግ በአንቀጽ 34/1/ ስር ደግሞ ወንድና ሴት በጋብቻ አፈፃፀም በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት እንዳላቸው ተደንግጓል፡፡ ለጉዳዩ የተለየ ትኩረት በመስጠትም አንቀጽ 35/2/ ስር ሴቶች በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት እንዳላቸው በአንቀጽ 35/1/ ስር ደግሞ በህገ መንግስቱ የተረጋገጡ መብቶችን በመጠቀም ረገድ ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል መብት እንዳላቸው ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ልዩ ትኩረት እንደሚሰጥ (አንቀጽ 35/2/) ንብረትን በማስተዳደር እኩል መብት እንዳላቸው /አንቀጽ 35/7/ በቅጥር እድገት አፈፃፀም እና በጡረታ መብት አፈፃፀም ረገድም እኩል መብት እንዳላቸው ደንግጓል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡን ባሳለፍናቸው ዘመናት ሴቶች በህብረተሰቡ ውስጥ በተለይ ጋብቻንና ቤተሰብን በተመለከተ ይደርስባቸው የነበረውን ስር የሰደደ እና ስርዓታዊ (systematic) የሆነ ባህላዊ እና ኃይማኖታዊ መገለል አጥብቆ ለማስቀረት ህገ መንግስቱ መፈለጉን ነው፡፡ በተለይ በተቀመጡት ጉዳዮች ላይ ሴቶች በህግ ጭምር በግልፅ ልዩነት የተደረገባቸው ነበሩ፡፡ የጡረታ መብት ማስተላለፍ ላይ የሴቶች መብት ተገደው መቆየቱ በምሳሌነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

<u>ህግ ማውጣት</u>

በመሠረቱ የቤተሰብ ህግን የማውጣት ስልጣን ለፌዴራል መንግስቱ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቀጥታ የተሰጠ ስልጣን አይደለም፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር በፌዴራል መንግስቱ ህግ እንዲወጣባቸው ያልወሰነባቸው የፍታብሄር (የቤተሰብ) ጉዳዮች በክልሎች ስልጣን ስር የሚያርፉ ናቸው፡፡ በዚህ መልኩ የፌዴሬሽን ም/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሌላ በመሆኑ ክልሎች የራሳቸውን ህግ እያወጡ ሲሆን የፌዴራል መንግስቱም በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ተፈፃሚ የሚሆን የቤተሰብ ህግ አውጥቷል፡፡

በዚህ መሠረት የፌዴራል መንግስቱ እና የተወሰኑ ክልሎች (ትግራይ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሐረሪ...) የቤተሰብ ህጋቸውን አውጥተዋል፡፡ የቤተሰብ ህግ ባላወጡ ክልሎች

ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የፍታብሔሩ የቤተሰብ ህግ የሲሆን አፈፃፀሙም ከፍ ሲል ከተመለከተው የህገ መንግስት መርህ ጋር እስካልተጋጨ ድረስ ነው፡፡ ስለሆነም በህገ መንግስቱ መሠረት መደበኛ የሆነ የህግ ብዝሀነት (formal legal pluralism) በስርዓታችን ውስጥ በግልፅ ይታያል ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል ከህገ መንግስቱ ጋር የማይጋጩ ባህሎች እኩል እንዲራመዱ እና እንዲጎለብቱ የማድረግ ኃላፊነት በመንግስት ላይ የተጣለ በመሆኑ እነዚህ ባህሎች የቤተሰብ ግንኙነትን በመምራት አንድ የኢኮኖሚ እና ፖለቲካዊ ህብረተሰብ ለመመስረት መሰረት ይሆናሉ፡፡ <u>የህገ መንግስቱ መግቢያ አንቀጽ 91 ለአብነት ይመልከቱ</u> በተከራካሪዎች ፈቃድ ባልና ሚስት በባህላቸው ወይም በኃይማኖታቸው ሊዳኙ ይችላሉ፡፡ ይህም በህገ መንግስቱ መደበኛ ያልሆነ የህገ ብዝሀነት (informal legal pluralism) በተመሳሳይ ተፈቅዷል ማለት ነው፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የቤተሰብ ህጉ በተለይ ሴቶችን ጨቋኝ በመሆኑ የሌሎች የፍታብሄር ህጎች ከመሻሻላቸው በፊት አስቀድሞ ተሻሽሏል፡፡ የፍታብሔር ህጉን ለረዥም ጊዜ ማስቀጠል ጭቆናው እንዲቀጥል ሆኖ ሴቶች እና ህፃናት ይበልጥ መጉዳት በመሆኑ ማዘግየቱ አልተመረጠም፡፡ ይህ በመሆኑም ከፍታብሔር ህጉ ተነጥሎ ዝርዝር በሆነ መልኩ የወጣም በመሆኑ በቤተሰብ ጉዳይ ላይ የተሟላ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡

በሌላ በኩል በቀድሞ ህግ ውስጥ የነበሩና ፋይዳ የሌላቸው የወንጀል ድንጋጌዎች ራሱን በቻለ በወንጀል ህግ ውስጥ መካተት ያለባቸው በመሆናቸው እንዲቀሩ ሆኗል፡፡ በአጠቃላይ በወጡ ህጎቹ ውስጥ ከህገ መንግስቱ መርሆዎች አንፃር የሚከተሉት ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡

ጋብቻ በተጋቢዎች ሙሉ እና ነፃ ፈቃድ ላይ መመስረት ያለበት በመሆኑ ይህንን የሚሸረሽር የመተጫጨት ድንጋጌ ቀሪ ሆኗል፡፡ አለዚያም ይህንን ሙሉ እና ነፃ ፈቃድ በማያስቀር መልኩ ተስተካክሎ ታውጇል፡፡ (ለምሳሌ የአማራ የቤተሰብ ህግ) የጋብቻ ፈቃድ ሙሉ እና ነፃ መሆን የሚችለው ከእድሜም አንፃር በመሆኑ ይኸው ፈቃድ በአግባቡ ይገለፅበታል (የጤንነት እና ህይወት ሁኔታንም ግምት ውስጥ በማስገባት) በሚባለው እድሜ ጋብቻ እንንዲፈፀም ህገ መንግስቱ ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሠረት ዝቅተኛ የጋብቻ እድሜ 18 እና ከዛ በላይ (ለምሳሌ ትግራይ ክልል 21 ነው) ሆኗል፡፡

የሴቷን እና የህፃናት መብትን ለማስከር ሲባል የቀድሞ ጋብቻ ከቀረ በኋላ አንድ ሴት 180 ቀን በብቸኝነት ለመኖር የምትገደድ ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ የሚገኝ ልጅ አባት በትክክል ከታወቀ ወይም በዚህ ጊዜ ውስጥ ፅንስ አለመኖር ከተረጋገጠ ጋብቻ ሊፈፀም ይችላል፡፡ ይህም ህፃናት በህገ መንግስቱ ላይ የተቀመጠውን ወላጅን የማግኘት መብት ትርጉም ባለው መልኩ እንዲፈፀም ያስችላል፡፡

በህገ መንግስቱ ላይ በግልፅ እንደተደነገገው ቤተሰብ የህብረተሰብ የተፈጥሮ መሠረታዊ መነሻ ነው፡፡ ቤተሰብ ለመመስረት ደግሞ ጋብቻ ያስፈልጋል፡፡ ቤተሰብ ህብረተሰቡ እና ከመንግስት ጥበቃ የማግኘት መብት ያለው በመሆኑ ጥበቃው የሚጀምረው ቤተሰብ ከመመስረቱ በፊት መሆኑ ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሠረት በዝርዝር በወጡ ህጎች ውስጥ ሰው ጋብቻ ለመፈፀም የማይገባበት ምክንያት ብለው እንዳግባቡ በመንግስት (በዐ/ህግ በኩል) ወይም ህብረተሰቡ ተቃውሞ ሊያቀርብ እና እንዳይመሰረት ማድረግ ይቻላል፡፡

ለቤተሰብ ጥበቃ የሚደረግበት ሌላው መንገድ ምዝገባ ነው፡፡ አለም አቀፍ ስምምነቶች (ምሣሌ በኢትዮጵያ የፀደቀው በሴቶች ላይ አድልዎ የማስቀረት የወጣው ስምምነት እና በሴቶች ላይ የሚፈፀም ጥቃትን ለማስወገድ የተፈረሙ ኮንቬንሽን) ጋብቻ እንዲመዘገብ ያስገድዳሉ፡፡ ይህ ምዝገባ በአንድ የመንግስት አካል ብቻ እንዲፈፀም ይጠበቃል፡፡ ምዝገባ በዚህ እና በውጤታማ የፍትህ አስተዳደር ጭምር አስፈላጊ በመሆኑ መዝጋቢው (የክብር መዝጋቢ ሹም) በራሱ አሳሽነት ጭምርም እንዲመዘገብ ይጠበቅበታል፡፡ ከጋብቻ በተጨማሪም የህፃናት መብት ኮንቬንሽንም (በሀገራችን የፀደቁ) ህፃናት እንዲመዘገቡ ያስገድዳል፡፡

በተጋቢዎች በጋብቻ ጊዜም ግንኙነታቸው በሙሉ ነፃነት እና ፈቃደኛነት ላይ መመስረት ያለበት በመሆኑ የሚፈፀሙት ውል ከጋብቻ ልዩ ግንኙነት የተነሳ ነፃነቱ እንዳይሸረሸር ተጨማሪ ጥበቃ ያስፈልጋል (ለምሳሌ በፍ/ቤት ማስፀደቅ) ውሉን ለማሻሻልም በተመሳሳይ የህገ መንግስቱ መርህ ይፈፀማል፡፡

በተጠቀሱት የእኩልነት መርሆዎች መነሻነትም በጋብቻ ጊዜ የአዛዥነት የወንድ የበላይነት የአለቅነት የበላይነት ግንኙነት አይኖርም፡፡

በህገ መንግስቱ አንቀጽ 41/1 መሠረት ማንኛውም ሰው ለመተዳደሪያ የመረጠውን ስራ የመስራት ህገ መንግስታዊ መብት ያለው በመሆኑ ባል የሚስትን ሙያ ሊቃወም

አይችልም፡፡ ይህ በቀድሞው የፍትሐብሔር ህግ ውስጥ የተቀመጠ ቢሆንም በህገ መንግስቱ መሠረት ያለ ልዩ ሁኔታ የሚከበር መርህ ነው፡፡ ሙያ ከመምረጥ አልፎ በዝርዝር በቤት ውስጥ መከናወን ያለበትን ነገር መደንገጉም ቢሆን አስፈላጊ ባለመሆኑ (too domestic) ዝርዝር ጉዳዮችን በዚሁ ዝርዝር ይመራሉ፡፡ ከፈረንሳዩ ሲቪል ኮድ በፊት ወጥቶ የነበረው የፕሩሺያ ሲቪል ኮድ ሳይፈፀም የቀረበው አላስፈላጊ የሆኑ ዝርዝር ጉዳዮችን ይዞ ስለነበረም ነው፡፡

በነፃ ገበያ ስርዓት ውስጥ የንብረት ጥበቃ የተለየ ቦታ አለው በዚህ ረገድ የህብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑት ሴቶች የንብረት መብታቸው ካልተከበረላቸው ነፃ ገበያ ትርጉም የማይኖረው በመሆኑ ህገ መንግስቱ ለዚህ መብትም የተለየ ትኩረት ይሰጣል፡፡ የአርሶ አደር ሴቶች በተለይ ያለባቸውን ልዩ ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት በመሬት ጉዳይ በተለይ በማለት የእኩልነት መብታቸውን አረጋግጧል፡፡ ለውርስ አፈፃፀም (በተለይ ጡረታ) እኩል መብት አላቸው፡፡

የባልና ሚስት ንብረትም በህገ መንግስት መርህ መሠረት የጋራ ሆኖ ይቆያል፡፡ ንብረት በተለይ ካልተመለከተ በቀር የጋራ (single patrimony) መሆኑ ለንብረት የተሻለ ጠበቃ ያስገኛል፡፡

ጋብቻ በተጋቢዎች ሙሉ እና ነፃ ፈቃድ ላየ መመስረት እንዳለበት ህገ መንግስቱ የሚደነግግ በመሆኑ ለፍቺ የሚቀመጥ ቅድመ ሁኔታ ጋብቻ ከነፃ ፈቃድ ውጪ እንዲቆይ የሚያደርግ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ የህገ መንግስቱ መርህ በሙሉ ይፈፀም ዘንድ ጋብቻ ከነፃነት ውጪ እንዲቆይ የሚያደርግ ድንጋጌው ሁሉ ህገ መንግስታዊ አይሆንም፡፡ በሙሉ ነፃነት እና ፈቃድ የቆመ ጋብቻ በተመሳሳይ ሊፈርስ ይገባል፡፡

ከህገ መንግስቱ ጋር የማይጋጩ ባህሎች ወጎች እና ልማዶች እንዲጎለብቱ የማድረግ ኃላፊነት በመንግስት ላይ የተጣለ በመሆኑ በዚሁ አግባብ እስከሰሩ ድረስ የቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች ተገቢው ቦታ በህጉ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በባልና ሚስት ጉዳይ ውሣኔ እንዲሰጡ ቢደረግ ህገ መንግስታዊ ስለማይሆን ከዝህ መለስ እንደ አንድ አማራጭ የሙግት መፈቻ መንገድ (Court Annexed Mediation) ችግርን ለመፍታት ያገለግላሉ፡፡ በዚህ መሠረትም የእርቅ ደንብ (መመሪያ) ከህብረተሰቡ ባህል ጋር ተመዛዝኖ እንዲከተሉ ይጠበቃል፡፡

ህገ መንግስቱ ለቤተሰብ ጥበቃ ያደርጋል፡፡ ቤተሰብ መሠረቱ ጋብቻ ይመስላል፡፡ (አንቀጽ) ነገር ግን ከዚህ በተለየ መልኩ ቤተሰብ ከጋብቻ ውጪም ሊመሰርት ይችላል የሚል አቋም ያላቸው ፀሐፍቶች አሉ (አቶ መሀሪ 121)፡፡ የሆኖ ሆኖ ከጋብቻ ውጪ አብረው የሚኖሩ ሴቶች ቢኖሩ በህግ ክልከላ ያልተደረገ በመሆኑ ግንኙነት በተለይ ከንብረት መብት አንፃር የሚያስከትለውን ውጤት የሚመራ ህግ ቢወጣ ኢ ህገ መንግስታዊ አይሆንም፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በህገ መንግስታችን መሰረት ቤተሰብ የምንለው የትኛውን ተቋም' ቡድን ወይም በስምምነት የተሳሰረ አካል ነው? የትርጉሙ መስፋት ወይም መጥበብ ምን ፋይዳ አለው?
2. ከቤተሰብ ህጋችን አንፃር ህገ መንግስቱ መሠረት ያደረጋቸው ዋና የመርህ ለውጦች የትኞቹ ናቸው?
3. በህገ መንግስቱ ውስጥ የእኩልነት መርህ በጥቅሉ ተገልፆ እያለ በቤተሰብ ህግ ውስጥ በተደጋጋሚ መግለፅ ለምን እንዳስፈለገ በዝርዝር ተወያዩበት፡፡
4. ቤተሰብ የህብረተሰብ እና የተፈጥሮ መነሻ ነው በማለት ህገ መነገስቱ የደነገገው ለምንድን ነው?
5. የቤተሰብ ጉዳይ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለማምጣት ምን ያህል ጠቃሚ ነው? ጉዳይ የክልል መንግስታት ጉዳይ መሆኑ ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው?
6. የቤተሰብ ንብረት አስተዳደርን አስመልክቶ የህገ መንግስቱ መርህ ንብረት ለማፍራት ያለውን ፋይል ዘርዝረህ ተወያይ፡፡
7. የቤተሰብ ከረክር ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ምን ግንኙነት አለው? የክርክር አፈታት አግባቡ ምን ይዘት ሊኖረው ይገባል?

# ክፍል ስድስት

# በውል ህግ የህገ መንግስቱ መሠረታዊ

# መርሆዎች እና አቅጣጫዎች

1. ጠቅላላ

ውል የምንለው በሁለት ሰዎች መሀከል የሚፈፀምና የሚያስገድዳቸው ስምምነት ነው፡፡ ይህንን ስምምነት የሚፈቅድ የሚመራና የሚቆጣጠር የህግ ዘርፍ የውል ህግ ሲሆን በይዘቱም የተዋዋይ ወገኖችን ገንዘብ ነክ ጠባይ ባለው ጉዳይ ላይ የሚያደርጉትን ስምምነት' ችሎታን' ማታለል' ማጭበርበር እና ኃይል የሌለበትን ስምምነት እንዲሁም ህጋዊነትን' ከህብረተሰቡ ሞራል ጋር ተቃርኖ የሌለው መሆንን ይይዛል፡፡ ቶማስ የተባለ ፀሐፊ የውል ህግ አላማ በሰዎች መሀከል የሚፈጠርን ግጭት በቅጣት (punishment) ሳይሆን በህብረተሰቡ ውስጥ ባለ የጎንዮሽ እኩልነት (horizontal equation)መፍታት ማስቻል ነው በማለት ይረዳዋል፡፡ ፈር ሐነሪ ሮበትም ይህንኑ በማጠናከር የማህበረሰቡ እድገት ግንኙቶች በደረጃ (status)ላይ ከሚመሰረቱ ይልቅ በውል ላይ የሚመሰረቱበት ነው ይለዋል፡፡

የውል ህግ ማህበራዊ ግንኙነቶች እና ግዴታዎች መደብን መሠረት ካደረገው ክፍፍል (class — based -hierarchy) ይልቅ በእኩልነት መርህ ላይ እንዲመሠረት ያደረገ ነው፡፡ ቶማስ ውልን እንደ ለውጥ መሣሪያ (vehicle for change) አድርጎ ይወስደዋል፡፡ በሌላ በኩል የውል ህግን ሰዎች እንደ ሙያቸው በተለያየ መልኩ ይረዱታል፡፡ ለምጣኔ ሳይንስ ባለሙያ ውል ማለት ለሚገኝ ጥቅም (benefit) ተጨባጭ ወጪን (cost) የሚያስከትል ግንኙነት ነው፡፡ ለጠበቃ ከማስረጃ እንደ አንዱ ሊወስድ ይችላል፡፡ ለህግ ምሁር የህግ ስርዓቱ አስገዳጅ (binding) የሚያደርገው ስምምነት ሊሆን ይችላል፡፡ ለማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያ ደግሞ ውል ማለት የማህበረሰቡ እና አካባቢ ውጤት ብቻ ሳይሆን በማህበረሰቡ እና አካባቢው ላይ ተፅዕኖ የሚፈጥር ስምምነት ማለት ሊሆን ይችላል፡፡ ለተራው ዜጋ ደግሞ ከእነዚህ ውስጥ አንዱን ሊመስለው ይችላል፡፡ የሆነ ሆኖ የውል ህግ በሰዎች መሀከል የሚደረግ ግንኙነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ግንኙነቱ ጥቅምና ጉዳቱን በሚመዝን ጨዋታ "game" ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ግንኙነቱን ለመመስረት የሚነሳ ሰው ሌላው ሰው በግንኙነት (ውል) መሠረት የሚፈፀም ስለመሆኑ እርግጠኛ ሳይሆን ነው ወደ ግንኙነቱ የሚያመራው፡፡ ሁለተኛው ሰው ባይፈፅም ለኪሳራ ኃላፊ የሚሆን ከሆነ የመጀመሪያው ወደ ውሉ የመግባት እድሉ ይሰፋል፡፡ በሌላ በኩልም የውል አለመፈፀም ኪሳራ(cost of breach)ከፍተኛ በሆነ ቁጥር የውል መቋቋም እና አፈፃፀም እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ከስነ ልቦና ኪሳራ እና ታማኝነት ጋር በተያያዘም ውል የመግባት እድል ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡ የፍትህ ስርዓቱ ጠንካራ መሆን ወይም ደካማ መሆንም በውል ግንኙነት መመስረት እና መፈፀም ላይ ተመሳሳይ ተፅዕኖ

ያግድራል። በዚህ ደካማ የፍትህ ስርዓት ውስጥ ሙስና እና መሰል አፍራሽ ችግሮች ይጠቀሳሉ። ከእነዚህ ችግሮች ጎን ለጎንም የማህበራዊ ኖርም (social norm) ጥንካሬ ወደ ውል ለመግባት እና ለመፈፀም የራሳቸው ሚና አላቸው። በህብረተሰቡ ውስጥ ያለ እምነት (trust) እና ማህበራዊ ካፒታል (social capital)በጥሩ ሁኔታ በተገነባ ቁጥር ግንኙነቶች በውል ላይ የመመስረት እድላቸው ይጨምራል። እንደውም አንዳንድ ሀገራት ውልን ተፈፃሚ ለማድረግ በርካታ ህግ ("more-law") ከማውጣት ይልቅ በተዋዋይ ወገኖች መተማመን ላይ የተመሰረተ እና አንደኛው ተዋዋይ የሌላኛውን የመተባበር (cooperation)ባህሪ ለመገመት የሚያስችለውን ባህል ማሳደግ ይመርጣሉ። በቀድሞ ሶቭየት ህብረት በተደረገ ጥናት("nomenclatura")የሚታመን መንግስት በሌለ ቁጥር ተዋዋዮች የሚመሰረቱት ግንኙነት የግል ጥበቃ ዋስትና ያለበት መሆኑ ተመልክቷል (Simis & vanesc 1982 & 1994)። ለተራው ዜጋ ይህ እምነት(trust) ብቻ ነበር ለውል ግንኙነት መመስረት ወሳኝ ነጥብ የሆነው። በላቲን አሜሪካም ተመሳሳይ መደምደሚያ ላይ የተደረሰ ሲሆን በአህጉሩ አባባል "for friends everything, for enemies nothing, for the stranger the law" የሚለው ይህንን በትክክል ይገልፀዋል።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ሰው በእኩልነት የውል ግንኙነት ውስጥ ይገባ ዘንድ መሠረቱን ይጥላል። ህብረተሰቡ ግንኙነቱ በመንግስት መተማመን ላይ እንዲመሠረት የመንግስት ስልጣን በህገ መንግስቱ እና ስርዓቱ ብቻ እንደሚያዝ ይደነግጋል፡1 መንግስት ይህንኑ እምነት በይበልጥ ለማሳደር በግልፅነት' ተጠያቂነት መርህ የሚሰራ ነፃ የሆነ ጠንካራ የፍትህ ስርዓት የመገንባት ግዴታም አለበት። ሰዎች ሰብአዊ ክብራቸው እንዲከበር(አንቀጽ 24)፣ ህዝቦች መልካም እና የጋራ ጥቅም የማሳደግ ፍላጎት ያላቸውና (መግቢያው) መንግስትም ይህን የመጠበቅ ግዴታ የተጣለበት መሆኑ (አንቀጽ 91) ብንመለከት በግለሰቦች እና በህብረተሰቡ ውስጥ ቀና የሆነ የመተባበር መንፈስን ለመፍጠር የሚያስችሉ ምሳሌዎች ሲሆን ሰዎች ወደ ውል እንዲገቡ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች ናቸው። በዚህ ተማምኖ ውል ውስጥ የገባ ሰው በውል ህጎች መሠረት ተገቢውን ካሳ እንዲያገኝ የውል እና ልዩ ልዩ ህጎች ያስገድዳል። ሀገራችን የነፃ ገበያ ስርዓትን የምትከተል እንደመሆኗ መጠን ከፍ ሲል የተገለፁትን የህገ መንግስቱን ምቹ ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ የሚፈፀሙ የውል ግንኙነቶች እየበዙ እና እየተወሳሰቡ መምጣታቸው አይቀርም። የፍትህ ስርዓቱም የውል ግንኙነቶች

ከምጣኔ ሐብት(Economics) አንፃር ያላቸውን ግንኙነት በጥንቃቄ ካልተረዱ በኢኮኖሚ እድገት ሚናቸውን መጫወት አይችሉም፡፡ በስርዓቱ ውስጥ የሚፈፀም ግንኙነት የአንድ ጊዜ ግንኙነት ብቻ ሣይሆን ተከታታይነት ባለው መልኩ የሚፈፀም በመሆኑ በአንድ የውል ግንኙነት ላይ የሚፈፀም ስህተት ተከታታይነቱ በቀላሉ የማይስተካከል አፍራሽ ጡዘት ውስጥ ሊከት እንደሚችል ምንግዜም መረሳት የለበትም፡፡

## ጥቅም' ፍላጎት' ኢኮኖሚያዊ ውጤት

የህብረተሰቡ እድገት ከመደብ (class) ግንኙነት ወደ ውል ግንኙነት ነው ፡፡ በውል ግንኙነት የተሳሰረ ሰው የወል ግዴታውን የሚወጣው በመሠረቱ ለፅድቅ (benevolence) ሳይሆን የራሱን ቁሳዊ ፍላጎት መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ፍላጎቱን የሚያሟላውም ቃል በመግባት እና ቃል በመቀበል ነው፡፡ ይህ ቃል አፍቃሪዎች ለመጋባት' ወታደሮች ድል ለማግኘት' ልጆች የተሻሉ ጎበዝ ተማሪዎች. . . ለመሆን ከሚገቡት ቃል ይለያል፡፡ በመሆኑም በውል ህግ ውስጥ ከዚህ ጋር ተያይዞ የትኛው ቃል በህግ አስገዳጅነት ሊፈፀም ይገባዋል? ቃል ባይከበር ማካካሻው(remedy)ምንድን ነው? የሚሉት ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በ19ኛ እና 20ኛ ክፍል ዘመን ገኖ የነበረው የድርድር ንድፈ ሃሳብ (Bargain Theory) በመሠረቱ ሊፈፀሙ የሚገባቸው ውሎች የድርድር ውጤት የሆኑት ብቻ ናቸው ይለናል፡፡ በድርድር ውስጥም ድርድር (ቃል) አቅራቢ' ተቀባይ እና ጥቅም (offer, Acceptance, Consideration)ይኖራሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከ3ቱ በተጨማሪ የተወሰነ ስነ ስርዓት እንዲፈፀም ይጠበቃል፡፡ ለምሳሌ የቤት ሽያጭ ውል ምዝገባ ለዚህ ይጠቀሳል፡፡ በቃል ሰጪው እና በቃል ተቀባዩ መሀከል ጥቅም አለ፡፡ ይህ ጥቅም የገንዘብ' የሸቀጥ' የአገልግሎት' ወይም ሌላ ቃል (promise for promise)ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም በዚህ ቲወሪ መሠረት በመሀል ያለው ጥቅም ውልን ተፈፃሚ ያደርገዋል፡፡ ይህ ጥቅም ፍትሐዊ (fair)ተመጣጣኝ(proportional) ቢሆንም ባይሆንም በዚህ ንድፈ ሃሳብ መሰረት በፍ/ቤት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ የዚህ ቁምነገር መነሻው በአንድ ውል ውስጥ ያለው የጥቅም ልውውጥ ተመጣጣኝ መሆን አለመሆኑን ፍ/ቤቶች ይመርምሩ ቢባል ለውሣኔ ከሚያስፈልገው በርካታ መረጃ የተነሳ ፍ/ቤትን ሊያጨናንቅ ብቻ ሳይሆን የንግድ እንቅስቃሴን ይገታል የሚል ነው፡፡ ከዚህ ንድፈ ሐሳብ በሌላ ጎራ የምንገኘው በአብዛኛው ሲቪል ሎው ሀገራት ውስጥ የሚሰራበት

የ"ምክንያት "(cause) አስተሳሰብ ነው፡፡ በዚህ "ፍላጎት ንድፈ ሃሳብ" (will Theory) መሰረት አስገዳጅ ውል ተዋዋይ ወገኖች ለመገደድ ሆነ ብለው አስበውበት የገቡት ውል ብቻ ነው፡፡

ውሉ የማይፈፀም ቢሆን ውል አፍራሽ ኃላፊ መሆን የሚገባው በድርድር ጥቅም ልክ (benefit of the Bargain) እንደሆነ የድርድር ውል ያስቀምጣል፡፡ ይህም ማለት ውል የፈረሰበት ወገን ከውል መፈፀም ምክንያታዊ በሆነ አግባብ የሚጠብቀውን ያህል ጥቅም በካሳ ሊያገኝ ይገባዋል ማለት ሲሆን ይህም "expectation damages" በመባል ይታወቃል፡፡ እነዚህ ንድፈ ሐሳቦች በተለይ የድርድር ንድፈ ሐሳብ የውል ህግ ለኢኮኖሚ እድገት ያለውን ጠቀሜታ ለማሳየት እንደ መንደርደርያነት ተመልክተነው እንጂ ያለሁለትዮሽ ድርድር የሚፈፀሙ ውሎችን እንዲሁም ድርድር ሁሉ የሚፈፀም አድርጎ የሚያስብ የተሳሳተ ቲወሪ መሆኑ ተዘንግቶ አይደለም፡፡ ሆኖም ይህንን ቲወሪ የበለጠ ቀኖናዊ ባልሆነ (less dogmatic) እና ለተዋዋይ ወገኖች ፍላጎት የበለጠ ምላሽ ወደሚሰጥ ቲወር ማሳደግ ተገቢ ነው፡፡ ከምጣኔ ሐብት አስተሳሰብ (Economic theory of contract) አንፃር የውል ህግ efficient ነው ለማለት ውሉ በተፈፀመበት ጊዜ ተዋዋዮች ለመፈፀም (ለመገደድ) ፍላጎት የነበራቸው መሆን ይገባዋል፡፡ አንደኛው ወገን ያለበት ግዴታ ከሞራል ግዴታ በላይ የህግ ግዴታ እንደሆነ ማሰብ ይኖርበታል፡፡ ይህ ሐሳብ በሰዎች መሀከል ልውውጥ (exchange) እንዲኖር የሚያበረታታ ብቻ ሳይሆን ለለውጥ በመተባበር (coopration) መንፈስ እንዲፈፀም የሚያደርግ ነው፡፡ ይህን የሚያስፈፅም ፍ/ቤት ተዋዋይ ወገኖች የሚፈልጉትን እንዲያገኙ በማድረግ በልውውጥ ውስጥ የመኖሩ መጠራጠርን (uncertainity) እና አደጋ (Risk) ይቀንሳሉ፡፡ በትብብር መስራቱ ሁለቱንም ምርታማ (productive) በማድረግ ከውሉ መፈፀም የሚገኘውን ትርፍ በዘላቂነት እንዲካፈሉ ያደርጋሉ፡፡ ትርፍን የሚያካፍል (division) እንጅ ሀብትን የሚያዞሩ (Productive) ባለመሆኑ የረዥም ጊዜ ውጤቱ አጥጋቢ ነው፡፡ ይህ የእስረኞች ጌም በመባል በሚታወቀው ሰንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| |
|---|
| <u>አበበ</u> |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ቢያምን | ቢክድ |
| -<br>ከበደ | አ<br>በ<br>በ<br><br>እ<br>አ<br>በ | ቢያምን | 8<br>8 | 15<br>3 |
| | | ቢክድ | 3<br><br>15 | 15<br><br>15 |

አበበና ከበደ ወንጀል ፈፅመዋል፡፡

- ወንጀሉ ከ3-15 ዓመት እስራት ያስቀጣል እንበል ሁለቱም ካመኑ /በመመካከር/ - ቅጣቱ 8 አመት፣
- አንዱ ሲያምን ሌላው ቢክድ - መነው በበ3 እና የካደው በ 15 አመት፣
- ሁለቱም ቢክዱ በነጻ የሚለቀቁበት (ማስረጃ ስለማይገኝ)

ይህ ሳጥን የመረጃ ልውውጥ በሌለበት ሁኔታ የአጭር ጊዜ ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት ግራ መጋባት (dilemme) እንደሚፈጠር ያመለክታል፡፡ ይህ ውጤት የሚገኘውም በሌላው ሰው ከራሱ/እቅድ ላይ ተመስርቶ በመሆኑ ዘላቂ አይደለም፡፡ ዘላቂ እና ለሁሉም አዋጭ የሚሆነው በመረጃ ልውውጥ ላይ ለተመሰረተ ዘላቂ እና ሁሉንም የሚያተርፍ ስምምነት ነው፡፡ (ሀሳቡ Disputing procedure" ከተባለ መፅሐፍ ስለድርደር ከተፃፈው ውስጥ የተወሰደ ነው፡፡)

በዚህ ሂደት ውስጥ ከተዋዋዮች ውጪ ያሉ ነገሮች ለምሳሌ ተልዕኮውን በሚገባ የሚወጣ ከሙስና የፀዳ ፍ/ቤት መኖር ግምት ውስጥ ይይዛል፡፡ ከላይ በተመለከተው ሰንጠረዥ ውስጥ ያሉ ሰዎችን ተዋዋይ አድርገን ብንወስዳቸው ለሁለቱም ዘላቂ የጋራ ልማት የሚጠቅማቸው ውል ውስጥ መግባት እና የገቡትን ውል ለመፈፀም በቁርጠኝነት መተባበር ነው፡፡ ይህ ቁርጠኝነት እና ትብብር በመሰረቱ የመረጃ ልውውጥ ይፈልጋል፡፡ የወል ህግ የትኛውን መረጃ ተዋዋይ ወገኖች መጋራት እንደአለባቸው(asymmetric

information) እንዲሁም የትኛው መረጃ ከዚህ ውጪ ነው የሚለውን ይለይልናል፡፡ ይህ የወል ህግ ከምጣኔ ሀብት ሃሳብ አንፃር ሁለተኛ ተግባሩ ነው ብንል ተዋዋይ ወገኖች ለውሉ መከበር (ወይም መፈፀም) የመጨረሻውን ቁርጠኝነት እንዲያሳዩ ማድረግ ሶስተኛ ተግባሩ ነው ለማለት እንችላለን፡፡ ይህን በማድረግ ውል ለመፈፀም ቃል የገባው ቃሉን ቢያጥፍ የሚከተለው የኃላፊነት መጠን ቃሉ ከመታጠፉ የተነሳ በሌላኛው ወገን ላይ ከሚደርሰው ጉዳት ጋር እኩል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ቃል የገባ ተዋዋይ ቃሉን ለመፈፀምም ሆነ ለማጠፍ አዋጭነት (efficiency) የሚመዝንበት ነጥብ ይህ ነው፡፡ ይህ ነጥብ ተዋዋዮች ለመፈፀም ቁርጠኛ የሚሆኑበት ነውና በውሉ አስፈፃሚ አካላት ዘንድ በጥንቃቄ መመዘን ያለበት ነው፡፡

ተዋዋዮች ይህን ቦታ በማሰብ ውል ውስጥ ሲገቡ «ኢንቨስት» ያደርጋሉ ቃል የገባ ሰው ውሉን ለመፈፀም ቃል ተቀባይ ደግሞ ቃሉን በማመን ኢንቨስት ያደርጋሉ፡፡ በሁለቱም ወገን የሚደረግ «ኢንቨስትመንት» ገንዘብን፣ ጊዜን እና (በጉልበት የሚደረግ) ጥረትን ያጠቃለላል፡፡ በሌላ በኩልም በዚህ ውል ውስጥ በመግባታቸው የሚያጡት በጎ ነገር ካለም (opportunity cost) ኢንቨስትሜንት ነው፡፡ አንድ ሰው መሬት ተከራይቶ (ውል) አበባ ለማልማት ቢፈልግ ምን ምን አይነት የውል እና ከውል ውጪ ግንኙነቶች ውስጥ እንሚገባና ምን ሲያገኝ ምን እንደሚያጣ አስቡ፡፡ የጉልበት ሰራተኛም እዚህ ስራ ቦታ ቢቀጠር በተመሳሳይ መልኩ ይህንን በበርካታ አምራቾች አባዙት የጉልበት ሰራተኛው በአበባው እርሻ ውስጥ ለመቅጠር የሚፈልገው ቅጥሩ እሴት (Value) የሚጨምርለት መሆኑን ባለአበባው በቅጥሩ መሠረት የመፈፀም እድሉን አባዝቶ ነው፡፡

<u>ክፍተት (Gap)</u>

ውሎች እንደ ህጎች ውሉ ክፍተት (Gap) ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህ ክፍተት በፍ/ቤት ሊሞላ ይገባል፡ ፍ/ቤትም ይህንን ክፍተት ሲሞላ የወደፊት ተዋዋይ ወገኖች ባህሪ ሊመራ በሚችል (Normative Coause Theorem) መልኩ መሙላት ይጠበቅበታል:: ሁለቱም ወገኖች በኢኮኖሚ ሊያተርፉ በሚችሉበት አግባብ ክፍተቱ ቢሞላ ለገበያ ያዋጣል፡፡ ጉዳዩን በአዎንታ (positively) ካየነው ተዋዋይ ወገኖች በጉዳዩ ላይ ቢደራደሩ ሊስማሙ ይችላሉ ተብሎ በሚጠይቀው አኳኋን መሞላት ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ ፍ/ቤት ክፍተት ከመሙላት በተጨማሪ ጉዳዮች በተጨማሪ የውሉ አደጋ (Risk) እና ወጪ (Cost) ማንኛው ወገን ላይ ማረፍ ይገባዋል የሚለውን ይመለከታሉ፡፡

ይህ ተግባር ደግሞ ተዋዋይ ወገኖች ያላቸውን መረጃ (በድርድር) እና የንግዱን ልማድ በጥልቀት ማወቅን ይጠይቃል:: ያለዚህ ግንዛቤ የሚሰጥ ውሣኔ ገበያንና ተጨማሪ ውልን አደጋ ላይ የሚጥል ሊሆን ይችላል:: የሚደርስ አደጋ በልምዱ መሠረት በየትኛ ውም ወገን አስቀድሞ ሊታይ የማይችል ( unforseeable) ከሆነ ጉዳቱን በተዋዋዮች መሀከል (blameless parties) ሊከፈል ይችላል፡፡

<u>የመንግስት ጣልቃ መግባት</u>

ውል ተፈፃሚ መሆን አለበት ማለት ግን ተዋዋዮች በውላቸው ውስጥ ያስገቡት ጉዳይ ሁሉ ይፈፀማል ማለት አይደለም:: ህግ እና ደንብ የውል ጉዳይን ሊመሩ፣ ሊተኩ ይችላሉ:: ለዚህ የሚኖረው አንድ ምክንያት ገበያን በነፃም በህግም መምራት አስፈላጊ መሆኑ ነው:: የውል ግንኙነት ከተዋዋይ ወገኖች ውጪ ሌሎች ሰዎችን ይነካል:: ይህ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች (Spillover effect) የሚሉት በውል ግንኙነት ውስጥ ያለ ሲሆን በሌሎች ህጎች (ንብረት'ቶርት'ወንጀል) የሚታይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ነፃ የውል ግንኙነት እንዲኖር የመረጃ ልውውጥ የሚያስፈልግ ቢሆንም ይህ ልውውጥ በበቂ ሁኔታ ላይፈፀም ይችላል:: ማታለል፣ ማሳሳት፣ ማስገደድ፣መረጃን በእኩል አለመረዳት፣ መደበቅ ወዘተ የውል ግንኙነት መዛባት ይፈጥራሉ:: ገበያ በሞኖፖሊ ቁጥጥር ስር ሊወድቅ እንደሚችል ሁሉ አንዳንድ ውሎችም በዚህ መልክ ሊፈፀሙ ይችላሉ::

በተግባር አንድ ሰው ብቻ የውል ተጠቃሚ እንዲሆን ውል ሊገባ የሚችልበት አጋጣሚ የሲቪል ሎው ሀገራት "lesion" የኮመን ሎው ሀገራት ደግሞ "Unconscionable contract" የሚሉት ነው:: እነዚህ ሁኔታዎች የውል ህግ ከመፈፀሙ በላይ መደበኛ ህግ (እንደ market failure) እንዲፈፀመ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ገበያ ነፃ ቢሆንም የገበያ ውድቀት (market failure)እንደሚገጥመው ሁሉ ውልም ነፃ ሆኖ ተመሳሳይ ውድቀት ሊገጥመው ይችላል፡፡ የገበያን ውድቀት እጅግ ከፍተኛ በሆነ ጥንቃቄ መንግስት ጣልቃ በመግባት የሚያስተካክለው ሲሆን የውልንም መውደቅ በተመሳሳይ መልኩ ጣልቃ እየገባ ያስተካክላል፡፡

በሀገራችን የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም መቀረፁ ይታወቃል:: የዚህ ስርዓት መቀረፅ አስፈላጊ ካደረጉት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የፍትህ ስርዓቱ ከምትከተለው የዲሞክራሲ እና የነፃ ገበያ ስርዓት ጋር የማይሄድ መሆኑ ነው፡፡ በስርዓታችን የውል ህግ ካለው በርካታ ጥቅሞች ውስጥ በግለሰቦች መሀከል ያለን ልውውጥ (exchange)

ማቀላጠፍ ማስቻል ነው፡፡ይህ ልውውጥ በበርካታ መልኩ የሚፈፀም ሲሆን የውል ግንኙነት አንዱ መንገድ ነው፡፡ የውል ግንኙነት በጠንካራ የፍትህ ስርዓት (ፍርድ ቤት) ሊፈፀም ይገባዋል፡፡ በ16ኛ ክፍለ ዘመን የኖረው ቶማስ ሆብስ የዳኝነት ስርዓት ከሌለ ነጋዴዎች ትርፍ (Surplus) የሚያስገኝ ልውውጥ ቢገጥማቸውም ልውውጡ ላይከበር ስለሚችል ወደ ግንኙነቱ መግባት አይፈልጉም በማለት የገለፀው ውል ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ያለውን ግንኙነት ለማሳየት ጠቃሚ ነው፡፡ ኖርዝ የተባለ ኢኮኖሚስትም በተመሳሳይ ሃሳብ ይስማማል፡፡ እንደ እርሱ አባባል በአነሰተኛ ወጪ (low cost) ውል ያለመፈፀሙ ለእድገት ጠንቅ እና ለ3ኛ አለም አለማደግ(stagnation and underdevelopment) ምክንያት ነው፡፡

የበለፀጉ ሃገራት ያላቸው ከፍተኛ ኢኮኖሚ ደረጃ (high performing economy) በውል ላይ በመተማመን በሚፈጠሩ የረዥም ጊዜ የውል ግንኙነት ውጤት ናቸው (ዊልያምስ)፡፡ የፍትህ ስርዓት ጠንካራ ባልሆነበት ሁኔታ ከፍተኛ የንግድ ግንኙነቶች ውሎች ለመጨረሻ እድል በሌለባቸው ሁኔታ ብቻ ይፈፀማሉ፡፡ ይህም በረዥም ጊዜ የሀገር ኢኮኖሚ ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ እነዚህ በፅንሰ ሐሳብ ደረጃ የተቀመጡ ሃሳቦች በተለያዩ ሐገራት በተደረጉ ጥናቶች ተረጋግጠዋል፡፡ በጋና በተደረገ ጥናት ተመሳሳይ ድምዳሜ ላይ ተደርሷል፡፡ በፔሩ በተደረገ ጥናት ለጥያቄ ምላሽ ከሰጡ ሰዎች መሀከል 1/3ኛ የሚሆኑት እንዳረጋገጡት አዲስ አቅራቢ አነስተኛ ዋጋ ይዞ ቢቀርብ እንኳን በአፈፃፀሙ ላይታመን ስለሚችል ከፍተኛ ዋጋ ይዞ ከሚቀርበው ከለመዱት አቅራቢ ጋር መዋዋል ይመርጣሉ፡፡ በኢኳዶር በተደረገ ጥናት ነጋዴዎች ውል ስለሚፈፀምበት ጊዜ እርግጠኛ ባለመሆናቸው ኢንቨስት ለማድረግ የሚያመነቱ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡ በብራዚል በተደረገ ጥናትም የብራዚል ፍ/ቤቶች እንዳደጉት ፍ/ቤቶች ቢሆኑ ኖሮ (በውል አፈፃፀም) የሐገር ውስጥ ኢንቨስትመን በ10 በመቶ ይጨምር እንደነበር ተረጋግጧል፡፡

የፍትህ ስርዓቱ ጠንካራ ሲሆን ተገማች ይሆናል፡፡ በ69 ሀገራት ውስጥ የሚገኙ 3600 የንግድ ድርጅቶች (firms) በንግድ ስራቸው ውስጥ ዋናው ችግር ተገማች ያልሆነ ፍርድ ቤት እንደሆነ ምላሽ ተስተዋል፡፡ (አለም ባንክ 1997)፡፡ ቀልጣፋ ያልሆነ የዳኝነት ስርዓት የልውውጥ (ውል) Transaction Cost እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

የኢፌዲሪ ህገ መንግስት በመግቢያው ላይ ብሔር ብሔረሰብ እና ህዝቦች ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገታቸው እንዲፋጠን ቆርጠው መነሳታቸውን አስቀምጧል፡፡ የህዝቦችን የጋራ ጥቅም በማስከበር የጋራ እድልን መወሰን አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመገንባት

እንደሚያስችል ይገልፃል። ፈጣን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት ማምጣት የህገ መንግስት አላማ ሲሆን የውል ህግ የሚመራበት መርህ ነው። ንብረትን በውል የማስተላለፍ መብት በህገ መንግስቱ የተከበረ ነው። የኢትዮጵያውን ኢኮኖሚ ሁኔታ በተናጠል ሊሻሻል(አንቀጽ 89/2) ከሚችልበት መንገድ ውስጥ አንዱ በህግና አፈፃፀሙ ላይ እምነት ጥሎ የሚመሰረት የውል ግንኙነት ነው። ከዚህ በተጨማሪም ወረድ ብለን እንደምንመለከተው የእኩልነት መብት፣ ፍትህ የማግኘት መብት፣ ማንኛውም ሰው በመረጠው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራት እና የመረጠውን ሥራ የመስራት መብት እና የንብረት መብት የውል ህግ ሊመራባቸው የሚገቡ መርሆዎችን የያዙ ናቸው።

የህግ ስርዓታችን ግለሰቦች በንብረታቸው በመሰላቸው እንዲያዙበት ይፈቅዳል። ንብረትን ለሌላ ሰው በነፃ ወይም በሌላ ንብረት (ገንዘብ) በመለወጥ «ማጥፋት» (dispose) ማድረግን ይፈቅዳል። በዚህ ረገድ ሰዎች ያላቸው ነፃነት በስምምነታቸው መሠረት በንብረታቸው ላይ በህግ ፊት አስገዳጅ የሆነ ውል መዋዋልን ይጨምራል። የውል ህግ በስርዓታችን ውስጥ በህግ ፊት አስገዳጅ የሆኑት እና የሚሆኑትን ስምምነቶች የመለየት' መብትና ግዴታዎችን የመለየት እና ያልተፈፀመ ውል ቢኖር ውጤቱን ለማመልከት እንዲሁም ነፃ የጉልበት' ገንዘብ እና ንብረት ዝውውር እንዲኖር በመሰረታዊነት ያገለግላል። አልፎ አልፎ የውል ህግ በህብረተሰቡ ውስጥ ፍትሐዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል (fair division of wealth) እንዲኖር ያስችላል። በእርግጥ በውል ህግ ውስጥ ያሉ የወለድ መጠን ገደቦች፡በውል የሚወሰኑ አነስተኛ ደመወዝ፣ የስጦታ ውል የመሳሰሉት እነዚህን ግቦች አላማ ያደረጉም ናቸው። የውል ህግ አላማ ሐብትን ማከፋፈል ነው ወይስ ይህ ግምት ውስጥ ሳይገባ የንብረት ዝውውርን ማፋጠን ነው የሚለው አከራካሪ ነው። የንብረት ዝውውር በህገ ወጥ መንገድ (ምሳሌ ስርቆት) እንዳይፈፀም ስርዓታችን ይከለክላል። በሌላ በኩል የሀብት ክፍፍል ከውል ግንኙነት ውጪ በግብር ህግ እና ሌሎች የፍ/ብሔር ህጎች ሊፈፀም የሚችል በመሆኑ የሀገራችን የውል ህግ አላማ መሠረታዊ አቅጣጫ ይህ ነው ለማለት አይቻልም። ይሁን እንጂ በተዋዋዮች ፈቃድ ይህ ሊፈፀም ይችላል።

ሲጠቃለል የውል ህግ መሠረት የሚያደርጋቸው ቲዎሪዎች የተለያዩ ቢሆንም ከምንከተለው ስርዓት አንፃር የምጣኔ ሃብት ቲዎሪ እጅግ ጠቃሚዎች ነው። የምንከተለው የነፃ ገበያ ስርዓት እንደመሆኑ ንብረት ጉልበት እና ገንዘብ በነፃነት በገበያ ውስጥ ሊዘዋወሩ ይገባል። የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ በተለያየ መልኩ የሚፈፀም የኮንትራት

ኢኮኖሚ ነው:: ውሎች ካልተፈፀሙ ነፃ የገበያ ስርዓትም አይኖርም ማለት ነው:: የፍ/ብሔር ህጋችን ውሎች በተዋዋይ ወገኖች ነፃ ስምምነት መፈፀም እንዳለባቸው ይደነግጋል:: የነፃ ገበያ በተዋዋይ ወገኖች መሀከል የመረጃ ልውውጥ ይፈልጋል፣ጥቅም ጉዳትን መዝኖ የሚገቡት ግንኙነት ነው:: በዚህ መልኩ ስምምነት ከሌለ ውል የለም:: የተዋዋይ ወገኖች ትብብር እና ጠንካራ የፍትህ ስርዓት ይፈልጋል:: ውል የጎን ውጤት ያለው በመሆኑ ከህግ በላይም መንግስት ጣልቃ የሚገባባቸው አጋጣሚዎች አሉ::

ተዋዋዮች ስምምነታቸውን የሚገልፁት ከህግ ጥላ ስር በመሆን ሲሆን በዚህ መልኩ የተገለፁ ስምምነት አስተማማኝ ጥበቃ እንደሚደረግለት በረባ ባልረባ ምክንያት ፍርስ እንደማይሆን በመተማመን ነው:: ስለሆነም ከህገ መንግስቱ አንፃር የውል ህጋችን መሠረታዊ አቅጣጫ:

- ውሎች በነፃነት እንዲፈፀሙ ማድረግ፣
- ተዋዋዮች የገቡት ውል በአስተማማኝ መልኩ እንደሚፈፀሙላቸው እርግጠኛ መሆን (game-theory) ፣
- ተዋዋዮች ውሉ በጥቃቅን ምክንያት የማይፈርስ ለመሆኑ የሚተማመኑበት፣
- ውሉ ቢፈርስ እንኳን ውሉ ለፈረሰበት ወገን በቂና ተመጣጣኝ ካሳ የሚያስከፍል መሆን ፣
- ውልን ለማስከበር እጅግ አጭር ጊዜ የሚወስድ መሆኑ፣
- ውሉ ከመፈረሙ አንስቶ እስከ አፈፃፀሙ ድረስ በተቻለ መጠን ግልፅ እና ለአፈፃፀሙ የሚመች መሆኑ (ምሳሌ በፅሁፍ መስፈር የሚረጋገጥበት)፣
- በነፃነት የተገባን ግዴታ ከመፈፀም በቀር ሌላ አማራጭ ያለመኖሩን የሚያረጋግጥ የህግ እና ፍትህ ስርዓት (እንደ በለፀጉት ሃገራት ሁሉ)፣
- የተፈፀመ ውል በአንደኛው ወገን ጥቅም (እጅግ አጥብቆ ከታየ Liberalism advantage taking) የሚያስገኝ ብቻ ሳይሆን ተዋዋይ ወገኖች ከነበረበት ሁኔታ ሁሉ የተሻለ ደረጃ ላይ የሚያስገኛቸው፣ በግላቸው የኢኮኖሚ እድገት (economic growth) የሚያስገኝላቸው ከዚህም ሀገር ከምታተርፈው እድገት (development.) የማያገኙ መሆናቸው፣

- ችግሮችን የሚፈታ አካል ሁሉ የውል ግንኙነት ያለውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ጠንቅቀው የሚረዱ በዚህም የነፃነት (liability) መርህ እና ፍትሐዊነት (ህጋዊነት ሞራል የሚችል መሆን ተጨምረውበት) አመዛዝነው የሚሰሩ መሆኑን፣
- ውል ፈራሚዎች ውሉ እንደሚፈፀም በቂ ዋስትና ያላቸው፣
- ስርዓቱም ይህንን ግንኙነት ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጠቀሜታ በአግባቡ የተረዳ፣ ሰዎች በዚሁ ተማምነው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ውሎች ከጠባብ ምዕራፍ በመውጣት ከቤተሰብ ጎረቤት ዘመድ ወይም ከቀደመው ተዋዋይ ጋር ብቻ ሳይሆን ከማንኛውም ሰው ጋር ለመፈፀም የሚተማመኑበት የሚሆን፣
- የውል ግንኙነቶች ካልተከበሩ የተዋዋይ ወገኖች ብሎም የህብረተሰቡን ማህበራዊ ግንኙነት በመጠበቅ በዚሁ ዘርፍም ያድግ ዘንድ በስምምነት፣ በድርድር፣ በእርቅ በአስታራቂ ዳኛ . . . እና መሰል አማራጭ የሙግት መፍቻ የሚታዩበት' እድል የሚፈጥርና የሚያበረታታ፣ ይህ ተሞክሮ ባልተሳካ ቁጥር ግን የጠፋውን ጊዜና ጉልበት በሚገባ የሚረዳ ጠንካራ የፍትህ ስርዓት አስተማማኝ ምላሽ የሚሰጥ፣
- የፍትህ ስርዓቱ በአካሄድም ሆነ በውጤቱ ለተዋዋይ ሆነ በህብረተሰቡ ተገማች የሆነ፣
- በማጭበርበር፣ ማታለል . . . ላይ የተመሠረቱ ውሎችን በአግባቡና በፍጥነት የሚቆጣጠር ጠንካራ የፍትህ ስርዓት ለውል ግንኙነቶች ብቻ ሳይሆን የወንጀል መከላከል ስራን የሚፈፀምና በዚህ ረገድም ማህበራዊ እድገት እንዲፋጠን የበኩሉን የሚያበረክት የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ያለተጨማሪ ስጋት እንዲካሄዱና ተጨማሪ ባለሀብት በመስኩ እንዲሰማራ በር የሚከፍት፣
- በጉዳይ አያያዝ ከህግ እውቀት በተጨማሪ የውል ግንኙነት ከምጣኔ ሐብት ጋር ያለውን ግንኙነት በሚገባ የተረዳ ባለሞያ፣ ከዚህ በላይም የውል ግንኙነት ላይ ጊዜው ከማንም በላይ ጠቃሚ ሀብት መሆኑን የተገነዘበ፣

መሆኑን የፍትህ አካላት በሚገባ ሊረዱት ይገባል። ይህንን አቅጣጫ ተረድቶ የራስ ማድረግ እና መፈፀም ሀገሪቱ ራዕይ ላደረገችው በመካከለኛ ገቢ ሀገራት ተርታ መሰለፍ ወሳኝ ነው።

## <u>የመወያያ ጥያቄ</u>

1. የውል ህግ እና ነፃ ገበያ ያላቸውን ግንኙነት ዘርዝር በማድረግ ተወያዩበት።

2. የውል ህግ ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ያለውን ግንኙነት ተወያዩበት፡፡ ከህገ መንግስቱ አንፃር የውል ህግ ሊመራበት የሚገባው ንድፈ ሀሳብ ምንድን ነው?
3. በህገ መንግስቱ ላይ የተመለከተውን የኢኮኖሚ እድገት ከውል ስርዓት አፈፃፀም በመነሳት ለማሳካት የፍትህ አካላት ሚናን በዝርዝር ተወያዩበት፡፡
4. በወል ህግ ውስጥ የመረጃ ልውውጥ' ትብብር' እርግጠኛነት' አደጋ (Risk). . . ለኢኮኖሚ እድገት ምን ፋይዳ አላቸው?
5. በነፃ ገበያ ውስጥ የውል ህግ እና የንብረት ህግ የተለየ ቦታ አላቸው? ሁለቱን ምን ያመሳስላቸዋል? የውል ህግ ያለ ንብረት ህግ አለዚያም የንብረት ህግ ያለ ውል ህግ ትርጉም አለው ትላለህ?
6. ከህገ መንግስቱ የሚመነጩ መሠረታዊ የውል ህግ አቅጣጫዎችን ዘርዝረህ ተወያይ፡፡

# ክፍል ሰባት

# ከንግድ እና ኢንቨስትመንት አንፃር የህገ መንገስቱ መሰረታዊ መርሆዎች እና አቅጣጫዎች

## ጠቅላላ

በየትኛውም ጫፍ የሚገኝ ሀገር ቢሆን በኢኮኖሚ ለማደግ የማይፈልግ አይኖርም፡፡ ይህንን እድገቱን እውን ለማድረግ ሀገሩ ያለፈበትን ታሪክ ከመዳሰስ አልፎ በቅርብ እና በሩቅ ያሉ ሀገራትን ልምድ መቃኘቱ አይቀርም፡፡ በዚህ ቅኝት ውስጥ የአንድ ሀገር መሪ በኢኮኖሚ እድገት ላይ ያለው ሚና ምንድን ነው? መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረው ተሳትፎ ምን መልክ ይኖረዋል? የግል ባለሀብቱ በምን መስክ ላይ ቢሰማራ ይመረጣል? የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ላይ የሚኖረው ፖሊሲ ምንድን ነው? አሁን ባለንበት ዘመን አንድ ሀገር ከአለም ተነጥሎ በመጓዝ የሚያተርፈው የኢኮኖሚ እድገት ይኖራል? የሚሉ እና መሰል መሰረታዊ ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ ቀደም ሲል አለም በሁለት ጎራ ተከፍላ እንደነበር ይታወሳል፡፡ የቀድሞ ሶቭየት ህብረት ጎራ ከፈረሰ በኋላ ሀገራት ፍጥነቱ እና ይዘቱ በተለያየ መልኩ ወደ ነፃ ኢኮኖሚ ስርዓት እየገቡ ናቸው፡፡ በዚህ የለውጥ ሂደት ውስጥ የፖለቲካ አመራር ቁርጠኝነት ወሳኝ ነው፡፡ (ለምሳሌ ለቻይና ንግድና ኢንቨስትመንት ማሻሻል የዲንግዜዬፒንግ ሚና ወሳኝ ነበር፡፡) ለሚወጡት

የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች እና ለሚጠበቀው እድገት የፖለቲካ መረጋጋት ወሳኝ መሆኑም አያጠራጥርም፡፡ መንግስት በዚህ ረገድ የሚኖረው የፖለቲካ ቁጥጥር ወሳኝም ነው፡፡ አንድ ሀገር በታሪኳ የንግድ እና የባህል ማዕከል በመሆን ገናና የነበረችበት ዘመን ከነበር (ምሳሌ ቻይና) ይህንን ቦታ ለመመለስ የሚደረግ የንግድ እና ኢንቨስትሜንት ማሻሻያ ትግልም በኢኮኖሚ ማሻሻያ ውስጥ ቦታ አለው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በፍጥነት እያደጉ የመጡትን የኤሲያ ሀገራት ኢኮኖሚ እድገት እነዚህን ነጥቦች መነሻ በማድረግ በተለይ ትኩረት የሚያደርጉት የውጭ ገበያ መር ንግድን(expert derive mercantilism): የሀገር ውስጥ ቁጠባን የሚያስፋፋና ልቅ ያልሆነ የውጪ ካፒታልን የሚያስገባ ስልጣኔን: ለመሰረተ ልማት አውታሮች ግንባታ ቅድሚያ የሚሰጥ የመንግስት አትኩሮት እና መሰል ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ ከዚህ በተለየ ቻይና የገበያ መር ሶሻሊስታዊ ስርዓት እና የህዝብ እድገት ቁጥጥርን እንደ ስትራቴጂ በተጨማሪነት ትጠቀማለች፡፡

በሌላ በኩል የአህጉራችንን ኢኮኖሚ በተለይ ከሰሃራ በረሃ በታች ያሉ ኢኮኖሚን ስንመለከት በዚህ መልኩ ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት እየተመዘገበ አለመሆኑን እንረዳለን፡፡ በጥቅሉ ስንመለከት በዚህ የአህጉራችን ክፍል ውስጥ ምንም እንኳን ግሎባላይዜሽን እየጨመረ የመጣ ቢሆንም የአለምአቀፍ ገበያ ተሳትፎ ዝቅተኛ የሆነበት የእርሻ ምርታማነትም ባለበት የቆመበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ለዚህም እንደምክንያት የሚጠቀሰው ከኢኮኖሚ ጋር የማይሄድ የህዝብ እድገት መኖሩ፣ የጤናና የትምህርት ደረጃዎች ተወዳዳሪ አለመሆን፣ የእርሻ ምርታማነት ዝቅተኛ መሆን፣ የፖለቲካ ስርዓቱ ግልፅ እና ተጠያቂነት የሌለበት መሆን፣ ኢንቨስትሜንትን ለመሳብ በሚያስችል መጠን የተረጋጋ አለመሆን፣የመልካም አስተዳደር አለመኖር በተቃራኒው የደካማ አስተዳደር(poor Goverance)መኖሩ የአካባቢ መራቆት:HIV/AIDS መስፋፋት (ሁሉን የኢኮኖሚ ሴክተር የሚጎዳ መሆኑ) ለገበያ በር ዝግ እየሆነ መምጣት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ከዚህ በተረፈም አብዛኛው የአፍሪካ ሀገራት በንፅፅር ያላቸውን የእርሻ እና የተፈጥሮ ሀብት በምርት ሂደቱ ውስጥ በአግባቡ በቅድሚያ አለመጠቀም ተመሳሳይ ምክንያት ይሆናል፡፡ በእነዚህ አይነት ሀገራት የእርሻቸውን ምርታማነት (Agricultural productivity) ማሳደግ በአለም አቀፍ ገበያ ውስጥ ያላቸው ድርሻ እንዲጨምር እንዲሁም የነፍስ ውከፍ ገቢ(Per capital income) ከፍ እንዲል ያደርጋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የመሠረተ ልማት አውታር ዝርጋታ ነው፡፡ አህጉሩ በህዝብ እድገት ከፍተኛውን (በንፅፅር)ቦታ ብትይዝም ህዝቡ ግን ተበታትኖ የሚኖር ነው፡፡

ይህም ሸቀጦች እና ለኢኮኖሚ አስፈላጊ የሆነ ግብአቶች ለአምራች ክፍሉ የሚደርሱበት አግባብ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ እና ወጪን የሚያስከትል ምርታማነትን የሚቀንስ ያደርገዋል፡፡

ወደ ሀገራችን ስንመለስ ከፍ ሲል በመደጋጋም እንደተገለፀው ሀገራችን የነፃ ኢኮኖሚ ስርዓትን የምትከተል ሲሆን ህዝቡም ኢኮኖሚው በፍጥነት እንዲያድግለት ይፈልጋል፡፡ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመገንባት ፍላጎትም አለ፡፡ ለንግድ እና ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ አስፈላጊ የሆነውን ሰላም በዘላቂነት ለመመስረት ብሔር’ ብሐረሰቦች እና ህዝቦች ቆርጠው መነሳታቸውን በህገ መንግስቱ መግቢያ ላይ አስቀምጠዋል፡፡ ህዝቦች ህገ መንግስቱን ለወደፊቱ ቢያፀድቁ "አኩሪ ባህል" እንዳላቸው’ የጋራ ጥቅም እና አመለካከት ካለፈው በጋራ ያፈሩ መሆናቸውን አረጋግጠው ነው፡፡ የኢኮኖሚ እድገት ተስፋው ከታሪክ ከተወረሰው "የጋራ ጥቅም" ማሳደግ ላይም የሚመሰረት ነው፡፡ ይህንን ፍላጎት ተግባራዊ ለማድረግ በህገ መንግስቱ ውስጥ ሰፊ እንድምታ ያላቸው ድንጋጌዎች ተቀምጠዋል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ውስጥ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገራችን ውስጥ በማናቸውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ የመሰማራት መብት አንዱ ነው፡፡ በሌላ በኩል ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሥራውን እና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው(የህገ መንግስቱ አንቀፅ 41)፡፡ በዚህ መልኩ ከሚመረጡ ስራዎች ውስጥ ንግድ ያልሆኑ የሚገኙበት ሲሆን በንግድ ህጉ ውስጥ የተቀመጡት የንግድ ሙያዎችም የሚካተቱበት ነው፡፡ በሌላ በኩል ህገ መንግስቱ ግልፅነት’ ተጠያቂነት እና በመሳሰሉት የመልካም አስተዳደር መርሆዎች የሚመራ ነው፡፡ በዚህ መርህ መሰረት ለመመራት የትኛው ክፍል ኢኮኖሚ ሊመራ እንደሚገባ በፖሊሲ ሰነድ ላይ ተብራርቷል፡፡ ሀገሪቷ በስፋት ያሉትን ሀብት (ጉልበት’ መሬት) ከሚያጥራት ጋር (ካፒታል’ የበቃ የሰው ኃይል . . .)ጋር እንዴት አጣጥማ እድገት ልታስመዘገብ እንደምትችል ለይታ አስቀምጣለች፡፡ ይህ በዝርዝር በሌላ ክፍለ ትምህርት የሚሸፈን ሲሆን በውጤቱ የተመዘገበው ከፍ ሲል ከተመለከተው የሰሃራ በረሃ በታች ሀገራት በእጅጉ በተቃራኒው ነው፡፡ ንግድና ኢንቨስትመንትን ገበያው የሚመራው ሲሆን የኢፌዲሪ መንግስት ኃላፊነት ለዚሁ ምቹ ሁኔታን መፍጠር እና የቁጥጥር ተግባር ላይ መሪ መሆን ነው፡፡ ምቹ ሁኔታዎች ከሚፈጠሩባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ እና ዋነኛው ለንግድ እና ኢንቨስትመንት አስፈላጊ የሆኑ የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን(የኤሌክትሪክ) ኃይል’ መንገድ’ ስልክ’ ትራንስፖርት. . . )ማከናወን ነው፡፡ የኢሲያ ሀገራት እድገት ማዕከላዊ የትኩረት ነጥብ

ውስጥ ከተመለከቱት ዋና ኃላፊነቶች ውስጥ አንዱ ይህ ነው፡፡ እድገቱ ስራው "ዘላቂ"/የህገ መንግስቱ መግቢያ/ መሆን ያለበት ስለሆነም የንግድ እና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ አካባቢን ከመጠበቅ ጋር ተጣጥሞ መሄድ ይኖርበታል፡፡ ይህ በተመዛዘነ መልኩ እንዲፈፀም የህገ መንግስቱ አንቀጽ 92 ስር የተቀመጠው አላማ ግድ ይላል፡፡

በሌላ በኩል ይህንን መብት እውን ለማድረግ ይቻል ዘንድ ከሚወሰዱ ርምጃዎች ውስጥ በመንግስት በኩል የሥራ እድል ለመፍጠር የሚያስችሉ ኘሮግራሞችን ማውጣት’ ፖሊሲ መከተል’ ኘሮጀክት ማካሄድ ይጠቀሳል፡፡ ገበሬዎችና እና አርብቶ አደሮች ለምርት ካደረጉት አስተዋፅኦ ጋር የሚመጣጠን ገቢ የማግኘት መብት ያላቸው ሲሆን የመንግስት ፖሊሲም በዚሁ አላማ እንዲመራ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 41 ጨምሮ ይደነግጋል፡፡ ለመንግስት ከተሰጡት ስልጣኖች (ኃላፊነቶች) ውስጥ፣

- በክፍሎች መሀከል የሚደረግ ንግድን የመቆጣጠር፣
- የውጪ ንግድን የመቆጣጠር፣
- የውጪ ኢንቨስትሜንትን የመቆጣጠር፣
- የአየር’ ባቡር’ ፖስታ’ ስልክ’ የባህር መጓጓዦዎች መቆጣጠር እና ማስተዳደር
- ሁለት ወይም ከሁለት ክፍል በላይ የሚያገናኙ አውራ ጎዳናዎችን መቆጣጠር፣ ማስተዳደር፣
- የንግድ ህግ (ኮድ) ማውጣት፣
- ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሀገሪቱን እውቀትና ሀብት እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሀብት ክፍፍል ማድረግ፣
- በሁሉም መስክ በእኩልነት መርህ የመመራት፣
- የኢኮኖሚ ርምጃ አካባቢን የማያናጋ መሆኑን የማረጋገጥ፣

ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ስልጣኖች እና ኃላፊነቶች በህገ መንግስቱ የተቀመጡ ሲሆን ከምንከተለው የነፃ ኢኮኖሚ ስርዓት እና አለም ካለችበት ሁኔታ አንፃር ለንግድ እና ኢንቨስትመንት ካላቸው ፋይዳ አንፃር መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

<u>ህግ ማውጣት</u>

ወደ ሃገራችን ስንመለስ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት የንግድ ህግን የሚመለከቱ ጉዳዮች በፌዴራል መንግስቱ ስልጣን ስር መሆኑን በአንቀጽ 51(2)(4) ስር ደንግጓል፡፡

ለኢኮኖሚው አስፈላጊ የሆነው መሬት በመንግስት እና ህዝቡ ባለቤትነት ስር ነው። መሬትን በተመለከተ በፌዴራል መንግስት ስልጣን ስር ሲሆን ሊዝንና መሬትን ማስተዳደር ግን በክልል መንግስታት ስር ነው።

ኢትዮጵያ በ1960 የወጣ የንግድ ህግ አሉት። የንግድ ህጉ በፈረንሳይ የህግ ባለሙያ የተፃፈ ሲሆን በርካታ የሲቢል ሎው ሀገራትን ፅንሰ ሃሳቦችን የያዘ ነው። የንግድ ህጉ ሀገር በቀል ለሆኑ የንግድ ተቋማት እውቅና ያልሰጠ ቢሆንም በተግባር ግን የዚህ አይነት የንግድ ተቋማት በሀገሪቱ ለረዥም ጊዜ ቆይተዋል።

የንግድ ህጉ በጊዜው ዘመናዊ የሆኑ ሐሳቦችን የያዘ ቢሆንም በንጉሱ ዘመን እነዚህ ፅንሰ ሐሳቦች በሕብረተሰብ ዘንድ ሰርፀው ሊገቡ አልቻሉም።

በደርግ ዘመን የንግድ ህጉ ሳይሻርም ሆነ ሳይሻሻል የቆየ ሲሆን በዚሁ ዘመን የወጣው የግል ንብረትን የመንግስት ያደረገው ህግ (የአ.ቁ.26/68) የንግድ ድርጅቶችን የሚመለከተው የህጉ ክፍል ሽባ(inoperative)እንዲሆን አድርጓል። ከዚህ ስርዓት መለወጥ በኋላ የንግድ ህጉን በተመለከተ ህጉ በኢኮኖሚ ስርዓት ውስጥ የንግድ ስራ (commercial, trade, business) የሚላቸውንና የንግድ ስራ ያልሆኑትን ይለያል/የህጉ ቁጥር 5) የንግድ ሕጉ አንቀጽ 124 ስርም "ቢዝነስ" ለሚለው ትርጉም ይሰጣል። በህጉ መሠረት በአንቀጽ 5 ስር የተዘረዘሩትን 21 ተግባራት ሙያ አድርጎ ለትርፍ የሚሰራ ነጋዴ ነው። እነዚህን ተግባራት በመደሰት (hobey) እውቀትን ለማሰራጨት በማሰብ የከወነ ነጋዴ አይሰኝም። ሙያ ተብለው በዘልማድ የሚታወቁት እንደ ህክምና' ህግ' ምህንድስና የመሳሰሉትም ሁኑ ሌሎች ተግባራት (ሂሳብ አያያዝ፣ ማማከር፣ ዲዛይን፣ ፋሽን፣ ኮምፒውተር ኘሮግራመር' የfax, email ንግድ ተግባራት ወዘተ) በተመሳሳይ በንግድ ዝርዝር ውስጥ አይደሉም። ሌላው ቀርቶ ዘልማዳዊው የእኔ ጥበብ ስራ(handicraftsmanship) በዚህ ስር አይሸፈንም። ስለሆነም ይህንን ክፍተት ከህገመንግስቱ መርህ ጋር ለማጣጣም በርካታ የንግድ እና የኢንቨስትመንት ህጎች የወጡ ሲሆን ዝርዝራቸው በሌላ የህግ ትምህርት ይሸፈናል።

<u>ተወዳዳሪነት</u>

የምንከተለው የነፃ ኢኮኖሚ የንግድና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴን መስፋፋት የግድ ይላል። የንግድ እና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ በአለም ላይ እጅግ የተቆራኘ (የተሳሰረ)ነው። በግሎባላይዜሽን ዘመን የመጨረሻው ሀብታም እና ድሃ ሀገር ሳይቀር

የሚቆራኝበት እና የሚተሳሰሩበት አንድ የኢኮኖሚ መስክ ንግድ እና ኢንቨስትመንት ነው፡፡ የአለም ገበያ ውስጥ ንግድ እና ኢንቨስትመንታችን መግባቱ ግድ ከሆነ ደግሞ ተወዳዳሪ (competitive) መሆን ይኖርበታል፡፡ የንግድ እና ኢንቨስትመንት በዚህ መልኩ ተወዳዳሪ መሆን በአለም ገበያ ውስጥ ለመግባት የሚያስችለው ብቻ ሣይሆን በሀገር ውስጥ ገበያ መግባቱ የማይቀረው የውጭ ንግድ እና ኢንቨስትመንት እንዳያጠፋው ጭምር ዋስትና ይሆነዋል፡፡ ይሁን እንጂ የሀገራችን ነጋዴ እና ባለሀብት ተወዳደር ስለተባለ ብቻ ሊወዳደር አይችልም፡፡ ያለንበት ነባራዊ እውነታ በተለያየ መልኩ (በፋይናንስ' የሰው ኃይል') ከተጠናከረው የውጪ ባለሀብት ጋር እንዳይወዳደር ያደርገዋል፡፡ ይህንን ነባራዊ ሁኔታ በህገ መንግስቱ መርሆዎች እና ድንጋጌዎች መሠረት መዋጋት እና ለውድድሩ በቅቶ መገኘት ያስፈልጋል፡፡ የተወሰኑትን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

በህገ መንግስቱ ላይ ከተቀመጡት መብቶች ውስጥ የዜጎች የመስራት፣ እኩል እድል የማግኘት እና የፍትሐዊ ሀብት ክፍፍል ተጠቃሚ መሆን ይገኝበታል፡፡ ይህን ድንጋጌ በመጋፋት የሀገሪቱን ሀብት እኩል ከመካፈል ይልቅ በህገ ወጥ መንገድ ለመስራት የሚጥሩ በንግድና ኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሀብቶች (ሰዎች) ይኖራሉ፡፡ በህገ ወጥ መንገድ ለማካበት የሚደረግ ጥረት ለብቻ የሚሞከር ከሚሆነው ይልቅ ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር በመሆን በጋራ የሚፈፀምም ሊሆን ይችላል፡፡ ለዚህም የመንግስት ቢሮክራሲ አወቃቀር እና ከህዝቡ ጋር ያለው ግንኙነት ይዘቱ ወሳኝ ናቸው፡፡ የመንግስትን ቢሮክራሲ ከተመለከትነው በተለያየ ቅርፅ፣ መልክ እና ይዘት የሚመጣ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይዘቱን ኢኮኖሚ እድገት (ንግድ እና ኢንቨስትመንት)ጋር ካያያዝነው አንዳንዱ ለኢንቨስትመንት ሊውል የሚችለውን በርካታውን ትርፍ(surplus) ለራሱ ከሰበሰባ በኋላ ለማህበራዊ አገልግሎት የሚውል ገንዘብ (collective goods) የማይተው መንግስት ነው፡፡ ይህም የኢኮኖሚ እድገትን ቀፍድዶ የሚይዝ ነው፡፡ ይህንን የመንግስት አይነት "አዳኝ" (predatory) በማለት ፒተር.ቢ.ኢቫንስ የተባለ የ(ማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያ) ይጠራዋል፡፡ የዚህ አይነቱ መንግስት ለታዳኝ(prey)ምንም አይነት ርህራሄ የሌለው ያገኘውን ታዳኝ ሁሉ የሚበላ ነው፡፡ የሞቡቱ ሴሴሴኮ ዘመን ዛየር መንግስት በዚህ ይገለፃል፡፡ ሌሎች የመንግስት አይነቶች የኢንቨስትመንት እንቅፋቶችን በማስወገድ ኢንቨስትመንት እና ንግድ እንዲስፋፋ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ አንዱ ንግድ ሌላውን እየወለደ እንዲስፋፋ የሚያደርግ የረዥም ጊዜ ስራ ፈጣሪያዊ እይታ (entrepreneurial

perspective) ያላቸው ናቸው፡፡ ከንግድ የሚገኙ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጥቅሞችን ለራሳቸውና ለወዳጃቸው ሳይሆን ለህብረተሰቡ በጠቅላላው እንዲውል የሚያደርጉ ሲሆን የኢኮኖሚ እድገትን የሚያቀላጥፍ ናቸው፡፡ ጀንስን ዋይት እና ዋድ የዚህ አይነት መንግስታትን ልማታዊ መንግስት (developmental state)በማለት የሚገልፁት ሲሆን ጃፓን እና ሀገራችን በምሳሌነት ትጠቀሳለች፡፡ በመሀል በርካታ አይነት መንግስታት ያሉ ሲሆን ሚዛኑ ወደ አዳኙ የተጠጋና ለልማት እንቅፋት የሆነው ኪራይ ሰብሳቢ (Rent seekers) ይባላል፡፡ አዳኝ እና ኪራይ ሰብሳቢ የሆኑትን መንግስታት የተመለከትን እንደሆነ በንግዱ አለም ውስጥ ከሚገኙ "ደጋፊዎቻቸው" ጋር በልውውጥ የሚሰሩ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ይህ የልውውጥ ግንኙነት ገበያው በነፃ እንዳይሰራ በማድረግ "ደጋፊ"ን ብቻ የሚወግን ይሆናል፡፡ ይህ በመሆኑም የገበያ ውድድር አይኖርም፡፡ የሚኖረው ውድድር የኪራይ ሰብሳቢነት ቦታ ለመያዝ ነው፡፡ ክሩገር እንዳለውም የመንግስት ቦታን ለመያዝ የሚደረግ ውድድር በከፊልም ለ"ኪራይ ሰብሳቢነት" የሚደረግ ውድድር ይሆናል፡፡ ንፁሃንም ወደዚህ እንዲሳቡ ሆኖ የተሳካ(efficient) ንግድ እና የገበያ መሳለጥ (dynamism) ያቆለቁላል፡፡

የዚህ አይነት መንግስት እድገትን ገትቶ ሃገርን የሚያጠፋ ነው፡፡ ይሁን እንጂ መንግስት በዚህ መልኩ መስራት የሚችል ስለሆነም ብቻ መንግስት አያስፈልግም አያስብልም፡፡ ከከራይ ሰብሳቢው የተለየ ልማታዊ መንግስት በተቃራኒው ይሰራል፡፡ ልማታዊ መንግስትም በገበያ ውስጥ በተለያየ መልኩ ጣልቃ እየገባ ይሰራል፡፡ መንግስት የቀደመ ተግባሩን (ማስገደድ) ወይም ውልን የማስፈፀምን ኃላፊነት ብንመለከት እንኳን በገበያ ውስጥ በምንም መንገድ ሊገባ አይገባም የሚባል አይደለም፡፡ ከቀደሙት ፀሐፊዎች አንስቶ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ያሉት መንግስት በገበያ ውስጥ ቁርጠኛ እና ውጤታማ (determined and effective)ሚና ሊኖረው ይገባል በማለት ይስማማሉ፡፡ ዋይት እና ዋድ የተባሉ ፀሐፊዎችም በዚሁ ሐሳብ በመስማማት ወደኋላ ላይ እያደጉ የመጡ ሀገራት ውስጥ ያሉ መንግስታት ሚናቸው ስትራቴጂካዊ አመራር መስጠት ሆኖ የሀገር ውስጥ እና አለምአቀፍ ገበያውን በማላመድ ለብሔራዊ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲውል በማድረጋቸው እንደሆነ ይገለፃል፡፡ መንግስት ይህንን መሰል ለውጥ ለማምጣት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ውስጥ ከላይ የተመለከትነው የውስጥ አንድነት (Internal Coherence) እና ከህብረተሰቡ ጋር ያለው ግንኙነት በመርህ ላይ የተመሰረተ መሆኑ

ወሳኝ ናቸው፡፡ እነዚህን ነጥቦች በተመለከተም ህገ መንግስቱ ከተወዳዳሪነት አንፃር የሚከተሉት መርሆዎች አሉት፡፡

**መሪነት**

መንግስት ለንግድ እና ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታዎችን ከመፍጠር በተጨማሪ ለዚሁ አስፈላጊ የሆኑ ሀብቶችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡ (አንቀጽ 84/1/'(5)) ገበያው ነፃ ይሁን እንጂ የመንግስት መሪነት ሚና ግን ወሳኝ ነው፡፡ የጃፖን እድገት ልምድ የሚያሳየን ይህንን ሲሆን የሀገራችን ነባራዊ ሁኔታም መንግስት የመሪነት ሚናውን እንዲጫወት ግድ ይለዋል፡፡ ወደ እድገት ጎዳና ዘግይተን እየገባን ያለን እንደመሆናችን መጠን ሒርሽማን እንዳለው በፈጠነ እና በተጠና (less spontaneous and more deliberate)መንገድ ማድግ ይኖርብናል፡፡ በተፋጠነ መልኩ ለማደግ ብሔር ብሕረሰቦች እና ህዝቦች መቁረጣቸውን በህገ መንግስቱ መግቢያ ላይ ተመልክተናል፡፡ የወረስነው ታሪክ በአመዛኙ ስራ ከመፍጠር ይልቅ ተቀጥሮ ማገልገል የሚበዛበት በመሆኑ መንግስት ዜጎች ስራ እንዲፈጥሩ የማበረታታት እና ሥራ ራሱም የመፍጠር ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 41(6)(7)ስር መንግስት የሥራ እድል ለመፍጠር የሥራ ኘሮግራም እንደሚያወጣ እና ኘሮግራሞችን እንደሚያካሂድ ተገልጿል፡፡ መንግስት በንግድ ስራ መስክ በተመረጠ መልኩ ስራ ፈጣሪ እና ሥራ ለመፍጠር የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች (enterpreuner State)ነው ማለት ነው፡፡

**ጣልቃ መግባት**

በሌላ በኩል በየትኛውም ሀገር እንደሚያጋጥመው ሁሉ በንግድ እና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ውስጥ የገበያ ጉድለት (market failure) ሊያጋጥም ይችላል፡፡ በሀገራችን በስፋት ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ይህንን ጉድለት ገበያው እና ተዋንያኑ በተለይ ሊፈቱት ይጠበቃል፡፡ ይሁን እንጅ ከአጭር ጊዜ አንፃር መንግስትም ይህንን ጉድለት ለማስተካከል ጣልቃ መግባቱ አይቀርም፡፡ ለምሳሌ ገበሬዎች እና አርብቶ አደሮች በገበያ ካላቸው ልምድና እውቀት የተነሳ የገበያው ዋጋ ለምርት ካደረጉት አስተዋፅኦ ጋር የተመጣጠነ ክፍያ ሊፈጸምባቸው ይገባል፡፡ ይህንን ገበያው የሚፈፅመው ሲሆን በአንቀጽ 41/8/ መሠረት መንግስት የሚመራበት መርህም ነው፡፡ የልማት መብትም ዋና አላማ የዜጎችን እድገት ማረጋገጥ መሠረታዊ ፍላጎታቸው እንዲሞላ ማድረግ በመሆኑ የግል ባለሀብቶች በማይገቡባቸው ወይም ቢገቡባቸውም በዚህ መሠረት በማይፈፀሟቸው ተግባራት

እንዲሁም በሌሎች የንግድ ጉዳዮች ላይ መንግስት ንግዱን የመምራት እና የመቆጣጠር ኃላፊነት ተጥሎበታል:: (የህገ መንግስቱ አንቀጽ 43/1/' 3' 51/4/'9'12 ለአብነት ይመልከቱ፡፡) ንግድ እና ኢንቨስትመንት በነፃ ገበያ ውስጥ በጠንካራ የውድድር መንፈስ ብቻ ካልተመራ በውጤቱ አንደኛው አቅራቢ እና ተወዳዳሪ ብቻ ያለአግባብ መጠቀሙ አይቀርም፡፡ ይህ ደግሞ ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እንዲከፋፈል የማያደርግ በመሆኑ መንግስት በህገ መንግስት አንቀጽ 89/2/ በተቀመጠው ፍትሐዊ የሆነ የሀብት ክፍፍልን ማረጋገጥ መርህ መሰረት ጣልቃ ሊገባ ይገባዋል፡፡

መንግስት ጣልቃ ሊገባ የሚገደድበት ሌላው ምክንያት ልማታዊ መንግስት እንዳይሆን የሚፈታተኑ ተግባራት ሲፈፀሙ ነው፡፡ ይህም የመንግስትን የውስጥ መናበብ (Internal Coherence) መርህ የሳተ ያደርገዋል፡፡ የህገ መንግስቱን መርህ ማዛባት በመንግስት ባለስልጣናት እና በንግድ ድርጅቶች እንዲሁም በግለሰቦች ሊፈፀም ይቻላል፡፡ ከመገለጫዎች አንዱ በግልፅ የሚታወቀው የሙስና ተግባር ነው፡፡ የሙስና ተግባር ገበያን ለማዛባት ሊፈፀም የሚችል ሲሆን በሌላ በኩል የጉደለን ገበያ ለማስተካከል መንግስት ጣልቃ በገባ ጊዜም ቢሆን የመፈፀም እድል አለው፡፡ ይህንን ለመዋጋት የሚያስችል ትልቅ መርህ ህገ መንግስቱ አስቀምጧል፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 12/1/ መሠረት የመንግስት አሰራር ለህዝብ ግልፅ መሆን አለበት፡፡ መንግስት በንግድ እና ኢንቨስትመንት ስራ ውስጥ ጣልቃ ሲገባ አገባቡ ለህዝቡ በአጠቃላይ ለንግዱ ማህበረሰብ በተለይ ግልፅ መሆን አለበት፡፡ ይህንን አለመፈፀም ኃላፊነትን ማጓደል እና ህገ መንግስትን መጣስ ነው፡፡ ኃላፊነቱን የሚያጓድል የዚህ አይነቱ ኃላፊ ደግሞ በአንቀጽ 12/2/ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ከኃላፊነቱ እንዲነሳ በህዝቡ እና በመንግስት ሊጠየቅ ይችላል አንቀጽ 12/3/፡፡ የስነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን በወንጀል ድርጊት በፍ/ቤት ሊጠይቀው ይችላል፡፡ (በፍ/ብሔር ህግ ቁጥርግ 2033 መሠረትም በፍ/ብሔር የሚያስጠይቅ ጥፋት ነው)፡፡ እንደሁኔታውም በፍ/ብሔር ክርክር ሊጠየቅ ይችላል፡፡ ገበያው እንዲዛባ ያደረገው ግለሰብ ወይም የንግድ ድርጅት በሆነ ጊዜም በተመሳሳይ መልኩ ይጠይቃል፡፡ ለዚህ እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ የሚችሉት በነፃ ገበያ ስርዓት ውስጥ ሰዎች በንብረት የመጠቀም መብታቸው እንዳይከበር የሚያደርጉ' የማስገደድ' የማታለልና' የማሳሳት እና የመሳሰሉት ተግባራት ናቸው፡፡ እነዚህን መሰል ተግባራት ለመቆጣጠር መንግስት የወንጀል ክስ በመመስረት ገበያውን ለማረጋገት ጣልቃ ይገባል፡፡ በተለምዶ የደረቅ ቼክ የሚባሉ' የአራጣ' ብድር' የታሪፍ ማጭበርበር' የግብር ስወራ'

የVAT ክፍያን ለራስ ማስቀረት እና የመሳሰሉት ተግባራት ገበያውን የሚያዛቡ ከመሆናቸውም በላይ ወንጀል በመሆቸው ለፍ/ቤቱ የሚቀርቡ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ የነፃ ገበያ ስርዓት ጀማሪዎች እንደመሆናችን መጠን የዚህ አይነት ክሶች ተበራክተው መቀጠላቸው አይቀርም፡፡ ወደፊት የሚፈፀሙ ወንጀሎችም ከለመድናቸው ወንጀሎች የተለዩና የማታለል ይዘት ያላቸው ውስብስብ እና በኢኮኖሚ አደጋ እየሆኑ መምጣታቸው አየቀርም፡፡ ስለሆነም መንግስትም በዛው ልክ እና አይነት ጣልቃ መግባቱ ግድ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ግለሰቦች (የንግድ ድርጅቶች) በፍ/ብሔር ክስ ሊቀርብባቸው ይችላል፡፡ ያልተከፈለ ግብር እንዲከፈል' በድርጊታቸው ያደረሱት ጉዳት በተመጣጣኝ ካሳ እንዲመለስ በፍ/በሔር ጉዳይ ይጠይቀሉ፡፡ በንግድ እና ኢንቨስትመንት የተሰማራ ሰው በዚሁ ስምሪት የተነሳ በሌላው ሰው ላይ ጉዳት እንዳያደርስ የፍ/ብሐር ክልከላ ያሉበት ከመሆኑ በላይ በንግድ ህጉ መሠረት "ነጋዴ" የሚሰኝ በመሆኑም በሙያው የተደነገጉ የንግድ ደንቦችን መጠበቅ ይገባዋል፡፡ ይህንን ባይፈፀም በፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 2031 መሠረት በመስኩ ሙያዊ ጥፋት መፈፀም ነው፡፡ በንግድ ስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት በገንዘብ ብቻ ላይካስም ስለሚችል አግባብ ባለው በሌላ አኳኋንም እንዲካስ ጥያቄ ሊቀርብ ይችላሉ፡፡ የጠፋ ስም እንዲመለስ፣ የተወሰደ እቃ ከኪሳራ ጋር እንዲተካ ወይም በአይነት እንዲመለስ፣ ጉዳት እያደረሰ ያለው ድርጊት እንዳይቋረጥ ወይም እንዳይጀመር እንዲሁም ተገቢ ያልሆኑ ውድድሮች እንዲቆሙ ለማዘዝ ይችላሉ (ቁ.2118 - 2122)፡፡ በሌላ በኩልም በሰው ጉልበት ወይም ሀብት ያላግባብ የበለፀገ ሰው ጉዳት በደረሰበት ሰው ኪሳራ መክፈል እንዳለበት የፍ/ብሐር ሕግ ቁጥር 2162 እና ተከታዩች ቁጥሮች ይደነግጋሉ፡፡ ይህ ጥፋት በህገ መንግስት ላይ የተደነገገውን ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል መርህ የሚጥስ ነው፡፡ እነዚህ እና መሰል መብቶች ውል ሳይኖር ለደረሰ ጉዳት አግባብ ያላቸው ሲሆን በጥንቃቄ መፈፀማቸው የገበያ ጉድለትን በማስተካከል እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡ የንግድ እንቅስቃሴ አሳሳች እንዳይሆን የሚያስችሉ ድንጋጌዎች በተመሳሳይ በንግድ ህጎቻችን ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እነዚህን በቀጥታ የማስፈፀም ኃላፊነት የፍትህ አካላት ሲሆን መንግስት ገበያውን ለማስተካከል በዚህ ረገድ ያሉት ኃላፊነት  የንግድ እና ኢንቨስትመንት ስርዓት በገበያ ውስጥ ያላቸው ሚና በአግባቡ የተረዳ ጠንካራ የፍትህ ስርዓትን መገንባት ነው፡፡ ይህ ዘርፍ ከዘርፉ የተጠያቂነት ማዕቀፍ ለ"ኪራይ ሰብሳቢነት" ለመዋጋት አስተማማኝ መሠረት ናቸው፡፡ ዝርዝሩ በሌላ ህግ የሚታዩ ቢሆንም የውል ሳይኖር ኃላፊነት ህግ በአግባቡ ከተፈፀመ ወንጀልን ለመከላከል ብቻ

ሳይሆን በህገ መንግስቱ ላይ የተመለከተውን በህይወት የመኖር እና አካል ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የመጠበቅ መብትንም በሚገባ ማስከበር ያስችላል፡፡

መንግስት በፍትህ ስርዓቱ ውስጥም ሆነ በአስተዳደሩ (ቢሮክራሲው) ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች በብቃታቸው እና በታታሪነታቸው የተመሰገኑ ከሙስና የፀዱ መሆናቸውን በምልመላ በስርዓቱም ሆነ በግልፅነት እና ተጠያቂነት አሰራሩ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ የበቃ (meriterious) ባለሙያ እና ኃላፊ መኖር የልማታዊ መንግስት አንዱ መገለጫ መሆኑን ፀሐፊዎች ያሰምሩበታል፡፡ መንግስት የውስጥ አወቃቀሩ ይህንን ያዘለ መሆኑ በገበያ ውስጥ መቼ እና በምን ሁኔታ ጣልቃ ይግባ የሚለውን በተጠናከረ መልክ እንዲመልስ ያደርገዋል፡፡

<u>ሌሎች መርሆዎች</u>

መንግስት በንግድ እና ኢንቨስትመንት ውስጥ የሚገባበት ሌሎች የህገ መንግስት መርህ የእኩልነት እና ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል መርህ ናቸው፡፡ ነጋዴ በውድድር አለም ገበያ ውስጥ በመግባት ከመወዳደር ይልቅ በተለያዩ የድጎማ ማበረታቻዎች (በታክስ ክፍል ውስጥ እንመለከተዋለን) ለመንጠላጠል የመፈለግ አዝማሚያው ቀላል አይሆንም፡፡ በሀገራችን በተለይ በውድድር ለመስራት የቀደሙ ስርዓቶች ያልፈቀዱና አመለካከታችን በዚሁ ያልተቀረፀ በመሆኑ ችግሩ ሰፊ ነው፡፡ በቀላሉ ምሳሌ የባንክ ወለድ ይሰረዝልኝ በማለት ከሚጠይቀው አንስቶ ከታክስ ነፃ ልሁን እያለ በተለያየ ደረጃ ጥያቄ የሚያቀርብ በርካታ ነው፡፡ ይህ ቢፈፀም ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልን የሚያደናቅፍ' የእኩል እድል መርህን የሚነካ በመሆኑ አይበረታታም፡፡ ከህገ መንግስቱ መርህ አንፃር ይህ የማይበረታታ ሲሆን ባለሀብቱ (ነጋዴው) ወደ ብሔራዊ እና አለምአቀፍ ገበያ መግባት ይችል ዘንድ ግን መጠናከር ይገባዋል፡፡ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ነጋዴው ለዚህ ደረጃ ለመብቃቱ ሊጠናከር የሚችለው ያለንን ውስጥ የካፒታል አቀም በቁጠባ እንዲሁም ያለንን ስፊ የሰው ጉልበት በስፋት መጠቀም ሲቻል ነው፡፡ የማክሮ ኢኮኖሚውን ማረጋጋት' አሰራሩ ሁሉ የገበያ ውድድርን የሚያጠናክር' የህግ ማዕቀፎች እና ትርጉማቸው ይህንን ሁሉ የሚደግፍ እንዲሆን ማድረግ' ስለታክስ በተመለከተው ክፍል እንደተመለከተው የግብር ስርዓቱ ልማታዊውን የሚበረታታ ማድረግ' በምዝገባ (ለንብረት' ውል' ንግድ' ሂሳብ' መሠረታዊ መረጃ' ---)የተጠናከረ ስርዓት መዘርጋት' የረዥም ጊዜ ንግድ እና ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ በመረጃ የታገዘና ብቃት ያለው

የፋይናንስ ስርዓት(ባንክ' ኢንሹራንስ' ጡረታ' ዋስትና' ባንክ ነክ አገልግሎት- - - )መዘርጋት እና ጠንካራ እና አስተማማኝ የመሰረተ ልማት አገልግሎት ማቅረብ ካፒታልን ጉልበትን በአግባቡ ለመጠቀም ያስችላል፡፡ ጠንካራ የፍትህ ስርዓት አለ ለማለት ይህንን የንግዱን መሳለጥ የህብረተሰቡ እና የነጋዴውን ሚና በጥንቃቄ እና በዝርዝር ተረድቶ ለኢኮኖሚ እድገት የበኩሉን አስተዋፅኦ ሲያበረክት ሊታይ ይገባዋል፡፡

ለማጠቃለል ህገ መንግስቱ በህግ የበላይነት መርህ ላይ የተመሰረተ መሆኑ በመግቢያው ላይ ተሰምሮበታል፡፡ በንግድ እና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ውስጥም የተፋጠነ እድገት ለማምጣት መሠረቱ ህግን መሠረት ያደረገ አካሄድ (law based approach)ነው፡፡ በዚህ መሠረት በመንግስት የሚወጡ የንግድ እና ኢንቨስትመንት ህጎች እንደ ክር በመሆን የኢኮኖሚ፣ፖለቲካዊ፣ እና ማህበራዊ ግቦችን ያስተሳስራሉ፡፡ እነዚህ አላማዎችም ግልፅ እና ፍትሐዊ በሆነ አግባብ እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡ በርካታ ዲሲፕሊኖችን ያቀፈ በመሆኑም የህግ ባለሙያው ከምጣኔ ሐብት ባለሙያ' ፖሊሲ አውጪው' አስፈፃሚው' ሂሳብ ባለሙያው ጋር በቅርበት እንዲሰራ ያስገድዳሉ፡፡ ከህግና ከባለሙያዎች በተጨማሪ ጠንካራ ፋይናንስ ተቋማት እንዲኖሩን ተቋማቱ ንግድና ኢንቨስትመንትን የሚያበረታቱ ቁጠባን ባህል በማድረግ ውጤታማ በሆነ አግባብ ጥቅም ላይ እንዲውል ስለሚያደርጉ የንግድ እና ኢንቨስትመንት ተግባራት በጠንካራ (Robust) መሠረት ላይ ይጣላል፡፡ የንግድ እና ኢንቨስትመንት ስርዓታችን ከላይ በተመለከተው አግባብ በመርህ ወጥነት (Coherent) ላይ ተመስርቶ ቅደም ተከተሉ(Sequenced)ይኑረውም እንጂ አንዱ ከሌላው ጋር በጥበቃ የተሳሰረ (interconnected)' በግልፅ እና ሙስናና አለምአቀፍ ወንጀሎችን በየደረጃው ለማጥፋት የሚያስችል አወቃቀር እና ተቋም ያለው እንዲሁም የወረስናቸውን የንግድ እና ኢንቨስትመንት ችግሮች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እና አመራር እየገመገመ (Evaluation) ለህገ መንግስቱ ግብ መሳካት መስራትን ያለመ ነው፡፡ በተቋሙ ውስጥ ያሉ አመራሮች እና ፈፃሚዎች በአጠቃላይ በተለይ ደግሞ የፍትሕ ስርዓቱ እነዚህን የህገ መንግስት መርሆዎች ከንግድ እና ኢንቨስትመንት አንፃር ያላቸውን የጀርባ ምክንያት በሚገባ ተረድቶና ራሱን አብቅቶ ከፈፀመ የንግድና ኢንቨስትመንት ማህበረሰብ እምነት (confidence) ማትረፍ የሚችል ሲሆን በዚህም የሀገር ኢኮኖሚ በአስተማማኝ መሠረት ላይ ተጥሎ እድገቱ እንዲፋጠን ያደርጋል፡፡

## የመወያያ ጥያቄ

1. ንግድና ኢንቨስትመንትን በተመለከተ የህገ መንግስቱ መሰረታዊ መርህ ላይ ተወያዩ።
2. ህገ መንግስቱ ከንግድ እና ኢንቨስትመንት አንፃር ግብርና' ኢንዱስትሪ' የውጪ ባለሀብት' መንግሰት እና የገንዘብ ተቋማትን'
   - እንዴት ወጥ አቋም እንዳለው
   - እንዴት እንደሚያስተሳስራቸው
   - ከረዥም እና አጭር ጊዜ አንፃር የሚከተላቸው መርሆዎች
   - እንደ ጤና (በተለይ HIV/Aids)' ትምህርት ንግድና ኢንዱስትሪ ላይ ያላቸውን አሉታዊ እና አፍራሽ ሚና ተወያይ። ጠንካራ የፍትህ ስርዓት መኖሩ በተ.ቁ 2 ስር የተመለከቱ አካላትን እንዴት ሊያበረታታ እንደሚችል እና በኢኮኖሚ እድገት ምን ፋይዳ እንዳለው በመዘርዘር ተወያይ።
3. በህገ መንግስቱ የንግድ ህግ ማውጣት ስልጣን ለፌዴራል መንግስቱ የተሰጠበትን ምክንያት አብራርተህ ተወያይ።
4. ከንግድና ኢንቨስትመንት አንፃር የኢፌዲሪ መንግስት በምን ይገለፃል? በምን?
5. ሀገሪቱ በተከታታይ እያስመዘገበች ባለው የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ የፍትህ አካላት ሚና (በአሉታዊ በእምነታ)ምን ሊሆን እንደሚችል በማበራራት ተወያዩበት።

# ክፍል ስምንት

# ከአሰሪና ሰራተኛ ህግ አንፃር የህገ መንግስቱ መሠረታዊ መርሆዎች እና አቅጣጫዎች

## 1. ጠቅላላ

የአሰሪና ሠራተኛ ህግ ስንል በጥቅሉ የአስተዳደር አካላት ደንቦች፣ የፍ/ቤት ውሳኔዎች፣ የሌሎች ህጎች ስብስብ ሆኖ የሰራተኛውን እና አሰሪውን (ድርጅቱን) የስራ መብት እና ገደብ የሚመለከት ህግ ነው። በሰራተኛ ማህበራት፣ ሰራተኛ እና አሰሪ መሀከል እና

በመንግስት መካከል ያሉ (የሚኖሩ) ግንኙነቶችን የሚቃኝ (የሚያስታርቅ) ህግ ነው፡፡ ግንኙነቱ የ3ትዮሽ እና የሁለትዮሽ ሲሆን ስለሚችል በወል እና በግል የስራ ግንኙነት ተለይቶ ይጣራል፡፡ የተሻለ የስራ ሁኔታ ፍለጋ እና የመደራጀት ፍላጎት በሰራተኛው በኩል እያደረ መምጣቱ፣ በሌላ በኩል የስራ ዋጋን ዝቅ የማድረግ የአሰሪ ፍላጎት የፈጠሩት ፍትጊያ እና ትግል ለህጉ መዳበር አስተዋፅኦ ማድረጋቸው ይነገራል፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ህግ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚካሄዱ የተለያዩ ትግሎች ውጤት ነው፡፡ ህግ የትግሉ ውጤት ብቻ ሳይሆን ትግሉ የህጉ አካል (Component) ነው፡፡

አለማችን ላለፉት አስርት አመታት ይበልጥ እየጠበበች አንድ ማህበረሰብ የሚኖርበት የምትመስል መንደር መምሰሏ ተደጋግሞ የተገለፀ ነው፡፡ የግሎባላይዜሽን ዘመን ነፃ የኢኮኖሚ ስርዓትን በተመሳሳይ መልኩ አስፋፍቷል፡፡ ነፃ የሰራተኛ ዝውውርም እንዲኖር አድርጓል፡፡ ነፃ የሰራተኛ ዝውውር ማለት ግን ለሰራተኛው የሚከፈል የጉልበት ክፍያ ከስብዕና ውጪ ምክንያታዊ ያልሆነ ሊሆን ይችላል ማለት አይደለም፡፡ የስራ እና ንግድ ግንኙነት ከዚህ በላይ ከመሠረታዊ የሰው ልጅ መብት አንፃር መታየት ያለበት ነው፡፡ ሀገራችን የተቀበለችው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች(Covenants) እና ሁሉ አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ መግለጫ (Universal Declaration Of Human Rights) እነዚህን መብቶች ይዘዋል፡፡ የንግድ ነፃ መሆን (liberalization of trade) እና የኢንቨስትመንት መስፋፋት የሰራተኛን መደራደር አቅም በማሳጣት ለጉልበት ብዝበዛ እንዳይዳርጉት በማሰብ የተቀመጡ ድንጋጌዎች (ስምምነቶች) ይከበራሉ፡፡ ከእነዚህ ስምምነቶች ውስጥ በተለይ አሰሪና ሰራተኛን የሚመለከተው የአለምአቀፉ ሥራ ድርጅት International Labour Organiation (IL0) ስምምነቶች ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ይህ ስምምነት መሠረታዊ መርሆዎችን የያዘ ሲሆን ድንጋጌዎቹም በመሠረቱ በየትም ሀገር ውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ የሚሆኑ ናቸው፡፡ የአፈፃፀሙ ሁኔታ ግን እያንዳንዱ ሀገር በደረሰበት ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ የእድገት ደረጃ አንፃር የሚወሰን ነው፡፡ ይህ የተለማጭነት (Principle of Flexibility) መርህ በኋላ የመጣ ሲሆን አለም አቀፍ የስራ ደረጃዎች አፈፃፀም የየሀገሩን የእድገት ደረጃ ልዩነት መሠረት በማድረግ እንደ ምቹነታቸው መፈፀም እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ነው፡፡ የእድገት ደረጃ ልዩነት ግን በጋራ መደራደር እና የመሰብሰብ ነፃነት ላይ፣ በግዳጅ ስራ ላይ፣ በቅጥር እና በደመወዝ ክፍያ ላይ ልዩነት አለማድረግ እና የህፃናት ጉልበት ላይ የተደረሱ አለም አቀፍ ስምምነቶችን ለመጣስ ይቅርታ የሚያሰጡ አይደሉም፡፡

እነዚህ ድንጋጌዎች በILO ስምምነቶች ውስጥ ብቻ ሳይሆን በ1966 በወጡት አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች ውስጥም ተካተው ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ የ1966 ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ስምምነት ሰነድ በአንቀፅ 6 ስር ስራን በነፃ ፈቃድ መምረጥ (free choice of employment)፣ በአንቀጽ 7 ስር ተስማሚ እና ተገቢ (just) የሆነ የስራ ቦታ ሁኔታ ማግኘትን፣ በአንቀጽ 8 እና 9 ስር የመሰብሰብ እና በጋራ የመደራደር (bargaining) መብትን እንዲሁም በአንቀጽ 10 ስር የህፃናት ጉልበት ብዝበዛን ማጥፋትን የሚመለከት ድንጋጌዎችን ይዟል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሲቪል እና የፖለቲካዊ መብቶች ስምምነት በአንቀጽ 8 ሰር እንደባርነት' በግዴታ አገልጋይነት (servitude) የመሳሰሉት የግዳጅ ስራዎች የተከለከሉ መሆናቸው ሲደነገግ የ1989 ህፃናት ስምምነት በበኩሉ ስለህፃናት ጉልበት፣ ህፃናትን አደገኛ በዝባዥ ጤናማ ካልሆኑ የስራ ሁኔታዎች ለመጠበቅ፣ የወደፊት የትምህርት እድላቸውን (prospectus)አደጋ ላይ ከሚጥል ስራ የመጠበቅ፣ ሀገራት አነስተኛ የህፃናት ሥራ እድሜ ከመወሰን ባለፈም የስራ ሁኔታዎቻቸውና ጊዜው(ሰዓት) በልዩ ሁኔታ ተወስኖ ቁጥጥር እንዲደረግበት የሚያስገድድ ድንጋጌዎችን የያዘ ነው፡፡

በILO ስምምነቶች እና በቀሪ አለምአቀፍ ስምምነቶች መሀከል ያለው መወራረስ የሚያሳየን የስራ ሁኔታን በተመለከተ የወጡት ስምምነቶች አለምአቀፋዊ' ሆነው በሁሉም ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ሁኔታዎች ውስጥ ተፈፃሚ መሆን እንዳለባቸው ነው፡፡ በ1945 የተቋቋመው የተባበሩት መንግስታት አባል ሀገራትም እነዚህን መርሆዎች ዘርን፣ ፆታን፣ ቋንቋን፣ ኃይማኖትን መሠረት በማድረግ ልዩነት ሳያደርጉ እንዲከበሩ የማድረግ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል፡፡

የስምምነቶች መሠረት በርካታ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ለሰው ልጅ ሊሰጠው የሚገባው ክብር (Dignity) ሲሆን በተለይም የሰው ልጅ በስራ ቦታ እና በስራ ላይ ሊኖረው የሚገባው ክብር ነው፡፡ ይህ "ጉልበት ሸቀጥ" አይደለም በሚለው አባባል የሚገለፅ ነው፡፡ በሌላ በኩል የነፃ ኢኮኖሚ የሚያስገኘው ጥቅም ሰራተኞች ፍትሐዊ የሆነ ድርሻቸውን(fair share) ያገኙ ዘንድ የእነዚህ መሠረታዊ መብቶች መከበር አስፈላጊ ነው:: ነፃ መሆን የማያልፋቸው መለኪያዎች (Standards)የግድ ያስፈልጉታል፡፡ በነፃ ገበያ ስርዓት ውስጥ ጉልበት እንዲለማ እና በነፃነት የመዘዋወር ዋስትና እንዲያገኝ

የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በሌላ ጎኑ ሲታይም ለነፃ ኢኮኖሚ እድገት መጠናከር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡

በሀገራችን በተለይ ከ1941 (በኋላ) የኢንዱስትሪ ማቆጥቆጥ ጋር ተያይዞ በደመወዝ ላይ የተመሰረተ የሥራ ግንኙነት መጀመሩ ይነገራል፡፡ ይህ ጊዜ ሰራተኞች የተናጠል ሳይሆን የጋራ እንቅስቃሴ ለጋራ ጥቅም ጠቃሚ መሆኑን የተረዱበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጊዜ የነበረው የጋራ ጥቅም እንቅስቃሴ በህብረተሰቡ ውስጥ በስፋት ከሚታወቁት መረዳጃ ማህበራት (እድር’ እቁብ . . .) አስተሳሰብ ብዙም ያልዘለለ ሆኖ ሰራተኛን ከስራ አደጋ፣ ስንብት እና ህመም የተነሳ የሚደርሱበትን ችግሮችን ለመርዳት ያለሙ ነበሩ፡፡ የዚህ ፍላጎት በተለይ እንግሊዝ በሀገራችን በነበረችበት ወቅት የፈረንሳይ ኢትዮጵያ ምድር ባቡር ሰራተኞች ማህበር እንዲመሰረት ያደረገ ሲሆን በኋላ ላይም የማህበር ምስረታን የሚያጠናክር የፋብሪካዎች አዋጅ(አ.ቀ. 58/36) ወጥቷል፡፡ ይህ ህግ በስፋት በስራ ላይ ሳይውል በ1966 ተሽሯል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የሰራተኛ ማህበር ምስረታን የሚደግፍ ህግ ከጊዜ በኋላ የወጣው (የተሻለ) በ1955 ህገ መንግስት ነው፡፡ ይሁን እንጅ የህገ መንግስቱን ድንጋጌ ስራ ላይ የሚያውል ህግ እና መመሪያ ባለመውጣቱ በመንግስት ሆነ በሰራተኛው ላይ የአሰሪና ሠራተኛው ድንጋጌ "መጠራጠርን’ ጥንቃቄ መውሰድንና እምነት ማጣትን ፈጥሮ" ነበር፡፡ በሰራተኛ እና አሰሪ መሀከል የሚነሳ አለመግባባት የሚፈታበት መድረክ ያልነበረ በመሆኑም ሰራተኞች አቤቱታቸውንና የህግ ጥያቄያቸውን በሰልፍ ቤተ መንግስት ከማቅረብ ያለፈ አማራጭ አልነበራቸውም፡፡ ችግሩ የፈጠረው ግፊት የሰራተኛው ግፊት እየጨመረ መምጣት፣ የተደራጀ ሰራተኛ እና አሰሪ ባለመኖሩ ሀገሪቱ አባል በሆነችበት ILO ውስጥ መሳተፍ አለመቻሏ፣ ከአፍሪካ የዚህ መሰል ህግ የሌላት ብቸኛ ሀገር መሆኗ፣ የውጪ ኢንቨስትሜንት ለመሳብ የነበረ ፍላጎት በተከታታይ ለወጡ የአሰሪና ሰራተኛ ህጎች እንደምክንያት ይጠቀሳሉ፡፡ በዚህ መልኩ ከወጡ የአሰሪና ሰራተኛ ህጎች ውስጥ በ1952 የወጣው የፍ/ብሔር ህግ፣ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ መሠረታዊ የሥራ ሁኔታ ደንብ፣ ትዕዛዝ ቁጥር 27/54፣ እንዲሁም ከ1954 እስከ 1958 የወጡ ልዩ ልዩ ደንቦች፣ ትዕዛዞች እና የህግ ክፍል ማስታወቂያዎች ይጠቀሳሉ፡፡

በዚህ ዘመን ሰራተኛ ማን ነው? የሰራተኛ ግዴታ ምንድን ነው? በምን ሁኔታ ይሰራበታል? የሙከራ ቅጥር ጊዜ በምን ሁኔታ ይፈፀማል? የክፍያ ሁኔታ በምን

መልኩ ይፈፀማል? በበዓላት ቀን ስለሚኖር ክፍያ እና ስራ? የትርፍ ሰዓት ክፍያ በምን መልኩ ይፈፀማል? ዕረፍት እና አይነቶቹ? የሥራ ላይ አደጋ እና በሽታ? እና ሌሎች ጥቅሞች ካሉ የሚመሩት በ1952 የፍ/ብሔር ሕጉ ነበር፡፡

አስገዳጅ ባይሆንም የስራ ክርክሮችን በማስታረቅ የሚፈታ አካል በወቅቱ "በሕዝባዊ እድገትና የማህበራዊ ኑሮ ጉዳይ ሚኒስቴር" በመባል የሚታወቀው መ/ቤት ውስጥ ለተቋቋመ የሥራ ክፍል ማቅረብ ይቻለ ነበር፡፡ በኃላ ላይ የተቋቋመው አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ(አ.ቁ.210/56(?))የማስታረቅ' የማገላገል ካስፈለገም የመወሰን ስልጣን እንዲኖረው በማድረግ አዋቅሮታል፡፡ በእርግጥ በወቅቱ የነበሩ ህጎች እና የህጎች አፈፃፀም ከላይ በተገለፁት የግፊት ኃይሎች የወጡ እንጅ ለውጦቹ ትርጉም ባለው መልኩ የወጡና የሰራተኛውን መብት ሙሉ በሙሉ ያስጠበቁ አልነበሩም፡፡ ፀሐፊዎች እንደሚስማሙበት ለአሰሪ የወገነ ህግ እና አፈፃፀም ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ ደርግ ስልጣን ከያዘ በተለይ ከአዋጅ ቁጥር 64/68 መውጣት በኂላ ስር ነቀል በሆነ ሁኔታ ተቀይሯል፡፡ ደርግ ይመራበት የነበረው የወታደራዊ አለምአቀፋዊ ፓርቲ እና የመደብ ፖለቲካ ህጎች እና አፈፃፀማቸው "ከበዝባዥ አሰሪ" ይልቅ ወደ ሰራተኛ ያዘመሙ ነበሩ፡፡ ሁለቱ ያለፉት ዘመናት አመለካከቶች' እና ተግባራቸው ወደ ሁለት የተለያዩ ጫፎች የተወጠሩ ነበር፡፡ በዚህ ረገድ ካሳለፍነው የስራ ባህል ስንነሳ መንግስት አሁንም ቀጣሪ ሲሆን ከምንከተለው የነፃ ኢኮኖሚ ፖሊሲ አንፃር ግን የመንግስት ሚና ከቀጣሪነት ይልቅ የመሪነት ሚና ሊላበስ ይገባዋል፡፡ ይህን ዝንባሌ የፍትህ አካሉ ሊረዳውና በአሰራሩ በጥንቃቄ ሊያስታውሰው ይገባል፡፡ መንግስት በዋነኛነት ከአሰሪነት ይልቅ የመሪነት ሚና ሊጫወት የሚገባው ሲሆን በነፃ ገበያ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ፍትህ ለማምጣት የሰብዓዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ከሰራተኛ አንፃር መከበራቸውን ማረጋገጥ ይሆናል፡፡ ከለውጥ በኂላ ሀገራችን የነፃ ኢኮኖሚ ስርዓትን ስትከተል በመካከለኛ ጊዜ መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሀገራት ተርታ የመሰለፍ እንዲሁም ማህበራዊ ፍትህ የነገሰበት ሀገር ለመገንባት ራዕይ ይዛለች፡፡ እነዚህ ሁለት ቁምነገሮች ከአሰሪና ሰራተኛ ህጎች አንፃር መሠረታዊ ናቸው፡፡ ፈጣን የኢኮኖሚ ልማት ለማምጣት፣ አሰሪና ሰራተኛ በመግባባት እና በሰለጠነ መንገድ ስራቸውን እንዲያከናውኑ እና ግጭቶችን እንዲፈቱ ያስፈልጋል፡፡ ከንትርክ እና ጭቅጭቅ የወጣ አሰራር ሊከተሉ ይገባል፡፡ ይህ ሲሆን በስራ አካባቢ የኢንዱስትሪ ሰላም ይፈጥራል፣ ሰላሙም በሀገር ደረጃ የመስፋፋት እድል ያገኛል፡፡ በአግባቡ የወጡ የአሰሪና ሰራተኛ ህጎች ማህበራዊ ፍትህ (Social Justice)

እንዲነግስ ያስችላሉ። ህጎቹ ደረጃቸውን የጠበቁ ከሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር አለምአቀፋዊ ወንድማማችነት' መግባባት እና ትብብርን ያነግሳሉ ። አለምአቀፍ የስራ ህግን ለማሳደግ አንድ ወሳኝ ነጥብ ሆኖ ይታይ የነበረው ይኸው የማህበራዊ ፍትህ ጥያቄ ነው። አለምአቀፍ የእድገት መለኪያዎችንስንመለከት ለኢኮኖሚ እድገት ይሰጥ የነበረው ብቸኛ መመዘኛ ተሻሽሎ በhuman Development index መቀየሩ የኢኮኖሚ እድገት በቀጥታ ማህበራዊ እድገትን ያመጣው' የሚለውን እጅግ አጠያያቂ ያደርገዋል። ይህ በመሆኑም የአሰሪና ሰራተኛ ህጎች በባህሪያቸው የኢኮኖሚ እድገትንና ማህበራዊ እድገትን በኢንዱስትሪ ሰላም ማምጣት የሚያስችሉ ናቸው። የኢንዱስትሪ ሰላም ሲፈጠር የሥራ እድል ይፈጠራል፣ ሰራተኛ የስራ ዋስትና ያገኛል፣ የኢንዱስትሪ መስፋፋት ይኖራል፣ በዚህም የሰራተኛው የሙያ እና የእውቀት ደረጃ የሚያድግበት እድል ይጨምራል። ሁለቱ የጋራ ጥቅም ያላቸው ሲሆን የአንዱ ጥቅም ሌላውን እየመገበ በጋራ የማደግ እድልን ያሰፋል። የጋራ ጥቅም እንደመፈጠሩ ሁሉ የጥቅም ግጭትም ወይም የፍላጎት ግጭት ሊፈጠር ይቻላል። ይህ ግጭት በሰለጠነ መንገድ በድርድር፣ በስምምነት . . . ካልተፈታ የእንዱስትሪው ሰላም ይጠፋና ወደ አለምአቀፍ ገበያ መግባት ቀርቶ ከሀገር ውስጥ ገበያ የመጥፋት እድል ይገጥማል። ይህም በጋራና የሁሉንም መውደቅ ያስከትላል። በመሆኑም አሰሪም ሆነ ሰራተኛ በጋራ ለኢንዱስትሪ ሰላም መስራት፣ በሰላሙ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ትርፍ በጋራ በመግባባት እና በድርድር መካፈል፣ ከክፍፍሉ ሰራተኛ እውቀቱን ትምህርቱን ታታሪነቱን ክህሎቱን የበለጠ በማሳደግ የበለጠ ምርታማ (Productive) የሚሆኑበትን መንገድ መፈለግ፣ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ሁሉ በሰላማዊ እና በሰለጠነ መንገድ በመፍታት ወደ አለም ገበያ በመግባት ማህበራዊ ፍትህንም ጐን ለጎን ማንገስ ይገባል። ግንኙነቱ በዚህ መልኩ ከተቀረፀ በአሰሪዎች መሀከልም ፍትሐዊ የሆነ መልካም ውድድር (Fair competition) የማምጣት እድል ይጨምራል። የአሰሪና ሠራተኛ ህግ በአሰሪዎች እንዲሁም በአለም አቀፍ ደረጃ የሚኖር የገበያ ውድድር ሰራተኛውን ሰለባ በማድረግ የሚፈፀም እንዳይሆን ያስችላሉ። በኢኮኖሚ ማደግ ማህበራዊ ፍትህ እና ሰላም ከማምጣት ጋር ተመዛዝኖ እንዲመጣ ያደርጋል።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ - መንግስት በአንቀጽ 42 ስር በርካታ የሰራተኛ መብት ድንጋጌዎችን ይዟል። የሰራተኛ መብቶች በእነዚህ ድንጋጌዎች ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በአጠቃላይ የሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ጭምር ያካተቱ ናቸው። ህገ መንግስቱ አሰሪና

ሰራተኛን አስመልክቶ ከያዛቸው ጉዳዮች ውስጥ መሠረታዊ የሆኑትን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

<u>መደራጀት</u>

የጋራ ግብን ለማሳካት የሚፈልጉ ሰራተኞች በተደራጀ መልክ ፍላጎታቸውን ማሟላት እንዲችሉ የሰራተኛ ማህበር (Trade Union) መመስረት ህገ መንግስታዊ መብት እንደሆነ በህጉ ላይ በግልፅ ተቀምጧል። ይህ መብት ከመነሻው ኢንዱስትሪዎች የሴቶችን፣ ህፃናትን፣ የገጠር ሰራተኞችን እና ስደተኞችን ጉልበት እየበዘበዙ በተስፋፋበት ጊዜ አስፈላጊነቱ ታምኖበት የሰራተኛ መብት ሆኖ የቀጠለ ነው። በዚህ መልኩ የተደራጁ ሰራተኞች የስራ ሁኔታን፣ ሰዓትንና የመሳሰሉ የጋራ ጉዳያቸውን በተዳራጀ መልኩ ከአሰሪያቸው ጋር በመነጋገር ለመወሰን ያስችላቸዋል። የድርጅቱ መሪዎች በሰራተኞች ስም የወል የሆነ የስራ ግንኙነት (Collective bargaining) ከአሰሪዎች ጋር ለመስማማት ያስችላል። በዚህ መሠረት የሰራተኛ ደመወዝ፣ የስራ መመሪያ፣ የአቤቱታ አቀራረብ ስነ-ስርዓት፣ የቅጥር፣ እድገት እና የስንብት አፈፃፀም፣ የስራ ቦታን ደህንነት እና ፖሊሲ.... ወዘተ በተመለከተ ሊስማሙ ይችላሉ። ይህ የመደራጀት መብት በተለይ በሀገራችን ኢንዱስትሪ እየተስፋፋ ባለበት ሁኔታ ያለው የሰራተኛ ኃይል በሚፈለገው መጠን ያልተማረ እና ያልተካነ በሆነበት ጊዜ ያላግባብ እንዳይበዘበዝ እና አነስተኛ ክፍያ እንዳይቀበል ያስችላል። የሰራተኛ ማህበር በዋነኛነት አላማቸው የስራ ሁኔታቸውን መጠበቅ እና ማሻሻል ነው። በሀገራት የሚቋቋሙ ማህበራት አላማቸው የተለያየ ቢሆንም በህገ መንግስቱ ውስጥ የተቀመጡት አላማዎች፦

ለአባላቱ ጥቅም መስራት፣

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የቀድሞ ማህበራት ለአባሎቻቸው ጥቅም የሚሰጡት አባሎቻቸው ከስራ ሲሰናበቱ’ ሲታመሙ’ አደጋ ሲደርሳባቸው’ እርጅና ሲያጠቃቸው እና መሰል ችግር ሲገጥማቸው ነበር። ይህ "የወዳጅነት ማህበር" በ"እድር" እና መሰል ተቋማት የሚሰራ ነው። ህገ መንግስቱ ማህበራት የአባላቱን "ኢኮኖሚያዊ ሁኔታም ለማሻሻል ይቋቋማሉ" ስለሚል እነዚህ አላማዎችም በተዘዋዋሪ ተካተዋል ለማለት ይቻላል። በሌላ በኩል ህገ መንግስት የፈቀደው የሰራተኛ መብት ማህበር ማደራጀት ብቻ ሳይሆን "ሌሎች ማህበራትን" ማደራጀትም ስለሆነ እነዚህን ህጋዊ አላማዎች ለማሳካት

የመደራጀት ስፊ መብት ሰጥቷል ለማለትም ይቻላል፡፡ በዚህ መልኩ በማህበር ለመደራጀት ሰራተኛ ከመሆን በቀር ሌላ ቀዳሚ ፈቃድ አያስፈልግም፡፡

በተደራጀ መልክ የሰራተኛውን የስራ ሁኔታ ለማሻሻል፣

በማህበር የተደራጀ ሰራተኛ በሥራ ሁኔታ ላይ ያላውን ቅሬታ በስራ ማቆም ማሰማት ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ሰራተኞች ወደ ስራ ቦታ መግባት ቢከለከሉ (Lock out)' ማህበራት ያላቸውን ቅሬታ በሌላ ማናቸውም ህጋዊ መንገድ ለሚመለከተው ማሰማት ይችላሉ፡፡ ስለሆነም በማህበር መደራጀት ከግለሰብ በተለየ መልኩ በህገ መንግስቱ የመስማት መብት (Right to be Heard) ያስገኛል፡፡ ስለዚህ ማህበራት "Juridical Person" አይነት ነው ለማለት ይቻላል፡፡

ማህበራት የሰራተኛውን የሥራ ሁኔታ ለማሻሻል ይጠቅማሉ፡፡ ማህበራት በመሰረቱ ለዚህ ሁኔታ ይቋቋሙ እንጂ የአባላት ጥቅም በአሰሪ ወይም በሌላ ድርጅት(ሌላ የሰራተኛ ማህበር) ቢነካ ጥቅሙን ለማስጠበቅም መደራደር ይችላሉ፡፡

የማህበራት ጥቅም የሚሻሻለው በህግ ጭምር ስለሆነም በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ህግ እንዲወጣ የPromotion ስራ ሊሰሩ ይችላሉ ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን የፖለቲካ ቅስቀሳ ማድረግ' የፖለቲካ ፖርቲን እና አባሉን በገንዘብ መደገፍ እና በመሳሰሉት እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ህጉ አይፈቅድም፡፡

በህገ መንግስቱ የተመለከቱት እነዚህ መብቶች በተደራጁ ሰራተኞች የተፈቀዱ በመሆናቸው በማህበር የተደራጀ ሰራተኞች ካልተደራጁት በዚህ ረገድ የተሻለ ጥቅም ሊያገኙ ይችላሉ ማለት ነው፡፡ ይህ ጥቅም ግን በህግ ከተቀመጠው አነስተኛ ጥቅም በላይ ባለው ላይ የሚገኘውን የሚመለከት ብቻ ነው፡፡ ሰራተኞች ካለመደራጀት ከሚመጣ መድልዎ(anti-union discrimination) የተጠበቁ ናቸው፡፡

<u>እኩልነት</u>

በህገ መንግስቱ ውስጥ 7 ዓይነት ስታንዳርድ የሚወጣባቸው መብቶች የተጠቀሱ ሲሆኑ ከመብቶች ውስጥ ሴቶች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የሚከፈላቸው መሆኑ አንዱ ነው፡፡ "ክፍያ" የሚለው ቃል በዝርዝር ህግ የሚወሰን ከስራ ግንኙነት የተነሳ በማናቸውም መልክ የሚከፈል ደመወዝ እና ተጨማሪ ማናቸውም ክፍያዎችን የሚያካትት ሲሆን በስራ ቦታ ፆታን መሠረት በማድረግ አድልዎ እንዳይፈፀም

የሚከለክል ነው፡፡ የአለም አቀፍ የስራ ድርጅትም (ILO) ይህንን መብት በኮንቬንሽን ቁጥር 100 ራሱን ችሎ እንዲወጣ አድርጓል፡፡ አለምአቀፍ የሥራ ድርጅት በ1998 ካወጣው የስራ ቦታ መሠረታዊ መብቶች እና መርሆዎች ውስጥም ይኸው በቅጥር እና በስራ ላይ መድልዎን የሚያስቀረው መርህ አንዱ ነው፡፡ ይህ መብት በተለይ በዚህ መልኩ ሲደነገግ አለም አቀፍ ሰነዶች የሰውን ልጅ ክብር፣ ሰው በመሆን ብቻ የሚገኝ ሌሎች መብቶች፣ የእኩልነት ድንጋጌዎች በሙሉ ሴቶች ከወንዶች እኩል በፖለቲካው፣ ኢኮኖሚው፣ ባህላዊ፣ ማህበራዊ እና ማናቸውም መስክ እኩል መሆናቸውን እያስታወሱ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በድህነት ውስጥ በተለይ ሴቶች ምግብ፣ ጤና፣ ትምህርት፣ ስልጠና፣ የቅጥር እድል የማግኘት እድላቸው በተግባር የሚቀንስ ከመሆኑ በላይ ይህ ልዩነት ሴቶች ሙሉ አቅማቸውን ተጠቅመው ለራሳቸው ስብዕና ብሎም ለቤተሰባቸው እና ለራሳቸው እድገት ማበርከት ያለባቸውን ሚና እንዳያበረክቱ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህ በመሆኑም ለተመሳሳይ ስራ ተመሳሳይ ክፍያ ሊፈፀም ይገባዋል የሚለው በተለይ ህገ መንግስታዊ እውቅና አግኝቶ እንዲደነገግ ሆኗል፡፡ በሌላ በኩል በህገ መንግስቱ አንቀጽ 25 ስር ሁሉም ሰው በፆታ ልዩነት ሳይደረግበት በህግ ፊት እኩል መሆኑ' እኩል የህግ ጥበቃና ዋስትና የማግኘት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ ይህ መብት በአንቀጽ 35 ስርም ተደንግጓል፡፡ መብቱ በተለይ ከአሰሪና ሰራተኛ ህግ የእኩልነት አፈፃፀም አንፃር ሲታይ'

- የመስራት የማይገፈፍ መብት(Right to work)'
- ለመስራት (በቅጥር) እኩል እድል የማግኘት መብት(ከድጋፍ ርምጃ ጋር)'
- ሙያና ስራቸውን በነፃነት የመምረጥ መብት& የማደግ' የስራ ዋስትና . . . እና ሌሎች ጥቅሞችን በተመሳሳይ የማግኘት'
- የማህበራዊ ዋስትና የማግኘት መብት'
- ከስራ ቦታ አደጋ/ህመም/ የመጠበቅ

እና የመሳሰሉትን ያለ አድልዎ የማግኘት መብትን የሚያካትት ሲሆን በእርግዝና' ወሊድ…ጊዜ ልዩ ድጋፍ የማግኘት መብትን ያካትታል፡፡ እነዚህን ዝርዝር መብቶች የህገ መንግስቱን መርህ ተከትሎ በአ.ቁ. 377/96 አንቀጽ 87 እና ተከታዮች ስር ተደንግገዋል፡፡

## ምቹ የሥራ ሁኔታዎች

ሰራተኛ የሥራ ሰዓት፣ ዕረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ፣ የእረፍት ቀኖች፣ በህዝብ በዓላት ቀናት ደመወዝ የማግኘት፣ ጤናማ እና አደጋ የማያደርስ አካባቢ የማግኘት መብት አለው። እነዚህ መብቶች በህገ መንግስቱ አንቀጽ 42/2/ ላይ በጥቅሉ የተቀመጡ ሲሆን በዝርዝር ህግ (በህብረት ስምምነት) "በአግባቡ መወሰን" እንደሚገባ በመርህ አስቀምጧል። ይህ የሰራተኛ መብት በህገ መንግስቱ ውስጥ እውቅና ሲያገኝ በጊዜ' በገንዘብ. . . ተለውጦ ሰራተኛው የሚያገኘው የመብት ጥቅም ግን በዝርዝር ህግ የሚወሰን ነው። በዝርዝር በሚወሰንበት ጊዜ "በአግባቡ"(Reasonably) የተወሰነ መሆኑ የህገ መንግስቱ መርህ ነው። በዚህ መሠረት ደመወዝ ሲወሰን(አነስተኛ ዝቅተኛ አንስቶ) የሰራተኛውን ክብር የሚያስጠብቅ ድህነትን የሚቀንስ ከመሆኑ ጋር እጅጉን ከፍ ብሎም ስራ አጥነትን የማያባብስ መሆኑ "በአግባቡ" መረጋገጥ አለበት። ከዚህም በላይ ሰራተኛው ጠንክሮ እንዲሰራ ያደርጋል? በቀጣሪ ላይ የበጀት ጫናው ምን ያህል ሆኖ ቅጥርን ያበረታታል/ያደናቅፋል? ለአስተዳደር ይቀላል/ይከብዳል? የትኛውን (ትንንሽ ወይም ትልልቅ)የንግድ ድርጅት ላይ ጫና ፈጥሮ ለሀገር ይጎዳል? ድርጅቱ የማይሰራ (dysfunctional) ያደርገዋል? የሥራ ጥራት ላይ ምን ጫና አለው? ድህነት ቅነሳ ላይ ምን ሚና አለው? አንስተኛ ደመወዝ ክፍያን ለማካካስ የዋጋ ጭማሪ እየተደረገ የዋጋ ግሽበት እንዲኖር ያደርጋል? ወዘተ የሚሉትን በአግባቡ ማጥናት ይጠይቃል። ይህ ጥናት ከሀገር ሀገር ውጤቱ የተለያየ ስለሚሆን አለምአቀፋዊ መርሁ የተለማጭ መርህን መከተል ነው። ጤናማ እና አደጋ የማያደርስ አካባቢ የማግኘት መብትም በተመሳሳይ የሚታይ ነው። ይህ መብት የተለያዩ ዲሲፕሊኖችን የሚመለከት ሲሆን የሰራተኛውን ደህንነት' ጤንነት እና ምቾት (Welfare)የሚመለከት ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የስራን ደህንነትም ይመለከታል። ደህንነቱ የተጠበቀ የስራ አካባቢ የመፍጠር አላማ ያለው ቢሆንም የሌሎች ሰራተኞችን፣ የቤተሰብ አባላት፣ ቀጣሪ፣ ደንበኛ፣ አቅራቢ፣ የአካባቢ ህብረተሰቡን እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚመለከት ነው። ከሙያም ህክምና፣ የጤና ሳይንስ፣ የምህንድስና (Safety engineering)፣ ኬሚስትሪ፣ የአካባቢ ጤና፣ የህዝብ ፖሊሲ፣ ሶስሎጂ፣ ሳይኮሎጂ ወዘተ ድብልቅ ነው። ስለሆነም በህገ መንግስቱ መርህ መሠረት "በአግባቡ" ተጠንቶ መወሰን ያለበት መሆኑ ተገቢ ነው። በአግባቡ ተጠንቶ መወሰኑ የሰራተኛውን የአካል' አዕምሮ እና ማህበራዊ ደህንነትን መጠበቅ እና ማጎልበት ነው። በዚህም ስራ ለሰው (ለሰራተኛ) እንዲስማማ ማድረግ ሲሆን በተገላቢጦሹም ሰራተኛው ለስራው የተስማማ እንዲሆን ማድረግ ነው።

ይህም ለኢንዱስትሪ ሰላም እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ነገሩን በሌላ መልኩ ስንመለከተውም ለአደጋ(ሞት' አካል) የተጋለጠ ሰራተኛ ሞራል ጉዳት ይደርስበታል፡፡ አደጋውን ለመካስ ወይም ለማስተካከል የገንዘቡ ወጪ በአሰሪ (ወይም መንግስት)ላይ ይወድቃል፡፡ በተለያየ መልኩ ወጪን የሚያስከትል እና ምርታማነትን የሚቀንስ ከመሆኑም በላይ የፍ/ብሔር እና/ወይም የወንጀል ተጠያቂነትም ያስከትላል፡፡ ስለሆነም ከሞራል አንስቶ እስከ ወንጀል ተጠያቂነት ድረስ ያለው ኃላፊነት ለሀገር እድገት አፍራሽ ሚና ያለው በመሆኑ ጉዳዩን በአግባቡ አጥንቶ በአግባቡ ለሚወስን አካል መተው ተመራጭ ነው፡፡

<u>የስራ ውል እና ገደቡ</u>

የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት የሚመሰረተው በውል ላይ በተመሰረተ ግንኙነት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም የውል ግንኙነት ይፈፀማል ማለት አይደለም፡፡ የሰራተኛውን የተለያየ ፍላጎት' የህብረተሰቡን ፍላጎት እና ሀገራችን የምትከተለውን የነፃ ገበያ ፍላጎት መሠረት በማድረግ የጉልበት ዝውውር እንዲኖር ለማስቻል በተወሰነ ደረጃ የመዋዋል ነፃነትም ሊገደብ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ይህንን ፍላጎት ለመጠበቅ ሲባል ሰራተኛ በፈቀደው ምክንያት የስራ ውሉን ማቋረጥ ሲችል አሰሪ ግን በተዘረዘሩ ህገወጥ በተባሉ ምክንያቶች የስራ ውልን ሊያቋርጥ አይችልም፡፡ በዚህ ስምምነት መሠረት በገበያ አቅርቦት እና ፍላጎት (Supply & demand) ላይ ተመስርቶ አነስተኛ ደመወዝ (lowest wage) መወሰን የሚቻል ሲሆን ይህ ስምምነት ግን አጠቃላይ ዝቅተኛ ደመወዝ (minimum wage)ሊያንስ አይችልም፡፡

በውል ህጎች ድንጋጌ መሠረት ህፃናት የሚፈፅማቸው ውሎች ፈራሽ የሚሆኑ(voidable) ሲሆኑ በልዩ ሁኔታ ህፃኑን የሚጠቅሙ ከሆኑ ግን ፀንተው ሊቆዩ ይችላሉ፡፡ በአሰሪና ሰራተኛ ህግ መሠረት ግን የመዋዋል ነፃነት በዚህ ረገድም ገደብ አለው፡፡ ህገ መንግስት በአንቀጽ 36 ስር በህፃናት ጤና፣ ትምህርት እና ደህንነት ላይ አደጋ የሚያደርሱ ስራዎችን እንዲሰሩ ህፃናት መገደድ የለባቸውም በማለት ከደነገገው በላይም ይህን ስራ እንዳይሰሩ መጠበቅ እንዳለባቸውም ደንግጓል፡፡ በዚህ መልኩ ከወጡት ህጎች ውስጥ 14 ዓመት ያልሞላቸው ህፃናትን መቅጠር የተከለከለ መሆኑን አ.ቁ.377/96 ሲደነግግ ከ14-18 ዓመት ድረስ ያሉትን ወጣቶች ግን ህይወታቸውን ወይም ጤንነታቸውን ለአደጋ በማያጋልጥ ስራ ቀጥሮ ማሰራት እንደሚቻል ደንግጓል፡፡

እነዚህን ወጣቶች በቀን ከ7 ሰዓት በላይ ማሰራት የማይቻል ሲሆን በተለይ መስራት የሌለባቸው ስራዎችም(እንደአስፈላጊነቱ ከሚጨመሩ ዝርዝርም ጋር) ተዘርዝረዋል፡፡

በአጠቃላይ የስራ ውልን በነፃነት የመዋዋል መርህ በህገ መንግስቱ ተቀባይነት ያለው ሲሆን ይህ ነፃነት ግን ለህፃናት እና ለወጣቶች ጥቅም ሲባል ገደብ ያለበት ነው፡፡ ገደቡም ህፃናት ያላቸውን ልዩ የአካል እና የአዕምሮ ሁኔታ በማገናዘብ በትክክለኛ እድሜያቸው ላይ ትምህርት ቤት' የተወሰነ የስራ ቦታ እና ሙሉ ስራ ላይ በየደረጃው እንዳገኙ ለማስቻል ነው፡፡

<u>ቅሬታ አፈታት</u>

የስራ ማቆም አድማን በተመለከተ በህገ መንግስቱ ላይ የሰፈረ የሰራተኛ መብት መሆኑን ተመልክተናል፡፡ ይህ መብት በአሰሪና ሰራተኛ መሀከል የተፈጠረን ግጭት ለመፍታት የሚያስችል ጠንካራ መብት ነው፡፡ ይህ መብት በህገ መንግስቱ ላይ እንደተመለከተው የቅሬታ ማቅረቢያ አንዱ መንገድ ነው፡፡ ብቸኛ መብት ተደርጎ አልተቀመጠም፡፡ ስራ ማቆም አድማ ብቸኛ እና የመጀመሪያ ቅሬታ ማቅረቢያ መንገድ ባለመሆኑ ሰራተኛ ስራ ከማቆሙ በፊት ማስጠንቀቂያ የመስጠት፣ የስራ ማቆም አድማውን ውሣኔ ዲሞክራሲያዊ በሆነ አግባብ ማሳለፍ (wildcat ያልሆነ)፣ በህጉ ላይ እንደተመለከተው ጉዳዩ የሰራተኞችን መብት እና ጥቅም ለማስከበር እንጂ የሌላ ድርጅት ሰራተኛ (sympathy strike)ወይም በሌላ ጉዳይ ማስፈፀሚያ ጠቅላላ ስርዓት ለማጥፋት(General strike)አለመሆኑን ማረጋገጥ ወዘተ ይጠበቃል፡፡ የመብት እና ጥቅም ጥያቄው በተሻለ መንገድ ምላሽ ማግኘት ከቻለ (በድርድር' በፍ/ቤት ወይም በቦርድ ውሣኔ . . .) እንዲሁም ጉዳዩ በዚህ ደረጃ እየታየ ከሆነ ይህን ስርዓት በህጉ ገደብ ማስጨረሻ ይጠበቅም ይሆናል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ሰራተኛ ቅሬታ የሚያቀርብበት በርካታ ህጋዊ መንገድ የተፈቀደ በመሆኑ የትኛውም ሀገር ህግ እንደማይፈቅደው ሁሉ ቅሬታን ስራን በማጓተት (go-slow)፣ ተንኮል ወይም አሻጥር (sabotage) በመስራት፣ ድርጅትን ከገበያ ውጪ ለማድረግ በስውር በመስራት (ምሳሌ ቦይኮት ማድረግ)' እና በመሳሰሉት መንገዶች ቅሬታ ማቅረብ አልተፈቀደም፡፡ የኢንዱስትሪ ሰላም መስፈን የመንግስት፣ ህብረተሰቡ፣ አሰሪ እና ሰራተኛ ፍላጎት ነው ተብሎ የሚገመት በመሆኑ ከላይ የተመለከቱትን ስነ ስርዓቶች እና እንደ ድርድር ያሉ የግጭት አፈታት ስርዓቶችን መከተል ከመጨረሻው የስራ ማቆም በፊት ይጠበቃል ለማለት ይቻላል፡፡

ሰራተኞች ቅሬታቸውን ሊያቀርቡ ከሚችሉባቸው መንገዶች ውስጥ ሌላው መሰብሰብ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ስብሰባ በተለይ ከስራ ማቆም አድማ በኋላ ከስራ ቦታ፣ አጥር ግቢ ውጪ የሚፈፀምና የሰራተኛው መኖር ከስራ ማቆም አድማው ጋር ተጨማሪ ስሜት እንዲፈጥር ለማድረግ ታስቦ የሚደረግ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ የፒኬቲ (pickets) ስርዓት ቅሬታ ማቅረብ የሚቻልበት መንገድ ቢሆንም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 30 ስር በተመለከተው የመሰብሰብ መብት መንፈስ እና ስርዓት መፈፀም ያለበት ነው፡፡

<u>የግዴታ ሥራ</u>

የአሰሪና ሰራተኛ ከፍ ሲል በተገለፀው መልኩ በህግ እና በውል የሚመራ በመሆኑ ህጉም የስራ ውሉ ስራ በፈቃድ (at will) መሠራት እንዳለበት ያምናሉ በማለት በቀላሉ መስማማት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የዚህ ጉዳይ ከተሰጠው ልዩ ትኩረት በመነሳት የኢፌዲሪ ህገ መንግስት ማንኛውም ሰው በኃይል ተገዶ ስራ መስራት የለበትም' አንድን ግዴታ ለማሟላትም በተመሳሳይ ስራ መሠረት የለበትም በማለት በአንቀፅ 18 ስር መብቱን ህገ መንግስታዊ አድርጎ ደንግጓል፡፡ ይህ መብት በILO ስምምነት ቁጥር 29 እና 105 መሠረትም የተፈቀደ ነው፡፡ ይህ መብት በህገ መንግስቱ ላይ እንደተደነገገው ሊገደብ የሚችለው በተወሰኑ ምክንያቶች ሲሆን ከሰራተኛ አንፃር መብቱ ሊገደብ የሚችለው የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ እና በህዝብ ፈቃድ ለአካባቢያዊ ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ የልማት ስራ ብቻ ነው፡፡ ከፍ ሲል የተጠቀሱት ስምምነቶች በተለይ ስምምነት ቁጥር 29 መብቱ የሚገደብበትን መንገድ በልዩ ሁኔታ ሲያስቀምጥ ከኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንፃር ሰፊ አድርጎታል፡፡ ስለሆነም ህገ መንግስቱ የግዴታ ሥራ ማሠራት የተከለከለ ነው ሲል መብቱን በተሻለ ስፋት ለሰራተኛ ሰጥቷል ማለት ነው፡፡

## <u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. የአሰሪና ሰራተኛ ህጋችን መሰረታዊ የህገ መንግስት መርህ ምንድን ናቸው?
2. የአሰሪና ሰራተኛ ህጋችን አሰሪና በአለምአቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ የሚያደርገው ምን ምን መመዘኛዎችን ሲያሟላ እንደሆነ ምክንያቱን እያብራራህ ተወያይ፡፡
3. በህገ መንግስቱ መግቢያ ላይ የተቀመጠውን ማህበራዊ ፍትህ ለማምጣት የኢንዱስትሪ ሰላም ሚና ይኖረዋል? እንዴት?

4. ከህገ መንግስቱ መርህ አንፃር በአሰሪ ሰራተኛ ጉዳይ ውስጥ የመንግስት ምነኛ ሚና ምን መሆን አለበት? ለወደፊቱ በምን ደረጃ ነው በአሰሪነት መቀጠል የሚገባው?
5. የእኩልነት መርህ በአሰሪና ሰራተኛ ህግ ውስጥ በምን ይገለፃል? ሴቶች በዚህ ህግ ውስጥ ሊሰጣቸው ከሚገባው ድጋፍ አንፃር እንዴት "ልዩ ትኩረት" ሊያገኙ ይችላሉ?
6. ከህገ መንግስቱ አንፃር የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር በዋነኛነት የሚታበትን አግባብ እና ቀድሞ ተከተል ከነምክንያቱ በማስቀረጥ ተወያዩበት፡፡

# ክፍል ዘጠኝ

# ከአስተዳደር ህግ አንፃር የህገ መንግስቱ መሠረታዊ መርሆዎች እና አቅጣጫዎች

1. ጠቅላላ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ- መንግስት በአንቀፅ 50 ስር ኢ.ፌ.ዲ.ሪ በፌዴራል መንግስታት እና በክልሎች የተዋቀረ መሆኑን ይደነግግና የፌዴራል መንግስትም ሆነ የክልል መንግስት የህግ አውጪነት' የህግ አስፈፃሚነት እና የዳኝነት ስልጣን አላቸው በማለት በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ የፌዴራል መንግስቱ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለፌዴራል መንግስቱ በተሰጠው ክልል ውስጥ ህጎችን ያወጣል' በጠቅላይ ሚኒስቴሩ ሰብሳቢነት የሚመራው የሚኒስቴሮች ምክር ቤት የወጡ ህጎች በስራ መተርጎማቸውን ለማረጋገጥ ህግ ያስፈፅማል እንዲሁም ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይህ የስልጣን ክፍፍል በተመሳሳይ መልኩ በክልል ጉዳይ ህግ ለማውጣት ለክልል ም/ቤቶች' በዚህ መልኩ የወጡ ህጎችን ለማስፈፀም ለክልሎች መስተዳድር እንዲሁም በክልል ጉዳዮች ለመዳኘት ለክልል ፍ/ቤት ተሰጥቶ ተከፋፍሏል፡፡ በዚህ መልኩ የመንግስት ስልጣን በ3ት የተለያዩ አካላት መሀከል መከፋፈል እና መፈፀም ከምዕተ አመት በፊት አንስቶ የህግ ባለሞያዎች' ፍርድ ቤቶች' የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን እና አጠቃላይ ህብረተሰቡ የነፃነት የማዕዘን ድንጋይ እንደሆነ ተቀብሎት ሲታገልለት የቆየ መርህ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ ተቀባይነት ካገኘ የቆየ ቢሆንም የስልጣን ክፍፍሉን ወሰን እንዲሁም እያንዳንዱ አካል ምን መከወን አለበት በሚለው ላይ ወጥ የሆነ ስምምነት አለ ለማለት ግን አይችልም፡፡

በዚህ የተነሳም የተጠቀሱት ስልጣኖች በተግባር ወይም ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሲታዩ በፍፁም የተነጣጠሉና የማይገናኙ ናቸው አይባልም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሥልጣኖቹ በአንድ አካል ተደራርበው የሚገኙበት ጊዜ አለ፡፡ ይህ መሆን አለበት በማለት የሚያስቡ የመስኩ ፀሐፊዎችም አሉ፡፡ አንድ አስፈፃሚ ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ የግድ ለህግ ትርጉም ሰጥቶ በተግባር እንዲውል ያደርጋል፡፡ በርካታ ህገ-መንግስታት ለህግ አውጪው አካል የዳኝነት /መሰል/ ስልጣን ይሰጣሉ፡፡ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ተግባር በሚያከናውኑበት ጊዜም በምክር ቤት የወጡ ህጎችን ከመተርጎም በተጨማሪ በቀጥታ በማስፈፀም (application) አስተዳደራዊ /አስፈፃሚያዊ/ ተግባርን ያከናውናሉ፡፡ በስልጣን ክፍፍል ውስጥ የዚህ አይነት የስልጣን መደራረብ ሊኖር እንደሚችል ከመነሻው በህግ ተመራማሪዎች (jurists) እና ፀሐፊዎች ዘንድ ግንዛቤ የተወሰደበት ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከአስተዳደር ህጎች ውልደት እና እድገት ጋር ተያይዞ ይህ የስልጣን መደራረብ የተለየ አትኩሮትን ስቧል፡፡

መንግስት ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ መንግስት ለህብረተሰቡ ሊፈፅማቸው የሚገቡ ግዴታዎች እየተቀያየሩ መጥተዋል፡፡ የመንግስት ኃላፊነት /ግዴታ/ ከሰዎች የርስ በርስ ግንኙነቶች መቀያየር፣ የሚያስተዳድረው ድንበር መጥበብ /መስፋት/፣ የሥነ ጥበብ እና ሳይንስ እድገት' የህብረተሰብ ፍላጎት እና መሰል ምክንያቶች ጋር እየተያያዘ ተቀያይሯል፡፡ አሁን ባለንበት ዘመን የመንግስት ኃላፊነት ድንበር ከመጠበቅ እና ገቢ ከመሰብሰብ በላይ ሰፊና ውስብስብ እየሆነ መጥቷል፡፡ የዘመኑን የመንግስት ኃላፊነት የተረዱ ሀገራት የመንግስትን ኃላፊነት ለውጡን ባገናዘበ መልኩ እንዲቀረፅ አድርገዋል፡፡ያለንበት ዘመን ከተለዋዋጭ ሁኔታ ጋር በፍጥነት የሚለወጥ ህግ እንዲወጣና ከዚሁ ሁኔታ ጋር የሚሄድ ውሣኔ ሰጪ አካል ይፈልጋል፡፡ አዲስ እየመጡ ያሉት የንግድ ግንኙነቶች' የፈጠራና ሳይንሳዊ ግኝቶች' ከተለመደው "ዝሆናዊ" (Elephantic) የህግ አወጣጥ እና ውሣኔ አሰጣጥ በተለየ የሚሰራ ስርዓት ይፈልጋል፡፡ የዘመኑ ችግሮች አፈታት ከፊል ህግ አውጪነት፣ ከፊል አስፈፃሚነትን ከፊል ዳኝነት ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡ የወደፊትን በመመልከት በፍጥነት ህግ የሚያወጣ፣ የተፈጸመን መርምሮ ውሣኔ የሚሰጥ እና የአሁኑን ሁኔታ በሚገባ የሚዳስስ ስርዓት ይፈልጋል፡፡ አዲሱ አደረጃጀት እነዚህን የተለዩ ኃላፊነቶች እንዳመጣጣቸው በአግባቡ የሚፈታ (Custom-tailored)የሆነ ስርዓት ይፈልጋል፡፡ ይህ የተለየ ፍልስፍና የሚጠይቅ ሳይሆን በህብረተሰቡ ውስጥ በእርግጥ እየተከናወኑ ያሉ ለውጦችን እና እውነታዎችን

በመመልከት ሊደረስበት የሚችል ነው፡፡ በመንግስት አሰራር ውስጥ ያለው እውነታ' እንዲሁም በንግድ እና ኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለው ሀቅ እዚህ መደመደሚያ ላይ ያደርሰናል፡፡ ለዚህም ነው ቁጥሩ በተለያየ ጊዜ የሚጨምር ወይም የሚቀንስ የአስተዳደር አካል በየጊዜው የሚቋቋመው፡፡ እነዚህን እና መሰል ተግባራት በብቃት በመወጣት የህብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ለውጥ ፍላጎት ለማርካት ዘመናዊ መንግስት ህግ ከማስፈፀም በላይ ደንብ እንዲያወጣ እንዲሁም በአለመግባባቶች ላይም ውሣኔ እንዲሰጥ ይጠበቅበታል፡፡ ተግባራቱም አዳዲስ የመንግስት አካላት እንዲቋቋሙ አለዚያም ነባር የመንግስት አካላት እንዲታጠፉ (እንዲከስሙ) ያደርጋል፡፡ እርግጥ ነው ያሳለፍነውን ዘመን በመመልከት ይህንን የዘመናዊ ህብረተሰብ ፍላጎት መንግስት በአስተዳደር አካሉ ይውጠዋል? የሚል ጥያቄ የሚያነሱ አሉ፡፡ በሌላ በኩል በተመሳሳይ መልኩ ባሳለፍነው ዘመን የዳኝነት አካሉ መሠረታዊ ለሆኑ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ለውጦች ሲሰራ ባለመስተዋሉ በተመሳሳይ መልኩ የዘመናዊ ህብረተሰብን ፍላጎት ፍ/ቤቶች ተረድተው የተፈለገውን ኢኮኖሚያዊ' ማህበራዊ' ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ለውጥስ ያመጣሉ? የሚሉ ጥያቄዎችን በጥርጣሬ የሚያነሱ አሉ፡፡ ጥብቅ የሆነውን የስልጣን ክፍፍል መሠረት በማድረግም የአስተዳደር አካላት ህግን ከማስፈፀም በቀር ተጨማሪ ህግ የማውጣት እና የመተርጎም ስልጣን ሊሰጣቸው አይገባም የሚል ክርክር የሚያቀርቡም አሉ፡፡

የህብረተሰቡን ፍላጎት እና ግፊት በተግባር ከመፍታት አንጻር በዚህ ጉዳይ ላይ ለሚደረግ ክርክር የሚጠፋ ጊዜ እና ጉልበት እንደባከነ የሚቆጠር ነው የሚሉ ፀሐፊዎች አሉ፡፡ ይህ እውነት ቢሆንም በታሪክ ያለመቀበል አዝማሚያ ግን ነበር፡፡ የእንግሊዝ የህግ ፈላስፋ /ዴሴይ/ በእንግሊዝ ውስጥ የአስተዳደር ህግ የሚባል የለም በማለት በአንድ ወቅት የገለፀው ሰፊ ተቀባይነት አግኝቶ ቢቆይም በጥቅሉ ሲታይ በእንግሊዝ ውስጥ ከሚገኘው ኰመን ሎው ውስጥ ሁለት ሶስተኛ የሚሆነው የአስተዳደር ህግ ነበር፡፡ ከላይ የተገለፀው የእንግሊዙ የህግ ምሁር እምነት ቢኖርም የህግ አወጣጥን ብቻ ብንመለከት እንኳን በ1989 በሀገሪቷ ውስጥ ጠቅላላ አዋጅ (Act)46 ሲወጣ (2,489) ገጽ የያዘ) ከ2,500 በላይ የሚሆኑት (ከ6,700 ገጽ በላይ የሆኑት) በውክልና አስፈፃሚው አካላት የወጡ ህጎች ናቸው፡፡ በፈረንሳይ ሀገር በህገ መንግስቱ ከተዘረዘሩት ጉዳዮች በቀር በስሩት ህግ እንዲያወጣ ስልጣን የተሰጠው አስፈፃሚ አካል ነው፡፡

በመደበኛ ፍ/ቤቶች እና በምክር ቤቶች ላይ የጊዜ ጫና አለ፡፡ ስለሆነም አጠቃላይ መርሆዎች በህግ አውጪው (ምክር ቤት) የሚወሰን ሆኖ ዝርዝሩን በአስተዳደር አካሉ መሙላት ተገቢ ነው፡፡ በዚህ መልኩ በዝርዝር የሚወጡ ደንቦችም በተለየ መስክ የተለየ ክህሎትን ይበልጥ የሚጠይቅ እንጂ ጠቅላላ መርህ መደንገግን ግድ የሚሉ አይደሉም፡፡ ለእንደዚህ አይነቱ ዝርዝር አፈፃፀም ጉዳይ "Overresponsive" ከሆነው ፓርላማ እንዲሁም "Overinsulated" ከሆነው ፍርድ ቤት ይልቅ የአስተዳደር አካሉ ይመረጣል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በፍጥነት በሚለዋወጥ አለም ውስጥ በተለይ ከለውጡ ጋር የተለየ የኤክስፐርት እውቀት እና ክህሎት በሚጠይቅበት ሁኔታ አስተማማኝ ፈጣንና ተለዋዋጭ (ግን የረጋ) መልስ ሊሰጥ የሚችል አካል ይመረጣል፡፡ አንዳንድ ውሣኔዎችም በሙከራ(experimentation)የሚታዩ ናቸው፡፡ ስለሆነም አለም የሚስማማው ከተለመደው የስልጣን ክፍፍል በመጠኑ የላላ (less rigid design)የስልጣን ክፍፍል ለዘመኑ የመንግስት አሰተዳደር አስፈላጊ እንደሆነ ነው፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ- መንግስት መንግስት የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት አፋጣኝ እና መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጡ ርምጃዎችን እንዲወስድ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ የሀገሪቱ ዜጎች ከተጠራቀመ እውቀትና ሀብት የሚጠቀሙበትን መንገድ የመቀየስ' በእኩል እድል ኢኮኖሚያቸው እንዲሻሻል የማድረግ' የሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ አደጋን የመከላከል፣ ወደኂላ ለቀሩት ልዩ ድጋፍ የማድረግ ግዴታዎች በመንግስት ላይ ተጥሏል፡፡ (አንቀጽ 89) በተጨማሪም የመኖሪያ ቤቶችን ችግር የመቅረፍ፣ የመሰረተ ልማት አውታሮችን የመዘርጋት' ትምህርት እድሎችን የማስፋፋት' የህብረተሰቡን ጤና የመጠበቅ መሬትን በማከፋፈል ህዝቡን ተጠቃሚ የማድረግ' ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው (ሴቶች ብሔረሰቦች) የልዩ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ ዘርን' ፆታን' ኃይማኖትን እና ሌሎች መሰል ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ የሚፈፀሙ አድልዎችን ለመከላከል የወጡ ህጎችን አጥብቆ ተፈፃሚ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን የማስከበር/የማክበር/:በተለያየ መልኩ ህግ ማውጣት እና ፍትህ የመስጠት ግዴታም በህገ መንግስቱ ተጥሎበታል፡፡ ይህን መሰል ዘመናዊ ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት የመንግስት ኃላፊነት እና አደረጃጀት ከላይ በተመለከተው አጠቃላይ መርህ መሰረት ማደራጀት በማስፈለጉ ሕገ መንግስቱ ለዚህ ምላሽ ይሰጣል፡፡ይህንን ዘመናዊ አስተዳደር የሚመራ እና የሚቆጣጠር የአስተዳደር ህግም ያስፈልጋል፡፡

የአስተዳደር ህግ የምንለው የፐብሊክ ሎው እየተባለ የሚጠራው የህግ ክፍል አካል ነው፡፡ ትርጉሙ የሚያከራክር ቢሆንም በስፋት ካየነው የፐብሊክ ህግ አካል ሆኖ የመንግስት አሰተዳደራዊ ፖሊሲዎች የማስፈፀም ኃላፊነት ያለባቸውን አካላት (የአስፈፃሚውን)ጥንቅር’ ሊከተሉት ስለሚገባው ስነ-ስርዓት፣ ስልጣን፣ ግዴታ፣ መብት እና ኃላፊነት የሚመለከት ፖሊስ እና ህግ ነው፡፡ "ህግ" የሚለውን ፅንሰ ሐሳብ በውክልና የሚወጡትን (Delegated legislations) የሚመለከት ነው በማለት ህጉን በጠባቡ የመረዳት ሁኔታ በቀደመው ዘመን ነበር፡፡ ከላይ የተጠቀሰውን ስልጣን እና ግዴታ እንዲሁም ቁጥጥር /የዳኝነት ጭምር/ እያካተተ የመጣው ወደ ኂላ ዘመን ተቀባይነት ያገኘው ትርጉም ነው፡፡ በአስተዳደር አካላት የሚፈፀሙት ፖሊሲዎች እና ህጎች በህግ አውጪው ወይም በአስፈፃሚው አካል የወጡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ ትርጉም መሠረት የአስተዳደር ህግ ሁለት ጫፎችን ይይዛል፡፡

1. በአንድ ጫፍ የአስተዳደር ህግ የህገ መንግስት መርሆዎችን እና በህገ መንግስት የተቋቋሙ ተቋማትን የሚይዝ ሲሆን፣
2. በሌላ ጫፍ ደግሞ በአንድ ሚኒስቴር መ/ቤት ውስጥ የሚገኙ ዝርዝር ደንቦችን ይይዛል፡፡ እነዚህ ዝርዝር ደንቦች ደግሞ ገንዘብ ነክ’ ግብር ነክ’ አካባቢ ነክ’ ማህበራዊ ጡረታና ዋስትና ነክ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በትርጉሙ ውስጥ ሁለቱ ጫፎች ያሉ ቢሆንም ሁለቱም ራሳቸውን የቻሉ የህግ ማዕቀፍ ያላቸውና ብዙ ጊዜም በራሳቸው የሚታዩ ናቸው፡፡ ህገ መንግስቱ የህጎች ሁሉ የበላይ በመሆን በራሱ የሚታይ ሲሆን የግብር፣ አካባቢ፣ መሬት፣ማህበራዊ ዋስትና ወዘተ ጉዳዮችም ራሳቸውን በቻሉ ዝርዝርና ተናጠል ህጎች የሚታዩ ናቸው፡፡

ከላይ የተመለከቱት ሁለት ጫፎች እንደተጠበቁ ሆነው የአስተዳደር ህግ በርካታ ተግባር እንዳሉት ግን ጠቅላላ ስምምነት አለ፡፡ በጥቅሉ የአስተዳደር ሕግ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንፃር ስንመለከተው’

- የአስተዳደር አካላት በመንግስት እና በጠቅላላ ህዝቡ ፍላጎት የወጡ ፖሊሲዎች፣ ህጎችንን በመንግስትና በህዝብ ስም ያስፈፅማሉ፡፡
- በመንግስት የአስተዳደር መ/ቤቶች መሀከል ያለውን ግንኙነት ይመራል(ይቆጣጠራል)፡፡

- የአስተዳደር መ/ቤት በስልጣኑ ስር ባለ ጉዳይ ከሚመለከታቸው ግለሰቦች ወይም ሌሎች አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት ይመራል' ስለሆነም ግለሰቦች የአስተዳደር አካል ከስልጣን አሳልፎ ቢሰራ በግለሰቦች ጥያቄ እንዲቀርብበት ያስችላሉ፡፡
- የአስተዳደር አካላት የሚሰጡት ውሣኔ በህግ መሠረት ብቻ እንዲሆኑ ያስችላሉ፡፡
- አስተዳደር አካላት በተጠያቂነት መንፈስ እንዲሰሩና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ያደርጋሉ፡፡
- በአስተዳደር አካላት ስራ ውስጥ የህዝብ ተሳታፊ እንዲኖር ያስችላሉ፡፡
- የግለሰቦች መብት እንዲሁም የአስተዳደር አካል ስልጣን ገደብ ያለው መሆኑን ያመለክታሉ::

<u>አስተዳደራዊ ፍትህ</u>

በአስተዳደር ህግ ውስጥ ሳይጠቀስ የማይታለፈው የዳኝነት ስርዓቱ (Administrative justice) ነው፡፡ በመንግስት የአስተዳደር ስራ ላይ ውሣኔ እንዲሰጡ የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው የዳኝነት አካላት (tribunals) አሉ፡፡ ብዛታቸው እና ጥንቅራቸው ከሀገር ሀገር ይለያያል፡፡ ለእነዚህ አካላት መቋቋም አንድ ምክንያት በመንግስት /እና ሌሎች አካላት/ መሀከል የሚፈጠርን ግጭት የህግ መርህን ወይም ስታንዳርድን ብቻ መሠረት በማድረግ በመደበኛ በፍ/ቤት ብቻ መፍታት አይቻልም ነው፡፡ በሌላ በኩል የነዚህ አካላት አስፈላጊነት፡-

- የየሀገሩ ህገ መንግስት፣
- ፍ/ቤቶች ከሚከተሉት ስነ-ስርዓት ጥብቀት፣
- ፖሊሲን ተግባራዊ በማድረግ ስርዓት ውስጥ ወጭ ቆጣቢ' ፈጣን' መንገድ ከማስፈለጉ አንፃር፣
- የኤክስፐርት እና የተካኑ ሰዎች እውቀት ከማስፈለጉ አንፃር፣
- በልዩ ፍ/ቤቶች እየበዛ ከመጣው የስራ ጫና አንፃር' እና ከሌሎች የአማራጭ ሙግት መፍቻ መንገድ ጥቅሞች አንፃር እየተመዘነ የሚወሰን ነው፡፡

በዚህ መልኩ የሚቋቋሙ የዳኝነት አካላት ቁጥራቸው እና አይነታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚቀያየር ይሆናል፡፡ በ1991-92 በእንግሊዝ ሀገር የነበረውን ሁኔታ ብንመለከት እንኳን

የዚህ አይነት ስልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች ዝርዝር በየዓመት እየታተመ ግልፅ እንዲሆን የሚደረግ ሲሆን በአይነታቸው ከ16 በላይ ናቸው፡፡[1]

የተወሠኑት የአስተዳደር ፍ/ቤቶችም አካላት የራሳቸው ይግባኝ ሰሚ አካላትም አሏቸው፡፡ እነዚህ አካላት በጥቅሉ ሲታይ ማህበራዊ ዋስትና እና ማህበራዊ አገልግሎት'መሬት:ንብረት እና የቤት ጉዳይ' የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና ግብር እንዲሁም ፈቃድ መስጠትን እና የኢንዱስትሪ እና ስደተኞች ጉዳይን በልዩ እውቀት እንዲዳኙ የተቋቋሙ ናቸው፡፡ ይህ ማለት ግን ሁሉም አካላት ተመሳሳይ ስልጣን አላቸው ማለት አይደለም፡፡ በሌላ በኩልም ጥንቅራቸው፣ የዳኞች አሿሿም፣ ስልጣናቸው፣ የሚከተሉት ስነ-ስርዓት' ውሣኔያቸው የመጨረሻ ስለመሆኑ አለመሆኑ እና የሚታተም ስለመሆኑ' የዳኝነት አካሉ እና የሚገኝበት የአስተዳዳር አካል ያላቸው ግንኙነት እና በመሰል ነጥቦች ላይ ይመሳሰላሉ ማለትም አይደለም፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ- መንግስትን ስንመለከት የአስተዳደር ፍ/ቤት የማቋቋምን አስፈላጊነት በሚገባ ያገናዘበ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሰዎች ፍትህ የማግኘት መብት ያላቸው ፍርድ ቤት በመቅረብ ብቻ ሳይሆን "በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል" ፊት ቀርበው ውሣኔ ወይም ፍርድ በማግኘት ነው፡፡ (የህገ-መንግስቱ አንቀጽ 37'78 (4))ነው፡፡) ይህ የስልጣን ወሰን በክልል መንግስታት ደረጃም በተመሳሳይ መልኩ የሚፈፀም ነው፡፡ በዚህ መልኩ ሊቋቋም ከሚችሉ ፍ/ቤቶች ውስጥ የሥራ ክርክር ጉዳይን እና የግብር ጉዳይን ተመልክተው ውሣኔ የሚሰጡ ተቋማት ሊጠቀሱ እንደሚችሉ አቶ ፋሲል ናሆም በጽሁፋቸው ጠቅሰዋል(ፋሲል ገጽ' 101)፡፡ይሁን እንጂ ከእነዚህ አካላት በተጨማሪ ሌሎች ውሣኔ ሰጪ የአስተዳደር ፍ/ቤቶች ሊቋቋሙ ይችላሉ፡፡ አወቃቀራቸውም በአስፈሚው ውስጥ አለዚያም ከአስፈፃሚው ውጭ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ መልኩ ከተቋቋሙት የአስተዳደር ፍርድ ቤቶች ውስጥ፡-

- የመንግስት ሰራተኞችን ጉዳይ የሚመለከተው የአስተዳደር ፍ/ቤት በሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ውስጥ፣

[1] የእርሻ ጉዳይ የሚመለከት (Agricultural Land tribunal)፣ የሲቪል አቪየሽን፣የዳታ ጥበቃ፣የት/ት ጉዳይ፣የስደተኛ ጉዳይ፣ የኢንቨስትመንት ጉዳይ፣የአእምሮ ጤናን ጉዳይ፣የጡረታ ጉዳይ /የቦርድ ጉዳይ/፣የኪራይ ስሌት(Rent assessment)ጉዳይ፣የማህበራዊ ዋስትና ጉዳይ፣የአካል ጉዳት ጉዳይ፣የገቢ ግብር ጉዳይ፣የትራፊክ ጉዳይ፣የvat ጉዳይ፣የህፃናት ጉዳይ ለመስማት

- የጡረታና ማህበራዊ ጉዳይ ላይ ውሣኔ የሚሰጠው ጉባዔ በጡረታና ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን ስር፣
- ግብር ይግባኝ ሰሚ ቦርድ፣
- የቦታ ማስለቀቅ ጉዳይ ይግባኝ ሰሚ ወዘተ ይጠቀሳሉ፡፡

የአስተዳደር ፍ/ቤቶች በጥንቅራቸው' በስልጣናቸው' በአደረጃጀታቸው እና የሚቋቋምበትን ምክንያት በተመለከተ ከላይ የተመለከተው አጠቃላይ ምክንያት በተመሳሳይ ለሀገራችንም ይሰራል፡፡ሁሉም ፍ/ቤቶች በሚሰጡት ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ከተገኘ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ስህተቱን የማረም ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ህገ መንግስቱ የዳኝነት ስልጣን የፍ/ቤቱች ነው በማለት የደነገገ በመሆኑ በዚህ መልኩ በመደበኛ ፍ/ቤት መመርመራቸው ተገቢ ነው፡፡ የፍ/ቤቶቹን ማቋቋሚያ አዋጆችን ስንመለከት ከላይ የተጠቀሱት ጥቅል አላማዎች በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ ተካተውባቸው እናገኛለን፡፡ ለእነዚህ አካላት ጉዳይን አቅርቦ ውሣኔ ማግኘት በህገ መንግስት አንቀጽ 37/1/ ስር የተመለከተውን ፍትህ የማግኘት መብት በተጨባጭ (Access to justice) ማረጋገጥ ነው፡፡

ከዚህ በተረፈ በአስተዳደር ጉዳይ ውሣኔ እንዲሰጡ ሳይሆን የአስተዳደር ስራን እንዲያግዙ በተለይ የሚቋቋሙ አካላት ይኖራሉ፡፡ የህዝብ ጉዳይ አጣሪ /Public Inquiry/ በተለይ ለሚጣሩ ጉዳዮች ወይም የተለየ ክስ /ሙስና/ በቀረበ ጊዜ በገለልተኛነት አጣርተው ፍሬ ነገሩን በወሳኝ መልኩ የሚያቀርቡ አካላት ይጠቅሳሉ፡፡ አስተዳደራዊ በደል ተፈፀመ ሲባል ቅሬታ የሚሰማበት የእንባ ጠባቂ ተቋም ወይም የሰብአዊ መብት ኮሚሽን በዚሁ ሊካተቱ ይችላሉ፡፡ እነዚህ አካላት የፖርላማ ተጠሪ ሆነው ከዳኝነት አካሉ ጋር ግን ግንኙነት የላቸውም፡፡

<u>የአካባቢ አስተዳደር</u>

በአስተዳደር ህግ ውስጥ ሊጠቀስ የሚገባው የአካባቢ አስተዳደር (Local Government)ጉዳይ ነው፡፡ መንግስት በብሔራዊ /ክልላዊ/ ደረጃ የሀገርን ኢኮኖሚ የመምራት' አካባቢን የመቆጣጠር' መሠረታዊ አገልግሎቶችን የመስጠት ወዘተ ኃላፊነቶች ያሉበት ሲሆን ፍፁም አካባቢያዊ የሆኑ ግልጋሎቶች ደግሞ በአካባቢ መስተዳድር ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ተግባራት ውሰጥ የቁጥጥር ተግባር' ፈቃድ የመስጠት (Lincensing, Regulation) በእነዚህ አካላት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህ ስራም

በአካባቢ ም/ቤት' ኮሚቴ' የመንግስት ሰራተኛ ባልሆኑ ሰዎች የሚሰጥ ነው፡፡ ተግባራቸው ግን ተጠያቂነትን የሚያስከትል' የህዝብ ፍላጎትን መሠረት የደረገ ሆኖ የ"Ultra Virus" ህግም ተገዥ ናቸው፡፡

ከአካባቢ አስተዳደር ጋር ተያይዞም ሀገራችን የፌዴራል ስርዓትን የምትከተል ሲሆን ያልተማከለ አስተዳደርንም ተግባራዊ አድርጋለች፡፡ ይህ መብት በህገ መንግስቱ መግቢያ' አንቀፅ 39(3) '98(1)' ላይ የተቀመጠ ነው፡፡በዚህ መሠረት ህዝቡ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ በቀጥታ በመሳተፍ በቋንቋውና በባህሉ መሠረት ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት አቅዶ ውጤታማ ስራ እንዲሰራ ያስችለዋል፡፡ የአካባቢ አስተዳደሩ በስልጠና የሰው ኃይል' ፋይናንስ' ዘመናዊ መሳሪያዎች የሚሟላ ሲሆን የህዝብ አደረጃጀቶችን ያቋቁማል፡፡ የዚህ መርህ አላማም ለህዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ እና ውሣኔ ሰጭነት አካባቢውን በማልማት ለሀገር ልማት አስተዋፅኦ ማበርከት ነው:: የህዝቡ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ጉዳይ ከህገ መንግስቱ ፖለቲካ ነክ አላማዎች ውስጥ አንዱ ነው(የህገ መንግስቱ አንቀጽ 88/1/)፡፡ እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ እና ህዝብ በክልል እና በፌዴራሉ መንግስት ውስጥ ፍትሐዊ የሆነ ውክልና የሚኖረው ሲሆን በአካባቢው የራሱን የአስተዳደር ተቋም (Institutions of Government)የማቋቋም ዲሞክራሲያዊ መብት አለው(አንቀፅ 39/3/)፡፡ ስለሆነም ከህገ መንግስቱ አንፃር የአካባቢ አስተዳደር (ህግ) እውቅና አግኝቷል፡፡

<u>ህግ ማውጣት</u>

አስፈፃሚው አካል ከላይ የተገለፀው ህግ የማስፈፀም ኃላፊነት በህገ-መንግስቱ የተሰጠው ከመሆኑ በተጨማሪ "አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ" የማውጣት (ከማስፀደቁ ጋር)እንዲሁም ከተወካዮች ምክር ቤት በሚሰጠው ውክልና መሠረት ደንቦችን የማውጣት ስልጣን አለው(አንቀፅ 77/13)፡፡ የተወካዮች ምክር ቤት ያወጣቸውን ህጎች እና የተሰጡ ውሣኔዎችን ለማስፈፀም "መመሪያ የመስጠት" ስልጣንም አለው፡፡(የህገ መንግሥቱ አንቀፅ 77/1/)

በጥቅሉ የአስፈፃሚውን አካላት አደረጃጀት' ሀገራዊ:ህግ ነክ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ስልጣን አለው፡፡ የመንግስት መ/ቤቶች የአስተዳደር ፍ/ቤት እንዲኖራቸው ቢወሰን ስለአደረጃጀት (Organization) የመወሰን ስልጣን ያለው የአስፈፃሚው አካል ነው፡፡ ህግና ስርዓት መከበሩን (አንቀፅ 77/9/) የማረጋገጥ ኃላፊነትም ተጥሎበታል፡፡

በአጠቃላይ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት 3ት የመንግስት አካላትን በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ያደራጀ ሲሆን የአስፈፃሚው አካል ከዚህ በላይ በተመለከተው አግባብ ህግና ስርዓት መከበሩን ለማረጋገጥ ከተሰጠው የአስፈፃሚነት ስልጣን በተጨማሪ ለዘመኑ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ህግ የማውጣት እና የዳኝነት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

የአስተዳደር አካል ይህን ስልጣን በተግባር በሚያውሉበት ጊዜ ለሚፈፅማቸው ስህተቶች ሊከሰስና ሊጠየቅ ይችላል፡፡ስልጣኑ በተግባር የሚውለው አስቀድመው በተቀመጡ ደንቦች መሠረት ነው፡፡ ይህ በግልፅ የሚፈፀም ሆኖ ’ በሚስጥር እና በዘፈቀዳዊነት የማይፈፀም ነው፡፡

<u>መርሆዎች እና ህገ መንግስቱ</u>

ከፍ ሲል ለማመልከት የተሞከረው የአስተዳደር አካላት እነማን ናቸው? ምን ተግባር ያከናውናል? ለምን? የሚለውን እና መሰል ጥያቄዎችን ነው፡፡ ቀጥሎ የምንመለከተው የአስተዳደር አካላት በሚያከናውኑት ተግባር ሁሉ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ህገ መንግስት አንፃር ሊከተሏቸው የሚገቡ ጠቅላላ መርሆዎችን እና አቅጣጫዎችን ነው፡፡

የአስተዳደር አካላት የመዳኘት ስልጣን ሊሰጣቸው እንደሚቻል አይተናል፡፡ ምንም እንኳን የአስተዳደር አካላት ውሣኔ የመስጠት ስልጣን የተሰጣቸው ቢሆንም የሚሰጡት ውሣኔ ላይ ቅሬታ ቢኖር ለመደበኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ይመረመራል፡፡ መደበኛ ፍ/ቤት የሚያከናውነው ምርመራ/ክለሳ/ ሙሉ ነው ወይስ በተወሰነ ነጥብ ላይ የሚለው የልዩነት ነጥብ ነው፡፡ ይሁን እንጅ የአስተዳደር አካላት በሚወሠስንበት ጉዳይ ላይ ልዩ የሆነ የሙያ ክህሎት ያላቸው ሲሆን መደበኛ ፍ/ቤቶች ደግሞ ልዩ የሆነ የህግ እና የመርህ ክህሎት ያላቸው በመሆኑ የክለሳ ወሰኑ ይህንን ያጣጣመ ሊሆን እንደሚገባው የአብዛኛው ስምምነት ነው፡፡ መደበኛ ፍ/ቤት የሂሳብ፣ የምህንድስና፣ የህክምና ወዘተ ኤክስፐርት ሊሆን ይቸገራል፡፡ ስለሆነም የአስተዳደር አካላት የሚሰጡት ውሣኔ በፍሬ ነገር ደረጃ የመጨረሻ እንዲሆን ነገር ግን ከህግ አንፃር የቀረበ ቅሬታ በመደበኛ ፍ/ቤት በክለሳ እንዲመረመር ስምምነት አለ፡፡ የአስተዳደር አካላት ይህንን ስልጣን በቅንነት ሌላውን ላለመጉዳት እንዲገለገሉበት ይጠበቃል፡፡ የህግን ልዩ ኘሮሰስ ጠብቀው ዘፈቀዳዊ ባልሆነ መንገድ እንዲተገበሩትም ይጠበቃል፡፡ ከፍ ሲል የጠቀስናቸው የሀገራችን የአስተዳደር ፍ/ቤቶች በማቋቋሚያ ህጎቻቸው ላይ እንደተመለከተው በፍሬ ነገር ላይ

የሚሰጡት ውሣኔ የመጨረሻ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በህግ ጉዳይ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ከፈፀሙ ጉዳይ እንዳግባቡ ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ወይም ለክልል ጠ/ፍ/ቤት ቀርቦ ይመረመራል፡፡ ጠ/ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ውሣኔ ለመስጠት ወይም በአስተያየት (Recommendation) ለአስተዳደር ፍ/ቤቱ የመመለስ ስልጣን አለው፡፡ በህገ መንግስት ላይ እንደተመለከተው የውሣኔ ሰጭ አካላት ስልጣን በዘፈቀደ የሚከናወን ሳይሆን "በህግ በተደነገገ የዳኝነት ስርዓት" (Legally prescribed procedure)የሚመራ ነው(አንቀፅ 78/4/)፡፡ ይህ ስልጣን አንድን ሌላ ሰው ለመጉዳት በማሰብ ተግባር ላይ ከዋለ የህገ መንግስቱ አንቀፅ 25 ስር የተቀመጠው የእኩልነት መብት ይጣሳል፡፡ ጉዳዩ በስልጣን ያላግባብ መገልገል ከሆነ በወንጀል የሚያስጠይቅ ሲሆን ተግባሩም በፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 404 አንፃርም ፈራሽ (Ultra virus)ሊሆን ይችላል፡፡

የአስተዳደር አካላት በውክልና ህግ በሚያወጡበት ጊዜ ስልጣናቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ይጠበቃል፡፡ ይህ ባይፈፀም የወንጀል ተጠያቂነትን ያስከትላል' የወጣው ህግ እንዲፈርስ ይደርጋል፡፡(የህገ መነግስቱ አንቀፅ 9/1/)

ከብዙ ህጎች ውስጥም አንድ የመንግስት ሠራተኛ ለፈፀመው ጥፋት በአስተዳደሩ የሚጠየቅ ከሆነ ጥፋቱ እንዲገለፅበት ብቻ ሳይሆን ራሱን የሚያሰማበት እድል ሊሰጠው እንደሚገባ አ.ቁ.515/99 አንቀጽ 67/2/ ስር ደንግጋል፡፡

በተናጠል ጉዳዩ አ.ቁ.515/99 በመንግስት ሰራተኛ ላይ የሥነ-ሥርዓት ርምጃ ከመወሰዱ በፊት የሚመለከታቸውን ሰዎች መስማት' ማስረጃ መስማት እና መመዘን' ክርክር መስማት በዚሁ ስር የሚታይ የውሣኔ ሰጪ ግዴታን የሚያሳይ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

የአስተዳደር ውሣኔ ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ሊሰጥ ይገባዋል፡፡ ይህ ጊዜ ገደብ በልዩ ህግ ተወስኖ ከሆነ ይኸው ህግ መከበር ያለበት ሲሆን በልዩ ህግ ያልተወሰነ እንደሆነ ግን በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት አንድ ምክንያታዊ የሆነ የአስተዳደር አካል በሚያስፈልገው ጊዜ ውስጥ ውሣኔ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ ይህ ጊዜም በጉዳዩ ላይ በጊዜው ይግባኝ የሚያስብል ' ወቅታዊ ትችት እና ተቃውሞ የሚቀርብበትም በመሆኑ ለዚሁ ተግባር ምቹ በሆነ ጊዜ ውስጥ መስጠት ይኖርበታል፡፡ ይህ ባይፈፀም የህገ መንግስቱ ተጠያቂነት መርህ ትርጉም ያጣል፡፡በአ.ቁ 262/2002 አንቀጽ 66 መሠረት ጉዳይን ሆነ ብሎ ማጓተት ከባድ በሆነ የዲሲፒሊን ቅጣት እንደሚያስቀጣ ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡ በ1996 በወጣው የወንጀል ህግ መሠረትም ጉዳይን ማጓተት በወንጀል

የሚያስጠይቅ ነው፡፡ በርካታ የአስተዳደር ፍ/ቤቶች ከሚቋቋሙበት ምክንያት ውስጥ አንዱ ጉዳዩን ያለ ብዙ ውጣ ውረድ በአጭር ጊዜ እልባት እንዲሰጡ ማስቻል መሆኑ ማስታወስም ይገባል፡፡

የሚሰጠው ውሣኔም ሆነ የሚወጣው ደንብ በምክንያት የተደገፈ መሆንም ይኖሩበታል፡፡ ይህም ደንቡ ወይም ውሣኔው የህግ' የመርህ' የፍሬ ነገር' የደረጃ (Standard) ወዘተ ምክንያት(ድጋፍ) ሊኖረው ይገባል ከሚለው ይጀምራል፡፡ መርሁ የመልካም አስተዳደር መሠረት ነው የሚሉ ፀሐፊዎች ያሉ ሲሆን የተደረሰበት መደምደሚያ (ደንብ ወይም ውሣኔ) ተጠያቂነት የሰፈነበት ትክክለኛና ፍትሐዊ መሆኑን ለማሳየት የሚጠቁም ከሚሆን በላይ የአስተዳደር አካሉ ውሣኔ ግልፅነት የሰፈነበት እውነት ላይ ለመድረስ ጥረት ያደረገ መሆኑን ያሳያል፡፡ የውሣኔዎች ወጥነት' ተገማችነት' ገለልተኛነት' ርቱዕ መሆንና ታማኝነትን ያረጋግጣል፡፡ የሚሰጠው ምክንያትም በበቂ ሁኔታ (Adquatly) መገለፅ ይኖርበታል፡፡ አንዳንድ ሀገሮች (ምሳሌ ፈረንሳይ) ውሣኔ በዚህ መልኩ በምክንያት መተንተን እንዳለበት ብቻ ሳይሆን ውሣኔ ለመስጠት ለምን እንዳስፈለገ ማሳየት ይኖርበታል (Motivated decision)ይላሉ፡፡

በአስተዳደሩ አካል የሚሰጥ ውሣኔ መብቱ ወይም ጥቅሙ የሚነካ ማንኛውም ሰው በጉዳዩ ላይ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ሁኔታው ሊገለፅለት፣ሊሰማ እና አስተያየቱን እንዲያሰማ እድሉ ሊሰጠው ይገባል፡፡ ይህ የመስማት መብት የዲዩ ኘሮሰስ አካል ነው ለማለትም ይቻላል፡፡ ይህ መፈፀሙ የአስተዳደሩ አካል ውሣኔ ህጋዊነት (Legitimacy)የተላበሰ ገለልተኛ(Impartial)፣ ፍትሐዊ እና ርቱዓዊ መሆኑን ለማሳየትም ይጠቅማል፡፡ እነዚህ መርሆዎች በህገ መንግስቱ እውቅና ያገኙ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ በአጠቃላይ በተለይ ደግሞ እያንዳንዱ ብሔር' ብሔረሰብ እና ህዝብ በቀጣይነት የመልማት መብት አለው፡፡ ህዝቡ በልማት ተግባር ውስጥ የመሳተፍ መብት ያለው ሲሆን አካባቢውን በሚነካ ፖሊሲ ወይም ኘሮጀክት ጉዳይ ላይ አስተያየቱ ሊሰማ (Consustation)ይገባል(አንቀጽ 43/2/):: መንግስት በዚሁ የምክክር መርህ መሠረት መመራት ያለበት ነው፡፡ ህዝቡ በቀጥታ በሚመለከተው ጉዳይ ላይ አስተያየቱን የሚሰጥበትን ምክክር የሚያደርግበት ደረጃ የይስሙላ ሳይሆን "ሙሉ" እንዲሆንም የህገ መንግስቱ አንቀጽ 92/2/ ያስገድዳል፡፡

የአስተዳደሩ አካል ደንብ በሚያወጣበት ወይም ውሣኔ በሚሰጥበት ጊዜ አግባብ ላላቸው ፍሬ ነገሮች እና ማስረጃዎች ሁሉ ተገቢውን ግምት ("Adequate consideration") መስጠት ይኖርበታል። የአስተዳደር አካሉ ለጉዳዩ ጭብጥ ማህበራዊ' ኢኮኖሚያዊ' ፖለቲካዊ ወዘተ ሁኔታዎች እና ለአማራጫቸው ሁሉ ይህን ተገቢ ትኩረት መስጠት ይጠበቅበታል። አንዳንድ ሀገሮች ይህንን ሁኔታ principle of due care, principle of proper investigation... እያሉ ይጠሩታል። አለመከበሩም ተግባሩን ህገ ወጥ ሊያደርገው ይችላል። አልፎ አልፎም ይኸው አካል በጉዳዩ የአዋጭነት ጥናት' (የተፅእኖ ጥናት) (Impact assessement)እና ልዩ ልዩ የዳሰሳ ጥናቶች እንዲያደርግ ሊጠበቅ ይችላል። የአስተዳደር አካሉ ህዝቡን የማማከር ጠቅላላ ግዴታ በዚሁ ስርም የሚፈፀም ነው። "ሙሉ ምክክር" ይህንን ያቅፋል።

ይህ የመሳተፍ መብት (Participation)' ተደራሽ መሆን (Access) ጉዳይ ከስነ-ስርዓት አንፃር ዋናው የዲሞክራሲያዊ ስርዓት መገለጫ እንደሆነ ፀሐፊዎች ይገልፃሉ (ምሳሌ ፒተር:ሱክ)። በህገ መንግስቱ አንቀጽ 89/6/ እና /7/ መሠረት የሀገር ፖሊሲ እና ኘሮግራም በሚዘጋጅበት ጊዜ ያለምንም ልዩ ሁኔታ መንግስት ህዝቡን ማሳተፍ ይገባዋል። ሴቶች ከወንዶች እኩል እንዲሳተፉ ግዴታም ተጥሏል።

የአስተዳደር አካላት የሚሰጡት ውሣኔ ወይም የሚያወጡት ደንብ የተለያዩ ፍላጎቶችን የሚያመዛዝን መሆን ይጠበቅበታል። የሚሰጠው ውሣኔ ከጉዳቱ (Cost) ጥቅሙ (benefit) የሚመዘን ሊሆን ይገባዋል(Principle of economy):: የህዝብ ጥቅምን ከግል ጥቅምም መመዘን ይጠበቅበታል። የጥቅም ግጭት ያለበት ውሣኔ ሊሰጥ አይገባውም።የተለያዩ ፍላጎቶችን ከመመዘን ጋር ሊታይ የሚችለው ሌላው ነጥብ የሚሰጠው ውሣኔ ሊያሳካው የሚፈልገው ግብ ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት ካለ ተመዛዛኝ (proportional)መሆን ይኖርበታል። ውሣኔ ሰጭ አካል ይህንን ጥቅምና ጉዳት በአግባቡ መመዘን ይጠበቅበታል። የህዝብ ጥቅም ከግለሰብ ጥቅም መዝኖ ሲገኝ በግለሰቡ ላይ የሚደርስ ጉዳት ካለ ተመጣጣኝ አስተዳደራዊ ካሳ በመክፈል ፍላጎትን ማመዛዘን ይቻላል(የህገ መንግስት አንቀፅ 44/2/):: በመንግስት ኘሮግራም የተነሳ ጉዳት የደረሰበት ሰው በበቂ የገንዘብ መጠን ወይም በአማራጩ ሊካስ የሚገባው ሲሆን በመንግስት ድጋፍም ሌላ ቦታ እንዲሰፍር ይደረጋል። ይህ የህገ መንግስቱ መርህ የተለያዩ ፍላጎቶች ከውሣኔ በፊት መመዘን እንዳለባቸው የሚያመለክተን ሲሆን በዚህ መሠረት በሚሰጥ

ውሣኔ የሚጎዳ ሰው ቢኖር አሁንም ካሳው በተመሳሳይ መርህ የሚመዘን መሆኑን ነው፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት ከሚመራበት መርህ ውስጥ አንዱ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታው እንዲሻሻል ማድረግ ሲሆን በዚህም የሀገሪቱን ሀብት እኩል እና ፍትሐዊ በሆን መንገድ እንዲከፋፈሉ ማድረግ ነው፡፡ ለግለሰብ ሳይሆን ለሁሉም ጥቅም ሲባል ወደ ኋላ ለቀሩ ብሔረሰቦች እና ሴቶች ልዩ ድጋፍ ሊደርግ ይገባል፡፡ /አንቀጽ 89 እና 25/፡፡ መንግስት መሬት በህዝብ ስም ይዞ የሚያስተዳድርውም ለጋራ ጥቅም እድገት (Common Benefit)ነው /አንቀጽ 89/5/::

የአስተዳደር አካል የሚሰጠው ውሣኔ ህጋዊ (legal)ነው ተብሎ መገመትም ከህጋዊነት መርህ (Principle of legality) ሊወጣ ግን አይገባውም፡፡ ይህን ለዚህ ፅሁፍ ሲባል ከሁለት ማዕዘን መመልከት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው የአስተዳደር አካሉ ውሣኔ በሚሰጥበት ጊዜ ራሱ ባላወጣው ሌላ ህግ በግልፅ የተሰጠው ስልጣን መኖሩን ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡ ስለሆነም አካሉ ለስራው መሠረት የሆነው ህግ ሊኖረው ይገባል፡፡ በሁለተኛ ደረጃም ስልጣኑን ከህግ በተቃራኒ መልኩ ስራ ላይ ማዋል የለበትም፡፡ በዚህ ጊዜ የአስተዳደር አካሉ ራሱ ካወጣውም ህግ ቢሆን በተቃራኒው ሊሰራ አይገባውም ማለት ነው፡፡ ይህ እንግሊዞች የህግ የበላይነት (Rule of Law)የሚሉት የህገ መንግስታዊነት አስተዳደር ከስልጣን አሳልፎ መስራትን(Excess of power) ለማስቀረት ያገለግላል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ልዩ ሁኔታ የለም፡፡ ይህ በፍፁም አስገዳጅነት የሚፈፀም ሊሆን በተቃራኒው ከተሰራ የፖለቲካ ተጠያቂነት የሚያስከትል እንዲሁም የፍ/ቤት ቁጥጥር የሚደረግበት ነው፡፡ ይህ ቢታለፍ ውሣኔው በክለሳ መልክ እንዲታይ እና ውድቅ ሆኖ የኢንጀክሽን(injection) ተዕዛዝ የሚሰጥበት ነው፡፡

የሀገራችንን የአስተዳደር አካላት ስንመለከት የስልጣናቸው ምንጭ ህገ መንግስቱ ስለሆነ የስልጣን ገደባቸውም ህገ መንግስት ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በመግባቢያው ላይ ህዝቡ በህግ የበላይነት መርህ ላይ ተመስርቶ ለመኖር መቁረጥን ያሰምርበታል፡፡ ሁሉም ህጎች ከዚሀ ህገ መንግስት ጋር ቢጋጩ አይፈፅሙም/አንቀጽ 9/፡፡ ለጠቅላይ ሚኒስቴሩ እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከተሰጡት ስልጣኖች ውስጥ በህግ አውጪው የወጡ ህጎች' ፖሊሲዎች መከበራቸውን የማረጋገጥ' በሀገሪቱ ህግና ስርዓት መስፈኑን የማረጋገጥ ግዴታ የአስተዳደር አካላት ስልጣን መሠረተ ህግ

መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ (አንቀፅ 74 እና 77)_የአስተዳደር ሕግ እድገትና መሠረቱ የአስፈፃሚውን ስልጣን በህግ አውጪው በወጣ ህግ መሠረት የመምራት ፍላጎት እና የ(Prerogative) ስልጣንን መቀነስ ነው፡፡ አዲስ የመንግስት ስልጣን ሲያስፈልግ ከህግ አውጪው መገኘት አለበት የሚለው እምነት የ1989 ቢል ኦፍ ራይትስ ውጤት መሆኑም ይታወሳል፡፡ አስተዳደሩ ወይም ባለስልጣኑ በተሰጠው ስልጣኑ ውስጥ "Intra vivos" መስራት ይኖርበታል ማለት ነው፡፡

የአስተዳደር አካላት ተግባር በህግ መመራት ይገባዋል ሲባል ግን በህግ ማዕቀፍ ውስጥ ያሉ ነገር ግን በአዋጅ አይነት በህግ ያልተፃፉ እንደ እቅድ ማውጣት (Planning)' የበጀት ዝግጅት' የመሳሰሉት ተግባራት ዋናውን ህግ በሚያሟሉ መመሪያዎች (rules) እና የውሣኔ ሰጭ አካላት ትርጉም አይሟሉም ማለትም አይደለም፡፡ በሌላ በኩል የአስተዳደር አካሉ በህጉ ውስጥ ለመወሰን የመምረጥ ነፃነቱን (discretionary power) አይጠቀምም ማለት አይደለም፡፡ ይህ ስልጣን አንድ ጉዳይ ከሌላው በተለይ በተመረጠ አንድ መንገድ የተወሰነበት ምክንያት ሌላውን ምክንያታዊ ሰው በሚያሳምን መልኩ መፈፀም ይኖርበታል፡፡ ስልጣኑ እጅግም ልል እጅግም ጥብቅ አይሆንም፡፡

የሚሰጡ ውሣኔዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሰዎችን በተመሳሳይ መልኩ& በተለያዩ ሁኔታ ውስጥ ያሉትን ደግሞ እንደ ልዩነታቸው መጠን ሊያስተናግድ ይገባዋል፡፡ ይህም ከመንግስት በሚገኝ አገልግሎት' በትምህርት እድል አሰጣጥ እና በመሳሰሉት ሊገለፅ ይችላሉ፡፡ የእኩልነት መርህ ጠቅላላ የህግ መርህ ሆኖ የአስተዳደር ህግ መርህም ነው፡፡ ገለልተኛ መሆን' አድልዎ አለመፈፀም' ፍትሐዊ መሆን በዚህ መልኩ ሊታዩም ይችላሉ፡፡ ከተለመደው መውጣት ሲያስፈልግም ከፍ ሲል በተገለፀው መልኩ በበቂ ምክንያት ሊታገዝ ይገባዋል፡፡ የአስተዳደር ቅሬታ ስሚ አካልትም ይህንን ነጥብ እንደ አንድ የውሣኔ መለኪያ ቼክ ሊስት የሚጠቀሙበት ሆኖ ተጥሶ ሲገኝ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ነው፡፡ (የህገ መንግስቱ አንቀፅ 26 ይመልከቱ)፡፡ በሌላ በኩል ይህ መርህ በልዩ ህጎች የተካተተ ሲሆን አ.ቀ.515/99 አንቀፅ 6, 22, 64…መሠረት ሰራተኛ ሲመለመል' ሲያጓድል' ሲሰናበት…በዚሁ መርህ መሠረት መፈፀም እንዳለበት ግዴታ ተጥሏል፡፡

ከፍ ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው ዜጎች ትክክለኛ ውሣኔ ሊያገኙ ይገባል፡፡ ትክክለኛ ውሣኔ አገኛለሁ በማለት ሊገምቱና እርግጠኛ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ይህ የቅንነት እና

የእርግጠኛነት መርህ (Principle of good faith & legal certainity)ነው፡፡ የዜጎች ተቀባይነት ያለው (legitimate) ትክክለኛ ውሣኔ የማግኘት ጉጉት /ፍላጎት/ ሊከበር ይገባዋል፡፡ የአስተዳደር አካሉ በሚሰጠው ውሣኔ ይህንን ፍላጎት ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡ የውሣኔ ሰጭ አካል ዜጎች አላስፈላጊ ጉጉት እንዲኖራቸው ማድረግ የሌለበት ሲሆን አስፈላጊውን ጉጉት ማርካት ያለበት መሆኑ የቅንነት መርህን ማሟላት ነው፡፡ በዚህ መርህ መሠረት ለምሳሌ አንድ የአስተዳደር አካል አስፈላጊ ያልሆነ ቃል ለዜጋው በመግባት አስፈላጊ ያልሆነ ተስፋ እንዲያድርበት ማድረግ አይኖርበትም፡፡ ለዚህ መርህ የተለየ ክብደት የሚሰጡ እንደ ቤልጅየም የመሰሉ ሀገራት የተገባው ቃል ከህግ ጋር የሚጋጭ ቢሆንም እንኳን ሁለቱ መርህ /ቅንነት እና ህጋዊነት/ ተመዝነው እንደሁኔታው አንዱ ሊመረጥ እንደሚቻል ይስቀምጣሉ፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ - መንግስት መሠረት የቤልጂየሙ አይነት ድንጋጌ የሌለ ሲሆን ህግ የበላይነት መርህ ላይ ልዩ ሁኔታ (exception)የለም፡፡ በተጨባጭ መሠራት ያለባቸው ሁኔታዎች እና መርሆዎች የተቀመጡ ሲሆን ከዚህ ውጪ ተስፋ በመስጠት ለሚድረስ ጉዳት አስተዳደሩ የወንጀል' አስተዳደራዊ እና የፍ/ብሔር ኃላፊነት ሊከተለውም ይችላል::(ምሳሌ የፍ/ብሔር ህግ ቁጥር 1689' 1161,1184' 2055)

ዜጎች በአስተዳደር አካሉ ተግባር ላይ እርግጠኛ እንዲሆኑ ከሚያደርጓቸው ነገሮችን ውስጥ ሌላው መጠቀስ ያለበት የሚወጡ ደንቦች እና የሚሰጡ ውሣኔዎች ግራ የማያጋቡ (forseeable) እና ተደራሽ መሆናቸው ነው፡፡ ደንቦች በህትመት መውጣታቸው' ወደ ኋላ ተመልሰው የማይሰራ መሆናቸው (ከልዩ ሁኔታዎች በቀር)' ግልፅ መሆናቸው' አንዳንድ ስህተቶችን በተወሰነ ጊዜ ለጥያቄ ካልቀረቡ መርጋት /ይጋር/ ያለባቸው መሆኑ' እና የመሳሰሉት ዜጎች በአስተዳደር አካሉ ተግባር የእርግጠኝነት ስሜት እንዲኖራቸውና የተረጋጋ ህይወት እንዲኖሩ የሚያስችላቸው በመሆኑ በአግባቡ ሊተገበሩ ይገባል(የፍ/ሕግ/ቁ.402/2/,1677/1845)፡፡ በህገ መንግስቱ ውስጥ የምናገኛቸው የዜጎች የመስማት እና ባልተሸራረፈ መልኩ በውሣኔ ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ የሚሰጡ ውሣኔዎች እና ደንቦች ግራ እንዳያጋቡ ያደርጋሉ፡፡ ከህገ-መንግስቱ መርሆዎች ውስጥ አንዱ የመንግሥት አሰራር በግልፅ መከናወን ያለበት መሆኑ ተግባሩ ተገማች' የሚታይ እና ግራ የማያጋባ እንዲሆን ያስችለዋል፡፡

ከህገ መንግስቱ አንፃር ሊጠቀስ የሚገባው ሌላው መርህ የአስተዳደር ህግ እና ውሣኔዎች ወደ ኋላ ተመልሰው መስራት ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለው የመርህ ጥያቄ ነው፡፡የወጡ ህጎች ወደ ኋላ ተመልሰው መሠረታቸውን በተመለከተ ህገ መንግስት በግልፅ የሚከለክለው የወንጀል ህግን በተመለከተ ነው፡፡ የወንጀል ህጉም በተለይ አንድ ድርጊት/አልድርጊት ወንጀል ነው አይደለም የሚለውን ለመወሰን እንዲሁም ቅጣትን በተመለከተ የሚወጡ ድንጋጌዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ሆኖ ህጉ ተከሣሹን እስከጠቀመ ድረስ ወደ ኋላ ተመልሶ ሊሰራ ይችላል፡፡ የአስተዳደር ውሣኔዎችን በተመለከተ ተመሳሳይ ክልከላ በህገ መንግስት ውስጥ የለም፡፡ ስለሆነም ከህገ መንግስቱ አጠቃላይ መርህ ተነስተን የአስተዳደር አካላት ውሣኔ የዜጎችን የልማት' የፖለቲካ ' የኢኮኖሚ' ባህላዊ ወዘተ መብት ለማረጋገጥ እስኪቻል ድረስ ወደ ኋላ ተመልሶ ይሰራል ለማለት እንችላለን፡፡

የአስተዳደር አካል አንድ ጉዳይ ላይ ውሣኔ ሲሰጥ የማያልፋቸው የመምረጥ ስልጣን (discretionary power)አለው፡፡ ይህ ስልጣን ግን አስፈላጊ ያልሆኑ ቁም ነገሮችን ግምት ውስጥ በማስገባት' ተገቢ ላልሆነ ተግባር (Purpose)ስራ ላይ ማዋል' የህግ ስህተት ለመፈፀም'  ባልተፈቀደ ሁኔታ ይህን ስልጣን በውክልና አሳልፎ በመስጠት እና ተገቢውን ፍሬ ነገር በአግባቡ ከመመርመር በፊት አቋም በመያዝ እና መሠል ምክንያቶች አላግባብ ስራ ላይ ሊውል አይገባውም፡፡ በዚህ ረገድ የኢ.ፌ.ዲ.ሪን ህገ - መንግስት ስንመለከት የአስተዳደር አካላት የሚሰጡት ውሳኔ በህገ መንግስቱ መርሆዎች እና አላማዎች መሠረት መሆን ይኖርበታል (አንቀፅ 85)፡፡ ከእነዚህ መርሆዎች ውስጥ የእኩልነት' የህዝብ ጥቅም' የጋራ ጥቅም' የወንድማማችነት እና የአንድነት' ፍትሐዊነት' ወቅታዊነት/89/' የህግ የበላይነት መርህ እና የመሳሰሉት ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች በስራ ላይ እንዳይውሉ ከልካይ ናቸው፡፡ የአስተዳደር አካላት ውሣኔ ሲሰጡ ያላቸው የመምረጥ ስልጣን(discretionary power)በአግባቡ እንዲፈፀሙ የሚያስችሉ ማሰሪያ መርሆዎች ናቸው፡፡

<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. በሀገራችን የፍትህ ስርዓት አስፈፃሚው አካል ያለውን የተለያየ ስልጣን ተመልከት፡፡ ምን ምን አይነት ስልጣኖች አሉት? ከህገ መንግስቱ የስልጣን ክፍፍል አንፃር የአስፈፃሚው አካል ያለውን ስልጣን በምን ትገልፀዋለህ?

2. በሀገራችን የተቋቋሙ የአስተዳደር ፍርድ ቤቶችን ዘርዝር፡፡ የእያንዳንዱ ፍ/ቤት የተቋቋመበትን ምክንያት ህገ መንግስቱ ላይ ከተቀመጡት ሀገራዊ ግቦች እና አላማዎች አንፃር ተወያይበት፡፡
3. በሀገራችን ያሉ የአካባቢ አስተዳደሮችን በመመልከት ከህገ መንግስቱ አንፃር ያላቸውን ተግባር እና የሚመሩባቸው መርሆዎች ላይ ተወያዩ፡፡
4. የአስተዳደር ህግ እና የህገ መንግስት መርሆዎችን ዋነኛ መለያ አስቀምጥ፡፡ በዝርዝርም ተወያዩባቸው፡፡
5. በአስተዳደር ህግ ውስጥ ያሉ መርሆዎች ቢጋጩ ከህገ መንግስቱ አንፃር እንዴት ይፈታሉ? (ለምሳሌ የህጋዊነት መርህ ከቅን ልበና መርህ ጋር ቢጋጭ)

# ክፍል አስር

# ከታክስ ህግ አንፃር የህገ መንግስቱ መሠረታዊ መርሆዎች እና አቅጣጫዎች

## 10.1. ጠቅላላ

ለዚህ ፅሁፍ አላማ ሲባል ታክስ (ግብር) ማለት ለህዝብ አገልግሎት እንዲውል ከተለያየ ምንጭ በህግ መሠረት የሚሰበሰብ የመንግስት ገንዘብ (Public finance) ነው ለማለት እንችላለን፡፡

ምንም እንኳን ታክስ የረዥም ጊዜ ታሪክ ያለው ቢሆንም ዘመናዊ የግብር አሰባሰብ ስርዓት ከእንዱስትሪ አብዮት በኋላ በምዕራብ አውሮፖ እና በሰሜን አሜሪካ እንደተጀመረ ይነገራል፡፡ ከዚህ ጊዜ አንሰቶም ለግብር አሰባሰብ መሠረታዊ የሆኑት ጉዳዮች በህግ ማዕቀፍነት እየፀደቁ በስራ ላይ መዋል ጀምረዋል፡፡ *በሁሉም መስክ*

*ሲታይ የግብር አሰባሰብ ስርዓት መሠረታዊ መዋቅሩ በህግ የበላይነት (Rule of Law) መርህ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህም በውስጡ በርካታ መሠረታዊ ቁም ነገሮችን የያዘ ነው፡፡*

በአንድ ሀገር ውስጥ የግብር አሰባሰብ መዕከላዊ ትኩረትን የሚወስኑ በርካታ ቁምነሮች ይገኛሉ፡፡ የገጠሩ ወይም የከተማው ሴክተር መጠናከር ወይም መዳከም የትኩረት

አቅጣጫን ይወስናል፡፡ የሰራተኛ ኃይል በከተማ መሰባሰብ’ የህብረተሰቡ የተማረ መሆን ወይም አለመሆን’ የኢንዱስትሪ መስፋፋት ወዘተ ተመሳሳይ ተፅዕኖ አላቸው፡፡ አንድ ሀገር የግብር አስተዳደር ስርዓቱን እና ፖሊሲውን በሚወስንበት ጊዜ የእነዚህ ቁምነገሮች ተፅዕኖ ወሳኝ ነው፡፡ በዚህ መልኩ የግብር ስርዓቱ እንደ ሁኔታው በኢክሳይስ (ለሀገር ውስጥ ፍጆታ በሚመረት ሸቀጦች ላይ የሚጣል ግብር)’ ግምሩክ (custom)’ የንብረት ግብር’ የኮርፖሬት ገቢ’ የግለሰብ የገቢ መጠን (progressive individual income)’ VAT’ flatter rate structures’ "double income tax" ወዘተ ላይ መሠረት ያደረገ ሊሆን ይችላል ፡፡ ከእነዚህ ቁምነገሮች በተጨማሪ የመንግስት ቅርፅ መስፋት /መጥበብ/’ ግብር የመሰብሰብ አስተዳዳራዊ ብቃት እና ውስንነት’ ተመሳሳይ ተፅዕኖ አላቸው፡፡ ከቤት ኪራይ ሊከፈል የሚገባው ግብር ላይ ያለው ህግ እና አፈፃፀሙ ከአስተዳደራዊ ግብር መሰብሰብ ውሱንነት ጋር ሊያያዝ ይችላል፡፡ ስለሆነም በግብር አስተዳደር ውስጥ የሚወጡ ደንቦች የማይተገበሩ ከሆነ ውስብስብ እና የተራቀቀ የግብር ህግ ማዘጋጀት ትርጉም የማይኖረው ይሆናል፡፡ አብዛኛው ገቢው ጉርሻ (TIP)ከሆነ አስተናጋጅ፣ በሰንበት ከሚሰጠው የምክር አገልግሎት ከሚገኝ ገቢ ላይ ግብር መሰብሰብ አስቸጋሪ መሆኑ በቀላሉ ይታያል፡፡ በዚህ መሰል ጉዳይ ላይ ህግ ማውጣት የሚያስፈልገው ህጉን መተግበር እስከተቻለ ድረስ ነው ማለት ነው፡፡

የግብር አስተዳደር በዚህ መልኩ በየሀገሩ ሊፈታ የሚፈልጋቸው ውጥረቶች እና የራሱ አላማ አለው፡፡ ለምሳሌ የግብር አስተዳደር ማሻሻያ ኘሮግራማቸው የግብር ሕግ አላማ የማክሮ ኢኮኖሚን መረጋጋትን ማምጣት እንዲሆን አስበው የሚቀርፁ አሉ፡፡ በእድገት እና በለውጥ ውስጥ ያሉ ሀገራት የማሻሻያ ኘሮግራማቸው አላማ እያደገ ለሚመጣው የገበያ ኢኮኖሚ ስርዓት (እናም እያደገ ለሚመጣው ግብር ከፋይ) ምላሽ መስጠት ነው፡፡ ለውስጥ ችግር ምላሽ ከመስጠት ባሻገርም የምንኖረው ከማናመልጠው የግሎባልይዜሽን ስርዓት ውስጥ ስለሆነ እያደገ ከሚመጣው የአለም(global) ኢኮኖሚ አንፃር የግብር አሰባሰብ ስርዓት /አስተዳደርን/ዘመናዊ ማድረግ ፈታኝ የማሻሻያ ስራ ነው፡፡ የግብር ከፋዩ ግዴታውን እንዲወጣ እና በስርዓት እንዲሰራ ማድረግ ግን የማይቻል አይደለም፡፡ ለዚህም የረዥም ጊዜ (በተቀናጀ መልኩ የሚፈፀም) ዝርዝር እቅድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በአፈፃፀሙ ቁርጠኛ መሆን ይጠይቃል፡፡ ግብር ከፋዩ በየጊዜው ግዴታውን እንዲወጣ የሚያስችሉ ዝርዝር ተግባራት በጥናት መፈፀም ይኖርባቸዋል፡፡ ከአስፈፃሚው አደረጃጀት’ የሰው ኃይል እና የዘመቻ(operation)ተግባራትን አፈፃፀም ውጤታማ

ከማድረግ ባሻገር የህግ ማዕቀፍን መፈተሽና ማስተካከልም ይጠይቃል፡፡ ፍፁም የተሟላ የግብር ህግ ተፈፃሚነት ይኖረዋል? የሚለው ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ ውጤታማ እና የተሻለ የግብር ስርዓት አፈፃፀም እንዲኖር ካስፈለገ ዝርዝር እና ግልፅ ህጎች ከመውጣታቸው ባሻገር ህግ ተላላፊዎችን በወንጀል አጥብቆ እስከመቅጣት መስራት ግን ግድ ነው፡፡ የሚወጡ የግብር ህጎችን ግልፅና በቀላሉ የሚፈፀሙ ማድረግ' እኩልነትን እና ርትዕን የሚያበረታቱ ማድረግ' ግብር ባለመክፈል የሚገኙ "ማበረታቻዎችን" ማስቀረት የሚችል መሆን ይኖርበታል፡፡

የሀገራችንን የግብር ስርዓት ስንመለከት ከለውጥ በፊት ሀገራችን በእዝ የኢኮኖሚ ስርዓት ስትመራ የቆየች መሆኗ ይታወቃል፡፡ ይህ የእዝ ስርዓት በተለይ በ1980ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ሀገሪቷ የውስጥ እና የውጪ ማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት (in balance) እንዲገጠማት አድርጓል፡፡ ለዚህ ማዛባት የግብር ስርዓቱ የነበሩበት ዘርፈ ብዙ ችግሮች አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ በሀገሪቱ ይሰራበት የነበረው የግብር አስተዳደር ህግ እጅግ ኋላቀር የሆነና ሀገሪቱ ከምትከተለው ገበያ መር ነፃ ኢኮኖሚ ስርዓት ጋር ያልተጣጣመ ነበር፡፡ የግብር ህጉ በዋነኛነት በ1953 የወጣ (ኢቁ 173/53) ሲሆን ከሀገሪቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንዲሁም ከግሎባላይዜሽን እና ከአውቶሜሽን ስርዓት ጋር ፈፅሞ አብሮ አይሄድም፡፡ በዚህ ህግ መሠረት የሚጣለው ግብር ከፍተኛ ሆኖ በርካታ (brackets) ያሉትም ነው፡፡ ይህ በመሆኑም ግብር ከፋዩም ሆነ ግብር ሰብሳቢው የሚሰበሰብ ግብርን በቀላሉ እንዳይወስኑ አድርጓቸዋል፡፡ የሚጣለው ግብር ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ የግብር መሠረቱ (tax base) ጠባብ ነበር፡፡ ያልተሰበሰቡ ግብሮችን ለመሰብሰብ የህግ መሠረቱ (Enforcement) በቂ አልነበረም፡፡ በዘመኑም ቀጥታ ካልሆኑ ገቢዎች ላይ እና ኤክሳይስ ታክስ ላይ ጥገናዊ ለውጥ እየተደረገ ገቢ ለመሰብሰብ ቢሞከርም ገቢው እያሽቆለቆለ ንግድና ኢንቨስትመንትም እየተጎዳ መጥቷል፡፡ በአጠቃላይ ከለውጥ በፊት በሀገሪቱ የነበረው የግብር ስርዓት ዘርፈ ብዙ ችግር ያለበት ሲሆን ለአብነት፣

- ደካማ የግብር አስተዳደር ስርዓት ነበር፣
- የሚሰበሰበው የግብር ገንዘብ መንግስት ለሚያስፈልገው ወጪ በቂ አልነበረም
- የኢኮኖሚው እድገት ከህዝብ እድገት ጋር በተጣጣመ መልኩ ሊያድግ አልቻለም
- (የማክሮ ኢኮኖሚው ሚዛን የተዛባ ነበር፡፡) ለምሳሌ ወደ ውጭ ከሚላክ ምርት የሚገኝ ገቢ ማቆልቆሉ፣

- ግብር አሰባሰቡ በሙስና ተዘፍቆ የነበረ መሆኑ
- የክፍያ ሚዛኑ መዛባት (balance of payment) እየባሰ መምጣቱ
- የእዳ መቆለል (mounting debts) እና የኢኮኖሚ እድገት ማቆልቆል
- የግብር ሰብሳቢ መ/ቤት በሰለጠነ የሰው ኃይል ያልተሟላ፣ ዘመናዊ አሰራር እና ሱሳቁስ የማይጠቅም መሆኑ፣ይጠቀሳሉ፡፡

የነበሩት ችግሮች ግብር ማስላት (assessement) መሰብሰብ፣ ክትትል እና ማስፈፀም (enfofcement) ላይ ስርዓቱ ደካማ እንዲሆን አድርገዋል:: የግብር ከፋዩ አይነት እና ቁጥር እንኳን በትክክል አይታወቅም ነበር፡፡ ከለውጥ በኋላ መንግስት ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት እንዲሁም ነፃ (liberalize) ለማድረግ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ኘሮግራም ነድፏል፡፡ ከእነዚህ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ኘሮግራሞች የግብር ፖሊሲ ማሻሻያ ኘሮግራም የሚገኝበት ሲሆን ወደ ኋላ ላይ ደግሞ የግብር አስተዳደር ማሻሻያ ኘሮግራም ተካቶበታል፡፡ ይህን ፖሊሲ እና ስትራቴጂ የማውጣት ኃላፊነት የፌዴራል መንግስቱ ነው፡፡ /አንቀፅ 51/2/4//:: የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀፅ 89 (2) ስር የሀገሪቱ ሀብት ለኢትዮጵያውያን ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እንዲከፋፈል የማድረግ ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ ግብር አንዱ አላማው ይህ እንደሆነ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን መንግስት ይህን ኃላፊነቱን ለመወጣት የግብር ስርናቱን ሊጠቀም ይችላል፡፡ (አንቀፅ 89/2/፣41(3))፡፡ የሀገራችን የግብር ህግ ዋነኛ አላማ ግን ሀብት ማከፋፈል ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡

በማሻሻያ ኘሮግራሙ መሠረት የግብር ሥርዓቱ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች በመቅረፍ

- የንግድ፣ ቁጠባ እና ኢንቨስትመንትን በማበረታታት ቀጣይነት ያለው እድገት ማምጣት
- የግብር መሠረቱን የማስፋት፣
- መንግስት ሊፈፅማቸው ለሚገቡ ልዩ ልዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች በቂ ገንዘብ እንዲያገኝ በማስቻል ድህነት የመቅረፍ፣
- የግብር አስተዳደሩ የማስፈፀም አቅም የመገንባት፣
- ርትዕ መሠረት ያደረገ ግብር አሰባሰብ እንዲኖር የማስቻል፣

- (ለህብረተሰቡ የሚያስፈልጉ ሸቀጦች እንዲመረቱ የማበረታታት በተቃራኒው የሚያስፈልጉትን አልኮል ሲጋራ ያለመበረታታት)፣
- ቫት፣ ኢክሳይስ ታክስ በተመረጡ አግባብ በስፋት (በተለይ ቫት) መተግበር
- የገቢ ግብር ያለ ልዩነት በተወሰነ ብራኬት አነስተኛ ገቢ (moderate income) ያለውን በመተው መፈጸም፣
- የግብር አሰባሰቡ ትክክለኛ፣ ፍትሐዊ ኤፍሸንት እንዲሆን ግብር ከፋዩ ተመዝግቦ እና የግብር ከፋዩ በትክክል ታውቆ እንዲከፍል ማበረታታት አላማው ያደረገ ነው፡፡

<u>የህግ የበላይነትና አፈጻጸሙ</u>

በግብር አሰባሰብ ስርዓት ውስጥ የመጀመሪያው ቁም ነገር ግብር የሚሰበሰበው በህግ (firm basis in law)መሠረት ብቻ ነው የሚል ነው፡፡ የበርካታ ሀገሮች (በተለይ ያደጉትን) ታሪክ ስንመለከት የህዝብ ተቃውሞዎች ዋና ማጠንጠኛ ዘፈቀዳዊ ግብር አጣጣል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በእንግሊዝ' ሞናርክ' በሀገራችን ንጉስ' በአሜሪካ ያለ ህግ አውጪው ፈቃድ ወዘተ ይጣሉ የነበሩ ግብሮች እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ግብር በህግ መሠረት ይሰብሰብ ብቻ ሳይሆን በህግ የበላይነት መርህ መሠረት በህዝብ በተመረጠ ተወካይ አማካኝነት በወጣ ህግ ይሰብሰብ የሚለው ጥያቄ የዘመናት ነው፡፡ ለዚህም ነው ጀምስ ኦፌስ"taxation without representation is a tyranny" በማለት የገለፀውን ህዝብ መፈክር አድርጎት የቆየው፡፡ ስለሆነም የዲሞክራሲ ስርዓት በሚከተሉት ሀገሮች ውስጥ የህግ አውጪው በዚህ ጉዳይ ላይ ስልጣን እንዲኖረው ሆኗል፡፡ ይህ ሁኔታም በሀገሮች ህግ ውስጥ በተለይም በህገ መንግስት ድንጋጌዎች ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ አንዳንድ ሀገሮች (ምሳሌ ስዊዘርላንድ)የዚህ አይነት ድንጋጌ በህጋቸው ውስጥ በግልፅ ባይኖራቸው እንኳን ሌሎች የህገ መንግስት ድንጋጌዎችን በመተርጎም ተመሳሳይ አቋም ላይ ይገኛሉ፡፡ የእኩልነት መርህ እንደ ምስሌ ይጠቀሳል፡፡ የሰው የመንቀሳቀስ ነፃነት(freedom of movement)ከህግ በቀር ሊገደብ አይገባውም' የአስተዳደር አካሉ ተግባር በህግ መሠረት መመራት ይገባዋል የሚሉት መርሆዎችም በተመሳሳይ ለተመሳሳይ አላማ የሚተረጎሙባቸው ሀገራትም አሉ (ምሳሌ ጀርመን) የሚፈፀም ግልፅ ህግ ከማውጣት ባሻገር መንግስት የግብር ስርዓቱን ውጤታማ ለማድረግ ፖሊሲውን እና አላማውን ለህዝቡ ግልፃ በማድረግ የተጠያቂነት ስርዓት

ያለበት መሆኑን ማስረዳት ይገባዋል። የግልፅነት እና ተጠያቂነት መርህ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት ከሚከተለው መሠረታዊ መርሆዎች ውስጥ አንዱ ነው (አንቀፅ 12)። የግብር አሰባሰብ ክፍተቶችን (Tax gaps) መረጃ በመሰብሰብ እና ለህዝቡ በመግለፅ እንዲሁም ለህግ አውጪው ሪፖርት በማድረግ አፈፃፀሙ እንዲሻሻል ማድረግ ይገባል። ይህም ግብር ከፋዩ በራሱ ጊዜ በታማኝነት ግብር ለመክፈል መነሳሳት እስከሚችልበት መጠን ድረስ አለዚያም በቀሪው የህብረተሰቡ ክፍል የሞራል ተፅዕኖ እስከሚደርስበት መጠን ድረስ መፈፀም የሚገባው ሲሆን ግብር ላለመክፈል የሚያነሳሳ መሆን የለበትም። የግብር ህግ በግብር ከፋዩ ተፈፃሚ የሚሆነው በአብዛኛው ባለማድረግ (Omission) ሳይሆን ሰነድ፣ ሂሳብ፣ ሪከርድ ወዘተ በመያዝና (በማድረግ) ነው። ስለሆነም ለግብር ከፋዩ የሚሰጠው መረጃ እና ትምህርት በዚህ ደረጃ ለድርጊት የሚያዘጋጀው ይሆናል። ከዚህ በተረፈ በግብር ከፋዩ የተለየ ብቸኛ ቁጥር መስጠት፣ የንግድ ግብይት (Vissibility) ግልፅ ማድረግ (ለምሣሌ በምዝገባ ስርዓት)፣ መረጃን ለማዛመድ የሚጠቅም የ3ኛ ወገኖችን (ቀጣሪ፣ ባንክ፣ትርፍ አከራይ) ለመረጃ ምንጭነት እንዲሁም ገቢን ሪፖርት እንዲያደርጉ «Watch dog» ስርዓት መቅረፅ'ኦዲት የመደረግ እድልን ማስፋት፣ ከገቢ እግ ወጪ (ሰጪና ተቀባይ) ጋር የተያያዙ እና ሌሎች መረጃዎችን እያገናዘቡ መስራት ለግብር ስርዓቱ ተፈፃሚነት ጠቃሚ ነገሮች ናቸው። የህግ አፈፃፀሙን በተመለከተ የአስተዳደር አካሉ ጥብቅ የሆነ የማስፈፀም ስልጣን (Enforcement power) የሚያስፈልገው ሲሆን ጥብቅ የሆነ ወጪን የሚክስ በፍትሐዊነት የሚፈፀም አስተማሪና አስጠንቃቂ የሆነ የገንዘብ እንዲሁም የወንጀል ቅጣት ለተመሳሳይ አላማ አስፈላጊ ናቸው። እነዚህ የተዘረዘሩት ቁምነገሮች አንዱ በሌላው ላይ ተመስርቶ የቆሙ በመሆናቸው እያንዳንዱን ተግባር የሚያስፈፅም አካል በዚሁ አግባብ በጥንቃቄ የተዋቀረ መሆን ይኖርበታል ማለት ነው። የህግ አወቃቀሩ ይህንን በተቻለ አቅም ውጤታማ (Maximize) በሚያደርግ አግባብ ይሆናል።

### 10.2. <u>ኢንቨስትመንት</u>

ከግብር ህግ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚችለው ሌላው ነጥብ ከኢንቨስትመንት ጋር ያለው ግንኙነት ነው። በማደግ ላይ ያሉ እንዲሁም በሽግግር ላይ ያሉ በርካታ ሀገራት ኢንቨስትመንትን ለመሳብ በማሰብ የግብር ማበረታቻዎችን ያደርጋሉ። አንዳንድ ሐገሮች ከሶሻሊስት የግብር ስርዓት ወደ ነፃ ኢኮኖሚ የግብር ስርዓት ሲገቡ የነበሩ ማነቆዎችን /ምሳሌ ግብር የድርጅት በጀትን በቆጣጠር ማለሙ /ለማሸነፍ በማሰብ ማበረታታቻ

ሲደነግጉ ባለሃብቶች ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ እንደ የመሠረተ ልማት አውታሮች አለመሟላት፣ የውስብስብ ህግ ችግሮች፣ የቢሮክራሲ መብዛት እና የደካማ አስተዳደር መኖር ወዘተ ችግሮች ማካካሻ ለማድረግ በማሰብ የሚደነግጉ ሃገሮችም አሉ። እነዚህ ችግሮች የተቃለሉ ቢሆንም እንኳን አንድ ሀገር በአለም አቀፍ ኢንቨስትመንት ተወዳዳሪ ለመሆን በሚያስችሉት የኢኮኖሚ እንቀስቃሴ ለመሳተፍ በተለየ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለተሰማራ ግብር ከፋይ ማበረታቻ ሲያደርግ ይስተዋላል። የቴክኖሎጂ እና የእውቀት ሽግግር ለማምጣት የሚጠቀምበትም አሉ። ይሁንና ለግብር ከፋይ የሚደረግ የዚህ አይነት ማበረታቻ በቀጥታ የኢንቨስትመንት ችግር የሆኑትን የማይነቅል በመሆኑ ውጤታማ ሊሆን ይችላል? አስፈላጊስ ነው? የሚሉ ክርክሮች ይነሳሉ። የግብር ማበረታቻዎች የራሳቸው እጥረት ቢኖራቸውም ሀገራት ግን ጥቅሙን ከጉዳቱ በመመዘን ለባለሀብቶች የግብር ማበረታቻ ሲፈቅዱ ይስተዋላሉ። የግብር ማበረታቻ የተለያየ መልክ የሚይዝ ነው። ለአዲስ አምራቾች የሚፈቅድ የግብር እፎይታ (tax holiday)፣ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ መቀነስ ወይም የግብር መጠንን መቀነስ፣ የማምረቻ እቃ (ንብረት) የአገልግሎት ዘመንን ማሳጠረ ወይም የአገልግሎት ዘመኑ የሚሻሉበትን ጊዜ ኢኮኖሚው ከሚያስበው በላይ ፈጠን ማድረግ (Timing difference)፣ የተወሰኑ መስፈርት ለሚያሟሉ ድርጅቶች (አምራቾች) ጠቅላላ የግብር ምጣኔ ቅነሳ ማድረግ አለዚያም ለግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት (ባለስልጣን) በዚህ ጉዳይ ላይ የማበረታቻ ውሣኔ እንዲሰጥ የመወሰን ስልጣን (discretion) መስጠት ወዘተ. . . ሊሆን ይችላሉ። ወደ ሀገራችን የግብር ስርዓት ስንመለስ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት በአንቀጽ 25 ስር ማንኛውም ሰው እኩል ነው በማለት ሲደነግግ አያይዞም በማናቸውም "አቋም" ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው ይላል። የኢትዮጵያውያንን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ለማሻሻል ለዜጎች እኩል እድል የመስጠት አላማም በአንቀጽ 89 ስር ተካቷል። ይህ የእኩል መብት እና እድል መርህ በሀገሪቱ የተለየ የግብር ማበረታቻ ማድረግ ኢ-ህገ መንግስታዊ ያደርገዋል። የመንግስት ትኩረት የሚሆነው የዚህ አይነት "ጥገኝነትን" ማስቀረት እና የግብር ከፋዩን አቅም በተለያየ መልኩ ማጠናከር ነው።

<u>የግብር ህግ ማውጣት</u>

መንግስት ህልውናውን ጠብቆ ለህብረተሰቡ አስፈላጊውን አገልግሎት እየሰጠ እንዲቀጥል ከግብር የሚሰበሰብ ገቢ ያስፈልገዋል። በእንግሊዝ ከ1215ቱ የማግኛ  ካርታ «ግብር ያለ

ውክልና አይጣልም» ከሚለው እና ከ1628ቱ የመብት መግለጫ (Petetion of rights) በኋላ ያለ ህግ አውጪው (ፖርላማ) ፈቃድ ግብር አይጣልም፡፡

ሀገራችን የፌዴራል ስርዓትን የምትከተል እንደመሆኗ መጠን የፌዴራል እና የክልል መንግስታት አሉን፡፡ እነዚህ መንግስታት በህግ የተሰጣቸውን ኃላፊነት መወጣት ያለባቸው ሲሆን ለዚህም የሚያስፈልጋቸውን ወጪ በራሳቸው እንዲሸፍኑ ይጠበቃል፡፡ (የህገ መንግስቱ አንቀጽ 94(1))፡፡ ይህ ወጪ ከሚሸፈንበት መንገድ ውስጥ አንዱ ግብር እና ታክስ መጣል ነው፡፡ የሚጣለውም ግብር እና ታክስ ለዚሁ አገልግሎት ተመጣጣኝ (Commensurate) መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ግብሩን ከዚህ ቀደም እንደነበረው ሳይሆን ከምንጩ ጋር የተያያዙ በአግባቡ ተጠንቶ የተወሠነ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው (አንቀጽ 100/1/፣/2/)፡፡ ይህ ግብር እና ታክስ በሚጥሉት ሁሉም መንግስታት ላይ የተጣለ ግዴታ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው ግብር በህግ አውጪው የሚጣል ነው፡፡ ህገ መንግስቱ የግብር ህግን የማውጣት ስልጣን የህግ አውጪው ነው በማለት ሲያስቀምጥ በዚህ ጉዳይ ላይ በውክልና ህግ ሊወጣ ይችላል/አይችልም የሚለውን በተመለከተ በተለይ ያስቀመጠው የተለየ ህግ የለም፡፡ ወደ አንድ ጫፍ ያዘመሙ ተከራካሪዎች የህጋዊነት መርህ የግብር ህግ በውክልና እንዲወጣ አይፈቅዱም በማለት ሲከራከሩ በሌላ ጫፍ ያሉት ደግሞ ህገ መንግስት ህግ ማውጣትን አስመልክቶ ጠቅላላ ውክልና ፈቃጅ ድንጋጌ ካለው ለግብር ህግም ይሰራል በማለት ይከራከራሉ፡፡ በመሀል ያሉት ደግሞ ዋናው ህግ መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ድንጋጌ ካለው ቀሪው ጉዳይ በውክልና ሊወጣ ይችላል በሚል ይከራከራሉ፡፡ በመሠረታዊ ጉዳይ ውስጥ ግብር ከፋይ ማን ነው? የግብር መሠረት (object) ምንድን ነው? የግብር መጠኑ (Rate) እና መሠረታዊ የአስተዳደር መርሆዎች ካሉበት ቀሪው በውክልና የሚወጣ ነው፡፡ አስፈፃሚው (አስተዳደር) አካል ይህን ቀሪ ጉዳይ በውክልና በድንጋጌ፣ በደንብ መልክ ሊያወጣው ይችላል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት የሀገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ፣ ገንዘብ እና ፋይናንስ ፖሊሲ የማፅደቅ ስልጣን የተወከዮች ምክር ቤት እንዲሆን ይደነግጋል፡፡ ለፌዴራል መንግስቱ በተከለለው የገቢ ምንጭ ላይ ግብር እና ታክስ የመጣል ኃላፊነትም የዚሁ ምክር ቤት ስልጣን ነው፡፡ (አንቀፅ 55 (10)፣11)

## የስልጣን ክፍፍል

በፌዴራል ስርዓት ውስጥ ከአንድ በላይ መንግስታት ሲኖሩ መንግስታቱ የዚህ ስልጣን ጥያቄ ማንሳታቸው አይቀርም፡፡ አንዳንድ ስልጣን ለማዕከላዊ መንግስት ሲሰጥ ሌላው ለግዛት መንግስታት ይተዋሉ፡፡ የአሜሪካን ስርዓት ብንመለከት ከእርሻ ስራ የተገኘ ገቢዎች ላይ የክልል መንግስታት ግብር የመጣል ስልጣን ሲኖራቸው በሌሎች ገቢዎች ላይ ግብር የመጣል ስልጣን ያለው የፌዴራል መንግስት ነው፡፡ ቀጥታ ታክስ (direct tax) የጋራ ስልጣን ሆኖ በህዝብ ቁጥር ተመጥኖ የሚጣል ነው፡፡በሀገራችን የፌዴራል መንግስትም ሆነ የክልል መንግስታት ተለይተው በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት ግብር ይጥላሉ፡፡ ተለይተው በተቀመጡ ጉዳዮች ላይም በጋራ ታክስ እና ግብር ይጥላሉ፡፡ በዚህ መልኩ በተናጠል እና በጋራ ያልተለየ ጉዳይ ላይ ግብር ለመጣል ስልጣን የሚኖረውን አካል የተወካዮች ም/ቤት እና የፌዴሬሽን ም/ቤት በጋራ ስብሰባ በ2/3ኛው ድምፅ ይወስናሉ (አንቀጽ 96 - 99) ፡፡ ህገ መንግስቱ ለፌዴራል መንግስቱ ከሰጠው ስልጣን ውስጥ በወጪና ገቢ እቃዎች ላይ የጉምሩክ ቀረጥ ታክስ እና ሌሎች ክፍያዎችን መጣል አንዱ ነው፡፡ ይህ ስልጣን ከሀገሪቱ የሚወጡ (ቡና፣ ቆዳ፣ ሌጦ . . . .) እና ወደ ሀገሪቱ የሚገቡትን (ዘይት ማሽኖች መለዋወጫ መድሐኒት ማዳበሪያ . . .) ሸቀጦች በማመጣጠን የንግድ ሚዛኑ (balance of trade) እንዲስተካከል ለማድረግ ያስችላል፡፡ ሚዛኑ ለማስተካከል ደግሞ የሚጣለው ግብር ከሀገር የሚወጡ ሸቀጦች መጠናቸው እና ጥራታቸውንና የጠበቁ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ግብሩ የተሻለ ንግድ እና ልውውጥ እንዲኖር ያስችላል፡፡

ለፌዴራል መንግስቱ ከተሰጡት ስልጣኖች ውስጥ የተወሰኑት ተጨማሪ ኢንቨስትመንት የሚጠይቁ (ቁ 96/5/ 16/) የተወሰኑት ደግሞ ሀገሪቱ በምትከተለው የኘራይቬታይዜሽን ፖሊሲ መነሻነት ሊቀንሱ የሚችሉ /96/3/ ሲሆን የዲኘሎማሲ ጉዳዮችንና ግንኙነቶችንም ግምት ውስጥ አስገብተው የሚፈፀሙም ይገኙበታል (ቁጥር 96/2/)፡፡ ክልሎችም በተመሳሳዩ ከተዘረዘሩ ተግባራት እና ሁኔታዎች ላይ ግብር ይጥላሉ፡፡ ከእነዚህ ግብር ክፍያዎች ውስጥ በተለይ ከመሬት የመጠቀሚያ ክፍያ የሚሰበሰቡት ግብር በክልሎች ከፍተኛ ገቢ ሊያስገኝ የሚችለው ነው፡፡

የፌዴራሉም ሆነ የክልል መንግስታት ከሚሰጧቸው አገልግሎቶች እና ፈቃዶች የሚሰበሰቡት ግብር በተመሳሳይ ከፍተኛ ገቢ የሚያስገኝ ነው፡፡

<u>የመፈፀሚያ ጊዜ</u>

ከላይ የተመለከትነውን የህጋዊነት መርህ ሰፊ አድርጎ በመተርጎም የ(Annuality) መርህ (የዘመኑ መርህ) የሚከተሉት ሀገራት አሉ፡፡ (ፈረንሳይ ቤልጅየም የህገ መንግስታቸው አንቀጽ 174 እና 47)፡፡ በዚህ መርህ መሠረት ግብር ያለው ውጤት ለአንድ የበጀት አመት ብቻ ሲሆን መንግስት ባለው ህግ መሠረት ግብር መጣሉን እንዲቀጥል ህግ አውጪው በየዘመኑ ፈቃዱን መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ ህግ አውጪው ፈቃዱን (consent) ብቻ ያስታውቃል እንጂ እንደገና ህግ በዝርዝር አያወጣም(አስፈላጊ ካልሆነ በቀር)፡፡ ይህ መርህ በበርካታ ሀገሮች የሚሰራበት በጀት ለማፅደቅ እንጂ ግብር ለመጣል የሚያስችል ፈቃድ ለማግኘት አይደለም፡፡ የሀገራችንም ህገ መንግስት ከዚህ መርህ በተለየ መልኩ በግብር ጉዳይ ላይ የአመት ግዴታ በመንግስት ላይ አያስቀምጥም፡፡

የህጋዊነትን መርህን አሁንም ሰፋ በማድረግ የሚተረጉሙ አሉ፡፡ የግብር አስፈፃሚ የአስተዳደር መስሪያ ቤት በግብር እዳ (Tax liabilty) ላይ ከግብር ከፋይ ጋር በመደራደር' በመስማማት ግብር እንዲቀነስ ማድረግን አይችልም በማለት እንደቻይና ያሉ ሀገራት ደንግገዋል፡፡ የዚህ መሠረቱም ግብር ለህዝብ ጥቅምና ለህዝባዊ አገልግሎት እንዲውል የሚሰባሰብ ገንዘብ በመሆኑ በጥብቅ ተፈፃሚ ሊሆን ይገባዋል የሚል ነው፡፡ ይህ መርህም የግብር ህግ በፍ/ቤት ዘንድ ሲተረጎም አጥብቆ ተፈፃሚ እንዲሆን የሚጠበቅ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት መርህ ተመሳሳይ ነው፡፡

<u>እኩልነት</u>

ሌላው ከግብር አሰባሰብ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የእኩልነት መርህ ነው፡፡ ይህ መርህ ትልቅ ቦታ ያለው ህገ መንግስታዊ መርህ ሲሆን በግብር አግባብ ተፈፃሚ ሲሆን የግብር ህግ (በስነ ስርዓቱም ሆነ በይዘቱ) ተመሳሳይ ሆኔታ ላይ ባሉ ግብር ከፋዮች ላይ በተመሳሳይ መልኩ መፈፀም አለበት ማለት ነው፡፡ የግብር ህግ የከፋዩን ደረጃ /ምሳሌ/ ሳይመለከት በሙሉ እና በገለልተኛነት ይፈፀማል፡፡

የህጉን አፈፃጸም ህጋዊነት ለሚጠይቅ ሰው የተለየ ድጋፍ (Preferential treatment) አይደረገም ማለት ነው፡፡ ለዚህም በህገ መንግስቱ ውስጥ ለልዩነት መሠረት ሊሆን አይገባቸውም የተባሉ ምክንያቶችን መመልከት ተገቢ ነው፡፡ ከዝርዝሩ ውጪ ባለ ጉዳዮች ለምሳሌ ከፍተኛ ገቢ ያሏቸው ከፍተኛ ግብር ለሚከፍሉ ሰዎች የአከፋፈሉን ስርዓት የተለየ ማድረግ (Granted rate) ልዩነት መፍጠር አይደለም የሚሉ አይጠፉም፡፡

## የህዝብ እምነት

ከግብር መርሆዎች ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ሌላው መርህ በግብር አስተዳደር ውስጥ የህዝብ እምነትን የማግኘት መርህ ነው፡፡ ይህ መርህ የአጠቃላይ አስተዳደር ህግ መርህ ሲሆን በሌላ ክፍል ተመልክተነዋል፡፡ መርሁ ከግብር ጋር ሲገናኝ የግብር አስተዳደር መስሪያ ቤት የግብር ከፋይን በተመለከተ ስለሚወስደው እርምጃ አስቀድሞ ለግብር ከፋዩ ማስታወቅ ይኖርበታል፣ የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ በሚሰጣቸው የግብር ህግ ትርጉሞች ሊገደድ ይችላል . . . . ወዘተ ማለት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ግብር ከፋዩ ከሀገር ይጠፋል ወይም ማስረጃ ያጠፋል፣ ሰነድ ይሰወራል፣ ይደልዛል በተሰጠው ትርጉም ከቅን ልቦና ውጪ ይጠቀማል የሚሉ ነጥቦች ከመርሁ በልዩ ሁኔታ የሚቀመጡ ናቸው፡፡ በህገ-መንግስቱ የመንግስት አሰራር በ"ግልፅ" መከናወን ይገባዋል የሚለው መርህ ይህንን አላማም ያቀፈ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

## ተመጣጣኝና ህጋዊ ግብር

ግብርንና አስተዳደሩን ፍትሐዊ ከሚያሰኙት ነጥቦች ውስጥ ሌላው መርህ የሚጣለው ግብር በግብር ከፋዩ የመክፈል አቅም ላይ መመስረት አለበት የሚለው ነው፡፡ «head ወይም ፖልስ ግብሮች አይሰሩም ማለት ነው፡፡ ይህ መርህ በሀገራት ህገ መንግስት ውስጥ ባይገኝ በእኩልነት መርህ ላይ ተመስርቶ ሊተረጎም የሚችል ነው፡፡ የኢጣሊያ ህገ መንግስት ግብር ከፋይ ባለው ሀብት (Resource) መጠን ለህዝቡ ወጪ ማዋጣት አለበት በማለት ይደነግጋል (አንቀጽ 53)፡፡በዚህ ድንጋጌ መሠረትም የተጋቡ ሰዎች ገቢ በአንድነት ግብር የሚጣልበት ቢሆን የመክፈል ችሎታ መርህን ይጥሳል ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ከተወሰነ ገቢ በታች ግብር አይከፈልበትም ተብሎ ቢደነግግ የከፋዩን ችሎታ ያገናዘበ ነው ወይንስ አይደለም የሚለው በተመሳሳይ የሚታይ ነው፡፡ ግብር በመክፈል ችሎታ ላይ ሊመሰረት ይገባዋል ማለት የሚጣለው ግብር መንግስት ሊከውነው ካሰበው ግብ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት የሚለውንም በውስጡ ያቅፋል፡፡ ይህ ማለት ግን ግብር ከመክፈል ችሎታ ጋር እያደገ ይመጣል (Progressiv tax) የሚለውን የሚያስቀር ሳይሆን ግብር ከመጠን ያለፈ (Excessive) ወይም (Confiscatory) መሆን የለበትም ማለት ነው፡፡ ግብር ሰው ተቀባይነት ያለው (decent life) ህይወት እንዳይኖር የሚያደርግ፣ በተወሠነ ሙያ ወይም ስራ ላይ በህገ መንግስቱ መሠረት እንዳይሰማራ የማያደርግ በህገ መንግስቱ የተቀመጡ የንብረት (ውርስ) ጥያቄ መብቶችን የሚነካ መሆን አይገባውም ማለት ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ግብር

ተመጣጣኝ ሆኖ ለመንግስት አገልግሎት በሚፈለገው ልክ ብቻ መጣል እንዳለበት እንደሚደነግግ ተመልክተናል፡፡ የህገ መንግስት አንቀጽ 100 ከመጠን ያለፈ ግብርም ሆነ ከመጠን ያነሰ ግብር (overtaxing,undertaking) መወገድ ያለበት እንደሆነ በመርህ ደረጃ አስቀምጧል፡፡ ይህ መርህ በተለይ የግል ባለሀብትን በእኩልነት ለማበረታታት እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ባለሀብቶች ኢንቨስት ለማድረግ ከሚመርጧቸው ነጥቦች ውስጥ የግብር ስርዓቱ ከመጠን በላይ ግብር እየጣለ በንብረታቸው ላይ የማዘዝ መብታቸውን የሚያሳጣ አለመሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም መርሁ የግል ባለሀብቶችን ለመሳብ ይጠቅማል፡፡

በሌላ በኩል በክልል መንግስታቱ መሀከል ያለው ግንኙነት እንዳይጎዳ የሚያደርግ መርህ ህገ መንግስቱ የያዘ ሲሆን አንዱ መንግስት በሌላው ንብረት ላይ ግብር እንዳይጥል (በትርፍ ከቆመ ድርጅት በቀር) ይከለክላል፡፡ እነዚህ የህገ መንግስት መርሆዎች በተመሳሳይ መልኩ በየግብር አይነት በተለያዩ አዋጆች ውስጥ ተካተው እናገኛቸዋለን፡፡

<u>ከፋይን መለየት (ማወቅ)</u>

ከፍ ሲል እንደተመለከተው ህገ መንግስቱ ግብር በአግባቡ በተጠና አግባብ መሰብሰብ እንዳለበት በመርህ አስቀምጧል፡፡ ይህን ለማድረግ ከሚያስፈልጉ ነገሮች ውስጥ አንዱ ግብር ከፋዩን ማወቅ ነው፡፡ ግብር ከፋዩን ለመለየትና የግብር መሰወርን በማስቀረት ቀልጣፋ እና ውጤታማ የሆነ የግብር ስርዓት እንዲኖር በማስቻል የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የመስጠት ስርዓት (Tax payer identification number-TIN ) ስራ ላይ ውሏል፡፡

የግብር ከፋዩ በ3ት ገደብ የተከፈለ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከእነዚህ ምድቦች ውስጥ በ«ሀ» እና «ለ» ምድብ ስር ያሉት በሚይዙት የሂሳብ ሰነድ መነሻነት ግብር የሚጣል ሲሆን በ«ሐ» ምድብ ያሉት ደግሞ የሚከፍሉት ግብር በዘፈቀደ የተሰላ እንዳይሆን በደረጃ ተለይተው በተሰላ ግብር መነሻነት እንዲከፍሉ ይሆናል፡፡ ይህ የ«Standard assessment» መንገድ ግብር በተቻለ መጠን የበዛ ያነሰም እንዳይሆን በህጉ መንግስቱ የተቀመጠውን መርህ ለማሳካት የተሻለ መንገድ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የቀድሞው የግብር አሰባሰብ ስርዓት በነሲብ(estimated standard)ላይ መመስረቱ ይታወሳል፡፡

ድህን ኤም አርዳን የተባሉ የመስኩ ባለሞያ የኢትዮጵያ ግብር ስርዓት የውስጥ እና የውጪ ቀጥታ የሀብት ፍሰትን ለማበረታታት የተዘጋጀ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ አያይዘውም የግብር መሰረቱ እንዲሰፋና አሰባሰቡም «ርትዕ ፍትህን ወጥነትን እና ታማኝነት

(honesty)» የሚያረጋግጥ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡ ህጎቹም ከመፅደቃቸው በፊት የንግዱ ማህበረሰብ እና የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ አስተያየት ሰጥተውበት አስተያየታቸው ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በዚህ መልኩ ከወጡት ህጎች ውስጥ የገቢ ግብርን ስንመለከት ከሰራተኛ እና ከትርፍ ገቢ እስከ 85 በመቶ እና 89 በመቶ (በተከታታይ) ይከፈል የነበረው እስከ 35 በመቶ እና 30 በመቶ ዝቅ ለማለት ችሏል (አ.ቁ 289/2002)፡፡ የግብር መጠኑ በዚህ መልኩ ስር ነቀል በሆነ አግባብ ከመቀየሩም በላይ የግብር መሠረቱ (tax base) ከፍ ብሏል፡፡ ለምሳሌ Rented tax,Urban Land Lease fee, capital gain tax... በስራ ላይ ውለዋል፡፡

በሌላ በኩል ግብር ከፋይ ሆነ ብሎ ግብርን ሳይከፍል እንዳይቀር (tax evasion) ወይም ይህንን ሁኔታ ለመቀነስ የዊዝሆልዴንግ ግብር ስርዓት ተመስርቷል፡፡ ይህ ስርዓት በጠቅላላ የግብርን ዋጋ 2 በመቶ (ለሀገር ውስጥ) ወይም 3% (ለውጪ ምርት) ያስከፍላል፡፡ የተጨማሪ እሴት ግብር ስርዓትም(value added tax-VAT) በተመሳሳይ የሽያጭ ግብር ስርዓትን ተክቷል፡፡ የሽያጭ ግብር መሠረቱ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ሸቀጦች በተመረቱ ንብረቶች እና በተመረጡ አገልግሎቶች ላይ ተመስርቶ ልዩ ሁኔታዎች የነበሩበት መሠረቱ ጠባብ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ሁኔታው በዚህ ቢቀጥል መንግስት በህገ መንግስቱ ላይ የተጣለበትን ማህበራዊ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ሊወጣ አይችልም፡፡ ቫት ወጥ የሆነ የግብር መጠን (15%) በአብዛኛዎቹ ግልጋሎት ላይ በሚውሉ ሸቀጦች እና የአገልግሎት ክፍያዎች ላይ የጣለ ሲሆን በበርካታ ሀገራት የሚሰራበትና በፍጥነት እየተስፋፋ የመጣ ስርዓት ነው፡፡የቫት ግብር መክፈል የማይገባቸው ማለትም አመታዊ ገቢያቸው ከብር 500=000 በታች የሆኑ) ለሸቀጦች 2% እና ለአገልግሎት 10% የተርንኦቨር ግብር እንዲከፍሉ ሆኗል፡፡ የቫት ስርዓትም ከህገ መንግስት አንፃር ሲታይ ወጥነት ያለው ልዩ ሁኔታዎች የጠበቡ የሚጣልበት ግብር መሠረትም በአንፃራዊነት የሰፋ አዲስ በተፈጠረ እሴት ላይ ሁሉ ተፈፃሚ የሚሆን የኤክስፐርት ላይ ያለው ምጣኔ 0ነ ስለሆነና በኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ ላይም የማይጣል በመሆኑ የውጪ ንግድንና ኢንቨስትመንትን በማበረታታት ኢኮኖሚው እንዲያድግ የሚያደርግ የቁጥጥር እና የአፈፃፀሙ ስርዓቱን ጠንካራ በመሆኑ የግብር መሰወር (evasion) አነስተኛ መሆኑ ተመራጭ ያደርገዋል፡፡

<u>ወደኋላ ተመልሶ መስራት (Retroactivity)</u>

የግብር ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ ሊሰራ ይገባዋል ወይስ አይገባውም የሚለው ሀሳብም የመርህ ክርክር ያለበት ነው፡፡ ሰዎች ምጣኔ ሀብታቸው ላይ ሊወስኑ የሚገባው የአለውን የግብር ህግ እንደ አንድ መሠረት አድርገው መሆን አለበት የሚሉ የግብር ፀሐፊዎች ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ ሊሰራ አይገባውም በማለት ይከራከራሉ፡፡ የሆኖ ሆኖ ዛሬ የሚወጣ የግብር ህግ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው በእጅ ባለ ንብረት፣ ሀብት ላይ እስካሁን ድረስ አለዚያም ባለፈው ውጤት ላይ በሚመሰረት የወደፊት ገቢ ላይ አስከሆነ ድረስ የወጣ ህግ በምንም ተአምር ወደ ኋላ ያለውን አይመለከትም ለማለት ያስቸግራል፡፡ ለዚህም ሀገራት የግብር ህጋቸው ወደ ኋላ ተመልሶ የሚሰራ ወይም የማይሰራ ለመሆኑ እንደአግባቡ ይወስናሉ፡፡ አንዳንድ የግብር ማሻሻያዎች ወደ ኋላ እንዳይሰሩ፣ በሂደት ላይ ላሉ ግብይቶች የእፎይታ (Relief) ጊዜ (ወደፊት) እንዲሰጡ ወዘተ  ሊወሰኑ ይችላሉ፡፡ የዚህ አይነት ድንጋጌ በህገ መንግስት ውስጥ በቀጥታ ባይገኝ በፍትሐብሔር ህግ ጠቅላላ መርህ (ድንጋጌ) ውስጥ ተካቶ የሚገኝበት እና ልዩ የግብር ህግ በሌለ ጊዜ ይህ የፍ/ብሔር ህግ የሚፈፀምበት ሁኔታም ሊኖር ይችላል፡፡ ህግ አውጪው ይህ ጠቅላላ መርህ በአሜሪካ፣ ፈረንሳይ ወዘተ ይሰራበታል፡፡ በጀርመን ጠቅላላ መርሆዎች ከልካይ ሲሆኑ በተለይ ለተዘጉ የኋላ ግንኙነቶች የግብር ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ እንዳይሰራ ይከለክላሉ፡፡ ያልተዘጉ ግንኙነቶች ሆነው ወደፊት ውጤት ያላቸው (በፍ/ብሔር ጉዳይ ተቀባይነት ያለው ግብ (legitmate legislative purpose) ከሌላው በስተቀር Retrospective) ከሆኑ ግን ህጉ ሊፈፀም ይችላል፡፡ መሠረት የሚያደርጉት መርህም የህግ ዋስትና (legal security) እና የህዝብ እምነት (Public trust) ናቸው፡፡ መርሁ ህጉ ወደ ኋላ ተመልሶ እንዳይሰሩ የሚከለክል  ሆኖ ህጋቸው የኃላ ውጤት የሚኖረው ምክንያታዊ ሲሆን ፡ የህዝብ ፍላጎት ሲኖር እና በመሳሰሉት የተለዩ ምክንያቶች ብቻ ነው፡፡ (ለምሳሌ በአልኮል መጠጦች ላይ (በመጋዘን ያሉም) የኤክሳይስ ታክስ መጨመር በተለየ ምክንያቱ ይፈቀዳል)፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው ህጉ ሲወጣ ግብር ከፋዩ የሚያውቀው (የሚገለፅበት) በመሆኑ አስቀድሞ ከህጉ ለማምለጥ የተንኮል ሥራ እንዳይሰራ ህጉ በህግ አውጪው ከቀረበበት ጊዜ ሳይሆን ከሌላ ጊዜ (ምሳሌ በህግ አውጪው ከቀረቡት) ቀን አንስቶ ተፈፃሚ እንዲሆን ሊወሰንም ይችላል፡፡ የሀገራችን የግብር ህጎች የወንጀል ጠባይ ያላቸው ከሆኑ በህገ መንግስቱ ላይ የተቀመጠው የወንጀል ህግ ወደ ኃላ ተመልሶ አይሰራም የሚለው መርህ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ በቀሪ ጉዳዮች ላይ ግን የተለየ ሁኔታ ካልተመለከተ በቀር የግብር ህግ እንደሌሎች የአስተዳደር ህጎች በህግ

መልክ ከወጡበት ወይም በህጉ ላይ በተለይ የተቀመጠ ቀን ካለ ከዚሁ ቀን አንስተው ለወደፊት የሚፈፀሙ ናቸው::

<u>መሠረታዊ መብቶች</u>

ከፍ ሲል በዝርዝር ከተገለፁት የህገ መንግስቱ መርሆዎች በተጨማሪ ሌሎች መርሆዎች ህገ መንግስት ውስጥ ተካተው ሊገኙ ይችላሉ:: የግብር አጣጣል (አወሳሰን) የግል ንብረት የማፍራት መብት ጋር መጋጨት የለበትም፣ ክልላዊ እኩልነት ሊኖር ይገባዋል፣ አንድ ንብረት ላይ ሁለት ጊዜ ግብር መጣል አይቻልም፣ ግብር ሰው ከተወሠነ መስመር በታች እንዲኖር የሚያደርገው መሆ" አይገባውም፣ ለቤተሰብ እና በጋብቻ ጥበቃ ሊያደርግም ይገባዋል (ጀርመን) ወዘተ የሚሉ ሊጠቀሱ ይችላሉ:: የግብርን መርህ ከሁሉም ህገ መንግስታዊ መብቶች ጋር ማገናኘትም ይቻላል:: የሚጣለው ግብር የመናገር መሰብሰብ መብት የማይገድብ፣ በመስጊድ ወይም ቤተክርስቲያን ላይ የሚጣል ከሆነም መጠኑ የኃይማኖት ነፃነትን የማይነካ መሆን ይገባዋል ማለትም ይቻላል:: በስዊዘርላንድ ግዛቶች (Cantones) የቤተስክርስቲያን ወጪን ለመሸፈን ግብር መጣል የሚችሉ ሲሆን መጠኑን ከዚሁ መብት ጋር ማያያዝ ይችላል:: በጣም አንስተኛ ቢሆንም ሰው አባል በሆነበት ቤተክርስቲያን ግብር መክፈል እንደሚችል (አባል ላልሆነበት ደግሞ መክፈል እንደማይገደድ . . . ጀርመን) የሚፈቅድ ስርዓትም አለ:: በአሜሪካ ግን የመንግስት እና ኃይማኖት መለያየት መርህን ይጋፋል በሚል የዚህ አይነት ግብር ኢ ህገ መንግስታዊ ተደርጎ ይወሰዳል:: በሀገራችንም መንግስት በኃይማኖት ስራ ኃይማኖትም በመንግስት ስራ ጣልቃ የማይገባና የተነጣጠሉ በመሆናቸው የዚህ አይነት ግብር የለንም:: በሌላ በኩል ከፍ ሲል እንደተገለፀው የግብር ስርዓታችን የሚመራበት መርህ እኩል የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ማስቻል፣ ማህበራዊ አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መጠን ግብር መሰብሰብ፣ መሠረቱን ማስፋት፣ ግልፅነት፣ ተጠያቂነት፣ ወንድማማችነት' አሳታፊነት፣ ፍትሐዊነት ፣ ውጤታማ፣ ከሙስና የፀዳ እና ተጠያቂነት ያለበት የግብር ስርዓትን መመስረት 'ው:: ሀገራችን ከድህነት ተላቃ ፈጣን እድገት እንድታስመዘግብ የሚያስችሉ መርሆዎች በመሆናቸው በህገ መንግስቱ ላይ የተቀመጡትን ሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በጣሰ መልኩ አይተገብሩም:: በጥቅሉ ከላይ የተገለፁትን መርሆዎች ስንመለከት ህገ መንግስቱን የማክበር እና የማስከበር ኃላፊነት የአስተዳደር አካሉም ጭምር ግዴታ በመሆኑ የግብር ስርዓቱም ይህንን የሚያስከብር ይሆናል::

በአንድ ሀገር ውስጥ ተፈፃሚ የሚሆኑ ህጎች ህገ መንግስት እና በተዋረድ የወጡ ብሔራዊ ህጎች ብቻ ሳይሆኑ ተቀባይነት ያገኙ አህጉራዊ እና አለምአቀፋዊ ስምምነቶችም ጭምር ናቸው፡፡ እነዚህ ህጎች በብሔራዊ የህግ ስርዓት ውስጥ ለመተግበር የሚያስችላቸውና የህግ አግባብ እስካገኙ ድረስ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው አለም አቀፍ ህጎችና ስምምነቶች የሀገሪቱ ህግ አካል በመሆን ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በአንቀጽ 9(3) ስር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም የግብር ህጉ ሀገራችን የተቀበለቻቸው አህጉራዊ እና አለምአቀፋዊ ስምምነቶች ውስጥ የሚገኙ መሠረታዊ መብቶችን ለመጠበቅ' ለማስከበር' እንዲከበሩም ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ያገለግላሉ፡፡

<u>የግብር ህግ አተረጓጎም</u>

የግብር ህግ እንደማንኛውም ህግ ሁሉ ትርጉም የሚፈልግበት ጊዜ ሊኖር ይችላል፡፡ በዚህን ጊዜ የህግ አውጪው(ሆላንድ)አለዚያም የህግ አውጭው ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ (ቻይና) ህጉን እንዲተረጉም ሊደረግ ይችላል፡፡ የተለመደ እንደሆነው ሁሉ ይህ ስልጣንም በውክልና ጉዳዩ ለሚመለከተው አስተዳደር አካል (ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት' የገንዘብ ሚኒስቴር) ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህ ባይሆን እንኳን አስፈፃሚው አካል ደንብ' መመሪያ' ሰርኩላር' ማስታወቂያ በማውጣት ትርጉም እንዲሰጥ ማድረግ የሚቻል ሲሆን በተናጠል ጉዳዮች ላይ ውሣኔ እንዲሰጥ ስልጣን በተሰጠው ጊዜም በተመሣሣይ መልኩ የህግ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል፡፡ ይህም በፍ/ቤት የሚደረግን የክለሳ(review) ተግባር ሳያስቀር ነው፡፡ በግብር ከፋይ እና አስከፋዩ መሃከል ክርክር በተነሳ ጊዜ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ያለው እንደሆነ ህጉን የመተርጎም እድል ያገኛል፡፡ ፍ/ቤትም በሚከተለው የህግ ስርዓት ተመርቶ ህጉን የሚተረጉም ሲሆን በአብዛኛው በስልጣናቸው ውስጥ ያለውን ጠቅላላ ህግ የመተርጎም መርህን ይከተላሉ፡፡ በግብር ህግ አተረጓጎም ውስጥ የህጉ አተረጓጎም ጥብቅ ወይስ የላላ መሆን አለበት? የግብይት ይዘት ወይስ ቅርፅ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው? የግብር ህግ ከሌላው ህግ በተለየ መልኩ "ምጣኔ ሀብታዊ" (principle of economics) አተረጓጎም አክለው ሊተረጉሙ ይገባል? የሚሉና መሰል ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት ግብር ለመጣል ስልጣን የተሰጣቸው መንግስታት በምን ጉዳይ ላይ ግብር መሰብሰብ እንደሚችሉ ጭምር ዘርዝሯል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የህገ

መንግሥት ድንጋጌዎች በመሆናቸው ክርክር ቢነሳ በጉዳዩ ላይ የትርጉም ውሣኔ የሚሰጠው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው፡፡

በግልፅ ከተዘረዘሩት ውጪም የህገ መንግስት ጥያቄ ቢነሳና ግብር ማን መወሰን አለበት የሚለው ጥያቄ ቢነሳ የሁለቱ ም/ቤቶች በጋራ ይወስናሉ፡፡ በዚህን ጊዜ የህገ መንግስት አተረጓጎም መርህን ምክር ቤቱ ይከተላል፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው የግብር ህግ ድንጋጌዎች ግልፅ ለማድረግ ስልጣን የተሰጠው አካል በሚያወጣቸው የውክልና ደንቦች መሠረትም ቀሪ የውሣኔ ሰጭ አካላት ትርጉም ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

በዚህ መሠረት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት በአ.ቁ 622/2001 አንቀጽ 107/2/ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚያወጣቸው መመሪያዎች ለትርጉም አግባብ ያላቸው ናቸው፡፡[2]

የግብር ክርክር ወሳኝ አካልም ክርክር በቀረበለት ጊዜ ከትርጉም መርሆዎች በተለይ የህገ መንግስት መርሆዎችን መሠረት በማድረግ ሊተረጉም ይገባዋል፡፡ በመግቢያችን ላይ የጠቀስናቸውን የኢኮኖሚ ማሻሻያ ኘሮግራም እና የግብር አስተዳደር መሻሻያ ኘሮግራሞችን አጥብቀው ሊከተሉም ይገባል፡፡ በዚህ ትርጉም ውስጥ ምጣኔ ሃብታዊ አተረጓጎም መርህን ሊከተል ይገባዋል? የሚለው አከራካሪ ቢሆንም ለሀገራችን የግብር ስርዓት አከራካሪ አይመስልም፡፡ የግብር ስርዓቱ ለኢኮኖሚ እድገት' ፍትሐዊ ለሆነ የሐብት ክፍፍል' ለቀጣይ እድገት ወዘተ ትኩረት የሚሰጥ በመሆኑ ውሣኔ ሰጪ አካላት የሚሰጡት የህግ ትርጉም በዚሁ መሠረት ምጣኔ ሀብትን ያገናዘበ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ጉዳዩ ለዳኝነት አካል በቀረበ ጊዜም የሚመረመረው የህግ ጥያቄ ትርጉም ካስፈለገው ይህንን አጠቃላይ መርህ መሠረት በማድረግ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ (ምሳሌ የፍ/ብሔር) ህግ አተረጓጎም መርሆዎችን አጣጥሞ መጠቀም ይጠበቅባቸዋል፡፡

[2] ባለስልጣኑ በጉምሩክ ስራ ላይ ለሚፈፀሙ ወንጀሎች በአስተዳደራዊ ውሣኔ ለመጨረሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ለመስጠት፣ ህገ ወጥ እቃዎችን በሚያጓጉዙ ላይ ስለሚወስድ አስተዳደራዊ እርምጃ፣ የእቃዎችን የስሪት ሀገር አወሳሰንን ለማስፈፀም የወጣ መመሪያ፣ የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አቀራረብን ለመወሰን እና ለሰብአዊ ርዳታ የሚገቡ እቃዎች ዲዩቲ ፍሪ አፈፃፀም ለመወሰን ያወጣቸው መመሪያዎች ለግብር ህግ አፈፃፀም ትርጉም አጋዥ ናቸው፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. የግብር ስርዓታችን የታክስ መሠረት መስፋት ህገ መንግስታዊ ነው? የታክስ መሰረትን (tax base) ከማስፋት በተወሰነ ግብር ላይ ከፍተኛ ግብር መጣል ይመረጣል?
2. የግብር ስርዓቱ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት ያስችላል?
3. የግብር ስርዓታችን በህገ መንግስቱ ላይ የተቀመጠውን ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል የማምጣት አላማ አለው? የግብር ስርዓታችን ዋነኛ አላማ (ከህገ መንግስቱ አንፃር)ምንድን ነው?
4. የግብር ህግን በመተርጎም ረገድ የፍ/ቤት ሚና ምንድን ነው?
5. ለግብር ከፋዩ የተለያዩ ማበረታቸዎችን ማድረግ(ምሳሌ የእፎይታ ጊዜ መስጠት' ለተወሰነ ጊዜ ከግብር ነፃ ማድረግ) ህገ መንግስታዊ ስርዓታችን ይፈቅዳል?
6. የግብር ስርዓት በህገ መንግስቱ ውስጥ የተቀመጡትን ሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ላይ በአሉታ ወይም በአዎንታ እንዴት ተፅእኖ ሊያደርስ እንደሚችል ተወያይ፡፡
7. ከህገ መንግስቱ አንፃር የግብር ህግን የማውጣት ስልጣን የህዝብ ተወካዩች ወይም የክልል ም/ቤት ስልጣን ብቻ ነው ትላለህ?
8. የህገ መንግስቱ የእኩልነት መብት በግብር ህግ አፈፃፀም ያለው ትርጉም ላይ ተወያይ፡፡

## ዋቢ መፅሐፍት እና ሕጎች


1. ፋሲል ናሆም' Constitution for a ration of nations: The Red Sea press, Inc. 1997
2. የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት' ህዳር 29/1987 የፀደቀ
3. የፍ/ብሔር ህግ (ኢትዮጵያ' 1952)
4. Wade and Bradreg: Constitutional and administration law; Longman London and New York 1993
5. የኢፊዲሪ ልዩ ልዩ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች

6. መሀሪ ረዳኢ የተሻሻለ የቤተሰብ ህግ ለመገንዘብ የሚረዱ አንዳንድ ነጥቦች ቅፅ አንድ (1995) እና ፅፅ ሁለት (1999)
7. ሁሉን አቀፍ የሰብአዊ መብት መግለጫ' እና አለም አቀፍ ስምምነቶች'
8. Journal of Ethiopia Law: vol. 7 /ቁጥር 1
9. Robert Cooter and Thomas vlen: Law and Economics(4th ed)Boston San Francisco and New York,2003
10.የኤፌዲሪ የቤተሰብ ህግ' የአማራ እና ትግራይ ክልል የቤተሰብ ህጎች
11.የአሰሪና ሰራተኛ ህግ (አ.ቀ.377/96)
12.የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ያወጣቸው ልዩ ልዩ መመሪያዎች
13. M.Trebilcock & R.J.Daniels: Rule of Law Reform and Adjustment, chanting the fragile path of progress.